# ገድለ አዳም



፯ኛ ዕትም

ትርጉም:-ተስፋ ሚካኤል ታከለ

አሳታሚና አከፋፋይ:-
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን
፳፻፱ ዓ.ም

(memo) Aug 9, 2018

# ገድለ አዳም

፬ ዕትም

ትርጉም፡- መምህር ተስፋ ሚካኤል ታከለ

አርትዖት፡- ሊቀ ትጉሃን ኃይለ ጊዮርጊስ ዳኜ
ዲያቆን ታደሰ ወርቁ

አሳታሚና አከፋፋይ፡-
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን
፳፻፱ ዓ.ም

# መታሰቢያነቱ

በቅኔ፣ በትርጓሜ መጻሕፍት እና በፍትሐ ነገሥት መምህርነት ተመርቀው ሹመቱ ሽልማቱ፣ ሳይበግራቸው የቅኔና የመጽሐፍ ወንበር ዘርግተው በማስተማር ለነገዋ ቤተክርስቲያን አለኝታ የሚሆኑ በርካታ ደቀመዛሙርትን ሳፈሩትና እያፈሩ ለሚገኙት ትውልዱ ለሚያነሣው የሃይማኖትና የሥነ ምግባር ጥያቄ በሚገባው መልኩ ከማስረዳትና እውነታውን እንዲከተል ከማድረጋቸው በተጨማሪ፣ ቀቋንቀቋ ሳይገድባቸው መልስ ለሚሰጡት፣ የውጪ ዜጎችን ሳይቀር የክርስቶስ ተከታይ እያደረጉ ላሉት የሕዝቡን ማኅበራዊና ሃይማኖታዊ ችግር በትምህርታቸው፣ በአባታዊ ምክራቸው ከመፍታት ባሻገር ገዳማዊ ሕይወትን ገንዘብ አድርገው ገዳማውያን ጠንክረው በመሥራት ራሳቸውን ችለው ችግረኞችን ሊረዱ ይገባል እንጂ ጥገኞች /ተረጂዎች/ መሆን የለባቸውም የሚል መጽሐፋዊ መመሪያን በመከተል ለልማት እየተጉ፣ ገዳማትንና አድባራትንም እያተጉ ለሚገኙት ለፈለገ ብርሃን ቅድስት ናዳ ማርያም ገዳም አስተዳዳሪ እና የፈለገ አእምሮ ጉባኤ ቤት ኃላፊ ቀሞስ መምህር ይባቤ በላይ ይሁንልን።

ማኅበረ ቅዱሳን

# ማውጫ

**ክፍል አንድ**


በእንተ ገድለ አዳም ........................................ 1

1. ገድል ምንድን ነው? ........................................ 1

2. ገድለ አዳም በሁለቱ አዝማናት ........................................ 2

2.1 ገድላት በዘመነ ብሉይ ........................................ 2

2.2 ገድላት በዘመነ ሐዲስ ........................................ 4

3. ገድለ አዳም በገድላት ........................................ 6

4. ገድለ አዳም እንዴት ተጻፈ?እንዴትስ ተተረጐመ ........................................ 9

4.1 ገድለ አዳም እንዴት ተጻፈ? ........................................ 10

4.2 ገድለ አዳም እንዴት ተተረጎመ? ........................................ 13

5. የገድለ አዳም አስፈላጊነት

5.1 የሰውን ልጅ ጥንተ ተፈጥሮ ማስረዳቱ ........................................ 15

5.2 የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነት ማሳየቱ ........................................ 16

5.3 ነገረ ድኅነትን ሂደታዊ በሆነ መልኩ መግለጡ ........................................ 16

5.4 ፍኖተ አበውን በሚገባ መተንተኑ ........................................ 17

5.5 የመላእክትን ተራዳኢነት እና የዲያብሎስን ተንኮል መግለ........ 17

5.6 የትርጓሜ መጽሐፍ ሆኖ ማገልገሉ ........................................ 18

5.7 ለጥናትና ምርምር ርእስ ጉዳይ መሆኑ ........................................ 18


**ክፍል ሁለት**

**ገድለ አዳም**


መቅድም ........................................ 20

ምዕራፍ ሁለት

ገድለ ሰዳም ዘግንቦት ..........................................43

ምዕራፍ ሦስት

ገድለ ሰዳም ዘሠኔ ..........................................59

ምዕራፍ አራት

ገድለ ሰዳም ዘሐምሌ ..........................................73

ምዕራፍ አምስት

ገድለ ሰዳም ዘነሐሴ ..........................................86

ምዕራፍ ስድስት

ገድለ ሰዳም

ዘመስከረም ..........................................98

ምዕራፍ ሰባት

ገድለ ሰዳም ዘጥቅምት ..........................................115

ምዕራፍ ስምንት

ገድለ ሰዳም ዘኅዳር ..........................................135

ምዕራፍ ዘጠኝ

ገድለ ሰዳም ዘታኅሣሥ ..........................................149

ምዕራፍ ዐሥር

ገድለ ሰዳም ዘጥር..........................................163

ምዕራፍ ዐሥራ አንድ

ገድለ ሰዳም ዘየካቲት ..........................................175

ገድለ አዳም ዘታኅሣሥ ....................................149

ምዕራፍ ዐሥር

ገድለ አዳም ዘጥር............................................163

ምዕራፍ ዐሥራ አንድ

ገድለ አዳም ዘየካቲት ....................................175

ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት

ገድለ አዳም ዘመጋቢት ....................................190

ዋቢ መጻሕፍት ..................................................106

## መግቢያ

አምላካችን እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ፍጥረታት ሁሉ በአርአያውና በአምሳሉ የፈጠረው አባታችን አዳምን ብቻ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ «ሰውን /አዳምን/ በመልኩ ፈጠረ» ከማለቱ በተጨማሪ «እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፤በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት፤ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ።» በማለት የአባታችን የአዳም አፈጣጠር ከሌሎቹ ፍጥረታት የተለየ መሆኑን አጉልቶ ይነግረናል።ዘፍ.፪÷፯

እግዚአብሔር አዳምን እንደዚህ አድርጎ ከፈጠረው በኋላም በልጅነት አከብሮ በገነት አስቀመጠው። «የፈጠረውንም ሰው ከዚያ አኖረው...» እንዲል። ዘፍ.፪÷፰አዳምን ፍጥረቱን ሁሉ ገዢ አደረገው። «እግዚአብሔርም ባረካቸው፤እንዲህም አላቸው፤ብዙ ፤ተባዙ፤ምድርንም ሙሏት፤ግዟትም» ብሏዋቸዋልና። ዘፍ ፩÷፳፰። ይህን ሁሉ ጸጋ ካጎናጸፈው በኋላም የገዢና የተገዢ ምልክት ትሆን ዘንድ ዕፀ በለስን እንዳይመገብ ከለከለው። «መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ» በማለት አዝዞታልና ዘፍ.፪÷፲፯።

ከዕፀ በለስ እንዳይበላ የከለከለውም ነፍጎት አልነበረም። አምላካችን እግዚአብሔር በሰጣታው ንፍገት፤በመንግሥቱ ሽረት የለበትምና። የእርሱን ገዢነት፤የአዳምን ተገዢነት የእሱን አዛዥነት፣ የአዳምን ታዛዥነት /ታዛዢነት/ ለማስረዳት ከዚህ አትለፍ የሚል ድንበር አበጀለት። ሥርዐት ሠራለት እንጂ። ከዚህም በተጨማሪ ሥርዐተ ጾምን ሲሠራለት እንዲህ አለው። የሰው ልጅ ከእንስሳትና ከአራዊት ከሚለይባቸው ግብራት አንዱ መጾሙ ነውና።

አባታችን አዳምም አትብላ የሚለውን የፈጣሪውን ትእዛዝ አክብሮ ሰባት ዓመት ከአንድ ወር ከዐሥራ ሰባት ቀን በገነት ከብሮ፤ገኖ ቆዩ። «ሰባቱ ዘመን

ባለቀ ጊዜ ሁለተኛው ወር በባተ /በገባ/ በዐሥራ ሰባተኛው ቀን በምድር ላይ የሚሄድ እባብ መጥቶ ወደ ሔዋን ቀረበ....» እንዲል ኩፋ.፬÷፲፯:

ከዚህ በኋላ ግን አምላክነትን ሽቶ፣ምክረ ከይሲን ሰምቶ ዕፀ በለስን በመብላቱ ትእዛዙን ተላለፈ:: ዘፍ. ፫÷፲፯:: ኮናኒ በጽድቅ ፈታሒ በርትዕ እግዚአብሔርም እውነተኛ ዳኛ እንደመሆኑ መጠን በአዳም ላይ ፈረደበት:: ዘፍ.፫÷፲፯:: ፈጣሪውን ማሳዘኑን የተረዳ፣እንደ ዲያብሎስ ልቡናው ያልደነደነ አባታችን አዳምም ፈጣሪው ይቅር ይለው ዘንድ ጽኑ ገድልን መጋደል ጀመረ:: ይኸ በስሙ የተሰየመው ገድልም የሚተርከው ይኸንኑ ነው::

ገድለ አዳም የአዳምንና ሔዋንን ገድል በዋናነት ወይም በማእከልነት ቢተርከም ብዙ ምሥጢራትን ያዘለ መጽሐፍ ነው:: የመጻሕፍት ዝግጅት ክፍልም ይኸን መጽሐፍ ከግእዝ ወደ አማርኛ ቋንቋ ሲተረጉም ይኸንኑ በመገንዘብ ነው:: ከዚህም በተጨማሪ ነቢያት፣ሐዋርያት፣ጻድቃን፣ሰማዕታትን ሁሉንም የሰው ዘር ያስገኘ የአባታችን አዳም ከውድቀቱ ይልቅ ገርነቱ፣የዋሕነቱ፣ቅዱስነቱ፣ታላቅነቱና አማላጅነቱ የሚገባውን ያህል በምእመናኑ ዘንድ ካለመታወቁም በላይ አስቀድመን እንደገለጽነው ገድሉ ከያዘው እምቅ ዕውቀት፣ ምሥጢር አንጻር ወደ አማርኛ መተርጐሙ እጅግ አስፈላጊ ነው::

ገድሉ የአባታች አዳምና ሔዋን ብሎም ከእርሱ በኋላ የተነሡ አበውን የተጋድሎ ሕይወት ምእመኑ እነዲያውቀው ከማገዙም በተጨማሪ ለሊቃውንተ ቤተክርስቲያን፣ለመምህራነ ወንጌል፣ለሰንበት ት/ቤቶች መምህራን በምንጭነት / Reference/ ይጠቅማል ብለን እናምናለን:: እንዲሁም ደግሞ ምእመናን በአዳምና ሔዋን የተጋድሎ ሕይወት ውስጥ የሚማሩባቸው ብዙ ቁም ነገሮችን አካቶ የያዘ መጽሐፍ በመሆኑ እነርሱም ተጠቃሚዎች ይሆናሉ::

ገድሉን በተለያዩ መረጃዎች ለማበልጸግ ሲባል ሰፊ ጊዜ ወስዷል:: በሌላ አገላለጽ ጊዜ የወሰደ የአርትዖት ሥራ ተሠርቶለታል:: በዚህም የአርትዖት ሥራ

ሁለት ሰዎች ተሳትፈዋል፡፡ እነዚህም ሊቀ ትጉሃን ኅይለ ጊዮርጊስ ዳኜ በጠቅላይ ቤተክህነት የዕቅድና የልማት መምሪያ ም/ሐላፊ እና ዲያቆን ኃይለ መርቀ በማኅበረ ቅዱሳን የመጻሕፍት ዝግጅት ክፍል ሐላፊ ናቸው፡፡ በዚህ የአርትዖት ሂደትም መጽሐፉ የበለጠ ምሥጢር ገላጭ ቃላትና በሠመረ የዐረፍተ ነገር አሰዳደርና አሰካክ የተዋበ እንዲሆን ያልተቆጠበ ጥረት ተደርጓል፡፡ የግእዝ ቋንቋችን ፊደላት እናት ቤተ ክርስቲያን ለውዲቱ ሀገራችን ኢትዮጵያ ያበረከተችው ወደር የማይገኝለት የዘለዓለም ውለታዋ ከመሆኑ ይልቅ ለትውልድ የተላለፈ ሕያው ቅርስ ስለሆነ አገባቡን ንቅስ በማድግ ለማረም ተሞክሯል፡፡ መብራራት የሚገባቸው ፅንስ ዐሳቦች እንዲሁም ደግሞ በመረጃ መበልጸግ የሚገባቸው የተለያዩ ንድፈ ዐሳቦች በግርጌ ማስታወሻ /foot note/ ለማብራራትና ለማበልጸግ ጥረት ተደርጓል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የእንግሊዝኛውን ትርጉም ቅጅ ገድለ አዳም እንደማጣቀሻነት ተጠቅመናል፡፡ በዚህ የአርትዖት ሥራ የቤተ ክርስቲያናችን የሊቃውንት ጉባኤ አባላትን በተናጠልም ሆነ በጋራ በጉዳዮች ላይ አማክረናል፡፡ በዚህ አጋጣሚ አስተያየትና ምክር ላደረሱን ምስጋናችን ይድረሳቸው እንላለን፡፡

መጽሐፉ ሁለት ክፍሎች ሲኖሩት በዐሥራ ሁለት ምዕራፎች የተከፈለ ነው፡፡ የመጀመሪያው ክፍል የአርትዖቱ ሥራ አንድ ክፍል ሆኖ ስለገድሉ አጠቃላይ መረጃ ለመስጠት ትንተና የቀረበበት ነው፡፡ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ በዐሥራ ሁለት ወራት የተከፋፈለውን በዐሥራ ሁለት ምዕራፎች የገድሉ አጠቃላይ ንባብ የቀረበበት ነው፡፡

መጽሐፉ በይዘት ሲዘረዘር በጥቅሉ ከላይ የተጠቀሰውን ቢመስልም ከመጀመሪያው ምዕራፍ እስከ መጨረሻው ምዕራፍ የተካተቱት መሠረታዊ የሚባሉትን የሰው ልጅን ጥንተ ተፈጥሮ፣የገነት ኑሮ፣ውድቀት፣ ተጋድሎ፣የአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ቃል ኪዳን አፈጻጸም፣ የአቤልና የቃኤል ግንኙነት፣በነገረ ድኅነት ጉዞ የአዳምና የልጆቹ ሱታፌ፣የዲያብሎስን

ተደጋጋሚ ተንከልና ፈተና አካቷል፡፡

በመጨረሻም የዚህ ገድል የትርጉም ሥራ ያለቀለትና የማያዳግም ነው ብለን አናምንም፡፡ በመሆኑም አንባብያን የጎደለውን በመሙላት፣ የጠመመውን በማቅናት እንድታነቡት እያሳሰብን መጽሐፉ የፍጡራን ሁሉ ሁለት ጥንት፣ አብ ወእም፣የአዳምና የሔዋን ገድል የመሆኑን ያኽል የመጽሐፉን የመጀመሪያ ምዕራፎች ስታነቡት እንደምትወዱት ባለሙሉ ተስፋ ነን፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

የመጻሕፍት ዝግጅት ክፍል

## ክፍል አንድ
## በእንተ ገድለ አዳም

### መግቢያ

አባታችን አዳም የአበው፣የነቢያት፣የሐዋርያት፣የጻድቃን የሰማዕታት አባት ነው። ሀብተ ትንቢት፣ሀብተ መንግሥት ሀብተ ክህነት የተሰጠውም ቅዱስ አባት ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታቦት ቀርጻ፣ቤተ ክርስቲያን አንፃ ምእመናን በአማላጅነቱ እንዲጠቀሙ አድርጋለች።

በመሆኑም የዚህን ታላቅ አባት ገድል ከማንበባችን በፊት ስለገድል አጠቃላይ ሁኔታ መገንዘብ አስፈላጊ በመሆኑ ይኸንን የመግቢያ ጽሑፍ አዘጋጅተናል። በዚህ ጽሑፍም ገድለ አዳምን ከተለያዩ አዝማናት እና ከገድላት መሠረታዊ ጠባይ አንጻር እንመለከታለን። ገድሉ መቼና በማን እንደተጻፈ፣ የተጻፈበት መንገድና የአተረጓጎሙ ሁኔታም ምን እንደሚመስል ከተመለከትን በኋላ የገድሉን አስፈላጊነት እንመለከታለን።

### ፩. ገድል ምንድን ነው;

ገድል የሚለው የግእዝ ቃል በቀጥታ ትርጉሙ ትግል፣ፈተና፣ውጊያ፣ሰልፍ፣ድልና አክሊል እስኪገኝ ድረስ የሚደከሙት ድካም፣የሚሠሩት ሥራ፣ የሚቀበሉት መከራ ማለት ነው። ከዚህ ጽሑፍ ዐውድ አኳያ ግን መንፈሳዊ ዜና፣ወግ፣ታሪክ፣የቅዱሳንን መከራ፣ ጻጋ፣ ተጋድሏቸውን የሚናገር መጽሐፍ የሚል ትርጉም አለው።[1] በአቻ ትርጉም ደረጃ ደግሞ ገድል በግሪክ ቋንቋ ሃጊዮስ /HAGIOS/ ሲባል ትርጉሙም የቤተክርስቲያን አባቶችና የሌሎች ቅዱሳንን ታሪክ የሚይዝ ጽሑፍ ማለት ነው። ይኸም ከላቲኑ አክት /ACT/ ጋር ተመሳሳይነት ሲኖረው ትርጉሙም ግብረ ቅዱሳን ማለት ነው።

ጥቅሱ «ገድል ገድሉ የተጻፈለትን ቅዱስ የተመለከቱ ወጐችን፣ታሪኮችን፣ ጸዋትወ መከራዎችን የያዘ፣ የተቀበለውን ጸጋና በእርሱ ቃል ኪዳን ምእመናን ሊያገኙ የሚችሉትን በረከት የሚያትት መጽሐፍ ነው።»በማለት ዲ/ን ኤፍሬም እሸቴ የገድላት አዝማናዊ አከፋፈልና ሥነ ጽሑፋዊ ፋይዳ በሚል ርእስ በ፲፱፻፺፪ዓ.ም ባዘጋጁት የጥናት ወረቀት ላይ ገልጸዋል።

## ፪. ገድለ አዳም በሁለቱ አዝማናት

በዚህ ንዑስ ርእስ ገድለ አዳምን የቅዱሳን ገድል መጻፍ ከተጀመረበትና ዕድገት ካሳየበት ሁለት ዘመናት አንጻር እንመለከታለን። ይኸውም ዘመነ ብሉይና ዘመነ ሐዲስ ነው። በዚህ ሂደትም ገድለ አዳም የተጻፈበትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት እንመለከታለን።

## ፪.፪ ገድላት በዘመነ ብሉይ

ይኸ ዘመን ከአዳም እስከ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ ያለው ጊዜ ሲሆን ሕገ ልቡና እና ሕገ ኦሪት በመባልም ለሁለት ይከፈላል። የመጀመሪያው ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ያለውን ጊዜ ሲያመለክት ሁለተኛው ደግሞ ከሙሴ ጀምሮ እስከ ጌታችን ልደት ድረስ ያለውን ጊዜ ያመለክታል። የቅዱሳን ገድል መጻፍ የተጀመረበትን ዘመን ስንመለከት እነዚህን ዘመናት ማእከል በማድረግ ነው።

ገድላት መጻፍ የጀመሩት ከብሉይ ኪዳን ዘመን ጀምሮ መሆኑን ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ያስረዳሉ። ይኸንን ተጨባጭ ለማድረግም ሁለት ዓይነት የአጻጻፍ መንገድ እንደነበረ ይገልጻሉ። የመጀመሪያው መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የቅዱሳን ታሪክ ዋና የታሪክ ማእከል ሆኖ የተጻፈበት መንገድ ነው። ይኸውም [illegible]ጼዴቅ፣የይስሐቅ፣የያዕቆብ፣የሙሴ፣የኢያሱ፣የዳዊት፣የሰሎሞን፣ ወዘተ ታሪክ የተጻፈው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሌሎች ታሪኮች ጋር ተዋሕዶ ነው።

ሁለተኛው መንገድ ደግሞ በቅዱሳኑ ስም ለብቻ መጻሕፍትን መጻፍ

ነው:: መጽሐፈ አስቴር፣መጽሐፈ ሩት፣መጽሐፈ ኢዮብ፣መጽሐፈ ዮዲት፣መጽሐፈ ሶስናና ግብረ ሐዋርያት ለዚህ ተጠቃሾች ናቸው:: በእነዚህ መጻሕፍት የቅዱሳኑ ታሪክ፣የሠሩት ሥራና ከልዩ ልዩ ፈተናዎች ጋር ያደረጉት ተጋድሎ በዝርዝር ተጽፏል::

እነዚህ ሁለት መጽሐፍ ቅዱሳዊ የአጻጻፍ መንገዶች ገድል፣ለሚለው ቃል ከሰጠነው ብይን አንጻር ስንመለከት በሁለት መንገድ የተጻፉት የቅዱሳኑ ታሪክ ገድላዊ ጠባይ ይታይባቸዋል:: ይህ መሆኑ ደግሞ ገድላት መጻፍ የተጀመሩበትን አዝማናት ከማመልከቱ ባሻገር ገድላት ያላቸውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ቁልጭ አድርጎ ያሳያል::

ገድለ አዳምን ከእነዚህ ሁለት የብሉይ ኪዳን አጻጻፍ አንጻር ስንመለከተው የመጀመሪያው የአጻጻፍ መንገድ እጅግ ጎልቶ ቢታይበትም የሁለተኛውንም መንገድ ይከተላል:: ይኸውም ምንም እንኳን የአዳምንና የሔዋንን ታሪክ፣የሠሩአቸውን ሥራዎች፣ ፈተናዎቻቸውንና ያደረጉትን ተጋድሎ በዋና የታሪክ ማእከልነት ቢተርከም ሌሎች ታሪኮችንም አብሮ ያነሣል:: በመሆኑም ገድለ አዳም የተጻፈበት መንገድ ከላይ የተመለከትናቸው አበው ታሪክ ከተጻፈበት መንገድ ጋር እጅግ ቁርኝት አለው:: ይኸ ደግሞ ገድለ አዳም ዘመነ ብሉይን በተለይ ደግሞ ዘመነ አበውን ከማሳየቱ ባሻገር የአጻጻፍ መንገዱም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑን ጭምር ያስገነዝባል::

ይህን ተጨባጭ ለማድረግ በመፍሐፈ ሩት ከተጠቀሰው የሩት ተጋድሎ ጋር ማነጻጸሩ አስፈላጊ ነው:: ትንታኔዎቻችንም መልክ ስለሚያስይዝልን በዚሁ መልክ መመልከት ተመራጭ ነው:: በመጽሐፈ ሩት ውስጥ የሩት ታሪክ ከሞዓብ እስከ ቤተ ልሔም አለ:: በዚህ የታሪክ ሂደት ውስጥ ያደረገችው ተጋድሎም በሚገባ ተጠቅሶ ይገኛል::

ተጋድሎዋም በሁለት መልኩ ተገልጧል:: የመጀመሪያው አማቷ ኑኃሚን ተመለሽ፤ እኔ ከአሁን በኋላ ተስፋ የለኝም፤ እያለቻት «አምላክሽ

አምላኬ ሕዝብሽ ሕዝቤ ይሆናል» /ሩት ፩፥፲፮/ ብላ በእግዚአብሔር ተማምና ወደ ኋላ መመለስን ስትዋጋው እናያለን:: በዚህም አኅቷ ዖርፋ ስትሸነፍ እርሷ አሸንፋ ወደ ቤተ ልሔም ከኑኃሚን ጋር መጣች:: በቤተ ልሔም ደግሞ ከድርቅና ከባዕድነት ጋር ታግላ አማቷን በትሕትና እየታዘዘች አገልግላታለች:: ከዚህም በተጨማሪ በትሕትና እየታዘዘች በታዛዥነትዋ ምክንያትም በኤዝን ስታገባው እናያለን::

ሁለተኛው የተጋድሎዋ መንገድ የተገለጠው ከተጋድሎዋ በኋላ ሦስት ዋጋዎችን ማግኘቷን መጽሐፈ ሩት በመናገሩ ነው:: የመጀመሪያዋ እስራኤላዊት ያልሆነችው ከእስራኤል ተቆጠረች:: ሁለተኛው ተስፋ የሚሆናትን ወንድ ልጅ ወለደች:: ሦስተኛው ደግሞ በጌታችን የዘር ሐረግ ገብታ ተቆጠረች:: ኑኃሚን ስትል ከሀገር በመለየት የተጀመረው የተጋድሎ ሕይወት በዚህ ዓይነቱ ክብር ተደመደመ::

ገድለ አዳም እግዚአብሔር ለአዳም አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም አድንሃለሁ፤ በማለት የገባለትን ቃል ኪዳን በክርስቶስ መወለድ እንዴት እንደተፈጸመ ለማሳየት ይኽን የሩት ተጋድሎን ይጠቅሳል:: ገድሉ ታሪኩን ከመጥቀሱ በላይ ደግሞ የራሱ የአዳምን ተጋድሎ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያለው መሆኑን በሚገባ ያሳያል:: ይኽንንም የገድሉን የተወሰኑ ገጾች ሲያነቡት የሚገነዘቡት እውነታ ነው::

## ፪.፪. ገድላት በዘመነ ሐዲስ

በገድለ አዳም እንደተጠቀሰው ይህ ዘመን እግዚአብሔር አምላክ «ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ::» የሚለውን ቃል ኪዳን ለአዳም በገባለት መሠረት ዘመኑ ሲፈጸም ቃል /ወልደ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ/ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከተወለደበት እንሥቶ ያለው ጊዜ ነው:: ይኽን ዘመን ሊቃውንተ ቤተ ክርቲያን ዘመነ ሐዋርያት፣ ዘመነ ሐዋርያውያን አበው፣ዘመነ ሊቃውንት፣ዘመነ ሰማዕታት ወዘተ በማለት ይከፋፍሉታል::

እኛም የገድላትን ጥንት በዚህ ዘመን ስንመለከት ከነዚሁ አዝማናት ዐውድ አኳያ ይሆናል፡፡

በብሉይ ኪዳን ዘመን እንደተመለከትነው በሐዲስ ኪዳንም ተመሳሳይ ነገር እንመለከታለን፡፡ ለዚህ ደግሞ ግብረ ሐዋርያትን መመልከቱ ተመራጭ ነው፡፡ ግብረ ሐዋርያት ሲጀምር ሐዋርያት በጌታችን መለየት አዝነው አይሁድን በመፍራት በአንድ ቤት ተቀምጠው ነው የምናነበው፡፡ በኋላ ግን ኃይለ መንፈስ ቅዱስን አግኝተው ተጋድሎ በጀመሩበት ወቅት ከዲያብሎስ፣ከሐሳውያን ወንድሞች፣ከባለ ሥልጣናት፣ከጠንቋዮች፣ለክርስትና መስፋፋት ጥቅማቸው ከተነካባቸው ግለሰቦች ጋር ሲጋደሉ ሲታሠሩ ሲገፉ፣ሲከሰሱ፣መርከባቸው ሲሰበር፣በባዕድ ሀገር ሲንገላቱና ከመናፍቃን ጋር ሲከራከሩ እናነባለን፡፡ ይኸ መጽሐፍ የሐዋርያትን ተጋድሎ፣ጽናት ከእግዚአብሔር ያገኙትን ጸጋና ኀይል ጠላት ዲያብሎስን እንዴት ድል እንዳደረጉት የሚተርክ ስለሆነ «ገድለ ሐዋርያት» ነው ማለት ይቻላል፡፡

ቅዱሳን ሐዋርያት በብሉይ ኪዳን ከነበሩት የገድል መጻሕፍት ጠቅሰው ያስተምሩ እንደነበር የሚያመላክት ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፏል፡፡ ይኸውም ሐዋርያው ይሁዳ በመልእክቱ ቁጥር ፱፥፲ የጠቀሰው የሙሴ ታሪክ ነው፡፡ ይህም «ዜናሁ ለሙሴ» ከተባለው የሙሴ ገድል የተወሰደ ነው፡፡ ይኸ ደግሞ በዘመነ ሐዲስ ሐዋርያት ገድላትን ለማስተማርያነት ከመጠቀማቸው በላይ ገድላት በዘመኑ የነበራቸውን ሐዋርያዊ ዋጋ ያሳያል፡፡

የገድለ አዳምን የአጻጻፍ ጥንት ከግብረ ሐዋርያት አንጻር ስንመለከት ይኸን ከላይ የተመለከትነውን የአተራረክ ሂደት በገድለ አዳም ውስጥ እናገኛለን፡፡ አዳምና ሔዋን ከደረሰባቸው ድቀት የተነሣ ማዘናቸው፣ዲያብሎስ በየዕለቱ ከሚያደርስባቸው መከራ የተነሣ በመፍራት በበአታቸው መቀመጣቸው፣በእግዚአብሔር ኃይልና ጸጋ ራሳቸውን ለተጋድሎ ማዘጋጀታቸውና መጋደላቸው እንዲሁም ደግሞ በእግዚአብሔር ቸርነት እንዴት

አድርገው ዲያብሎስን ድል እንዳደረጉት የሚተርክ መሆኑን ስንመለከት ገድለ አዳም እንደሌሎቹ ገድላት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያለው ገድል መሆኑን እንረዳለን:: ስለዚህ ገድለ አዳም የአጻጻፍ ስልቱ ከብሉይ ብቻ ሳይሆን ከሐዲስም ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ልብ ይሏል::

ከዚህም በተጨማሪ ከመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ የቅዱሳንን በዓል ማክበር፣ ዝክር መዘከር፣ሥዕላቸውን መሣል፣በስማቸው መማጸን፣ከወንድሞቻቸውና እኅቶቻቸው መካከል በሰማዕትነት የተለዩትን አፅማቸውንና ተረፈ አፅማቸውን በክብር በመቃብር ማስቀመጥ ልማድ ነበር:: ያ ቅዱስ ባረፈበት ዕለት በመቃብሩ /በአፅመ ቅዱሱ/ ዙሪያ ተሰባስበው ቅዳሴ በመቀደስ ሥጋ ወደሙ ተቀብለው በዓሉን ያከብሩ ነበር::

እንዲህ ዓይነቱ ሥርዐት ቀደም ብሎ በዘመነ አበው ይፈጸም እንደነበር ገድለ አዳም ይገልጽልናል:: ይኸውም በአዳም አፅም ዙሪያ በመሰባሰብ ማቱሳላ፣ኖኅ፣ሴም፣መልከ ጼዴቅ ወዘተ ጸሎት ያደርጉ፣ቍርባን ያሳርጉ እንደ ነበር ገድለ አዳም በሰፊው ይተነትናል:: ይህንንም ሥርዐት ከቀደሙት አበው መውረሳቸውን ከማሳየቱ ባሻገር ገድለ አዳምና መጽሐፍ ቅዱስ ያላቸውን ቁርኝት በእጅጉ ያሳያል::

## ፫. ገድለ አዳም በገድላት

ከላይ በዝርዝር ለማየት እንደሞከርነው የገድለ አዳም የአጻጻፍ መንገድ ከብሉይ ኪዳን ጀምሮ ከነበረው እና በሐዲስ የነበሩ ቅዱሳን አበውም ለእኛ ያቆዩን፣ከቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ሀብት ጋር በእጅጉ ያለውን አንድነት ተመልክተናል:: በዚህ ሂደትም የገድላትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረትነት ከመመልከታችን ባሻገር የገድለ አዳምን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይዘት በአጭሩ ተመልክተናል::

አሁን ደግሞ ገድለ አዳምን ከሌሎች ገድላት አንጻር ማየት ለዚህ ጽሑፍ ወሳኝ ነው:: ይኸም በሁለት ምክንያት ነው:: የመጀመሪያው ብዙዎች

ምዕራባውያን ጸሐፍት ገድለ አዳምን እንደ ገድል /Hagiographa/ ሳይሆን እንደ አንድ መጽሐፍ ቅዱስን መነሻ ያደረገ ታሪካዊ ልብ ወለድ /Pseudepigrpha/ ስለሚቆጥሩ መጽሐፉ ገድል መሆኑን በተጨባጭ ለማሳየት ስለሚያግዝ ገድለ አዳምን ከተለመደው የገድላት ጠባይ አንጻር ማየቱ ወሳኝ ያደርገዋል።

አብዛኞቹ ገድላት ተመሳሳይ ቅርጽ እና ፍሰት አላቸው። ከዚህ አንጻር በአብዛኞቹ ገድላት መጀመሪያ የሃይማኖት መሠረት የሆነው ምሥጢረ ሥላሴ እና ምሥጢረ ሥጋዌ በመግቢያነት ይቀርባሉ። ከዚያም የቅዱሱ የልደት ሁኔታ ትውልድ ይገለጣል። ቀጥሎም ገድሉ ይከተላል። ከዚያም የተሰጠው ቃል ኪዳን ይጻፋል። በመጨረሻም ተአምሩ እና መልከዑ ይቀርባል።

ገድለ አዳም እንደ አንድ የገድል መጽሐፍ የራሱ የሆነ ልዩ ጠባይ ቢኖረውም በቅርጽና በፍሰት ደረጃ ከሌሎች ገድላት ጋር በተለይ ደግሞ ከገድለ ክርስቶስ ሠምራና ከገድለ አርሴማ ጋር ተመሳሳይ ነው።

ገድለ አዳም መቅድም ሲኖረው በዚሁ መቅድም ላይ የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት ይተነትናል። እግዚአብሔር አምላክ የፍጥረት ሁሉ ባለቤት መሆኑን ከሰኞ እስከ ዐርብ ድረስ የተፈጠሩትን በመዘርዘር ይገልጣል። ከዚሁ ጋር አያይዞ ነገረ ሥጋዌውንም ይገልጣል። ከዚያ በኋላ ሌሎች ገድላት የባለ ገድሉን ወላጆች ሁኔታ፣አወላለዱን ከገለጡልን በኋላ አካባቢያዊ ሁኔታዎችን እና የትምህርታዊ ዕድገቱን፣ገዳማዊ ሕይወቱን የተቀበለውን መከራና ዕለተ ዕረፍቱን ይተርካሉ።

ገድለ አዳምም በተመሳሳይ መንገድ የአዳምንና የሔዋንን የተጋድሎ ሕይወት ይገልጥልናል። ምንም እንኳን አዳም የመጀመሪያው ሰው እንደ መሆኑ መጠን እንደሌሎች ቅዱሳን አስገኚ /ወላጆች/ አሉት ባይባልም አፈጣጠሩን አካባቢያዊ ሁኔታውን፣የተጋድሎ ሕይወቱን፣የተቀበለውን መከራና ዕለተ ዕረፍቱን በጥልቀትና በስፋት ይተርካል።

በብዙዎች ገድላት ጎልተው የሚታዩት ተአምር፣ራእይ፣ጾም ጸሎት በገድለ አዳምም ይታያሉ:: በሌሎች ገድላት ቅዱሱ ተአምር ሲያደርግና ሲደረግለት በራእይ እግዚአብሔር እንደሚገለጥለት እንዲሁም እንደሚጾምና እንደሚጸልይ ሁሉ አዳምና ሔዋን ይኸን በተደጋጋሚ ሲፈጽሙ በገድለ አዳም መጽሐፍም ይታያል::

ገድላት በጠባያቸው ከሚተርኩልን ኹነቶች /events/ መካከል ሦስት መሠረታዊ ጉዳዮች አሉ:: የመጀመሪያው ከእግዚአብሔርና ከመላእክት ለቅዱሱ የሚደረግለት እርዳታ ነው:: ሁለተኛው በባለ ገድሉ ቅዱስ ላይ የሚደርሰው ተቃውሞ /ፈተና/ ነው:: ሦስተኛው ደግሞ ቅዱሱ የተቀበላቸው ቃል ኪዳኖችና የቃል ኪዳኑ ተጠቃሚዎች ናቸው::

ገድለ አዳም ከእነዚህ ሦስት መሠረታዊ የገድላት ኹነታት /events/ አንጻር ሲቃኝ ሦስቱንም አጉልቶ እናገኘዋለን:: ለምሳሌ በክርስቶስ ሠምራ ገድል ላይ «ዲያብሎስ በሊቀ ጳጳስ ተመስሎ እጅግ አስደናቂና ግሩም በሆነ አርአያ ወደርስዋ መጣ:: እርስዋም ልትሰግድለት ወደደች:: ከኃዘኗ ያረጋጋት ዘንድ ከቅዱሳን አንዱ የመጣ መስሏት ነበርና:: ነገር ግን የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ፈጥኖ ደረሰና ይኸ ሰይጣን እንጂ ጳጳስ አይደለም ወይም ከቅዱሳን አንዱ አይደለምና አትስገጅለት» ብሎ ወደ ኋላ እንደ መለሰላት ተጠቅሶ እናገኛዋለን:: ከዚህ መረዳት የሚቻለው መላእክት ባለገድሉን ከሰይጣን የማስመሰል ፈተና እንደሚታደጉት ነው:: እንዲህ ዓይነቶቹ እገዛዎቹ ደግሞ በብዙዎቹ ገድላት የሚታዩ ናቸው:: ገድለ አዳምንም ከዚህ የመላእክት የትድግና አገልግሎት አንጻር ስንመለከት እንዲህ ዓይነቱን የመላእክት የትድግና አገልግሎት በብዛት በገድሉ ላይ እንመለከታለን::

ሰይጣን በተደጋጋሚ በሽማግሌ፣በሴት፣በመላእክት ተመስሎ አዳምን ፈትኖ ሲጥለውና ሊጥለው ሲል ደግሞ እግዚአብሔር አምላክ በመላእክት አማካይነት ሲታደገው ብዙ ቦታ ተጠቅሷል:: እንደ ሌሎች ገድላትም

እግዚአብሔር ራሱ በቀጥታ ከሰይጣን የተለያዩ ፈተናዎች ሲታደገው ዲያብሎስን ረግሞ ከእርሱ ሲያስወግድለት በገድለ አዳም ተዘርዝሮ እናገኛለን።

በገድላት የተለመደው ሌላው የትረካ ኹነት በተለያዩ አካላት በባለገድሉ ላይ የሚደርሰው ተቃውሞና መከራ ነው። በብዙዎቹ ገድላት የተጠቀሰው መከራ /ተቃውሞ/ ከሁለት አካላት የመጀመሪያው ከሰው ልጅ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ቀጥታ ከዲያብሎስ ነው። በአዳምና በሔዋን የደረሰው ፈተና ወይም መከራ ከሰው ሳይሆን ቀጥታ ከራሱ ከዲያብሎስ ነው። በእሳት ለብልቧቸዋል፤ ቋጥኝ ድንጋይ በላያቸው ለቅቆባቸዋል፤ የስንዴ ከምራቸውን አቃጥሎባቸዋል፤ የሚጠጡትን ውኃ ደፍቶባቸዋል። በገድሉ እነዚህንና የመሳሰሉ በርካታ መከራዎች ተዘርዝረው እናገኛለን። ከዚህ የትረካ ኹነት አንጻር፣ ከገደለ ክርስቶስ ሠምራ ጋር ይመሳሰላል። ልክ እንደ አዳምና እንደ ሔዋን የክርስቶስ ሠምራ ዋነኛ ተቃዋሚ በቀጥታ ራሱ ዲያብሎስ ነበር። በሌሎቹም ገድላት እንደተለመደው የተቃውሞ ምንጩ ቅንዓት መሆኑን ገድለ አዳም በሚገባ ያስረዳናል።

ገድላት የሚተርኩልን የመጨረሻ ኹነት ለቅዱሱ የሚገባው ቃል ኪዳንና የቃል ኪዳኑ ተጠቃሚዎችን ሁኔታ ነው። በሌሎች ገድላት እግዚአብሔር አምላክ በተለያየ መጠንና ዓይነት ለቅዱሳኑ ቃል ኪዳን መግባቱንና የቃል ኪዳኑን ምንነት እናገኛለን። በተመሳሳይ መልኩ ደግሞ እግዚአብሔር አምላክ ለአዳም የገባውን ቃል ኪዳን ገድለ አዳም በሚገባ ያስረዳናል። በሌሎች ገድላት የቃል ኪዳኑ ተጠቃሚዎች ባለገድላቱ ብቻ እንዳልሆኑ ሁሉ ለአዳም የተገባው ቃል ኪዳን ተጠቃሚዎችም አዳምና ሔዋን ብቻ ሳይሆኑ የሰው ልጆች በሙሉ መሆናቸውን ገድለ አዳም ይተርክልናል።

## ፬.ገድለ አዳም እንዴት ተጻፈ? እንዴትስ ተተረጐመ?

ከላይ በሰፊት ከተመለከትነው የገድሎች ጠባይ አንጻር ገድለ አዳም የገድል መጽሐፍ እንጂ የምዕራባውያን ጸሐፍት እንዳሉት ልብ ወለድ

አለመሆኑን እና የእኛ አባቶች ገድለ አዳምን ከገድል ሲቆጥሩ መነሻቸው ምን እንደሆነ በተጨባጭ ተመልክተናል ፡፡

አሁን በዚህ ንዑስ ርእስ የምንመለከተው ገድለ አዳም እንዴት ተጻፈ፣እንዴትስ ወደ ግእዝ ቋንቋ ተተረጐመ? የሚለውን ነው ፡፡

## ፩.፭. ገድለ አዳም እንዴት ተጻፈ?

ገድለ አዳም እንዴት እንደተጻፈ ከመግለጻችን በፊት ገድላት እንዴት እንደሚጻፉ መመልከት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ይኸም በሁለት ምክንያት ነው ፡፡ የመጀመሪያው ገድለ አዳም ገድል እንደመሆኑ ገድላት ከተጻፉበት መንገድ ውጭ አለመሆኑን ለመረዳት የሚያስችል ሲሆን ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ገድለ አዳም በየትኛው የገድላት አጻጻፍ መንገድ እንደ ተጻፈ ስለሚያመለክተን ነው ፡፡

በመሆኑም ገድላት የተጻፉት በተለያዩ አበውና በተለያዩ የአጻጻፍ አማራጮች ነው፡፡ ይኸውም ቅዱሱ ተጋድሎውን ሲፈጽም በአካል የነበሩ ሰዎች ገድሉን በዓይን ምስክርነት ይጽፋሉ፡፡ ይህም ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ የዓይን ምስክር ሆኖ የሐዋርያትን ገድል በሐዋርያት ሥራ እንደ ጻፈው ማለት ነው የሐዋ ፳፥፩-፰፡፡ ቅዱስ አትናቴዎስ የአባ እንጦንስን ገድል የጻፈው፣ አባ ማስያስ የግብጻዊቷን ማርያም ገድል የጻፈው በዚሁ መልክ ነው ፡፡

ሁለተኛው ገድላት የሚጻፉበት ሁኔታ ቅዱሳን ተጋድሎአቸውን ፈጽመው ካረፉ በኋላ ከደቀ መዛሙርቶቻቸው ፣ ከገዳማቸው ፣ ከእነርሱ ጋ ከተጠቀሙ ሰዎች ታሪካቸው ተሰብስቦ በአበው ይጻፋል፡፡ በዚህ መልኩ ከተጻፉት ገድላት መካከል ገድለ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ፣ ገድለ ተክለ ሃይማኖት ፣ ገድለ አባ መልከ ጼዴቅ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ሦስተኛው የሚጻፍበት ሁኔታ በራእይ በመገለጥ ነው፡፡ ይህም ማንም ሳያያቸው በዱር፣ በገደል፣ በየዋሻው ፣በየፍረኩታው የተጋደሉት ቅዱሳን ለድል ለሚመጣው ትውልድ ትምህርት ይሆን ዘንድ ለበቁ አበው እግዚአብሔር

እየገለጠላቸው ገድለ አዳምን የጻፉት ብሉይ ኪዳንን በሚገባ የተረዱ፣ከዕብራይስጥ ወደ ጽርዕ /ግሪክ/ ቋንቋ የተረጎሙ ሰብዐው ሊቃናት ናቸው:: ይኸንንም በገድሉ ተጠቅሶ እናገኘዋለን:: ከዚህ አንጻር የተጻፈበትም ዘመን ከክርስቶስ ልደት በፊት በሁለት መቶ ሰማንያ አራት አካባቢ መሆኑ ነው::

በሌላ መልኩ ደግሞ ገድለ አዳም የእንግሊዘኛው ትርጉም በመግቢያው ላይ ገድሉ ከክርስቶስ ልደት ጥቂት መቶ ዓመታት በፊት እንደተጻፈ አስረግጦ ከተናገረ በኋላ የአንድ ያልታወቀ ግብጻዊ ሥራ እንደሆነ ይገልጣል:: ይህም ግብጻዊ ገድሉን በአረብኛ ቋንቋ እንደጻፈው ይነግረናል:: የተጻፈበትን መንገድም ሲገለጥ ‹‹ በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ ቆይቶ በመጨረሻ አንድ ሰው ጻፈው›› በማለት ነው::[15] የገድለ አዳም የእንግሊዝኛው ትርጉም የተወሰኑት የገድሉ ክፍሎች በአይሁድ ታልሙድ ፣ በኢሳለም ቁርዐን እንደሚገኝ ይነግረናል::

የእንግሊዘኛው ትርጉም አንድ ያልታወቀ ግብጻዊ ጻፈው፤ ማለቱን በገድሉ ውስጥ ከተሰጠው አንጻር ለመቀበል ያስቸግራል:: ምክንያቱም የእንግሊዝኛው ቅጂ ትርጉም አንዱ የትርጉም ምንጩ ግእዙ ነው:: ስለሆነም በግእዙ ያልታወቀ ግብጻዊ ጻፈው ሳይሆን ሰብዐው ሊቃናት እንደጻፉት ስለሚገልጥ የተባለውን ለመቀበል ያስቸግራል:: ይኸንንም በመግቢያው ላይ ከመግለጹ ባሻገር ከግእዝ ቋንቋ ስለመተርጐሙ ሌላ ማስረጃ አለ:: በእንግሊዝኛው ትርጉም ገጽ /12/ ላይ ሚያዝያ የሚለውን / April / ብሎ ሳይተረጐም እንደአለ ሚያዚያ ብሎ ማስቀመጡ ሌላው ተጨማሪ ማስረጃ ነው::[16] የእንግሊዝኛውን ትርጉም መግቢያ የጻፉ ሰዎች ወደዚህ /ያልታወቀ ግብጻዊ ሰው ጻፈው፤ ወደሚለው /ድምዳሜ ያደረሳቸው አንዱ ምክንያት የተሟላ ቅጂ አለማግኘታቸው ይኸንን? ወይስ ሌላ?

[15] ይኸ በእንግሊዝኛው ሲቀመጥ «This book is simply a version of an account handed down by word of mouth, from generation to generation...» የሚል ትርጉም አለው:: The First book of Adam and Eve; prologue

[16] Ibid-pp 12

ከዚህም ባሻገር ገድለ አዳም በሰብዐው ሊቃናት ብዙ ተጻፈ ብሎ መደምደም የሚቻል አይመስልም:: ይህም ገድሉ ከያዛቸው የሐዲስ ኪዳን ታሪኮች አንጻር ነው :: ስለሆነም በገድለ አዳም መጽሐፍ ውስጥ በኋላ የተነሡ የሐዲስ ኪዳን ሊቃውንት መንፈስ ቅዱስ እንዳመለከታቸው በገድሉ ውስጥ እንደጨመሩበት መገመት ይቻላል :: በመሆኑም ገድለ አዳም በሰብዐው ሊቃናት ተጽፎ በኋላ በተነሡ የሐዲስ ኪዳን ሊቃውንት የጎደለው ተሟልቶለት ወጥ የሆነ ገድል መሆን ችሏል ማለት ይቻላል::

### ፩.፪ ገድለ አዳም እንዴት ተተረጎመ?

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉት ገድላት ምንጫቸው ሁለት ነው:: የመጀመሪያው በኢትዮጵያውያን ጸሐፍያን የተጻፉ ሁለተኛው በትርጉም ከግሪክ ፣ ከሶሪያና ከግብጽ የተገኙ ናቸው::[17] ከሁለቱ የወጣ /አንድም የግእዝ ገድል/ የለም:: ገድላቱ የተደረሱበትም ሆነ የተተረጎሙበት ዘመን ክርስትና በቤተ መንግሥት ተቀባይነት ካገኘበት ከአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ የመጨረሻዎቹ ገድላት ተጽፈውባቸዋል እስከሚባልበት እስከ ፲፰ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ባሉት ዓመታት ውስጥ ይጠቃለላሉ::[18] ከዚህ ዘመን በኋላ ገድል የተጻፈለት ቅዱስ አልተገኘም::[19]

የገድለ አዳም የትርጉም ሥራ ከላይ ከጠቀስናቸው /ከግሪክ ፣ ከሶሪያና ከግብጽ / ውጭ ሊሆን አይችልም:: የተተረጎመበትም ዘመን ከላይ ከተመለከትነው የዘመን መዳረሻ ውጭ አይሆንም:: ወደፊት የሚጠኑ ጥናቶች እስከ አላመላከቱ ድረስ እስከ አሁን ባሉት ጥናቶች ከ ፲፰ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኋላ ተገኝተዋል የተባሉ ገድላት የሉምና:: የእንግሊዝኛው ገድለ አዳም ትርጉም ቅጂ መግቢያ የገድለ አዳም ቅጂ በግሪክ፣በሶርያ በግብጽ በአብሲኒያ /ኢትዮጵያ/፣ በዕብራይስጥ መኖሩን ይገልጣል::

ገድለ አዳም ከየትኛውም አገር ቋንቋ እንደተተረጎመ እና መቼና ማን እንደተረጎመው የግእዙ ቅጂ ገድል አይገልጥም:: ነገር ግን የእንግሊዝኛው

17 ዲን ኤፍሬም እሸቴ ፲፱፻፺፱ዓ.ም፣፫

18 Ibid-pp 3

19 Ibid-pp 3

ትርጉም ቅጂ መግቢያ የሚነግረን የአረብኛው ገድለ አዳም የመጀመሪያው ቅጂ ተደርጎ እንደሚወሰድ ገልጦ የዚህ ትርጉም በግእዙ መኖሩን ይገልጣል:: ይኸንንም የእንግሊዝኛው ትርጉም ቅጂ ‹‹ This Particular version is the work of unknown Egyptian... The Egyptian author wrote in Arabic, but later translations were found written in Ethiopic >>[20] በማለት ነው የሚገልጸው:: ትርጉሙም ‹‹ ይህ ቅጂ ያልታወቀ ግብጻዊ ሥራ ነው:: ...ግብጻዊው ደራሲም የጻፈው በአረብኛ ነበር:: በኋላ ላይ ግን ትርጉሙ በግእዝ ተጽፎ ተገኝቷል:: ›› ማለት ነው:: ከዚህ ውጭ የግእዙ ትርጉም ስለተቀዳበት ዘመንና ተርጓሚ የሚለው የለም ::

ምንም እንኳን ወደፊት ጥናት የሚጠይቅ ቢሆንም ወይም ለጊዜው አሁን ትርጉሙ የተቀዳበትን ምንጭ መጥቀስ ቢያስቸግርም ከገድሉ አጠቃላይ ፍሰትና ቅርጽ አንጻር በየትኛው ዘመን እንደተተረጐመ የተወሰኑ ግምታዊ መረጃዎችን ማስቀመጥ ይቻላል ብለን እናምናለን :: ከዚህ አንጻር የእንግሊዝኛው ትርጉም ቅጂ ከአረብኛውና ከግእዙ ቅጂ እ.ኤ.አ. ፲፰፻ዎቹ መጨረሻ አካባቢ ዶክተር ኤስ.ሲ. ማላንና በዶክተር ኢ.ተሩምፕ በተባሉ ሁለት ግለሰቦች ተተረጐመ ይላል::[21] ይኸም ከዛሬ ሁለት መቶ ዐሥር ዓመታት በፊት መሆኑ ነው:: እንግዲህ ከግዕዙ የተቀዳው የእንግሊዝኛው ትርጉም ከተተረጐመ ይኸን ያህል ዓመታት ያስቆጠረ ከሆነ የግእዙ ቅጂ ምን ያህል ዘመን ሊሆነው እንደሚችል ለራስ ግንዛቤ መውሰድ ነው ::

ከዚህ አንጻር የግእዙ የትርጉም ሥራ የቅርብ ጊዜ አለመሆኑን እርግጠኛ መሆን ይቻላል:: ምንም እንኳን ጥልቅና ሰፊ ጥናት የሚጠይቅ ቢሆንም ወይም ለጊዜው ተጨባጭ ማስረጃ ማቅረብ ቢያስቸግርም ከገድሉ አጠቃላይ ፍሰትና ቅርጽ አንጻር ሲታይ ከ፲፫ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እስከ

[20] The First book of Adam and Eve; Prologue

[21] The First book of Adam and Eve; Prologue

፲፬ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ባሉ አዝማናት ውስጥ መተርጐሙን መገመት ይቻላል፡፡ ይኸም በእነዚህ ዘመናት ከተጻፉት ወይም ከተተረጐሙት ገድላት ጋር በፍሰትና በቅርጽ ተመሳሳይ ነው ከሚል አስተያት የመነጨ ነው፡፡ ለዚህም ገድለ ክርስቶስ ሠምራን መመልከት በቂ ነው፡፡

## ፫. የገድለ አዳም አስፈላጊነት

የገድለ አዳም አስፈላጊነት ለሚያነበው ሰው ብቻ ከሚሰጠው ጥቅም ወይም ገድሉም እንደ ገድልነቱ በሚኖረው ፋይዳ ብቻ ወይም ረጅም ዕድሜ ያስቆጠረ ቅርስ ብቻ በመሆኑ የሚታይ አይደለም፡፡ ይህ ገድል አንድና ሁለት ጥቅም ብቻ አለው ብለን የምናስቀምጠው ሳይሆን ከያዘው ዘርፈ ብዙ የነገረ እግዚአብሔር ዕውቀት ፣ የነገረ ድኅነት አገላለጥ፣ ከሰው ልጅ ጥንተ ተፈጥሮና ከያዞቸው የምሥጢር አመሠጣጠር ጭምር አስፈላጊነቱ ይመዘናል፡፡ በዚህ መሠረት ገድለ አዳምን አስፈላጊ የሚያደርጉትን ምክንያቶች በዝርዝር እንመለከታለን ፡፡

### ፫.፩ የሰውን ልጅ ጥንተ ተፈጥሮ ማስረዳቱ

ገድለ አዳም የሰው ልጅ ከምን ተፈጠረ ? እንዴት ተፈጠረ ? የትና መቼ ተፈጠረ ? እርሱ ከመፈጠሩ በፊትና በኋላ የነበረው ተክለሰብእና ምን ይመስል ነበረ ? ለሰው ልጅ ከጥፋት በፊትና በኋላ የነበረችው ዓለም ምን እንደምትታ ነበራት ? የሚሉትንና ሌሎች ጥያቄዎችን ከመመለሱም በላይ የሰው ልጅን ጥንተ ተፈጥሮ ከሥነ ቅርጽ እና ከሐላፊነቱ አንጻር ማራኪ በሆነ ትንተና ማስረዳቱ አስፈላጊነቱን እጅግ አድርጎ ያጎላዋል ፡፡

የሰው ልጅ በጥንተ ተፈጥሮ ሥነ ቅርጽ ከሌሎች ፍጥረታት በተለየ መልኩ መፈጠሩ በአጠቃላይ በሰማያዊና ምድራዊ ኑሮው ላይ ያለውን አዎንታዊ ተጽዕኖ ያስረዳል፡፡ ይህን የሰው ዘር በሙሉ መረዳቱ ደግሞ ከእግዚአብሔር እና አብረውት ከሚኖሩ ማኅበረሰቦች ጋር የሚኖረውን ግንኙነት ቅርጽና ውበት ያበጅለታል፡፡ ገድለ አዳምን እጅግ አስፈላጊ

ያደርገዋል፡፡ ምክንያቱም ሰው ጥንተ ተፈጥሮውን በረዳ ራሱን ጠፊና ኃላፊ በሆኑ አስተሳሰቦች አይጠመድም ነበር ፡፡ ይህን ለሰው ልጅ በማስገንዘብ ደረጃ ገድለ አዳምን የሚተካከል መጽሐፍ ስለማይኖር ገድሉን እጅግ አስፈላጊ ያደርገዋል፡፡

## ፩.፱ የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነት ማሳየቱ

ገድለ አዳም ለሰው ልጅ ከጥንተ ተፈጥሮ ጀምሮ የተሰጠውን ጸጋና በረከት በጥልቀትና በስፋት ከመዳሰሱ ባሻገር የሰው ልጅ ደጋግሞ በሚሠራቸው በደሎች ፈጥኖ ሳያጠፋው በቻይነቱ እግዚአብሔር በተግሣጽና በምሕረት ሲያልፈው ያሳያል፡፡ አዳምና ሔዋን በተደጋጋሚ እግዚአብሔር ከአላቸው ይልቅ ሰይጣን ያላቸውን በማድመጥና በማመን በተደጋጋሚ ሲወድቁ እናያለን፡፡ ገድለ አዳም እግዚአብሔር በቻይነቱ እየታገሰ፣በምሕረቱ እየታደጋቸው፣ ከዲያብሎስ ባርነት ነጻ እንዳወጣቸው በሰፊው ይተነትናል፡፡

በዚህ ሂደት የሰው ልጅ ከውድቀት በኋላ የነበረው ጊዜ ምን ያህል የመረረ የእግዚአብሔር ምሕረት ባይታከልበት አምስት ሺህ አምስት መቶው ዘመን ምን ያህል መራራ መሆኑን ስንረዳ የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነት እናደንቃለን፡፡ ይህንም ገድለ አዳም በሰፊና በጥልቀት በመተንተኑ አሁን ለአለን የአዳም ዘሮች እጅግ አስፈላጊ ያደርገዋል ፡፡

## ፩.፲ ነገረ ድኅነትን ሐደታዊ በሆነ መልኩ መግለጡ

ገድለ አዳም አዳምና ሔዋን ከእነርሱም በኋላ የተነሡ አበው ለድኅነት ያደረጉትን ተጋድሎ፣ የሠውትን መሥዋዕት፣የጸለዩትን ጸሎት፣የጾሙትን ጾም፣ የቆጠሩትን ሱባኤ ከመግለጹ በተጨማሪ ወደፊት የተፈጸመውን ድኅነት በምሳሌ ፣በምሥጢርና በተግባር ገልጦ ማሳየቱ ሌሎች መጻሕፍት ከገለጡት ይልቅ እያንዳንዱን የድኅነት ሥራ ሂደታዊና ተያያዥነት ባለው መልኩ ከአዳም ውድቀት እስከ ጌታ መወለድ ድረስ በጥልቀትና በስፋት ተንትኖ ማቅረቡ እና አዲስ ዕውቀት መጨመሩ ገድሉን እጅግ አስፈላጊ

ያደርገዋል ።

## ፭.፬ ፍኖተ አበውን በሚገባ መተንተኑ

ገድለ አዳም ከአባታችን አዳም ጀምሮ እስከ ጌታችን መወለድ ድረስ የነበሩ አባቶችን የዘር ሐረግ ከመዘርዘሩ ጎን ለጎን እነዚህ አባቶች የተጓዙበትን የሕይወት መንገድ በሚገባ ይተነትናል፡፡ ይኸም የሕይወት መንገድ ሁለት ዓይነት ገጽታ መኖሩን ገድለ አዳም ያሳያል ፡፡ የመጀመሪያው እግዚአብሔር አምላክ ያዘዛቸውን እየፈጸሙ እንደ ቀደሙት አበው ትውፊት፣ሥርዐትና ሕግ የሚኖሩ አካሄዳቸውን ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ያደረጉ አበውን ሕይወት ማሳየቱ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከመፈጸም ይልቅ የዲያብሎስን ፈቃድ እየፈጸሙ ከአባቶቻቸው ትውፊት፣ሥርዓትና ሕግ ወጥተው ለመጀመሪያ ጊዜ በምድር ላይ አምልኮ ጣዖትን አምልኮን፣ዝሙትን፣ሰውመግደልን፣ እናት አባትን አለማክበርን ስርቆትን፣ስካርን፣ቅናትን ጥላቻንና፣ትዕቢትን ወዘተ የጀመሩ ወይም ለምድራችን ያስተዋወቁ የአበውን ሕይወት መንገድና ውድቀት ቁልጭ አድርጎ ማሳየቱ ነው፡፡ ገድሉ በዚህ መልኩ የአበውን የሕይወት ጉዞ መተንተኑ የሰው ልጅ አሁን እየኖረው ካለው የኃጢአት ዕድገት ደረጃ ጋር አነጻጽሮ ለማየት ስለሚረዳ ገድሉን እጅግ አስፈላጊ ያደርገዋል ፡፡

## ፭.፭ የመላእክትን ተራዳኢነት እና የዲያብሎስን ተንኮል መግለጡ

ገድለ አዳም የሰው ልጅን ከጥንተ ተፈጥሮ ጀምሮ ቅዱሳን መላእክት እንዴት አድርገው እንደሚራዱት ሲገልጥ በሌላ መልኩ ደግሞ ዲያብሎስ በሰው ልጅ የሚፈጽመውን የረቀቀ ተንኮል ገድሉ ተጀምሮ እስኪፈጸም ሥዕላዊ በሆነ መልክ ይገልጸዋል፡፡

መላእክት አዳምና ሔዋንን እንዲሁም ደግሞ ልጆቹንና ከእነርሱ በኋላ የተነሡ አበውን ሥርዓት ሲያስተምሩ ጥንተ ጠላት ዲያቢሎስ ደግሞ ሕግ ተላላፊነትን ያስተምራል፡፡ ቅዱሳን መላእክት ለአዳምና ሔዋን የቅዱስ ጋብቻን

ሥርዓት ሲያስተምሩ ዲያብሎስ ደግሞ ዝሙት እንዴት እንደሚፈጸም ያስተምራል። ቅዱሳን መላእክት የሰውን ልጅ ከድካሙ ሊታደጉት ሲተጉ ዲያብሎስና ስራዊቱ ደግሞ በቅናትና በበቀል የሰው ልጅ ድኅነትን አግኝቶ ወደ ቀደመ ክብሩ እንዳይመለስ ይተጋሉ። ገድለ አዳም የቅዱሳን መላእክትን ተራዳኢነትንና የዲያብሎስን ረቂቅ ተንኮል እኛ በዚህ ዘመን ያለን ሰዎች ልንረዳው በምንችለው መንገድ ማቅረቡ ገድሉን አስፈላጊ ያደርገዋል።

**፩.፮ የትርጓሜ መጽሐፍ ሆኖ ማገልገሉ**

ገድለ አዳም እንደ አንድ የገድል መጽሐፍ ብቻ የሚያገለግል ሳይሆን እንደ አንድ ትርጓሜ መጽሐፍም ጭምር አገልግሎት የሚሰጥ መጽሐፍ ነው። ገድሉ የአዳምንና የሔዋንን የተጋድሎ ሕይወት ከሙተረኩ ጎን ለጎን የተለያዩ ፅንሰ ዐሳቦችን ይተረጕማል። ያመሠጥራል እንደ ትርጓሜ መጻሕፍት ሐተታ ይሰጣል ምሳሌ ይመሰላል። ለምሳሌ ይሆኑን ዘንድ ከገድሉ ውስጥ የተወሰኑ ነጥቦችን እናንሳ ። የሰው ልጅ ለምን ቀና ብሎ/ቆሞ/ እንዲሄድ ሆኖ ተፈጠረ ? እንስሳት አራዊትስ ለምን ዝቅ ብለው /አጎንብሰው/ እንዲሔዱ ሆነው ተፈጠሩ? በስደት ወቅት ሣራ አብርሃምን ለምን ወንድሜ ነው አለች? የሚሉትንና መሰል ምሥጢራትን በሚገባ የሚተረጕም መጽሐፍ ነው ። ከዚህ አንጻር ገድለ አዳም እንደ አንድ የገድል መጽሐፍ ከሚሰጠው አገልግሎት ባሻገር ይህን ዓይነቱን የትርጓሜ አገልግሎት መስጠቱ እጅግ አስፈላጊ ያደርገዋል።

**፩.፯ ለጥናትና ምርምር ርእሰ ጉዳይ መሆኑ**

የትኛውም ገድል ለመንፈሳዊ አገልግሎቶች ብቻ እንደማይውል ሁሉ ገድለ አዳምም እንዲሁ ነው። ገድላት በዚህ ዓለም ያሉ የሥነ ጽሑፍ፣የታሪክ፣የነገረ መለኮት፣የባሕልና ቅርሳ ቅርስ ባለሞያዎች ሰፊ ጥናትና ምርምር እንዲያደርጉ በምንጭነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ለዓለም እንደሚያበረክቱና እንደ አበረከቱ ገድላት ሁሉ ገድለ አዳምም ለዚህ ዓላማ መዋል የሚችል ታላቅ ገድል ነው ።

ገድሉ በራሱ ለጥናትና ምርምር ርእሰ ጉዳይ ሆኖ ከማገልገሉ ባሻገር ለተለያዩ ምርምሮች እንደ መጀመሪያ ደረጃ ምንጭ /Primery Sourse/ ሆኖ የሚያገለግል በመሆኑ ገድሉን እጅግ አስፈላጊ ያደርገዋል፡፡

## ማጠቃለያ

ገድለ አዳም በመጽሐፍ ቅዱስ ከተዘገቡት ገድላት እና በቤተ ክርስቲያናችን ካሉት የገድላት ጠባይ ጋር ያለውን ቁርኝት፣የተጻፈበት የአጻጻፍ መንገድ፣መቼና በነማን እንደተጻፈ፣ እንዲሁም ደግሞ ወደ ግእዝ ቋንቋ እንዴት እንደተተረጐመና ገድለ አዳም ያለውን አስፈላጊነት ከገድሉ አጠቃላይ ይዘት፣ጭብጥ፣ፍሰትና ቅርጽ እስካሁን ለመመልከት ተሞክሯል ፡፡

የቅዱሳንን ገድል ጽፎ ማስቀመጥና ትውልድ ከእነርሱ ሕይወት እንዲማር ማድረግ ከብሉይ ኪዳን ዘመን ጀምሮ የነበረ፤ በሐዲስ ኪዳን የነበሩ አበውም ለእኛ ያቆዩን የቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ሀብት እንጂ ልብ ወለድ ድርሰት አለመሆኑንም አይተናል፡፡ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንም የቀደሙቸውን ቤተ ክርስቲያን ትውፊት መሠረት በማድረግ በውጭ ቋንቋ የተጻፉትን ተርጉማለች፡፡ በአገር ውስጥ የነበሩ ቅዱሳንን ገድልም ጽፋ ደጉሳ አስቀምጣለች ፡፡

ከዚህ አንጻር ቤተ ክርስቲያን ባለቤት ከሆነችባቸው ቅዱሳን ገድላት መካከል አንዱ ይህ በወፍ በረር መልኩ የተመለከትነው ገድል ነው ፡፡

ይህ ገድል በራሱ ብዙ መፈተሽ፣ መመርመር፣መታየት ያለበት ያልታየ ድንግል ሀብት ነው፡፡ እኛም አንባቢያን ገድሉን ከማየታችን በፊት ስለ ገድሉ አጠቃላይ ሁኔታ መጠነኛ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማሰብ ነው ይህን ጽሑፍ ያዘጋጀነው፡፡ በዚህ ሂደትም አንባቢያን ስለገድሉ መጠነኛ ግንዛቤ እንደጨበጡ እናምናለን፡፡ ቀጣዩን የገድሉን ዐቢይ ክፍል እነሆ እንላለን ፡፡

# ክፍል ሁለት
# ገድለ አዳም

### መቅድም

ጥበብ ወልድን በወለደ፣በዮርዳኖስ በነጭ ርግብ አምሳል ወርዶ በክርስቶስ ራስ ላይ የተቀመጠ መንፈስ ቅዱስን በአሠረፀ በእግዚአብሔር አብ ስም ጥልቅ/ረቂቅ/የሆነ ከአብ የወልድ መወለድ፣የመንፈስ ቅዱስ መሥረፅ ይነገራል ግን አይደረስበትም፡፡ ለመስማትም፣ለመናገርም የረቀቀ ድንቅ ነው እንጂ፡፡

አብ ልብ ይባላል፡፡ ሁሉን የሚያስብ፣ልብንም የሚያለብም / እንዲያስብ የሚያደርገው/ እርሱ ነው፡፡ በባሕርየ መለኮቱ አንድ ሲሆን በተለየ አካሉ አካላዊ ልብ ነው፡፡ የመላእክት ጭፍሮችን ወደ እርሱ የሚጠራ አብ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ ነው፡፡ ሰማይ ከመዘርጋቱ ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት ከመመላለሳቸው በፊት፣ደመና ዝናብን ከመስጠቱ መሬት ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ፣ ከሰሜን እስከ ደቡብ ከመዘርጋቱ በፊት፣ ትጉሃን በሆኑ በአርባብ መላእክት፣በሱራፌና በኪሩብ አንደበት ከመመስገኑ በፊት ሳይተኛ ሁሉን ይጠብቅ ነበር፡፡

የወደደውን ይምራል፤የወደደውንም ያደንቃል፣ለዓመታቱም ስፍር ቁጥር የላቸውም፡፡ በዕለተ ዐርብ አዳምን ሲፈጥር ከዱዳሌብ አፈርን፣ከናጌብ ውኃን፣ከአዜብ ነፋስን፣ከኮሬብ እሳትን ለማምጣት የተመላለሰ አይደለም፡፡ ከዙፋኑ ፈጽሞ አልተንቀሳቀሰም፡፡ ዓለምን በሚዛኑ በለካት ጊዜ ፍጥረታት ሁሉ በእርሱ ዘንድ እንደ ጠብታ /ቅንጣት/ ናቸው፡፡ የተራበውን ያጠግባል፤ የተጠማውን ያረካል፤እንደ እናት ጡት ሁሉን የሚያሳድግ እርሱ ነው፡፡ በርኅራኄው ወተት በፍጹም ቸርነቱ ሁሉን ይመግባል፡፡ መለኮታዊ ክብሩም በሌላ አይሰጥም፡፡ ለዘለዓለሙ አሜን፡፡

በአንድነት ሦስትነት፣በሦስትነት አንድነት በእግዚአብሔር ወልድ ስም ወልድ ነባቢ ቃል /የሚያናግር/ ይባላል፡፡ በዕለተ እሑድ ሁሉን የፈጠር እርሱ ነው፡፡ በተለየ አካል ቃል አካላዊ ነው፡፡ በማይለይ ባህርየ መለኮቱ ግን ከአብ፣ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የማይለይ አንድ ነው፡፡ ክቡድ በሆነ በነፋስ ኀይል ዓለምን ከመፍጠሩ በፊት የሚያስፈራ፣ የሚያንቀጠቅጥም ነበር፡፡ ዐይኖቹም እንደሚነድ እሳት ናቸው፡፡ የራስ ፀጉሩም እንደበረዶ ነጭ ነው፡፡ የኢያስጲድ ዕንቊንም ይመስላል፡፡ መቅደሱም በእሳት የተከበበ መረግድ /ዕንቍ/ ነው፡፡

ጠፈርን ያለምሰሶ ያቆመ፣ የብስንም ያለ እጅ በቃሉ ብቻ /ያለመሠረት/ የፈጠረ እርሱ ነው፡፡ ለሦስትነቱም በእውነት ስግደት ይገባዋል፡፡

መባርቅት የሚታዘዙለት፣ ነጐድጓድንም የሚልክ በሰማያዊት አዳራሽ በሚቆሙ በነገደ መላእክት የሚመሰገን፣በመንፈስ ቅዱስ አክብሮ አዳምን በኤደን ገነት ያነገሠው፣ ስለቤተክርስቲያን በአደባባይ መከራን የተቀበለ እርሱ ነው፡፡ ከጐኑ በፈሰሰው በክቡር ደሙ ይቀድሳት ዘንድ ስለ እርሷ በመታሰር ግንድን ተሸከመ፡፡ የበደለው ሳይኖር እንደ በደለኛ የርኩሳን አይሁድን ምራቅ ታገሠ፡፡ ዓለምን ለማዳን የወደደ፣ቸርነት ልማዱ የሆነ አምላክ፣ልዩ በሆነ ዕፀ መስቀል ተሰቀለ፡፡ መለኮታዊ ክብሩም ለሌላ አይሰጥም፡፡ ለዘለዓለሙ አሜን፡፡

በማይዳሰስ /በማይጨበጥ/ ነበልባላዊ ኃይል፣ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ንጉሥ በሆነ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ስም፣ መንፈስ ቅዱስ ሕይወት፣ ሁሉን የሚያድን እስትንፋስ ይባላል፡፡ በልዩነት አካላዊ እስትንፋስ ነው፡፡ በመለኮታዊ ባሕርዩ ግን ከአብ፣ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ ነው፡፡

ነፋስ ከመንፈሱ፣መባርቅትም ከመመላለሳቸው በፊት በአዳም ፊት የሕይወትን እስትንፋስ እፍ ያለበት፣የተመሰገነ አዳምን ቆዳን ያለበሰው፣ለቅዱሳን ከሐር የተሠራ የተጌጠ ልብስን የሚያጐናጽፍ፣ንጹሐንን በክብር አክሊል / ዘውድ/ የሚያከብር እርሱ ነው፡፡ በዮርዳኖስ በክርስቶስ ላይ በርግብ አምሳል የወረደ፣ በባሕርም፣በየብስም በእግሩ የሚመላለስ፤ለሚቸገሩ /ላልተረጋጉት/

ፍጹም ጸጥታቸው፤በባሕርና በደሴት፣ነቢያትን ያለምንም መጠጥ /ምግብ/ ያዞራቸው ሐዋርያትን በጸርቴ፣በሜድና በኤላሚጤ ቋንቋ ያናገረ እርሱ ነው።

እርሱ ሲመክረን፣ሲያስተምረን ልዩ ለሆነ ሦስትነቱ እንስገድ፤ለእርሱ ምስጋና ይገባል። መጀመሪያም መጨረሻም ከሌለው ለልጅ ልጅ ከማይጠፋ ሦስትነቱ ጋር የበደለ ሰው ወደ እርሱ እስኪመለስ ድረስ የሚታገሥ፣መለኮታዊ ክብሩ የማይከፈል፣የማይፋለስ፣መንፈስ ቅዱስ ነው። ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ አሜን። ይሁን ይደረግ።

አብ፣ወልድና መንፈስ ቅዱስ ሰውን በአርአያችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር አሉ። በዕለተ እሑድ ስምንት ፍጥረታትን ፈጠሩ፤ ብርሃንና ጨለማን፣ ውኃንና መሬትን፣ ነፋስንና እሳትን፣ ሰማይንና መላእክትን፣ መላእክቱንም መቶ ነገድ አደረጋቸው። የመላእክት አለቃም ሰብልያኖስ /ሳጥናኤል/ ነበር፡ መላእክትንም ፈጥሮ ተሰወራቸው። በጨለማ ሸፈናቸው። እነርሱም እርስ በርሳቸው ማን ፈጠረን; ጌታችንስ ማን ነው; ተባባሉ። ሰብልያኖስም ወዲያና ወዲህ ተመለከተ፤ታላቃቸው እርሱ እንደሆነም አየ። እርሱም ፈጣሪያችሁ፣አምላካችሁም እኔ ነኝ አለ።

መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልም አሰምቶ ተናገረ፤ማኅበረ መላእክት ሆይ! በያለንበት በሃይማኖት ጸንተን እንቁም፤በዚህ መልአክ አትመኑ አላቸው። በዚህ ጊዜ የሥላሴ ብርሃን ታየ፤ ኪሩቤልና ሱራፌል ዙፋኑን ተሸክመው ታዩ። በሰማይ ጠፈርም ብርሃን ይሁን አለ። ለዘለዓለሙ አሜን።

ሰኞ ዕለትም የውኃ ሦስተኛውን እጅ ወደ ሰማይ አወጣው ጠፈርም አደረገው። እስከ ምድር ዳርቻ ድረስም አጸናው። ይኸው የውኃ ሦስተኛው እጅ ሀኖስ ነው። ሲነጋ በመጣ ጊዜም ወደ ጥልቁ ይወርድ ዘንድ ውቅያኖስን አዘዘው። ውኃ ወደ ቦታው ይሰብሰብ አለ። ከወሰኑ /ከድንበሩ/ እንዳያልፍ ገሠጸው /አዘዘው/፤ምንጮችና ፈሳሾች ግን ቀሩ። መሬትንም በውኃ ላይ

አስቀመጣት፡፡ ውኃዎች እንዳይጣሉም በቃሉ አጸናቸው፡፡

ማክሰኞ ዕለትም ምድር ለመነችው፡፡ ጌታዬ፣ አምላኬ ሆይ! የምለብሰውን ልብስ ስጠኝ አለችው፡፡ ለምድርም በእጅ የሚለቀሙ አትክልትን፣በማጭድ የሚታጨዱ ሣሮችን፣በምሳር የሚቆረጡ ዕፀዋትን በየወገኑ ሰጣት፡፡

በዕለተ ረቡዕም ፀሐይ፣ጨረቃ፣ከዋክብትን ፈጠረ፡፡ የፀሐይ አፈጣጠሯም ከነፋስ፣ከብርሃን፣ከእሳት ነው፡፡ጨረቃንም ከነፋስ፣ከብርሃን፣ከውኃ ፈጠረ፡፡ ከዋክብትንም እንዲሁ ፈጠራቸው፡፡

ሐሙስ ዕለትም በመጀመሪያው ሰዓተ ሌሊት እግዚአብሔር እንስሳትን፣ አራዊትን፣አዕዋፍን በየወገኑ ታስገኝ ዘንድ መሬትን ባዘዛት ጊዜ ታላቅ፣ታናሽ፣ሴት፣ወንድ ሁነው ተገኙ፡፡ ከዚህ በኋላ ብሄሞትና ሌዋታንን ፈጠራቸው፡፡ ብሄሞት በየብስ /በደረቁ ምድር/ ይኖራል፡፡ ሌዋታን ግን በባሕር ውስጥ ትኖራለች፡፡

ዐርብ ዕለትም ስድስተኛ ቀን ሆነ፣ጠዋት ፀሐይ ከወጣ በኋላ አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አዳምን ፈጠሩት፤ በፊታቸውም ቆመ፡፡ የሕይወት እስትንፋስንም እፍ አሉበት፡፡ አብ፣ወልድ፣መንፈስ ቅዱስ ሀብተ ክህነትን፣ሀብተ መንግሥትን ሰጠሁህ፣መለኮታዊ ሥልጣኔን አትፈልግ፡፡ በአምላክነት ክብሬም አትግባ ፤ከሰማይ በታች ከምድር በላይ የፈጠርሁልህን ልብህ እንደፈለገው ብላ ጠጣ፡፡ ነገር ግን ይህችን ዕፀ በለስ አትብላ [10]፡፡ ትእዛዜን ተላልፈህ ብትበላ ግን የሞት ሞት ትሞታለህ፤ እነሆ አዘዝሁህ፤ ከታዘዝኸው አትለፍ አለው ፡፡ ሦስት ሰዓት ሲሆንም ሔዋንን ፈጠሯት፡፡ በቀራንዮም ከአዳም ጋር አርባ ቀን አርባ ሌሊት አስቀመጧት ፡፡ ከዚህ በኋላም እግዚአብሔር ታላላቅ እንስሳትን፣ አራዊትን አዕዋፍን በየወገኑ ታወጣ ዘንድ መሬትን አዘዛት፡፡ እነዚህም የውጪ አራዊት የውስጥ አራዊት አራት እግር ያላቸው በልባቸው የሚሳቡትን ነው፡፡ እንዲሁም ሆነ /እንደቃሉ ተፈጠሩ/፡፡

[10] ዘፍ.፪+፲፯

የእንስሳት፣ የአራዊት፣ የተሐዋስያንን ሁሉ የመፈጠር ትርጉም ልናውቅ ይገባናል። ትርጉሙም ይህ ነው፡- ለመድኀኒትነት የሚሆን አለ። ከእነርሱም ለተልእኮ /ለመላላክ/ የሚሆን አለ። እግዚአብሔር ሰውን ለመፍጠር ፈቃዱ በሆነ ጊዜ የሚያገለግለውን ሁሉ አዘጋጀለት። ስፍር ቁጥር የሌለው ፍጥረት በየወገኑ የመፍጠሩን ጥበብ እናደንቅ ዘንድ /ለአንክሮ ለተዘክሮ/፤ ፍጥረታት ብዙ ሲሆኑ እንዴት እንደሚረዳቸው ፣እንደሚያስተዳድራቸው፣እንደሚመግባቸው እናደንቅ ዘንድ፤ከእርሱም ለሰው የሚያገለግል እንደ ላም፣እንደ ፈረስ፣እንደ አህያ የመሳሰለው ነው።

ሰዎች የሚመገቡት እንስሳም አለ። ላምን፣ በግን ፍየልን ይህን የመሳሰለውን ይመለከታል። ሰውም እንደወደደው ይጠቀምባቸዋል&ይመገባቸዋልም። ይኸም የሚያስደንቅ አይደለም። የሚያስደንቅስ ከአራዊት በልባቸው የሚሳቡ፣ከአዕዋፍም የሚረዳቸው ሰው ሳይኖር ከብዛታቸው ጋር በተፈጥሮ ጠባይ የተለያዩ ሲሆኑ ሊጠበቁም የማይፈልጉ ሲሆኑ ይጠብቃቸዋል፤ ይመግባቸዋልም።

ከእነርሱም ሣር የሚመገቡ አሉ፤ ሥጋን የሚመገቡም አሉ። እርሱም ከፍጡራን አንድ ስንኳን ሊመረምረው በማይችል ጥበባዊ ፍርዱ እያንዳንዱን ሁሉ በሚመገባቸው ቦታ ያስማራቸዋል።

ዳግመኛም ሁሉን እንስሳ ዝቅ አድርጎ መፍጠሩ ሁለት ትርጉም እንዳለው ያስረዳል። አንደኛው ለጌታው ራሱን ዝቅ እንደሚያደርግ አገልጋይ ዝቅ ማለታቸው አገልጋይ በመሆናቸው ነው። ሁለተኛው ማለታቸው ዝቅ /ቀና ብለው አለመሄዳቸው/ ከፍ ያለ ቦታ መንግሥተ ሰማይ/ የእነርሱ ባለ መሆኗ ነው። ወደ መሬት ዝቅ ያሉ እንደመሆናቸው በመሬት ይቀራሉ እንጂ። ሰውን ሲፈጥረው ግን እንደፈጠረው አድርጎለት ከፍ ያለች ሀገሩ መንግሥተ ሰማያትን ያይ ዘንድ ወደሰማይ ቀጥ ያለ፣ከፍ ያለ አድርጎታል። ምድርን ይመለከት ዘንድም ፈቃዱ ነው።

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ሰውን በአርአያችን እንደ ምሳሌያችን

እንፍጠር አሉ፡፡ በዚህ ቃልም በፍጹም ማስተዋል አዳም የሠላሳ ዓመት ሰው ሆኖ ተፈጠረ፡፡ እግዚአብሔር ሰውን በአርአያችን እንፍጠር ማለቱ ሦስትነቱን ያስረዳናል፡፡ እንደ አርአያችን፣እንደ ምሳሌያችን ማለቱም ክፉና ደግን ማወቁን ያስረዳናል፡፡ ስለዚህም ከሰማይ በታች ባለው ፍጥረት ሁሉ ንጉሥ፣ጌታም አደረገው፡፡ ከዚህ በኋላ በኤደን ገነት አስቀመጠው፡፡ ከአንዲት ዕፅ በቀር ዕፀዋትንም ሁሉ ብላ አለው፡፡ የከለከለውም ነፍጎት አይደለም፤እነሆ አምላክነቱን ሊያስረዳው እንጂ፡፡

በአዳም ላይ እንቅልፍ መላኩም ከእርሱ ዐፅምን በወሰደ ጊዜ ሕማም እንዳይሰማው ነው፡፡ በፍቅር የተሳሰሩ፣በግብርም የተካከሉ ይሆኑ ዘንድ ሔዋን ከአዳም ቀኝ ጐን ተገኘች/ተፈጠረች/፡፡ ሔዋን ከአዳም የራስ አጥንት ተፈጥራ ቢሆን ትታበይ /ትኮራ/ ነበር፡፡ ከእግሩ አጥንት ተፈጥራ ቢሆንም ፈጽማ በተዋረደች ነበርና፡፡ ይህች ሥጋ ከሥጋዬ ናት፤አጥንቷም ከአጥንቴ ናት፤ ይህች ሚስት ትሁነኝ፤ ማለቱም በእርሱ ባደረ መንፈስ ቅዱስ ያውቅ ዘንድ ስለተገባው ነው፡፡

አዳምና ሔዋንም ብርሃንን የተዘገናጸፉ ነበሩ፡ ሁለቱም የሚለብሱት ከፀሐይ መቶ እጥፍ ያበራ ነበር፡፡ መልካምን የሚጠላ ሰይጣን የክብራቸውን ታላቅነት፣ ምስጋናቸውን በተመለከተ ጊዜ በእነርሱ ላይ ቀናባቸው፡፡ በእባብ አካልም ተሰወረ /ተዋሐደ/፡፡ እባብም ሔዋንን በገነት ካለው ዕፅአት ብሉ ያላችሁ ለምንድን ነው?[12] አለቻት፡፡ ሰይጣን የእግዚአብሔርን ስም ማወቁም «እኔ እግዚአብሔር ብርሃን ይሁን አልሁ» ሲል የእግዚአብሔርን ቃል በመስማቱ ነው፡፡

ሔዋንም እባብን በገነት ካሉት ዕፀዋት ሁሉ እንመገባለን፤ በገነት ካለች ከአንዲት ዕፅ በቀር፡፡ ከእርሷ እንዳንበላ ፣እንዳንፈልጋትም እግዚአብሔር አዝዞናል፡፡ ይህም እንዳንሞት ነው አለችው፡፡ የሰይጣን መልስም ሞትን የምትሞቱ አይደለም፤ዕፀ በለስን በበላችሁ ጊዜ ዐይናችሁ ይገለጣል ክፉና

[12] ዘፍ. ፫÷፩-፫

በኀውን ታውቃላችሁ፤አምላክም ትሆናላችሁ፤ እግዚአብሔር ይህን ያውቃልና ከለከላችሁ አላት:::: ይህ ንግግር ግን ተንኮልና ሽንገላ ነበር:: እግዚአብሔርን እስኪሳደቡ ድረስም አደረሳቸው:: ቀናተኛና ንፉግም አሉት:: ከእግዚአብሔር ጸጋ፤ከዕውቀትም ተራቆቱ:: እርሱ /ሰይጣን/ ከመካዱ የተነሣ ከሕይወትና ከብርሃን ልብስ የተራቆተ ሆኗልና:: ጠቢብ እግዚአብሔር ግን ቀናተኛ ንፉግ አለመሆኑን ሰውን በአርአያችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር በማለቱ አስረዳ::

በሠርክ በገነት መካከል ሲመላለስ የእግዚአብሔርን ድምፅ በሰሙ ጊዜ አዳምና ሚስቱ /ሔዋን/ በገነት ዕፀዋት መካከል ከእግዜአብሔር ፊት ተሸሸጉ እንዲል መጽሐፍ እግዚአብሔርም ስሙ ቡሩክ /ምስጉን/ ነውና ለአዳም ድምፁን አሰማው:: ፍርሀትን የተመላ ይሆን ዘንድም በሚያስገርም ሁኔታ ተመላለሰ:: ዳግመኛም በፍርሀት ከመቃጠሉ የተነሣ ልቡ ቀለጠ::

እንደ ርኅሩኅና የልጅ ፍቅር እንዳሸነፈው አባት ቀጭን በሆነ ቃል አዳም ሆይ! ወዴት አለህ?[13] አለው:: ይህንም ማለቱ አዳም ያለበትን ቦታ የማያውቅ ሆኖ አይደለም:: ከምን ክፉ ምግባር ደረስህ ማለቱ እንጂ::

እግዚአብሔር በቀዳሚት ሰንበት በሰባተኛው ቀን ዐረፈ ማለቱም ካለው ፍጥረት ምንም እንዳልቀረ ያጠይቃል:: ባረካት፤አከበራት፤ቀደሳት ማለቱም ፍጥረታት ከተፈጠሩባቸው ዕለታት ይህች ዕለት /ቀዳሚት ሰንበት/ ዋጋ የለሽ ቀን እንዳትባል ነው::

የአባታችን የአዳምና የእናታችን የሔዋን መቅድም ተፈጸመ::

13 ዘፍ. ፫፥፱

## ምዕራፍ አንድ

## ገድለ አዳም ዘሚያዝያ

አንድ አምላክ በሆኑ በአብ፣በወልድ፣በመንፈስ ቅዱስ ስም አምነን ክብር ምስጋና ይግባውና እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ በሚያዝያ ወር[15] የሚነበብ የአዳምና የሔዋንን ገድል መጻፍ እንጀምራለን። ጸሎታቸው፣በረከታቸው ከወዳጆቻቸው ከሊቀ ጳጳሳችን ባስልዮስ ከንጉሣችን ኃይል ሥላሴ[16] ጋር ጸንቶ ይኑር ለዘለዓለም አሜን።

ከገነት ከወጡ በኋላ በእነርሱ ላይ የደረሰባቸውም በፈጣሪ በእግዚአብሔር ትእዛዝ በበአተ መዛግብት /ዕቃ ቤት/ መኖር ነበር። ምስጋና ይግባውና መጋቢ /ጠባቂ/ ነበራቸው። ፍጥረታትን ሁሉ የፈጠረ ሕያው እግዚአብሔር እርሱ በመሬት የምሥራቁ ክፍል ላይ በሦስተኛው ቀን ገነትን ተክሏልና፡ በምሥራቅ የዓለሙ የወጨረሻ ክፍልም ፍጥረት አይገኝም። ዓለምን ሁሉ የሰማይንም ጫፍ የምትዞር ውኃ ነበረች። ጥራቷም የዓለምን ጥልቅ ሁሉ ያሳይ ነበር። ሰው ከእርሷ በታጠበ ጊዜ በንጹሕነቷ ንጹሕ ይሆናል። ጨለማ በሆነ ጊዜም በነጭነቷ ነጭ /ብርሃን/ ይሆናል።

ይህችን ባሕር እግዚአብሔር በረድኤቱ አይለያትም ነበር። እርሱ ከሰው የሚመጣውን ያውቅ ነበርና፤ አዳም ከገነት እስኪወጣ ድረስም የሚያደርገውን ሕጉን መተላለፉንና በምድር መባዛቱን ያውቅ ነበር። ከእነርሱም ጻድቃን እንደሚሞቱ በኋለኛው ዘመንም እንደሚያስነሣቸው በንስሐ ከኀጢአት በሚመለሱበት ጊዜም በዚህ ውኃ እንደሚያያጠምቃቸው ያውቅ ነበር።

---

[15] የአባቶችን የአዳም ገድል የሚጀምረው ወርኃ ሚያዝያን መነሻ በማድረግ ነው። ምክንያቱም አዳም የተፈጠረበት በዚህ ዓለም ዘጠኝ መቶ ሠላሳ ዘመን ከኖረ በኋላ ያረፈበት በዚህ ወር ነውና። ስለሆነም ቤተ ክርስቲያናችን ሚያዝያ ስድስት ቀን ዓመታዊ በዓሉን ታከብራለች። ይህ ዕለትም ዕረፍቱ መሆኑን ልብ ይሏል።

[16] ብዙ ኢትዮጵያውያን ጸሐፍያን አንድን መጽሐፍ በሚጽፉበት ጊዜ የቤተ ክርስቲያኗን መሪ /ፓ ትርያርኩን/ የሀገሩን መሪ፤ቤተሰቦችንም በጽሑፉ ማስታወስ የተለመደ ነው። የገድለ አዳም ጸሐፊም መጽሐፉን የጻፈበት /የገለበጠበት/ ዘመን በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስና በዓፄ ኃይለ ሥላሴ የሥልጣን ዘመን በመሆኑ ስማቸውን አስከትሏቸዋል። ይህ መርህም የመጽሐፉን ዕድሜ በቀላሉ ከማሳወቁ በተጨማሪ ለጥናትና ምርምር የጐላ አስተዋጽኦ አለው፡፡ በሱብዐው ሊቃናት ከተጻፈ በኋላ ወደግእዝ የተተረጐመበት ዘመን በአቡነ ባስልዮስ በዓፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ሣይሆን አለመሆኑን ግን አንባቢ ያስተውሏል።

እግዚአብሔርም አዳምን ከገነት ባወጣው ጊዜ በደቡብ ከገነት ድንበር አላስቀመጠውም፡፡ ምክንያቱም አዳምና ሔዋን ወደ ባሕር ቀድመው ሔደው ከኀጢአታቸው ይነጹ ዘንድ እንዳይታጠቡ፡፡ ካልተገሰጹ ሕግ የተላለፉ መሆናቸውን ይረሳሉና፡፡ ዳግመኛም እግዚአብሔር አዳም በሰሜን ጫፍ ይኖር ዘንድ አልፈቀደም፡፡ የደቡብ ነፋስ በነፈሰ ጊዜ የጣፈጠ የገነት ዕፅ ሽታን በሰሜን በኩል ያወጣልና፡፡ እግዚአብሔር አዳምን የጣፈጠ የዕፀዋት መዓዛን እንዳያገኝ በዚያ አላደረገውም፡፡ አዳም ይህን ካገኘ መደፋፈሩን /ከሕግ መውጣቱን/ ይረሳዋልና፡፡ ስላደረገውም አይጸጸትም፤ የዕፀዋትን መዓዛ ይወዳልና፡፡ እግዚአብሔር ይኸን ያደረገው አዳም ሕግ ስለተላለፈ ይጸጸት ዘንድ ነው፡፡

ዳግመኛም ይቅር ባይ ቸር እግዚአብሔር እርሱ ባወቀው ፍጥረቱን ይመግባል፡፡ አባታችን አዳምን ከገነት በስተምዕራብ በኩል አስቀመጠው፡፡ የገነት ምዕራባዊው ክፍል ፍጹም ሰፊ ነበርና፡፡ እግዚአብሔርም በቋጥኙ ያድር ዘንድ አዘዘው፤ ይህችውም ከገነት በታች ያለች በአተ መዛግብት /ዕቃ ቤት/ ናት፡፡ አባታችን አዳምና እናታችን ሔዋንም ከገነት በወጡ ጊዜ የሚረግጡትን አያውቁም ነበር፡፡ ከገነት በር ውጪ በደረሱ ጊዜ በፊታቸው ሰፊ የሆነች ምድርን ተመለከቱ፤ ታላቅና ታናሽ ድንጋዮችን፣ አሸዋዎችንም ተመልክተው ፈጽመው ፈሩ፡፡ ከደረሰባቸው ፍርሀት የተነሣም በግንባራቸው ወደቁ፤ እንደሞተ ሰውም ሆኑ፡፡ በዕፀዋት ባሸበረቀች ገነት ውስጥ ነበሩና፡፡ ሰውነታቸውን በማያውቋት ባልተመለከቷት በኋላፊዋ ምድር አይተው እነርሱ ብርሃናዊት ጸጋን የተመሉ ነበሩና ማስተዋልም ነበራቸውና ፈሩ፡፡

ስለዚህ እግዚአብሔር ይቅር አላቸው፤ በተመለከታቸው ጊዜም በገነት በር ወደቁ፡፡ እግዚአብሔር ወደ አባታችን አዳምና ወደ እናታችን ሔዋን ቃሉን ላከ፡፡ ዐምስት ቀን ተኩል በሚለው ቃል ኪዳኑም ከወደቁበት አስነሣቸው፡፡ እግዚአብሔር አባታችን አዳምን አለው፡- በዚህች ምድር ቀንና ሌሊን ዓመታትንም ሠራሁ፡፡ ቀኖቹ፤ዓመቶቹ እስኪፈጸሙ ድረስ አንተ በእርሱ

ትኖራለህ፤ አንተን የፈጠረ ቃሌንም አልካለሁ ሕጉን ባፈረስህ ጊዜ ከገነት ያወጣህ እርሱ ነው:: በወደቅህ ጊዜም አንሣህ፡ዐምስት ቀን ተኩል ሲፈጸምም የሚያድንህ እርሱ ነው አለው::

አዳም ይህን ቃል ከእግዚአብሔር በሰማ ጊዜ ዐምስት ቀን ተኩል የሚለውን ትርጓሜ አላወቀም ነበር:: ዓለም እስኪፈጸም ድረስ ዐምስት ቀን ተኩለ ይሆነዋልን? እያለ ያስብ ነበር:: አዳምም ትርጉሙን ከእግዚአብሔር ያገኝ ዘንድ አለቀሰ:: እግዚአብሔርም ከዐምስት ሺህ ዐምስት መቶ ዓመት በኋላ እንደሚመጣ የእርሱን ሥጋ ተዋሕዶ እርሱንም፣ ዘሩንም እንደሚያድነው ተረጐመለት::

እግዚአብሔርም ከዚህ ኪዳን /ውል/ በፊትና አዳም ከገነት ከመውጣቱ በፊት ሔዋን ወስዳ /ቀጥፋ/ ለአዳም ካበላችው ዕፀ አጠገብ ነበር:: አዳምም ከገነት በመውጣቱ ኃላፊ /ሟች/ ሆነ:: በዚህን ጊዜም እግዚአብሔር ለወጣት፤በተለወጠች ጊዜም ደረቀች:: በዚያን ጊዜም ወደ እርሱ ሄደ:: ፈራ፤ ተንቀጠቀጠም፤ ወደቀም፤ እግዚአብሔርም በቸርነቱ አነሣው፤ ቃል ኪዳንም ገባለት::

ዳግመኛም አዳም በገነት በር ነበር:: የሚያብለጨልጭ የእሳት ሰይፍ በእጁ የያዘ ኪሩብንም ተመለከተ:: ኪሩብም ተቆጣ፤ ፊቱንም ቋጠረበት:: አዳምና ሔዋን ከእርሱ የተነሣ ፈሩ:: ይገድላቸው ዘንድ እንደሚሻም አሰቡ:: ከመፍራታቸው፡ከመንቀጥቀጣቸው የተነሣ በግንባራቸው ወደቁ:: እርሱ ግን ፈጽሞ ራራላቸው:: ይቅርም አላቸው፤ ተመልሶም ወደሰማይ ዐረገ:: አዳምና ሔዋንም ከእግዚአብሔር ዘንድ ይቅርታን ፈለጉ:: ኪሩብም እግዚአብሐር ሆይ! አንተ የገነትን በር እጠብቅ ዘንድ ላከኸኝ በእጄም የእሳት ሰይፍ ነበር:: ባሮችህ አዳምና ሔዋን በተመለከቱኝ ጊዜ በፊታቸው ወደቁ ፤እንደ በድንም ሆኑ:: ጌታዬ ሆይ! በባሮችህ ላይ የምታደርገው ምንድን ነው? አለ:: እግዚብሔርም

ራራላቸው፤ ይቅርም አላቸው:: መልአኩንም ገነትን ይጠብቅ ዘንድ ላከው:: የእግዚአብሔር ቃልም ወደ አዳምና ሔዋን መጣ አነሣቸውም::

እግዚአብሔር አዳም ከዐምስት ቀን ተኩል በኋላ ቃሌን እልካለሁ አድንኅምአለሁ ያልሁህን አጽንተህ ያዝ:: ባዘዝሁህ በዚህች መሬትም ኑር አለው:: አዳምም ይህን ቃል ከእግዚአብሔር በሰማ ጊዜ በእግዚአብሔር ቃል ተጽናና:: እርሱ ያድነዋልና:: አዳምና ሔዋን ግን ከመኖሪያቸው ከገነት በመውጣታቸው አለቀሱ:: አዳምም የተለወጠ ሥጋውን በተመለከተ ጊዜ እርሱም ሔዋንም መራራ ለቅሶን አለቀሱ:: ባደረጉት ስሕተትም ተጸጸቱ:: እነርሱም ወርደው በአተ መዘግብትን ረገጡ [ደረሱ]:: አዳምም በአተ መዘግብት በደረሰ ጊዜ ስለሰውነቱ አለቀሰ::

ሔዋንንም በዚህ ዓለም ለእኛ የሆነ የእስር ቤታችን፣የመደብደቢያ /የመሰቃያ/ ቤታችንን ተመልከቺ አላት:: ከመስፋት ይልቅ ምንኛ ጠባብ ነው? ከገነት ቦታዎች ይልቅ ምንኛ ድንጋያማ ነው? ከገነት ብርሃን ይልቅ በዚህ ቤት ያለ ጨለማ ከየት የተገኘ ነው? ከእግዚአብሔር ቸርነት የተነሣ በእኛ ላይ የምትጋረድ ድንኳን ከየት የመጣች ናት? ይህች መሬት በድንጋይ የተሸፈነች ናት:: ያች ምድር /ገነት/ ግን ባማሩ፣በሚጣፍጡ ፍሬያት የተሞላች [የተሸፈነች] ናት::

አዳምም ሔዋንን በዓይኖችሽ ተመልከቺ:: ዓይኖቻችን ሰማያውያን መላእክትን ያለማቋረጥ ሲያመሰግኑ ይመለከቱ ነበር:: አሁን ግን ይህን የምንመለከት አይደለንም:: ዓይኖቻችን ሥጋውያን ሁነዋልና:: እንደቀደመው የሚመለከቱ አይደሉም::

አባታችን አዳም «እናታችን ሔዋንን መጀመሪያ በገነት በነበርን ጊዜ ሥጋችን የት ነበር?» አላት:: ከዚህ በኋላ አዳም ወደማደሪያው ይገባ ዘንድ አልወደደም፤ወደ ድንኳኑ ግን ይገባ ነበር:: በእግዚአብሔር ትእዛዝ እንጂ ፈጽሞ አልገባም ነበርና:: በዚህች ባላድር ሁለተኛ ሕግ ተላላፊ እባላለሁ ይል ነበርና::

አዳምና ሔዋንም ገብተው ለእኛ በማይታወቅ ቋንቋ ይጸልዩ ነበር:: እነርሱ ግን ያውቁት ነበር:: በሚጸልዩበት ጊዜም አዳም ዓይኖቹን አነሣ፤በእርሱ ላይ የተጋረደች [የተጠለለች] የድንጋይ ድንኳንም ተመለከተ፤ ሰማይንና የእግዚአብሔርን ፍጥረታትንም ሁሉ ያይ ዘንድ አልቻለም:: አዳምም እስከሚወድቅ፣የሞተ ሰውም እስከሚመስል ድረስ ደረቱን ደቃ:: ሔዋንም የሞተ ሰው መስላት፤በአዳም ላይም ታለቅስ ነበር:: ቁማም እጇን ወደ እግዚአብሔር ዘረጋች:: ምሕረትን፤ ቸርነትን ከእርሱ ታገኝ ዘንድ ጌታዬ ሆይ! የሠራሁትን ኀጢአት ይቅር በለኝ፤ በእኔ ላይ ያለች በደሌንም አታስብብኝ:: በዚህ በደሌ አገልጋይህ አዳምን ከገነት እንዲወድቅ /እንዲባረር/ አድርጌዋለሁና:: ከብርሃን ወደ ጨለማ፣ከደስታ ወደ እስር ቤት መርቼዋለሁና:: ጌታዬ ሆይ! ወደ ወደቀው አገልጋይህ ተመልከት:: በእኔ ምክንያት ሕግህን በመተላለፉ ይጸጸት፣ያለቅስ፣ዘንድ በዚህ ቅጽበት ነፍሱን አትውሰድ:: ከመሞቱ በፊት በቀኖና ይጸና፣ፈቃድህንም ይፈጽም ዘንድ ተወወው እንጂ አለች::

በዚህ ቅጽበት የማታስነሣው ከሆነ ግን ከእርሱ ጋር ነፍሴን ውሰድ:: በዚህ እስር ቤት አንዲቱ እኔን ለብቻዬ አትተወኝ እኔ በዚህ ዓለም ከእርሱ ጋር ነው እንጂ ብቻዬን ቆሜ መኖር አልችልምና:: አቤቱ ጌታዬ ሆይ! አንተ በእርሱ ላይ እንቅልፍን አመጣህ:: በእንቅልፍ ላይ እያለም ከጎኑ አንዲት ዐፅምን ነሣህ:: ቦታውንም በመለኮታዊ ኀይልህ [ጥበብህ] ሥጋን መላኸው:: ወስደኸም በእርሱ አምሳል የምታበራ፣የምታውቅ፣የምትናገር ሴት አድርገህ እኔን ከዚህች ዐፅም ፈጠርኸኝ::[18]

አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ! እኔ አንዲት ነኝ፤ ፈጣሪያችንም አንተ ነህ በአንዲት ዕለት [ዐርብ ቀን] ሁለታችንንም የፈጠርህ አንተ ነህ:: ሕግ በመተላለፋችን በምንኖርባት በዚህች ኀላፊት ምድር ከእኔ ጋር ይኖር ዘንድ እግዚአብሔር ሆይ! ሕይወትን ስጠው:: ሕይወትን የማትሰጠው ከሆነ ግን እኔንም ከእርሱ ጋር ውሰደኝ:: በአንድ ቀን እንደፈጠርኸን በአንድ ቀን እንሞት

18 ዘፍ ፪÷፳፩

ዘንድ እያለች በሚቃጠል ልብ ታለቅስ ነበር። ከኃዘኗ ብዛት የተነሣም በአባታችን በአዳም ላይ ትወድቅ ነበር።

እግዚአብሔርም ወደ እነርሱ ተመለከተ፤ ከኃዘናቸው ብዛት የተነሣም እነርሱ ራሳቸውን ገድለዋልና። እግዚአብሔርም ያድናቸው፣ ያረጋጋቸውም ዘንድ ወደደ። ተነሥተው ይቆሙ ዘንድም ቃሉን ላከ። በዚያን ጊዜም እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ተነሡ አላቸው። እናንተ በፈቃዳችሁ ሕጌን ተላለፋችሁ። ካኖርኋችሁ ከገነት ለመውጣት እስከትበቁ ድረስ እናንተ ከእኔ ይልቅ እምላከነትን፣ ታላቅነትን፣ ትዕቢትን በመሻት በፈቃዳችሁ በደላችሁ። እኔም ብርሃናዊት ጸጋችሁን ገፈፍኋችሁ፤ ከገነት ወደ ምታስጨንቅ ድካምም ወዳለባት ወደዚህች ምድር አመጣኋችሁ። እናንተ ትእዛዜን ባታፈርሱ፣ሕጌንም ብትጠብቁ፣አትቅረቧት ካልኋችሁ ዕፅም ባትበሉ ከእርሱ ይልቅ ያማረ የገነት ዕፀዋት ሁሉ የእናንተ ነበሩ።[19]

ተፈጥሮውን ያልጠበቀ፣በሃይማኖቱ ያልጸና ሰይጣን ግን ለእኔ መልካም ነገር የለውም። እኔ ፈጠርሁት ግን ገሥጽሁት፤ ጣልሁትም። ከእርሱ ስምታችሁ እስከትበሏት ድረስ ዕፀ በለስን ለዓይናችሁ አሳምሮ ያሳያችሁም እርሱ ነው። በዚህም የተነሣ ይህ ሁሉ መከራ ችግር ደረሰባችሁ። እኔ አምላክ፣ፈጣሪም ነኝና። ፍጥረታትን በፈጠርሁ ጊዜ አጠፋቸው ዘንድ አልወደድሁም። ባስቆጡኝ ጊዜ ግን ንስሓ እስኪገቡ ድረስ በሚያስደንቅ በትር መታኋቸው። በስሕተታቸው ከጸኑ ግን እስከ ዘለዓለም ድረስ ይጠፋሉ።

ይህን ነገር ከእግዚአብሔር በሰሙ ጊዜ አዳምና ሔዋንም ፍጹም ለቅሷቸውን አስወገዱ። ልባቸውም በእግዚአብሔር ጸና። እግዚአብሔር እንደ እናትም፣እንደ አባትም ሆኖላቸዋልና። ስለዚህም በፊቱ አለቀሱ። ይቅርታውንም ፈለጉ። በዚህ ጊዜም እግዚአብሔር ይቅር አላቸው። አዳም ሆይ! እኔ በቃል ኪዳኔ ማልሁልህ፤ ከእርሱም አልመለስም። ቃል ኪዳኔ እስኪፈጸም ጊዜም ወደ ገነት አልመልስህም፤ ይኸውም ዐምስት ቀን ተኩል

---

[19] ዘፍ ፪÷፲፮

ነው፡፡

አዳምም እግዚአብሔርን አለው፡- አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ! በገነት እኖር ዘንድ አንተ ፈጠርኸኝ ፤አበጃጀኸኝ፤ትእዛዝህን ከመተላለፌ በፊትም ስም አወጣላቸው ዘንድ አራዊትን ወደ እኔ አመጣኋቸው፡፡ ጸጋህም በእኔ ላይ ነበረች፡፡ እንደ ትእዛዝህም ሁሉን በየስማቸው ጠራኋቸው [20]፤ ሁሉንም ለእኔ እንዲሰግዱ [እንዲገዙ] አደረግህ፡፡ እግዚአብሔር ሆይ!ዛሬ ግን ትእዛዝህን ከተላለፍሁ በኋላ ሁሉም ይበሉኝ ዘንድ ተነሣሱ፤ ሔዋን አገልጋይህንም እንዲሁ፡፡ ሕይወታችንንም ከምድር ገጽ ሊያጠፏት ነው፡፡ አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ! እኔ እለምንሃለሁ፡፡ ከገነት እንዳስወጣኸን በኃላፊቷ ምድርም እንዳስቀመጥኸን አራዊት በእኛ ላይ እንዲሠለጥኑ አትፍቀድላቸው አለ፡፡

እግዚአብሔርም ይህን ቃል ከአዳም በሰማ ጊዜ ይቅር አለው፡፡ እውነቱን እንደተናገረም ዐወቀ፡፡ በመተላለፋቸው ምክንያት እነርሱን ከተቆጣ አራዊት ይበሏቸው ነበርና፡፡ እግዚአብሔርም እንስሳትን፤አራዊትን፤አዕዋፍን፤የምድር ተሐዋስያንን ሁሉ ወደ አዳም ሂደው ይታረቁ ዘንድ በእርሱ፤በሔዋን እና በዘሩም ላይ እንዳይከፉባቸው አዘዛቸው፡፡

ከአራዊት ጋር ወደ አዳም እንዳትደርስ /እንዳትሄድ/ ከተቆጣት / ከረገማት/ ከእባብ በቀር ሁሉም ሂደው እንደ እግዚአብሔር ትእዛዝ ሰገዱለት፡፡ አዳም ግን አለቀሰ፡፡ እንዲህም አለ፡- እግዚአብሔር ሆይ! እኛ በገነት ነበርን፡፡ አእምሮአችንም ታላቅ ነበር፡፡ መላእክትንም ሲያመሰግኑ እንመለከት ነበር፡፡ ዛሬ ግን እንደለመድነው ማየት አንችልም፡፡ ወደ መሬት በወረድን ጊዜ ፍጥረታት ሁሉ ተሰወሩብን አለው፡፡

እግዚአብሔር አምላካችንም አዳምን እንዲህ አለው፡፡ «በመታዘዝ ሕይወት አያለህ ብርሃናዊት ጸጋ በውስጥህ ነበረች፡፡ ስለዚህም የራቁትን ፍጥረታት አቅርበህ ትመለከት ነበር፡፡ ሕገ እግዚአብሔርን ከተላለፍህ በኋላ ግን፡ብርሃናዊት ጸጋህ ተገፈፈች፡፡ በዚህም ጊዜ የራቀውን የማየት ጸጋ በአንተ ላይ

---

[20] ዘፍ ፪÷፲፱

የቀረ አይደለም:: እንደ ሥጋ ዕቅም /ጸጋ/ የቅርቡን ትመለከታለህ እንጂ:: ይኸም እንስሳዊ ዕውቀት ነውና::» አዳምና ሔዋንም ይህን የእግዚአብሔርን ቃል በሰሙ ጊዜ ወጥተው በፊቱ ሰገዱ:: በሚያዝን ልቡናም አመሰገኑት:: እግዚአብሔርም ቃሉን /ንግግሩን/ ከእነርሱ አቆመ::

አዳምና ሔዋንም ከማደሪያቸው ወጥተው ወደገነት ደረሱ፤ ከዚህ መውጣታቸውን እያስተዋሉም ቆሙ:: ከዚህ በኋላ አዳምና ሔዋን ከገነት ወደ ሰሜን ጫፍ ሄዱ::[21] ከዕፀ ሕይወት ሥር ወጥቶ ገነትን የሚያጠጣውን ውኃም አገኙ:: በመሬት ላይም ከአራት ተከፍሎ ይወጣ ነበር:: መጥተውም ከውኃው ደረሱ፤ አዩትም:: በገነት ካለች ከዕፀ ሕይወት ሥር እንደሚፈልቅም ዐወቁ:: አዳምም ፊጽሞ አለቀሰ:: ከዚህ በመለየቱም ፊቱን ጸፋ /መታ/::[22] ሔዋንንም «ይህን ፍጹም ግርፋት በእኔም፣በአንቺም፣በዘራችንም አደረስሽብን» አላት:: ሔዋንም «እስከማልቀስና ይህን ቃል እስከማለት ያደረሰህ ምን ተመልክተህ ነው;» አለችው:: ሔዋን ሆይ! ከገነት በእኛ ዘንድ ያለውን ይህን ውኃ አትመለከችውምን? ገነትን አጠጥቶ ወደ ውጪ ይወጣል:: እኛ በገነት ስንኖር ከእርሱ አንሻም ነበር፡ ዛሬ በዚህ ኃላፊ ምድር ከደረስን በኋላ ግን እርሱን እንሻለን፤ለሥጋችንም እንሠራለን አላት::

ሔዋንም ይህን ቃል ከእርሱ በሰማች ጊዜ አለቀሰች፤እርሱም እንዲሁ:: ከልቅሷቸው ብዛት የተነሣም ውኃው ውስጥ ወደቁ:: ሰውነታቸውን ያጠፉ ዘንድ እንዳይመለሱ፤እነርሱ ፍጥረታትን ከሚያዩ ይልቅ ራሳቸውን ማጥፋት ወስነዋልና:: ይቅር ባይ እግዚአብሔርም እነርሱን በውኃ ወድቀው ለሞት ተቃርበው ተመለከተ:: መልአኩን ልኮም ከውኃው አወጣቸው:: መልአኩም ወደ እግዚአብሔር ወጥቶ አቤቱ «እግዚአብሔር ሆይ!ባሮችህ ራሳቸውን አጥፍተዋል» አለ:: እግዚአብሔርም ቃሉን ወደ አዳምና ወደ ሔዋን ላከ:: ከሞትም አዳናቸው:: ከተነሡ በኋላ አዳም «አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ!በገነት

[21] የእንግሊዝኛው ትርጉም ግን ይኸን «...Adam and Eve went from before the gate of the garden to the southern side of it......»

[22] የእንግሊዝኛው ትርጉም «...Adam and beat his chest:-... አዳም ደረቱን ደቃ::» ይገልጸዋል:: /Ibide– chapter IX÷4pp-9/

ስንኖር ይህን ውኃ አንሻም ነበር፡፡ ምሕረትህ ከእኛ ጋር ነበረችና፤ይህን አላጣንም ነበር፡፡ ወደዚህ ምድር ከመጣን በኋላ ግን ያለውኃ መኖር አንችልም »አለ፡፡

እግዚአብሔርም አዳምን አለው፡፡ «በሕጌ ጥላ ሥር እያለህ አንተ ብርሃናዊ መልአክ ነበርህ፤ውኃንም ተጠቅመህ አታውቅም ነበር፡፡ ከትእዛዜ ከወጣህ በኋላ ግን ያለውኃ ትኖር፣ሥጋህንም ታረካው፣ታሳድገውም ዘንድ አትችልም፤እርሱ /ሰውነትህ/ እንደ እንስሳ በውኃ የሚኖር ሆኗልና፡፡» አዳምና ሔዋንም ይህን ቃል ከእግዚአብሔር በሰሙ ጊዜ መራራ ለቅሶን አለቀሱ፡፡ አዳምም ለሁለተኛ ጊዜ ውስጡን እስኪያዩ ድረስ ወደ ገነት ይመልሰው ዘንድ ምሕረትን ከእግዚአብሔር ዘንድ ፈለገ፡፡ እግዚአብሔርም አዳም ሆይ! ቃል ኪዳን ገብቼልሃለሁ፤ይህ ቃል ኪዳን ከተፈጸመ በኋላ አንተን ወገኖችህን ጻድቃንንም ወደ ገነት አስገባቸዋለሁ አለው፡፡ ከዚህ በኋላ ከአዳም ጋር የነበረውን ንግግር አቆመ፡፡

አዳምና ሔዋንም ከጽሙ፣ ከላቡ /ከሙቀቱ/ ብዛት የተነሣ ሰውነታቸው ተቃጠለ፡፡ አዳምም ሔዋንን እስከንሞት ድረስ ከእርሱ አንጠጣም አላት፡፡ ሔዋን ሆይ!ይህ ውኃ በሆዳችን በገባ ጊዜ የእኛ፣ከእኛም በኋላ የሚመጣው የዘራችንም ግርፋት ይበዛል አላት፡፡ አዳምና ሔዋንም ወደ ውኃው አቀኑ፤ግን ከውኃው ፈጽመው አልጠጡም፡፡ መጥተውም ወደ ማረፊያቸው ገቡ፡፡ አዳምም ሔዋንን ያያት ዘንድ አልቻለም ድምጿን ይሰማ ነበር እንጂ እንደዚሁም ሔዋን አዳምን አታየውም ነበር፡፡ ድምፁን ትሰማ ነበር እንጂ፡፡ አዳምም አለቀሰ፤ተቸገረ፤ደረቱንም ይመታ ነበር፡፡

ተነሥቶ በመቆምም ሔዋን ሆይ!የት ነሽ; አላት፤እርሷም በዚህ ጨለማ ውስጥ ቆሜያለሁ አለችው፡፡ እርሱም በገነት በነበርን ጊዜ የነበረችንን ብርሃናዊት ጸጋ አስቢ፡፡ ሔዋን ሆይ! በገነት ውስጥ በነበርን ጊዜ በእኛ ላይ የነበረችውን ጸዳል አስቢ፤ ሔዋን ሆይ! እኛ በመካከላቸው ሳለን በገነት ውስጥ

ያበሩ የነበሩ ዕፀዋትን አስቢ፤ ሔዋን ሆይ በገነት ውስጥ ስንኖር ሌሊትና ቀን የማናውቅ እንደነበርን አስቢ፤ ሔዋን ሆይ! ለእኛ ታበራ የነበረች ውኃም የሚፈልቅባት ዕፀ ሕይወትን አስቢ፤ ሔዋን ሆይ የገነትን ምድር ብርሃኑንም አስቢ።

ሔዋን ሆይ! በውስጧ ስንኖር ጨለማ ያልነበራት ገነትን አስቢ፤ ዛሬን ግን ይህ ሁሉ የለም አላት። ሔዋን ሆይ! ከዚህ ምድር በደረስን ጊዜ ግን ጨለማ ከበበን፤እርስ በርሳችንም አንተያይም። ከዚህ ምድር ኑሮ ለእኛ ምንም መልካም ነገር የለንም። አዳምም ሰውነቱን መታ። እርሱም፣ ሔዋንም ሌሊቱን ሁሉ እስኪነጋ ድረስ አለቀሱ። ከሌሊቱ ርዝመት የተነሣ አዳምና ሔዋን ተጨነቁ። እንደሚያዝያ[23] ሌሊት ሆኗልና። በቤት ከነበረው ከጨለማውና ከኃዘኑ ብዛት የተነሣም አዳም በቤተመዛግብት ውስጥ ሰውነቱን መታ፤ /አጐሰቆለ/። እንደሞተ ሰውም ሆነ። ሔዋንም ከመሬት እንደወደቀ ድምፁን በሰማች ጊዜ በእጆቿ ትዳስስ ጀመረች። እንደሞተ ሰው ሆኖ አገኘችው። ፈርታ፣እንደዲዳም ሆነች። በእርሱ ዘንድም ተቀመጠች።

ቸር አምላክ የአዳምን መሞት ከጨለማው ፍርሀት የተነሣ የሔዋንንም ዲዳነት ተመለከተ። የእግዚአብሔር ቃልም ወደ አዳም መጣ። ከሞቱም አስነሣው። የሔዋን አፍም ከዲዳነቱ ተፈታ። አዳምም በማደሪያው ቆመ። እንዲህ አለ፡- አቤቱ ጌታችን ሆይ! ብርሃን ከእኛ ለምን ተወገደ? ጨለማስ ለምን ገባን? በዚህ ጽኑ ጨለማስ በምን ተውኸን? አንተ እግዚአብሔር ስትሆን በዚህ ጨለማ የእኛን መሰቃየት ትሻለህን? አቤቱ አምላካችን ሆይ! ጨለማ ወደ እኛ እስኪገባ፣ እርስ በርሳችንም መተያየት እስኪሳነን፣ ረዳትነትህ የት አለ? እኛ በገነት እያለን ጨለማን ፈጽሞ አይተን አናውቅምና፤እስከማታየኝ ድረስም ከሔዋን አልተሰወረም፤እርሷም እስከማላያት ድረስ ከእኔ አትሰወርም ነበርና።

---

[23] የእንግሊዘኛውም ትርጉም ሚያዝያ /Miyazia/ የሚለውን ቃል እንጅ የሚለውን አልተጠቀመም። ይኸም ከግእዙ መተርጉሙን እንድ ማሳያ ነው።

በመካከላችንም ልዩ ጨለማ አያልፍም ነበርና፡፡ እኔም፣ እርሷም በአንዲት ብርሃን ውስጥ ነበርን እንጂ፡፡ እርሷ ታየኛለች፤ እኔም አያታለሁ፡፡ ወደዚህ ቦታ በመጣን ጊዜ ግን እኔ እስከማላያት ድረስ፣እርሷም እስከማታየኝ ድረስ ጨለማ ገባብን፤በመካከላችንም ለየን፡፡ አቤቱ ፈጣሪያችን ሆይ! በዚህ ጨለማ የእኛን መሰቃየት ትፈልጋለህን?

ቸር ይቅር ባይ እግዚአብሔርም የአዳምን ቃል ሰማው፡፡ አዳም ሆይ! ዲያብሎስ በትእዛዜ ሥር በነበረና ጥሩ በነበረ ጊዜ ብርሃናዊት ጸጋ በእርሱ በሰራዊቱም ላይ ነበረች፡፡ ከትእዛዜ በወጣ ጊዜ ግን ብርሃናዊት ጸጋውን ገፈፍሁት፡፡ ጨለማም ሆነ፤ በሰማያዊት ኢየሩሳሌም ቦታ ውስጥ ወደ ምድር አወረድሁት፡፡ በእርሱ ላይ የሚመላለስ ሆነ፡፡

አዳም ሆይ! አንተም በሕጌ ጥላ ሥር ሆነህ በገነት ስትኖር ብርሃናዊት ጸጋ ነበረችብህ፡፡ ከሕግ መውጣትን ባየሁ ጊዜ ግን ብርሃናዊት ልብስህን ገፈፍኋት፡፡ ቸርነቴ ግን በጨለማ አልተወህም ይህን ሥጋ አደረግሁልህ እንጂ፡፡ ዋዕየ ፀሐዩን፣ብርዱን የሚችል /የሚቋቋም/ ይህን ቆዳም ፈጠርሁልህ እንጂ[24]፡፡ ቁጣዬን በአንተ ላይ ባጸና ኖሮ ባጠፋሁህ፣ በጨለማም በተውኩህና በገደልኩህ ነበር፡፡ ነገር ግን በቸርነቴ እንዲህ አደረግሁህ፡፡ አዳም ሆይ! ትእዛዜን በተደፋፈርህ ጊዜ ከገነት አስወጣሁህ፤ ወደዚህች ምድርም አስወጣሁህ፡፡ በዚህች ቦታም ታድር ዘንድ አዘዝኩህ[25]፡፡ ሕጌን እንዳፈርስ፣አንተንም እንዳታለለ እንደ ዲያብሎስ ጨለማ ወደ አንተ ገባ፡፡ አዳም ሆይ!ይህች ሌሊት እስከ ዘለዓለም የምትረዝም አይደለችም፤ዐሥራ ሁለት ሰዓት ናት፡፡ እንጂ ሲያልቅም ቀን ይተካልና አትጨነቅ፣አትናወጽ፣በልብህም እኔ እንደማሰቃይህ አታስብ፡፡ ልብህን አጽና፤አትፍራ፤ይህ ጨለማ ብትር/ግርፋት/ አይደለምና፡፡ እኔ ቀንን ፈጠርሁ፡፡ ፀሐይንም አንተና ልጆችህ ስትሠሩ ያበራ ዘንድ አዘጋጀሁ እንጂ፡፡

[24] ዘፍ ፫፥፳፩

[25] ዘፍ ፫፥፲፰

እኔ ሕጌን ተላልፈህ ወደዚህች ምድር እንደምትወርድ አውቅ ነበር::[26] ነገር ግን በመውደቅህ አላስቃይህም፤አልፈርድብህም፤ከብርሃን ወደ ጨለማ፣ ከገነት ወደዚህች ምድር መውጣትህ አያስደንቅህ፡፡ ብርሃንን አደረግሁልህ፤እንደ አንተ ብርሃናውያንን አወጣ ዘንድ አልወደድሁም፤ነገር ግን አንተ አንዲት ዕለት ትእዛዜን አልጠበቅህም፡፡ ፍጥረታትን ፈጽሜ አስከቀድሳቸው፣አስከባርካቸው ድረስ እንዳትበላ ካዘዝሁ ከዕፀ በለስ በላህ፡፡ ነገር ግን ስራዊቱን ያሳተ ሰይጣን ዳግመኛ አንተንም እንደሚያስትህ አውቅ ነበር፡፡ ስለሆነም ወደ ዕፀ በለስ እንዳትቀርብ አመለከትሁህ፡፡ ከእርሱ እንዳትበላ፣የእርሱን ነገር እንዳትቀበልም፣እንዳትሰግድለትም፡፡ እሺም እንዳትለው ነገርሁህ፡፡ አዳም ሆይ ባልነግርህ ስለ ዕፀ በለስ ያለ ትእዛዜ ብተውህ መሰናከሉ በእኔ ምክንያት በሆነ ነበር፡፡

ተመልሰህም እኔን ትቆጣለህ፤ነገር ግን እኔ አዘዝሁህ፤መከርሁህም፤ አንተ ግን ወደቅህ፡፡ ፍጥረቶችም በአንተ ይሰናከላሉ፡፡ አዳም ሆይ! እኔ ቀንን ፈጠርሁልህ፤ከአንተ በኋላ ለሚነሡ ልጆችህም የሚያስጨንቃቸውን /የሚያስፈልጋቸውን/ ሁሉ ይሠሩ ዘንድ፣ሌሊትም ከሥራቸው ዕረፍት ትሆናቸው ዘንድ፣አውሬም በሌሊት ወጥቶ ምግቡን ይፈልግ ዘንድ ይሄዳል፡፡ አዳም ሆይ! ለጨለማው ጥቂት ቀረ፡፡ ቀንም ይገለጣል አለው፡፡

አዳምም «አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ! ነፍሴንም ውሰዳት ይህን ጨለማም ፤ ጨለማ ወደ ሌለበት ቦታም አውጣኝ» አለ፡፡ እግዚአብሔር አምላክም «አዳምን እውነት እውነት እልሃለሁ፤በአንተ ላይ የወሰንሁት፣የገባሁልህም ቃል ኪዳን ሲፈጸም ይህች ጨለማ ለሁል ጊዜ ከአንተ ትወገዳለች፡ አድንህምአለሁ ፤ዳግመኛም ወደ ገነት እመልስሃለሁ፡፡ ከወደድኸው ጨለማም ከሌለበት ቦታም አደርስሃለሁ፡፡[27] ይኸውም መንግሥተ ሰማያት ነው፡፡»አለው፡፡

---

[26] ዮሐ ፩፥፳፩
[27] ዮሐ ፲፱፥፵፯

ዳግመኛ እግዚአብሔር አዳምን አለው:: «ይህን ሁሉ ድካም ፈተና የምትቀበለው ትእዛዜን በመተላለፍህ ነው:: ከሰይጣን እጅ አልፈታህም፤ አላድንህም፤ እኔ ከሰማይ በወረድሁ፣ ከዘርህም ሥጋን በተወሐድሁ ጊዜ አንተ የደከምኸውን ድካም /መከራ/ እቀበላለሁ:: በዚህች ቦታ በአንተ ላይ የደረሰች ይህች ጨለማም በእኔ ላይ ትደርሳለች::[28] በመቃብር ውስጥም እንደወገኖችህ ዓመታት፣አዝማናትና ወራት እንደሌሉኝ እሆናለሁ:: አንተንም ለማዳን እንደሰው ልጆች እቆጠራለሁ::» አለው:: እግዚአብሔርም ከአዳም ጋር ንግግሩን አቆመ::

አዳምና ሔዋንም ከእግዚአብሔር ቃል /አነጋገር/ የተነሣ ፈጽመው አዘኑ:: እርሱ ላይ የተወሰነው የጊዜ ገደብ እስኪፈጸም ድረስ ወደ ገነት አይመለስምና:: ይልቁን ስለ እነርሱ ድኅነት መከራን እንደሚበቀል እግዚአብሔር ያላቸውን በሰሙ ጊዜ አዘኑ:: ከዚህ በኋላ አዳምና ሔዋን ከማደሪያቸው መቆምን አልተውም፤ ፀሐይ እስኪወጣላቸው ድረስም ያለቅሱ ነበር:: ብርሃን በወጣ ጊዜም ልባቸው ተመለሰ፤ ፍርሀታቸውም ከእነርሱ ተወገደ:: ልባቸውም ጸና፣አዳምም ከቤት ይወጣ ጀመር:: በቤቱ በር ውጪ በመጣ ጊዜም ፊቱን ወደ ምሥራቅ አዙሮ ቆመ:: ፀሐይን ተመለከተ፤ ወጣችም፤ የምታልብ /የምታቃጥል/ ነበረች:: ሥጋውንም አቃጠለችው:: ከማላቧ / ከማቃጠሏ/ የተነሣም ፈራ:: በልቡም ለቅጣት እንደወጣች አሰበ:: ከዚህም የተነሣ አለቀሰ፤ደረቱንም መታ፤ በፊቱም፤ ከመሬት ወደቀ::

እንዲህ እያለም ይለምን ነበር:: «አቤቱ አምላኬ ሆይ አትቅጣኝ፤አታቃጥለኝ፤ሕይወቴን ከዚህች መሬት አትውሰድ::» እርሱ ይህች ፀሐይ አምላክ እንደሆነች አስቧልና:: እርሱ በገነት ውስጥ ሲኖር የእግዚአብሔርን ቃል ድምፁን በሰማ ጊዜ ከድምፁ የተነሣ አይፈራም፤ የፀሐይን ጸዳልም አይመለከትም ነበርና:: በኋላ ግን ከሰውነቱም ላብ ይወጣ ነበር:: ስለዚህም ባላበው ጊዜ ከፀሐይ የተነሣ ፈራ:: እግዚአብሔር በእርሱ ላይ ይኸን



[28] ሉቃ ፳፫+፵፬

እስከወሰነው ጊዜ ድረስ እንደሚቀጣውም አሰበ፡፡

ዳግመኛም አዳም በልቡ «እግዚአብሔር በጨለማ አልቀጣንም፤እነሆ! በእሳት ነበልባል ሊቀጣን ፀሐይን አወጣ አለ፡፡» አዳምም በልቡ ስለዚህ ሲያስብ የአምላክ ቃል ወደ እርሱ መጣ፡፡ እንዲህም አለው፡- «አዳም ሆይ![29] ይህቺ ፀሐይ አምላክ አይደለችም፡፡ ባልሁህ ቤት በቀን ታበራ ዘንድ ተፈጠረች እንጂ፡፡ ቀን ያበራ ዘንድ ንጋት ይሆናል፡፡ የማረጋጋህ አምላክህ እኔ ነኝ አለው፡፡» እግዚአብሔርም ከአዳም ጋር ንግግሩን አቆመ፡፡

አዳምና ሔዋንም ከበአታቸው ውጪ ወጡ፤ወደገነትም ሄዱ፣ወደ ምዕራብ በር በደረሱ ጊዜ ሰይጣን ወደ እነርሱ ይገባ ነበር፡፡ አዳምና ሔዋንን ባሳታቸው ጊዜ ሰይጣን ያደረባት እባብን አገኟት፤ አዝና ተክዛ መሬትን ትጭር ነበር፡፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ በእርሷ ላይ ስለደረሰው መርገም በደረቷ በመሬት ላይ ትሄድ ነበር፡፡ ከአራዊት ሁሉ ልዕልት /ከፍ ከፍ ያለች/ ነበረች፤ እባብ የተናቀች፣የተረገመች ሆነች፡፡ ከሁሉ ይልቅ በደረቷ የምትሳብ፣በልቧም የምትሄድ ሆነች፡፡ከአራዊት ሁሉ የምታምር እርሷ ከአራዊት ሁሉ የከፋች ሆነች፡፡ ከጥሩ ነገር ትመገብ የነበረች መሬትን ወደ መብላት ሄደች፡፡ ጥሩ የነበረ ቤቷ ዛሬ ግን ማደሪያዋ መሬት ሆነ፡፡[30] በሁሉም እንስሳት ዘንድ የምታምር፣ከደም ግባቷ የተነሣም የምታስደንቅ እርሷ በእነርሱ ዘንድ የምታስጠላ ሆነች፡፡

ዳግመኛም በአንዲት ቦታ ታድር ነበር፡፡ ሁሉም ወደ እርሱ ይመጡ ነበር፡፡ እርሷ ከሁሉም ትጠጣ ነበር፡፡ ሌሎችም እርሷ ከጠጣችው ይጠጡ ነበር፡፡ ከእግዚአብሔር በመረገሟ መርዝ በሆነች ጊዜ ግን አራዊቱ ሁሉ ከቦታዋ የሚሸሹ፣ እርሷ ከጠጣችውም የማይጠጡ ሆኑ፡፡ ሁሉም እርሷን በተመለከቱ ጊዜ ከእርሷ ሸሹ፡፡

የተረገመች እባብም አዳምንና ሔዋንን በተመለከተች ጊዜ ራሷን

[29] እንግሊዝኛው ትርጉም ላይ #...Adam,get up on ypur feet...$ የሚለው ሲኖረው ግእዙ ላይ ግን አናገኘውም፡፡ ይኸም የሆነው እንግሊዝኛው አንድ የትርጉም ምንጩ ከግእዙ በተጨማሪ አረብኛው እንደመሆኑ መጠን ከዚያ አግኝቶት ሊሆን ይችላል የሚል ግምት አለን፡፡

[30] ዘፍ ፫+፲፬-፲፭

ወደላይ አነሣች፤በጅራቷም ቆመች። ዐይኖቿም ደም ይመስሉ ነበር። ትገድላቸው ዘንድም ወደደች። አስቀድማ ሮጣም ከሔዋን ዘንድ ደረሰች ፤አዳም ግን ቆሞ ያለቅስ ነበር። እባብን የሚመታበት በትር በእጁ አልነበረምና። እባብም እንደምትገድል ያውቅ ነበር። ነገር ግን በሔዋን ምክንያት ልቡ ተቃጥሎበት ነበር። ወደ እባብ ደርሶም ጅራቷን ያዛት፤ እርሷም ወደ እርሱ ተመለሰች።

አዳምንም «አዳም ሆይ! በአንተና በሔዋን ምክንያት በሆዴ እሄድ ዘንድ የተረገምሁ ሆንሁ» አለችው። እርሷም ከኀይሏ ጽንአት ብዛት የተነሣ አዳምና ሔዋንን ጣለቻቸው። ልትገድላቸው ፈልጋም በላያቸው ወጣች። እግዚአብሔርም መልአኩን ልኮ እባቧን ከአዳምና ከሔዋን አስወገዳት /ጣላት/። እነርሱንም አስነሣቸው። የእግዚአብሔር ቃልም ወደ እባብ መጣ። እርሷንም እንዲህ አላት «መጀመሪያ በሆድሽ ትሄጂ ዘንድ ረገምሁሽ፤ በልብሽም ትሳቢ ዘንድ አደረግሁሽ፤በአንቺ ነገር አልቆረጥሁም ነበር። ዛሬም ዲዳ ሁኚ፤አንቺ ዘመዶችሽም የምትናገሩ አትሁኑ። በመጀመሪያ ጊዜ የአገልጋዮቼ መውደቅ በአንቺ ምክንያት ሆኗልና። ዛሬም ግን ልትገድይው ሞከርሽ።» በዚያን ጊዜም እባብ ዲዳ ሆነች። ወደ መናገርም አልተመለሰችም።

ነፋስም በእግዚአብሔር ትእዛዝ እየነፈሰ መጣ፤እባብንም ከአዳምና ከሔዋን ፊት ተሸክሞ ሕንድ በሚይደርስ ባሕር ዳርቻ ጣላት። አዳምና ሔዋን ግን በእግዚአብሔር ፊት አለቀሱ። አዳምም «አቤቱ አምላክ ሆይ! በቤት እያለሁ ይህን ብዩህ ነበር። ጌታዬ ሆይ! አራዊት ሊበሉኝ፣ሕይወቴንም ሊያጠፏት ተዘጋጅተዋል» አለ። አዳምም ከደረሰበት ችግር የተነሣ መሬት አስኪወድቅ ድረስ ደረቱን ደቃ፤እንደሞተ ሰውም ሆነ። የእግዚአብሔር ቃልም ወደ እርሱ መጣ፤ አነሣውም። እግዚአብሔርም »አዳም ሆይ! ከአራዊት አንዱስ

እንኳን በአንተ ላይ ከፉ ነገር ሊያደርስብህ አይችልም» አለው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ እግዚአብሔር እንዲህ አለው፡- «እኔ አራዊትንና ተሐዋስያንን ወደ አንተ ባሰባሰብሁ ጊዜ ከእነርሱ ጋር እባብን ወደ ቤት አላከሁም፤ታስደነግጣችሁ ዘንድ በእናንተ ላይ እንዳትቆም፡፡ ከእርሷም የተነሣ ፍርሀት በእናንተ ላይ እንዳያድር እርሷ ከፉ የተረገመችም እንደሆነች አውቃለሁና፡፡ ስለዚህም ከአራዊት ጋር ወደ አንተ ትመጣ ዘንድ አልፈቀድሁላትም፡፡ አሁንም ልብህን አጽና፤የወሰንሁልህ ዘመን እስኪደርስ ድረስ እኔ ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራ አለው፡፡ አዳም ግን አለቀሰ፤እንዲህም አለ፤ «አቤቱ አምላካችን ሆይ! ሌላ ቦታ ለውጥልን፤ዳግምኛ ፈጽማ እባብ ወደ እኛ መጥታ እንዳትቆም፡፡ አገልጋይህ ሔዋንንም እንዳትገድላት ዐይኖቿም ፈጽመው የከፉ ናቸውና» አለ፡፡

እግዚአብሔርም «አዳምና ሔዋንን ዛሬ ግን አትፍሩ ወደ እናንተ ትደርስ ዘንድ አልተዋትም፡፡ ከእናንተ ወደ ሌላው ደብር /ተራራ/ አስወግዳታለሁና፡፡ እናንተን የሚጎዳ ነገር በውስጧ አልተውም» አላቸው፡፡ አዳምና ሔዋንም በእግዚአብሔር ፊት ሰገዱ፤ክብር ምስጋና ይግባውና ከሞት ያዳናቸው እርሱን አመሰገኑት፡፡

ነቢያትን፣ሐዋርያትን፣ጻድቃንን፣ ሰማዕታትን የወለዱ የአባታችን የአዳምና የእናታችን የሔዋን ዕረፍት በተፈጠሩበት ዕለት ዐርብ ሚያዝያ ስድስት ቀን ነው፡፡ ጸሎታቸው፣በረከታቸው ከጳጳሳቱ አለቃ ከአባ ባስልዮስ፣ከንጉሣችን ከኀይለ ሥላሴ ጋር ይሁን አሜን፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## ገድለ አዳም ዘግንቦት

አንድ አምላክ በሆኑ በአብ፣በወልድ፣በመንፈስ ቅዱስ ስም ግንቦት ስድስት ቀን የሚነበብ የአባታችን የአዳም፣የእናታችን የሔዋን የገድላቸው ዜና ይህ ነው፡፡ ጸሎታቸው፣በረከታቸው ከንግሥታችን ከወለተ ጊዮርጊስ፤ መንግሥትን ከሚወርስ ከአምኃ ሥላሴ ጋር ይሁን፤ለዘለዓለሙ አሜን፡፡

አዳምና ሔዋንም ገነትን ይፈልጉ ዘንድ ሄዱ፡፡ ሐሩረ ፀሐይም በእነርሱ ላይ ጸናባቸው፡፡ አዳምና ሔዋንም ከሐሩረ ፀሐዩ የተነሣ ደከሙ / ወዙ /፤ በእግዚአብሔር ፊትም አለቀሱ፡፡ ያለቀሱበት የነበረው ቦታም የገነት ምዕራባዊ በርና ከፍ ያለም ነበር፡፡ አዳምም ሰውነቱን ከላይ ወደ ታች ጣለ ፡፡ ሰውነቱም ተገፈፈ፤ ተላጠም፤ብዙ ደምም ከሰውነቱ ፈሰሰ፡፡ ለሞትም ደረሰ፤ሔዋን ግን ስለ እርሱ እያለቀሰች በተራራው ቆማ ቀረች፡፡ እርሱ የተጣለ ሆኗልና፡፡

ሔዋንም ከዚህ በኋላ ሕይወትን አልወድም፤ይህ ሁሉ የሚደረግበት በእኔ ምክንያት ነውና አለች፡፡ ወደ ኋላም ወደቀች፡፡ አካሏም ከድንጋዩ የተነሣ ፈጽሞ ተላጠ /ተመታ/፡፡ እንደሞተ ሰውም ወድቃ ቀረች፡፡ ፍጥረቱን የሚመለከት ቸር አምላክ እግዚአብሔርም አዳምና ሔዋንን ተመለከተ፡፡ ቃሉንም ወደ እነርሱ ልኮ አነሣቸው፤ አዳምን አዳም ሆይ! ‹‹ይህ የምታደርገው ቀኖና ለቀኖናነት አይጠቅምም፤አምስት ሺህ አምስት መቶ ዓመትንም አይከፍልህም /አይቀንስልህም/›› አለው፡፡

አዳምም እግዚአብሔርን አለው፡፡ እኔ ከሐሩር መጥቻለሁ፤ ከመንገድም የተነሣ ደከሜአለሁ፡፡ በማላውቀው በዚህ ዓለም ለዕረፍት ታወጣኝ ዘንድ ተጨነቅሁ፡፡ ምሲጋና ይግባውና እግዚአብሔ አምላክም ‹‹አዳም ሆይ! ዕለታቶችህን እስክትጨርስ ድረስ ይህ የሚሆን አይደለም፤ ከዚህች አድካሚ

ምድር አላወጣህም›› አለው፡፡ አዳምም እግዚአብሔርን እንዲህ አለው፡-‹‹ በገነት በነበርሁበት ወቅት ድካምን ሐሩር ፀሐይን መሔድ መፍራት፣መንቀጥቀጥን አላወቅም ነበር፡፡ ወደዚች ምድር ከደረስሁ በኋላ ግን ይህ ሁሉ ችግር ደረሰብኝ ››አለው፡፡

እግዚአብሔር አዳምን ትእዛዜን ጠብቀህ በምትኖርበት ጊዜ ብርሃኔ ጸጋዬም በአንተ ላይ ነበር፡፡ ሕጌን ባፈረስህ ጊዜ ግን ወደዚህ የኃዘን፣ የድካም ምድር ደረስህ አለው፡፡ አዳም ግን አለቀሰ፤ እንዲህም አለ ፡፡ አቤቱ ፈጣሪዩ ሆይ! በእኔ አትጨክን፤በጽኑ ግርፋትም አትግረፈኝ፤ እንደበደሌ ብዛትም አትክፈለኝ፤ እኛ በፈቃዳችን ትእዛዝህን ተላልፈናልና፡፡ ሕግህንም አቃልለናልና ፡፡ ጠላት /ዲያቢሎስ /ባታለለን ጊዜ እንደ አንተ አምላክ ለመሆን ፈልገናልና ፡፡

ዳግመኛም እግዚአብሔር አዳምን አለው ፤ ‹‹በዚህች ምድር ፍርሃትን ፣መንቀጥቀጥን፣መድከምን፣ወደ ተራራ መውጣትን፣መውረድን፣እንደ ተሸከምህ እስከማድንህ ድረስ ይህን ሁሉ እኔ ስለአንተ እቀበላለሁ›› አለው፡፡አዳም በመጀመሪያ ያሳረገው ቍርባንም ይህን ነው፡፡ ዳግመኛም አዳም አለቀሰ፤እንዲህም አለ፡፡ ‹‹ አቤቱ አምላክ ሆይ ! ለእኔ የሚገባውን መከራ እስከምትቀበል ድረስ እኔን ይቅር በል ፡፡ ›› እግዚአብሔርም ከአዳምና ከሔዋን ጋር መነጋገሩን አቆመ ፡፡

አዳምና ሔዋንም በእግራቸው ቆሙ ፡፡ አዳምም ሔዋንን ሔዋን ሆይ! ታጠቂ አላት፤እሷም ታጠቀች፤ዳግመኛም አዳምና ሔዋን ድንጋዩን አነሡ ፡፡ እንደ ታቦት አምሳልም አስቀመጡት ፡፡ ከገነት ውጪም ከዕፀዋት ቅጠልን ወሰዱ ፡፡ ደማቸውንም በድንጋዩ ላይ አሹባቸው፡፡ የነጠበውንም ከመሬቱ ላይ ወሰዱት፤ በመሠውያው ላይም እንደ ቍርባን ለእግዚአብሔር አቀረቡት ፡፡አዳምና ሔዋን አቤቱ ጌታችን ሆይ! ኀጢአታችንና በደላችንን ይቅር በለን፤ እያሉ ከመቅደሱ ታች በእግዚአብሔር ፊት ቆሙ ፡፡በምሕረት ዐይን

ተመልከተን፤እኛ በገነት ሳለን ምስጋናችን በእጃችን ታርግ ነበር፡፡ ዝማሬያችንም ያለመታጐል ያርግ ነበር ፡፡

ወደ ኃላፊቷ ምድር በመጣን ጊዜ ግን ንጽሕት የሆነች ምስጋና፣ ቅን የሆነች ጸሎት፣አስተዋይ ልብ፣መልካም አስተሳሰብ፣እውነተኛ ምክር፣ መልካም ፍርድ፣የቀና አስተሳሰብም አልቀረችልንም ፡፡ ሕጉን ከመተላለፋችን በፊት የነበረ ሥጋችን /አካላችን/ ተለወጠ፡፡ በእኛ በድንጋዩ ላይ የተሰዋውን ደማችንን ዛሬም ተመልከት ፡፡ በገነት እያለች እናደርግ እንደነበረው ምስጋናም ይህን ተቀበልልን፡፡ አዳምም ልመናውን ወደ እግዚአብሔር ያበዛ ጀመር ፡፡ሰውን ወዳጅ ቸር እግዚአብሔርም ወደ አዳምና ወደ ሔዋን መሥዋዕት አድርገው ወደ አቀረቡለት ወደ ደማቸውም ተመለከተ ፡፡ ከመሥዋዕቱ የተነሣም አደነቀ ፡፡ በቊርባናቸውም ተደሰተ ፡፡ እግዚአብሔርም ብርሃናዊት እሳትን ከእርሱ ላከ፡፡ ቊርባኑንም አቃጠለች፤እግዚአብሔርም ቁርባናቸውን ተቀብሎ ይቅር አላቸው ፡፡

የእግዚአብሔር ቃልም ወደ አዳም መጣ፡፡ ‹‹ አዳም ሆይ! አንተ ደምህን እንዳፈሰስህ ከዘርህ ሰው በሆንሁ ጊዜ እኔ እንደ አንተ ደሜን አፈስሳለሁ ፡፡ አዳም ሆይ!እንደሞትህ እኔም እሞታለሁ፤መሥዋዕትን እንደሠራህ እኔም በመሬት መሥዋዕትን እሠራለሁ ፡፡[31] ደምህን በእርሱ እንዳቀረብህ እንደዚህም በምድር መሠዊያ ላይ ደሜን አቀርባለሁ፡፡ በዚህ ደም ይቅርታን እንደለመንህ /እንደፈለግህ /ኀጢአትህን በዚህ አደመስሳለሁ ፡፡

ዛሬም እነሆ!ቊርባንህን ተቀበልሁ፡፡

አዳም ሆይ! የገባሁልህ የቃል ኪዳን ቀን አልደረሰም እንጂ ሲፈጸም ግን ወደ ገነት አስገባሃለሁ፡፡ ዛሬም ልብህን አጽና፤ በአንተ ላይ ሐዘን በደረሰም ጊዜም ቁርባንህን ዐሳርግልኝ አለው፡፡ እግዚአብሔርም በአዳም ኀሊና ያለውን ዐወቀ፡፡ እርሱ ብዙ ጊዜ ሰውነቱን ገድሏልና፤ቁርባንንም ከደሙ ያሳርግለት ነበርና፡፡ እግዚአብሔርም አዳምን አለው፡፡ ‹‹ አዳም ሆይ! ዳግመኛ በዚህ ሞት ሰውነትህን አትግደል፡፡ ይኸውም በተራራ ላይ መዘረርህ ነው፡፡››

[31] ማቴ ፳፮፥፳፰

አዳም እግዚአብሔርን ትእዛዝህን መተላለፌን በአንድ ጊዜ ለማጥፋት በአእምሮዬ ስላሰብሁ ነው። ከምታምር ከገነት በመውጣቴ፤ ከእኔ ላይ ስለወሰድሃት ብርሀት ጸጋ፤ያለማቋረጥ ከአፌ ይወጡ ስለነበሩ ምስጋናዎች፣ ታጎናጽፈን ስለነበር ብርሀት ጸጋ ነው አለው ። ዛሬ ግን እራቁቴን [32] ቀረሁ፤ አቤቱ ጌታዬ ሆይ! ስለቸርነትህ በመጨረሻ አላጠፋኸኝም ሁል ጊዜ ይቅር የምትለኝ ሆንህ እንጂ፤እሞታለሁ ታድነኝማለህ። ስለዚህ ማንም ይጠፋ፤ ይወድቅም ዘንድ እንደማትሻ ይቅር ባይም እንደሆንህ ታውቀ፤ ተረዳ። በአንዱ ስንኳን ፈጽሞ በከፉ ጥፋት አትፈርድም ። ከዚህ በኋላ አዳምም መናገሩን አቆመ ።

የእግዚአብሔር ቃልም ወደ አዳም መጣ፤እርሱን ባርኮ አጽናናው። የተወሰኑት ዓመታት ከተፈጸሙ በኋላ ሰውነቱን ያድነው ዘንድም ቃል ኪዳን ገባለት ።

ዳግመኛም አዳም ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ማቅረቡ የመጀመሪያው ነው። ይህም ለአዳም ልማድ ሆነ። ዳግመኛም አዳም ሔዋንን ወሰዳት። ወደ ነበሩበት መኖሪያ ውስጥ ይመለሱ ዘንድም ጀመሩ። ወደ እርሷ በቀረቡ ጊዜም ተመለከቷት። አዳምም ሔዋንን በተራራው ላይ በነበርን ጊዜ በእግዚአብሔር ቃል እንረጋጋ ነበር፤ ከእኛ ጋርም ይነጋገር ነበር። ከምሥራቅ የወጣው ብርሃንም በእኛ ላይ ያበራ ነበር፤ ዛሬ ግን የእግዚአብሔር ቃል ከእኛ ተሰወረ፤ በእኛ ላየ ያበራ የነበረው ብርሃንም ይሰወር ዘንድ ጀመረ። ጨለማ፣ ኃዘንም በእኛ ላይ ሠለጠነ። የእሥር ቤት የመሰለው ቤትም ወደ ውስጥ እንገባ ዘንድ ያስጨንቃል። ጨለማም በእኛ ላይ ይጋረዳል። አንቺ እኔን እንዳታዩ፤እኔም አንቺን እንዳልመለከት፣በመካከላችን ይለዩናልና አላት።

አዳም ይህን ቃል በተናገረ ጊዜ ሁለቱም አለቀሱ፤እጃቸውንም በእግዚአብሔር ፊት ዘረጉ፤ፀሐይ በእነርሱ ላይ ታበራ ዘንድ ወደዱ። ከጨለማው የተነሣም ፀሐይ እንዳትጠልቅ እግዚአብሔር ያዝዝላቸው ዘንድ ፈልገው ወደ እርሱ ያዝኑ፤ይተከዙ ነበር። ዳግመኛም በድንጋይ ድንኳን ውስጥ

---

[32] ዘፍ ፫፥፯

ይገባ ዘንድ ጨለማን ከሚያዩም ሞትን መረጡ ፡፡

እግዚአብሔርም የአዳምና የሔዋንን የሚያስጨንቅ ኃዘናቸውንም ተመለከተ፡፡ ይህን ሁሉ በሚያቃጥል ልብ የሚያደርጉት መጀመሪያ በውስጧ ስለነበሩባት በኃላፊዋ ምድር በእነርሱ ላይ ስለደረሰው ድካም /ችግር/ ነው፡፡ ስለሆነም እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ አልተቆጣም፤ ቸልም አላለባቸውም፤ቸርነቱን ያረዝምላቸው ነበር እንጂ፤እነርሱ ፍጥረቶቹ ናቸውና እንደ ልጅም ያስማማላቸው ነበር፡፡

የእግዚአብሔር ቃልም ወደ አዳም መጣ‹‹ አዳም ሆይ! ፀሐይን ባቆማት ዓመታት፣ሰዓታት ወራት ይጠፋሉ፤የገባሁልህ ቃል ኪዳንም አይፈጸምም፡፡ ስለሆነም አንተ በዚህ በታላቅ ግርፋት ውስጥ ትቀራለህ፤እስከ ዘለዓለም ድኅነት አይደረግልህም፡፡ ልቡናህን አስፋ፤ዘመናቱ እስኪፈጸሙ ድረስ ሌሊት በመቆምህ ሰውነትህን አሳምን፤ያን ጊዜ የቃል ኪዳኑ ዘመን ይደርሳል፤መጥቼም አድንሃለሁ፡፡ አዳም ሆይ!የሠራሃቸውን መልካም ተግባራት ባየሁ ጊዜ እንድታዝን አልወድም፤እንዴት እንደ ወጣህ አይቼም ይቅር እልህ ዘንድ በወደድሁ ነበር፡፡ ወደ ገነትም በመለስሁህ ነበር፡፡ ነገር ግን ከአፌ የወጣው ቃል ኪዳን አይመለስም /አይታጠፍም/፡፡ ጊዜው ሲደርስ አንተንም ዘርህንም እምራለሁ እንጂ፡፡ በውስጧም ኃዘን፤ መታመም ወደሌለባት ወደ ደስታዋ ምድር አስገባሃለሁ፡፡ ዘወትር ፍጹም ደስታ፣የማያልቅ፣የማይጠፋ፣የማያቋርጥ ምሲጋና ያለባት ገነትም ያማረች የማታልፍም ናት ፡፡››

ዳግመኛም እግዚአብሔር አዳምን አለው፡፡ ‹‹ ሰውነትህን አጠንክር፡፡ ወደ ቤትህም ግባ፤የምትፈራው ይህ ጨለማ አይረዝምም፤ዐሥራ ሁለት ሰዓት ነው እንጂ፡፡ ይህ ሲፈጸምም ፀሐይ ይወጣል፡፡›› አዳምም ይህን ቃል ከእግዚአብሔር በሰማ ጊዜ እርሱም ሔዋንም በፊቱ ሰገዱለት፤ልቡናቸውም ተረጋጋች ፡፡ እንደለመዱትም ወደ በኢታቸው ገቡ፡፡ ከዐይናቸውም ዕንባ ይፈስ

ነበር፡፡ከልባቸውም ያለቅሱ ነበር፡፡ ነፍሳቸውም ከሥጋቸው ትለይ ዘንድ ይሹ ነበር፡፡ ሌሊቱ እስኪጋርዳቸው ድረስም ይጸልዩ ዘንድ ቆሙ፤እርሱም ከእርሷ ተሰወረ፡፡ ለጸሎትም ቆመው ነበር፡፡ ቆመው ሲጸልዩም የመልካም ጠላት ሰይጣን ምትሐት አደረገባቸው፡፡

እግዚአብሔርም ከእነርሱ ጋር ይነጋገር ነበር፡፡ ያረጋጋቸው፣ቊርባናቸውንም ይቀበል ነበር፡፡ ሰይጣን ግን ምትሐትን አደረገ፡፡ ሰራዊቱንም ሰበሰበ፡፡ በእጆቹም የእሳት መባርቅት ነበሩ፡፡ በታላቅ ብርሃን ውስጥም ነበሩ፡፡ ዙፋንም ከቤቱ በር አጠገብ አስቀመጡ፡፡ ከጸሎታቸው የተነሣ ወደ ውስጥ መግባት አልቻሉምና ፡፡ በአዳምና በሔዋን ላይ እስኪታበራ ድረስም በቤቱ ውስጥ ብርሃን ሞላው፡፡ ሰራዊቶቹም ያመሰግኑ ዘንድ ጀመሩ፡፡ ሰይጣንም አዳም ብርሃን እስኪያይ ድረስ ይህን አደረገ፡፡ አዳምም በሰውነቱ ብርሃን እንደሆነ ያስብ ነበር፡፡ ይጠብቁት፣በጨለማም ያበሩለት ዘንድ እግዚአብሔር የላካቸው ሰማያውያን ሰራዊተ መላእክት መስለውትም ነበር፡፡

አዳምም ከቤቱ በወጣ ጊዜ ሰይጣን በእርሱ ላይ የሥለጠነ ይሆን ዘንድ ሲሰግድለት ያይ ነበር፡፡ በእግዚአብሔር ፊትም በእርሱ ላይ ፈጽሞ ያመካኝ ነበር፡፡ አዳምና ሔዋንም በተመለከቱት ጊዜ እውነት መሰላቸው፡፡ ልቡናቸውንም አጸኑ፤ይፈሩ ነበርና ፡፡ አዳምም ‹‹ሔዋን ይህን ታላቅ ብርሃን ፤ይህን ብዙ ምስጋናም፤በውጪ የሚቆመውን ይህን ሰራዊትም ተመልከቺ አላት፡፡ ወደ እኛ አይገቡም፡፡ መልእክታቸውንም ለምን አይነግሩንም? ይህ ብርሃን ምንድን ነው?ይህ ምስጋናስ ምንድን ነው ? ስለማን ወደዚህ ተላኩ፡፡ ወደዚህም ለምን አይገቡም? እነዚህ ከእግዚአብሔር ቢሆኑ ኖሮ ወደእኛ ቤት በገቡ ነበር፡፡ [የተላኩበትን] [33] መልእክታቸውንም በነገሩን ነበር››አላት፡፡

አዳምም ቁም በተቃጠለ ልቡና ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፤ እንዲህም አለ፡፡ «አቤቱ አምላክ ሆይ! በዚህ ዓለም ውስጥ መላእክትን በመፍጠርህ ከአንተ ጋር የሚተካከል ሌላ አምላክ አለን?በብርሃን ሞላቸው፡፡ ይጠብቁን

[33] The First book of Adam and Eve;Part III,chapter XXVII+7

ዘንድም ወደ እኛ ላካቸው፤ እርሱም ይመጣል፡፡ እነርሱም በቤታችን በር አጠገብ እንደሰራዊት ቁመው እንመለከታለን፡፡ እነርሱ በታላቅ ብርሃን ውስጥ ሆነው ብዙ ምስጋናዎችን ያመሰግናሉ፡፡ እነርሱ ከአንተ ሌላ አማልክት ከሆኑ አስረዳኝ /ንገረኝ/[34]፡፡ ለምን ተግባር እንደላከሃቸው አሳውቀኝ[35]፡፡»

አዳም ይህን ሲናገርም በቤት ውስጥ ከእግዚአብሔር ዘንድ መልአክ ታየው፡፡ አዳም ሆይ! ከዚህ ሰይጣን የተነሣ እርሱንና ሰራዊቱን አትፍራ፡፡ በመጀመሪያ እንዳሳታችሁ አሁንም ሊያስታችሁ ይሻልና ፡፡ እርሱ በመጀመሪያ በእባብ ተሰወረ፡፡ እንደዚሁም እስከትሰግዱለት ድረስ መላእክተ ብርሃንን መስሎ መጣ፡፡ በእግዚአብሔር ፊት በእናንተ ላይ የሠለጠነ ይሆን ዘንድ ፡፡

መልአኩም ወደ አዳም መጣ፡፡ ከበሩም ሰይጣንን ይዞ በአዳምና በሔዋን ያደረገውን ምትሐት አስወገደ፡፡ አዳምና ሔዋን ይህን ተመልክተው ፈሩ፡፡ መልአኩ ግን፥‹‹ አዳም ሆይ! ይህ ምሳሌው እግዚአብሔር በጣለው ጊዜ ከፉ ሆኗል፡፡ ወደ እናንተ ይመጣ ዘንድም አይችልም፡፡ እርሱ በብርሃን መላእክት አምሳል ተመሰለ እንጂ፡፡ መልአኩም ሰይጣንን አባረረው፡፡ አዳምና ሔዋንንም ማረካቸው፡፡እንዲህም አላቸው፤አትፍሩ፤የፈጠራችሁ እግዚአብሔር ይሻላችኋል፡፡ ከዚህ በኋላም መልአኩ ከእነርሱ ተለየ፡፡ አዳምና ሔዋንም በቤት ቁመው ቀሩ፡፡መረጋጋትም አልነበራቸውም፤ተጠራጣሪዎች ሆኑ እንጂ፡፡

በነጋ ጊዜም አዳምና ሔዋን ጸለዩ፡፡ ገነትን ይፈልጉ ዘንድ ከቤት ወጡ፡፡ ሸንጋይ ሰይጣን በተመለከታቸው ጊዜ ልቡናቸው ወደ እርሱ ሆናለችና፡፡ ስለ እርሱም አልተረጋጉም፡፡ እነርሱም ወደ ገነት ሄዱ፡፡ ሰራዊቱንም ሰብስቦ ያስታቸው ዘንድ በደመና ላይ ወጣ፡፡ አዳምና ሔዋንም በተመለከቱት ጊዜ በምትሐት ውስጥ ስለነበሩ የእግዚአብሔር መላእክት ከገነት በመውጣታቸው ያድኗቸው ዘንድ የመጡ እንደሆኑ አሰቡ፡፡ ዳግመኛም ወደ ገነት የሚመልሳቸው መሰሏቸው ነበር፡፡ አዳምም እጁን ወደ እግዚአብሔር ዘረጋ፡፡ ስለእርሱ ያስረዳው ዘንድም ለመነው፡፡

---

[34] Ibid chapeter XXVII+11

[35] Ibid chapeter XXVII+12

የመልካም ሁሉ ጠላት ሰይጣን ግን አዳምን አለው:: ‹‹ አዳም ሆይ ! የታላቁ የእግዚአብሔር መልአክ ነኝ::እነሆም ሰራዊቶቼ ከበውኛል››:: እኔንና እነዚህንም ወደገነት እንወስድህ ዘንድ እግዚአብሔር ላከን:: ከደቡብ ንጹሕ ወደምትሆን ውኃ በዚያችም አንተንና ሔዋንን እናጠምቃችኋል:: ዳግመኛ በደስታ ወደ ገነት እስከትገቡ ድረስ እናሳርጋችኋለን ›› አለው:: ይህ ቃልም ወደ አዳምና ሔዋን ልቡና ገባ:: አምላክም ፈጥነው እንዳይረዱት ንግግሩን አቆመ:: በገነት ውስጥ እያለች ሔዋን እንደተሸፈነች እርሱም ይሸነፍ እንደሆነ ኀይሉን እስኪረዳ ድረስ ታገሠ፤ሰይጣን ግን አዳምና ሔዋንን ጠራቸው:: ኑ ወደ ባሕሩ ውኃ እንሂድ አላቸው:: አዳምና ሔዋንም ተከትለውት ይሄዱ ዘንድ ጀመሩ:: እርሱም ከእነርሱ ርቆ ይከተላቸው ነበር:: ከገነት በስተደቡብ[36] በኩል በደረሱ ጊዜ እርሱ ከላይ ነበርና መውጫ አልነበረውም:: ዲያብሎስ ከአዳምና ከሔዋን ቀድሞ እስከተራራው ራስ / አናት / ድረስ በእውነት አወጣቸው፤ ምትሐትም አልነበረም:: ከተራራው ላይ ይወረውራቸው ዘንድም ወደደ:: ይገድላቸው ዘንድ ይፈልግ ነበርና:: ከምድረ ገጽ ያጠፋቸው ዘንድ መሬትም ለእርሱና ለሰራዊቱ ሆና ትቀር ዘንድ፤ ቸር እግዚአብሔር ሰይጣንን ተመለከተው:: በብዙ ምክንያት አዳምን ይገድለው ዘንድ እንደሚሻ እርሱም የዋህ እንደሆነ ተመለከተ::

ከእግዚአብሔርም ታላቅ ቃል ወደ ሰይጣን ወጣ:: ረገመውም፤ እርሱም ሰራዊቱም ሸሹ:: አዳምና ሔዋንም ከተራራው ራስ ቆመው ቀሩ:: ወደ ታችኛዋ ታላቅ ዓለምም ተመለከቱ:: እነርሱ ግን በጣም በከፍታም ነበሩ:: ከዐዩአቸው ሰራዊትም አንዱ ስንኳን ከእነርሱ ጋር አልነበረም:: አዳምና ሔዋንም በእግዚአብሔር ፊት አለቀሱ:: ከእርሱም ይቅርታን ፈለጉ::

ቃልም ከሰማይ ወደ አዳም መጣ:: እንዲህም አለው "እርሱንም / አዳምንም/ ሰይጣንን እወቅበት፤ ልብም አድርግ፤ እርሱ አንተን ከአንተም በኋላ የሚነሣ ዘርህን ያስት ዘንድ ይሻልና" አለው:: አዳምም በአምላኩ

36 አንግሊዘኛው ትርጉም «ከገነት በስተ ሰሜን ይለዋል»:: (First book of Adam and Eve,part III,Chapter XXVIII 10)

በእግዚአብሔር ፊት አለቀሰ፡፡ ከገነት ሥራን[37] ይሰጠው ዘንድ ፈልጎም ለመነ፡፡ ምልክት ይሆነው ይረጋጋበትም ዘንድ፡፡

እግዚአብሔርም የአዳምን ዐሳብ ተመለከተ፡፡ እስከ ሕንደኬ ባሕር ድረስ የሚያደርስ ከወርቅ ብትሮች ይይዙ ዘንድ ለአዳምና ለሔዋን ያመጣላቸው ዘንድ ቅዱስ ሚካኤልን ላከው፡፡ ይህም አምላክ በጥበቡ ያደረገው ነው፡፡ የወርቅ ብትሮችም በአዳም ዘንድ ይቀመጡ ዘንድ የጨለማው ፍርሀት ከእርሱ ልብ ይርቅ ዘንድ፤ በእግዚአብሔር ትእዛዝም መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል ወረደ፡፡ እግዚአብሔር እንዳዘዘውም የወርቅ ብትሮችን ያዘ፡፡ በእግዚአብሔር ፊትም አደረሳቸው፡፡

ከዚህ በኋላም እግዚአብሔር መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልን ወደገነት ይወርድ ዘንድ አዘዘው፡፡ የሚጠብቀውን ኪሩብንም "ወደ ገነት እገባ ዘንድ አምላክ አዝዞኛል፤ ከእርሱም ሽታው መልካም የሆነ ዕጣንን እወስድ ዘንድ፥ ለአዳምም እሰጠው ዘንድ፤ አለው፤" መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል፡፡

መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልም በእግዚአብሔር ትእዛዝ ወደ ገነት ወረደ፡፡ ኪሩብንም እግዚአብሔር እንዳለው ነገረው፡፡ ኪሩብም እሺ አለ፡፡ እርሱም ገብቶ ዕጣኑን ወሰደ፡፡ እግዚአብሔርም መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤልን ወደ ገነት ይወርድ ዘንድ አዘዘው፡፡ መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤልም ወረደ፤ እግዚአብሔር እንዳዘዘውም ለአዳም ከርቤ ይሰጠው ዘንድ ለኪሩብ ነገረው፡፡ ኪሩብም እሺ፥ አለው፡፡ ከርቤውንም ወሰደ፤ የወርቅ በትሮቹ ግን በውስጡ አዕናቍ [የከበሩ ማዕድናት] በሚገኝበት በሕንደኬ ባሕር ነበሩ፡፡

ዕጣኑ ግን ከገነት ጫፍ በምሥራቅ በኩል ነበር፡፡ ከርቤውም አዳም በገባበት ጫፍ ከገነት በምዕራብ በኩል ነበር፡፡ መላእክት እነዚህን ሦስቱን በእግዚአብሔር ፊት አደረሱ፤ በገነት ውስጥ ያለች ዕፀ ሕይወትንም፡፡ እግዚአብሔርም "መላእክትን በዐይነ ማይ አጥምቋቸው፤ ውኃንም ይዘችሁ

[37] እንግሊዝኛው ትርጉም "...አንድ ነገር ከገነት እንዲሰጠው ለመነ፤ ጸለየ፡፡" ከማለት በስተቀር እንደ ግእዙ "ከገነት ሥራ ይሰጠው ዘንድ ፈልጎም ለመነ፡፡" በማለት የለመነውን በግልጽ አያስቀምጥም፡፡ / Ibide,chapter xxvlx/

እርጬቻቸው፤ በውስጣቸው ካለ ብዙ ኃዘን ትንሽ ይረጋጉ ዘንድ፤ ለአዳምና ለሔዋንም ሰጧቸው" አላቸው:: መላእከትም ከእግዚአብሔር እንደታዘዙ አደረጉ:: ሰይጣን አውጥቷቸው በነበረውና ሊገድላቸውም በፈለገበት በተራራው ራስ ላይ ለአዳምና ለሔዋን ሰጧቸው::

አዳምም የወርቅ ብትሮችን፣ ዕጣኑን ከርቤውን ባየ ጊዜ ተደሰተ፤ አለቀሰም፤ ወርቁ ከእሱ የወጣ የንግሥና ምልከት እንደሆነ፤ ዕጣኑም ከእርሱ የተወሰደች የብርሃናዊት ከሀነት ምልከት እንደሆነ፣ ከርቤውም በእርሱ ያለ የኃዘን ምልከት እንደሆነ አሰበ:: ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር አለው፤ "አዳም ሆይ! ትረጋጋበት ዘንድ ከእኔ በገነት ሥራን ፈለግህ፤ እነሆ! እነዚህ ሦስት ምልከቶችን ትረጋጋባቸው ዘንድ ለአንተ ሰጠሁህ:: ለአንተ በሰጠሁህ ቃል ኪዳንም በእኔ ታምን ዘንድ እኔ መጥቼ አድንሃለሁ:: ሰው በምሆንበት ጊዜ ነገሥታቱ ወርቁን፣ ዕጣኑን፣ ከርቤውን ያመጡልኛል:: ወርቁ የንጉሥነቴ ምልከት ነው፣ ዕጣኑም የመለኮትነቴ ምልከት ነው፣ ከርቤውም የመታመሜ፣ የመሞቴ ምልከት ነው፤ አዳም ሆይ! እኒህን በአንተ ዘንድ በበአትህ አስቀምጣቸው:: ወርቁ በሌሊት ያበራልህ ዘንድ፤ ዕጣኑም መዓዛውን ታሸትተው ዘንድ፤ ከርቤውም ከኃዘንህ ያረጋጋህ ዘንድ" አለው::

አዳምም ይህን ቃል ከእግዚአብሔር በሰማ ጊዜ እርሱም ሔዋንም ሰገዱለት:: ከእነርሱ ጋር ምልከትን ስላደረገም ፈጽመው አመሰገኑት:: እግዚአብሔርም ቅዱሳን መላእከት ሚካኤልን፣ ገብርኤልን፣ ሩፋኤልን አዳም የመጣለትን ስጦታ ይሸከሙ ዘንድ አዘዛቸው:: አንዱ አንዱም ያመጡለትን ሁሉ ተቀበለ:: እግዚአብሔርም አዳምንና ሔዋንን ይሸከሙ ዘንድ ሱርያልን፣ ሰላትያልን፣ አዘዛቸው:: ከታላቁ ተራራ ራስም አወረዷቸው:: ወደ ቤታቸውም ወሰዷቸው:: ወርቁን ግን ከቤቱ በስተ ሰሜን[38] በኩል አኖሩት፤ ዕጣኑን በምሥራቅ፣ ከርቤውን በምዕራብ በኩል አኖሩት:: ቤቱም በዚያ ነበር:: መላእከትም አዳምንና ሔዋንን አጽናንተዋቸው ሄዱ::

38 እንግሊዝኛው በስተደቡብ በኩል ይለዋል:: Ibid part-4,chapter xxx-7

ወርቁም ሰባ ብትሮች[39] ሆነ፤ ዕጣኑ አሥራ ሁለት ልጥር[40] ሆነ፤ ከርቤውም ሦስት ልጥር ሆነ። እነዚህም በአዳም ዘንድ ከቤት ተቀመጡ። ስለዚህም የተሸሸገ ቤተ መዛግብት/ዕቃ ቤት/ ተባለ። ሌሎች መተርጕማን ግን የጻድቃን ወገኖች በውስጧ ስላሉ ስውር ቤተ መዛግበት /የዕቃ ቤት/ እንደተባለ ይናገራሉ።

እነዚህ ሦስቱ ዕቃዎች በቤተ መዛግብት ውስጥ ለአዳም ማታም ቀንም ያበሩለት ነበር። በእነርሱም ከኃዘኑ ይጽናናባቸው ነበር። አዳምና ሔዋን በዕቃ ቤቱ ውስጥ እስከ ሰባት ቀን ድረስ ቁመው ቀሩ። የምድር ፍሬን አልበሉም፤ ውኃንም አልጠጡም። በስምንተኛው ቀን ንጋት በሆነ ጊዜ አዳም ሔዋንን እኛ እግዚአብሔር በገነት ሥራን ይሰጠን ዘንድ እንጠይቅ አላት። መላእክቱንም ላከ፤ የምንፈለገውንም አምጡልን፤ ዛሬም በፊት ወደተመለከትነው የውኃ ባሕር እንሄድ ዘንድ ተነሽ፤ እግዚአብሔር ፈጽሞ ይቅር ይለን ዘንድ፣ ዳግመኛም ወደ ገነት ይመልሰን ዘንድ በውስጡ ቁመን እንጸልይ። ወይም ሥራን ይሰጠን ዘንድ ያም ባይሆን እኛ ከምንኖርበት በሌላ ምድር ያጽናናን ዘንድ አላት።

አዳምና ሔዋንም ከቤታቸው ወጥተው ሰውነታቸውን በውስጡ ይጥሉ ዘንድ በማስቀደም በባሕር ዳር ቆሙ። አዳምም "ሔዋንን ወደዚህ ቦታ ውረጂ፤ አርባው ቀን እስኪፈጸም ድረስም ከዚህ እንዳትወጪ፣ ወደ አንቺ እስከመጣ ድረስ በንጹሕ ልብ፣ በሚጣፍጥ ቃል ሆነሽ፤ ይቅር ይለን ዘንድ ከእግዚአብሔር ይቅርታን ለምኚ። እኔም ወደ ሌላ ቦታ ልሂድ፤ ወደዚያ ወርጄም እንደ አንቺ አደርጋለሁ" አላት። ሔዋንም አዳም እንዳዘዛት ወደ ውኃው ወረደች። ዳግመኛም አዳም ወደ ውኃው ወረደ፤ ወደ ቀደመ ሥራቸው ይመልሳቸው ዘንድ፤ በደላቸውንም ይቅር ይላቸው ዘንድ፤ ከእግዚአብሔር ይቅርታን ፈልገው ሊጸልዩ ቆሙ። ሠላሳ አምስት ቀን እስኪፈጸም ድረስም እንዲህ ይጸልዩ ነበር።

---

39 በዚህ ዐውድ /Context/ "ብትሮች" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ትልቅና ቀጠን ያለ የወርቅ ዘንግ ሆኖ መጠኑ እና ክብደቱ በግልጽ የማይታወቅ ነው። ይኸም "ብትር" የርዝመት መለኪያ ሲሆን ከ5.5 ያርድ/Yards/ አኩል ነው። እንዲሁም አንድ "ብትር" ከ30.25 ስኩዌር ያርድ /Square yards/ ጋር እኩል ነው።

40 ልጥር የሚዛን ስም ነው /ኪ.ዳ.ወ.ክፍሌ የሐ.፲፱+፫፤፲፱-፴፱/

የመልካም ተግባር ጠላት የሆነው ሰይጣን በቤት ፈለጋቸው:: ግን አላገኛቸውም:: ዳግመኛም ሲፈልጋቸው በውኃ ውስጥ ቆመው ሲጸልዩ አገኛቸው:: በልቡናውም እንዲህ አለ:: "አዳምና ሔዋን በዚህ ውኃ ውስጥ መቆማቸው እግዚአብሔር በደላቸውን ይቅር ይላቸው ዘንድ፤ ወደ ሥርዐታቸውም[41] ይመልሳቸው ዘንድ፣ ከእጄም ያወጣቸው ዘንድ ነው:: እኔም ከውኃው አወጣቸዋለሁ፤ የተመኙትም አይፈጸምላቸውም አለ:: የበጎ ጠላት /ዲያብሎስም/ ወደ አዳም አልሄደም:: የእግዚአብሔር መልአክን በመምሰል ወደ ሔዋን ሄደ እንጂ:: እርሱም ያመሰግን ይደሰትም ነበር:: /በሽንገላ/ ሔዋንንም "ሰላምታ ይገባሻል፤ ደስ ይበልሽ፡ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነውና አላት:: እርሱ ወደ አዳም ልኮኛል:: የመዳንን ዜናም ነገርሁት፤ ቀድሞ እንደነበረችው ገነትም በብርሃን ሞላኋት:: አዳምም ወደዚህች በመመለስ ደስ ስለተሰኘ ወደ አንቺ ላከኝ:: እንደ እርሱ በብርሃን እጋርድሽ ዘንድ ወደ እርሱ እንድትመጪ፡ ወደ አንተ አልመጣም ካለች በተራራው ራስ የነበረውን ምልክት ንገራት አለኝ" አላት::

[እርሱም ምልክቱን እንዲህ እያለ ይነግራት ጀመር] እግዚአብሔር መላእክትን ላከ፤ ተሸከመውም ወደ በአተ መዛግብት /ዕቃ ቤት/ አስገቡን፤ ወርቁን በሰሜን[42] በኩል አስቀመጡ፤ ዕጣኑንም በምሥራቅ
በኩል ከርቤውንም በምዕራብ በኩል አስቀመጡት፤ በላት" አለኝ:: ወደ እርሱም ነይ አላት:: ሔዋንም ይህን ቃል ከእርሱ በሰማች ጊዜ ደስ ተሰኘች፤ ምልክቱም እውነት እንደሆነ አመነች:: ከባሕር ውስጥም ወጣች፤ እርሱም በፊቷ ይሄድ ነበር:: ከአዳም ዘንድ እስኪደርሱ ድረስ እርሷም በኋላው ትከተለው ነበር:: ከፊቷ ተሰወራት፤ ታየው ዘንድም አልተመለሰም፤ መጥታም ከአዳም ዘንድ ቆመች:: እርሱም ከእግዚአብሔር ይቅርታን ያገኝ ዘንድ ከውኃው ቆሞ ይጸለይ ነበር:: ጠራቻው፤ አዳምም መለስ ቢል አገኛት፤ ባያት ጊዜም አለቀሰ፤ ደረቱንም መታ፤ ከኃዘኑ ጥልቀት የተነሣም ሰውነቱን ከውኃው ውስጥ አጠለቀው::

[41] የእንግሊዝኛው ትርጉም ግን "ወደ ቀደመ መንግሥታቸው ይመልሳቸው ዘንድ" ይለዋል::( Ibide,chapter xxxIII+2)

[42] የእንግሊዝኛው ትርጉም "በደቡብ በኩል" ይለዋል::( Ibide,chapter xxxIII+7)

እግዚአብሔርም የአዳምን ድካም፣ የሰውነቱን ስቃይም ተመለከተለት፤ የእግዚአብሔር ቃልም ከሰማይ መጣ፡፡ ከውኃውም አነሣው፤ ወደ ውጪ ወደ ሔዋንም ውጣ አለው፡፡ በወጣ ጊዜም ሔዋንን ወደዚህ ነይ ያለሽ ማን ነው? አላት፡፡ እርሷም የታያት የመልአኩን ነገር፤ የሰጣትንም ምልክት ነገረችው፤ አዳምም አዘነ፤ ሰይጣንም እንደሆነ አወቀ፤ አዳምም ሔዋንን ይዞ ወደ ቤት ተመለሰ፡፡ ወደ ውኃው መውረዳቸውም ከገነት ከወጡ በኋላ በሰባተኛው ቀን መጀመሪያ ነበር፡፡ በውኃው ውስጥም ሠላሳ አምስት ቀን ጾሙ፤ ከገነት ከወጡም አርባ ሁለት ቀን ነበር፡፡ አርባ ሦስተኛው ቀን ሲሆንም ከቤት ውስጥ ያዘኑ ያለቅሱ ነበር፡፡

ሥጋቸውም ከረኀቡ፣ ከጽሙ፣ ከጸሎቱ፣ ከኃዘኑም ብዛት የተነሣ ከስቶ፣ ደርቆም ነበር፡፡ ከቤታቸው በወጡ ጊዜም ከገነት በስተምዕራብ በኩል አዳምና ሔዋንም ያለቅሱ፣ ይጸልዩም ዘንድ ቆሙ፡፡ የበደላቸውን ይቅርታ ይሰጣቸው ዘንድ እግዚአብሔርን ተማጸኑ፡፡ ከጸሎታቸው በኋላም አዳም እንዲህ እያለ ከእግዚአብሔር ዘንድ ልመናን ጀመረ፡፡ አቤቱ ጌታዬ፤ አምላኪዬ፤ ፈጣሪዬ ሆይ! ይሰበሰቡ ዘንድ አራቱን ባሕርያት አንተ አዘዝሃቸው፡፡ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ይሰበሰባሉ፡፡ የአምላክነት እጅህንም ዘረጋህ፤ ከአራቱ ባሕርያት ከመሬት ፈጠርኸን፤ ዐርብ ዕለትም በሦስት ሰዓት ወደ ገነት አስገባኸን፡፡ ካመለከትኸን ቤት ውስጥ በመጀመሪያ እኔ ጨለማን አላውቅም ነበር፡፡ እኔ ብርሃን በተሞላበት ቦታ ነበርሁና፡፡ የነበርሁበትም ብርሃን ነበር፡፡ ሌሊትና ቀንን አውቅ ዘንድም አልቻልም ነበር፡፡

አቤቱ ጌታችን ሆይ! ዳግመኛም በፈጠርኸኝ በሦስተኛው ሰዓት አራዊቱን አንበሶችን፣ ሰጎኖችን፣ የሰማይ ወፎችን፣ የምድር ተሐዋስያንን / ነፍሳትን/ ከእኔ አስቀድም በዕለተ ዐርብ በጀመሪያው ሰዓት የፈጠርሃቸውን ሁሉ አመጣኸልኝ፡፡ አቤቱ አምላክ ሆይ! እያንዳንዳቸውን በሚገባቸው ስም እጠራቸው ዘንድ ፈቀድህ፡፡ ማስተዋልን፣ ምልክትን፣ ብሩህ ልቡናን፤ የቀና

አስተሳሰብንም ሰጠኸኝ፤ እንዳሰብኸው ሐሳብም ስም አውጥቼላቸዋለሁና:: አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ! ሁሉም ሰገዱልኝ:: እንደ ትእዛዝህም በእነርሱ ላይ እንደሰጠኸኝ ሥልጣን አንዱ ስንኳ ከትእዛዜ አልወጣም:: አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ! ሁሉም አራዊት ተለዩ:: ዐርብ ቀን ሦስት ሰዓት በሆነ ጊዜ የፈጠርኸኝ ሰዓት ናት፤ ከእርሷ እንዳልቀርብ እንዳልበላም ስለ ዕፀ በለስ አዘዝኸኝ:: ከእርሱ በበላህ ጊዜም ሞትን ትሞታለህ አልኸኝ::

እግዚአብሔር ሆይ! በእኔ ላይ ሞት ከምትፈርድብኝ በሰዓቴ ባጠፋኸኝ ነበር፤ ከዕፀ በለስ እንዳልበላ እንዳልቀርብም ባዘዝኸኝ ጊዜ ሔዋን ባትፈጠር ከጎኔም ባትወጣ ኖሮ ይህንም ትእዛዝ ከአንተ ባትሰማ ኖሮ አለ:: አቤቱ ፈጣሪ ሆይ! ሦስት ሰዓት ሲፈጸም ፍጹም እንቅልፍን በእኔ ላይ አመጣህ፤ ተኛሁ፤ በእንቅልፍም ተሰጠምሁ:: ከጎኔም አጥንትን አወጣህ:: በአርአያየ፡ በአምሳሌም ፈጠርሃት፤ ከዚያም በኋላ አነቃኸኝ፤ ባየኋት ጊዜም አወቅኋት:: ይህ አጥንቷ ከአጥንቴ፤ ሥጋዋም ከሥጋዬ፤ ነውና፤ ዛሬም ሴት ትባል አልሁ:: አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ! አንተን መፍራትን የደግነትህ ገናናነት፣ ከብርህን ዐይ ዘንድ ሁለታችንም ብርሃት በሆነች ሥጋ ፈጠርኸን፤ ሁለታችንንም አንድ አደረግኸን:: ጸጋህንም ሰጠኸን::

የተራብን፣ የተጠማን እንዳንሆን በመንፈስ ቅዱስ ምስጋና አጠገብኸን:: ኃዘን ምን እንደሆነ፣ የልብ ድካም፤ መታመም፣ መራብ ምን እንደሆነ አናውቅም ነበር:: አቤቱ ዛሬ ግን ትእዛዝህን በተላለፍን ጊዜ፣ ሕግህንም ባፈረስን ጊዜ ወደኋላፊዋ ምድር አወጣኸን:: በእኛ ላይም ሕመም፣ ረኀብ፣ ድካም፣ ጽም ደረሰብን:: ዛሬም አቤቱ ከገነት የምንበላውን፣ ከረኀባችንም የምንጠግብበትን፣ ከጽማችንም የምንረካበትን መጠጥ ትሰጠን ዘንድ እንለምንሃለን::

አቤቱ ጌታችን ሆይ! {ምግብ} ሳንቀምስ፣ ውሃም ሳንጠጣ ብዙ ቀናችን ነው:: ሥጋችን ደረቀ፤ ኀይላችን ደከመ፤ ከድካም፣ ከለቅሶ የተነሣም እንቅልፍ

ከዐይናችን ጠፋች፡፡ አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ! እኛም አንተን ከመፍራት የተነሣ ከዕፀዋት ፍሬ እንነካ ዘንድ አንችልም፡፡ ከዚህ በፊት ትእዛዝህን በተላለፍን ጊዜ አንተ ይቅር ብለኸናል፤+ አልገደልኸንምና ዛሬም ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ከዕፀዋት ፍሬ በበላን ጊዜ እርሱ በዚህ ምክንያት ዳግመኛ ያጠፉናል፤ ከምድረ ገጽም ይደመስሰናል፤ ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ከዚህ ውኃ ከጠጣንም እርሱ ያጠፉናል፤ ይደመስሰናል ብለን በልባችን አሰብን፡፡ አቤቱ አምላካችን ሆይ ዛሬም ከገነት ፍሬዎችህ ታጠግበን ዘንድ ለመንን፤ እኔም ሔዋንም ወደዚህ መጣን በምድር ያለውን ምግብም፣ በውስጧ የሚያስደንቀንን ሁሉ እንሻለን አለው፡፡

ዳግመኛም እግዚአብሔር የአዳምን ለቅሶ ጭንቀቱንም በፊቱ ተመለከተ፡፡ የእግዚአብሔር ቃልም ወደ እርሱ መጣ፡፡ አዳም ሆይ! በገነት ውስጥ እያለህ መብልን፣ መጠጥን፣ ድካምን፣ ሕመምን፣ የሥጋ መድረቅን፣ መለወጥን፣ የእንቅልፍ ማጣትን የምታውቅ አልነበርህም፡፡ ሕጌን ተላልፈህ ወደዚህች ኃላፊት ምድር በደረስህ ጊዜ ግን ፈተናዎች ሁሉ ደረሱብህ፤ እነርሱም ዐሥር ናቸው፡፡

እግዚአብሔርም ገነትን የሚጠብቅ፣ የእሳት ሰይፍን በእጁ የያዘ፣ ኪሩብን ከበለስ ዕፅ ፍሬን ወስዶ ለአዳም ይሰጠው ዘንድ አዘዘው፡፡ ኪሩብም የአምላኩን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተቀብሎ ወደ ገነት ገባ፡ ሁለት የበለስ ፍሬያትም ከሁለት ቅጠሎች ጋር አወጣ፡፡ ከፍሬያቱም አንዲቱ በሌላይቱ ላይ ተደርባ [ያፈራች] ነበረች፡፡ በሁለቱ ዕንጨቶች መካከልም እግዚአብሔር በገነት በተመላለሰ ወደ እነርሱም በመጣ ጊዜ አዳምና ሔዋን ተሸሸገውባቸው ነበር፡፡

አዳም አዳም ሆይ! የት አለህ? አለው፡ አዳምም አቤቱ ፈጣሪ ሆይ! እኔ በበለስ ዕንጨት ሥር ተሸሽጌያለሁ፡ ድምፅህን በሰማሁ ጊዜም ተሸሸግሁ፡፡ እኔ ራቁቴን ነኝና፤ አለው፡፡ ኪሩብም ሁለት ፍሬዎችን ወሰደ፡፡ ለአዳምና ሔዋንም ከሩቅ ወረወረላቸው፡፡ እነርሱ ግን ወደ ኪሩብ መቅረብ አልቻሉም፤

መጀመሪያ /ጥንቱን/ ግን መላእከት ከአዳም የተነሣ ይፈሩ ይንቀጠቀጡም ነበር:: ዛሬ ግን አዳም ከመላእከት የተነሣ እነርሱን ፈራ፣ ተንቀጠቀጠ፤ አዳም ከሁለቱ የበለስ ፍሬ አንዷን ወሰደ:: ሔዋንም ሌላዋን ወሰደች፤ በእጃቸው እያሉም ተመለከቷቸው:: እነርሱ ከተሸሸጉባቸው ዕፀዋት መካከል እንደሆኑም አወቁ::

አዳምና ሔዋንም ጽኑ ልቅሶን አለቀሱ:: አዳምም ሔዋንን ሔዋን ሆይ! እነዚህን የበለስ ዛፍ ፍሬዎች በተሰወርንባቸው ጊዜ የነበረ ቅጠላቸውንም ተመልከቺ፡ ከሚያበሩ ልብሶች በተራቆትን ጊዜ:: ዛሬም ከእነርሱ በበላን ጊዜ በእኛ ላይ የሚደርስብንን ድካም መከራ አናውቅም:: ሔዋን ሆይ! ዛሬም ሰውነታችንን እንግታ; ከእነርሱም እኔም አንቺም አንብላ; ከዕፀ ሕይወት ፍሬ ይሰጠን ዘንድም እግዚአብሔርን እንለምነው አላት:: አዳምና ሔዋንም ከእነዚህ የበለስ ፍሬዎች ላለመብላት ሰውነታቸውን ገቱ; ላለመብላት ወሰኑ::

አዳም ወደ እግዚብሔር ጸሎትን ጀመረ:: ከዕፀ ሕይወት ፍሬ ይሰጠው ዘንድም ፈለገ:: አቤቱ አምላካችን ሆይ! ዐርብ ዕለት በስድስተኛው ሰዓት ትእዛዝህን በተላለፍን ጊዜ ብርሃናዊት ልብስን ከእኛ ገፈፍህ፡ ትእዛዝህን ከተላለፍን በኋላም በገነት አላደርንም፡ ከምሽቱ በሦስት ሰዓት ከእርሱ አወጣኸን እንጂ:: አቤቱ ፈጣሪ ሆይ! እኒህ ኃዘኖች፣ ፈተናዎች አንድ ጊዜ በእኛ ላይ ደረሱ:: ቀኖቼም አርባ ሦስት ቀናት ናቸው:: እነርሱም በሰዓት ትእዛዝህን የመተላለፋችንን ዋጋ አይከፍሉም:: አቤቱ አምላክ ሆይ! በምሕረት ዐይንህ ተመልከተን:: በፊትህ ሕግን እንደመተላለፋችን አትክፈለን::

በዚህች ምድር ስቃይን፣ ሌላም መከራ እንዳንቀበል፡ አቤቱ ጌታችን ሆይ! ከዕፀ ሕይወት ፍሬ እንበላ፣ ሕያውም እንሆን ዘንድ ስጠን:: ትእዛዝህን በተላለፍን ጊዜ ከገነት አስወጥተኸናልና:: ከእርሷ በልተን ሕያው እንዳንሆን ዕፀ ሕይወትን ይጠብቅ ዘንድም ኪሩብን ልከኸዋልና፤ ትእዛዝህን ከተላለፍን በኋላም የመከራን ድምፅ እንድናውቅ:: አቤቱ ፈጣሪያችን ሆይ! ዛሬም በእነዚህ

ዕለታት መከራን እየተቀበልን አለን። አርባ ሦስት ቀናትንም ከበያልንበት ሰዓት ጋር የተስተካከለ አድርግልን አለ። ልመናቸው አማላጅነታቸው ከወራሴ መንግሥት አምኃ ሥላሴ፣ ከሁላችንም ከዘራቸው ጋር ይሁን፤ ለዘለዓለሙ አሜን፤ ይሁን ይደረግ።

## ምዕራፍ ሦስት

## ገድለ አዳም ዘሠኔ

አንድ አምላክ በሆኑ በአብ፤ በወልድ፤ በመንፈስ ቅዱስ ስም ሠኔ ስድስት ቀን የሚነበብ የአባታችን የአዳም፣ የእናታችን የሔዋን የገድላቸው ዜና ይህ ነው። ጸሎታቸውና በረከታቸው ከሊቃነ ጳጳሳቱ አለቃ ባስልዮስ፤ ከንጉሡ ኃይለ ሥላሴ ጋር ይኑር፤ አሜን።

ከዚህ በኋላ የእግዚአብሔር ቃል ወደ አዳም እንዲህ ሲል መጣ። አዳም ሆይ! የምትፈልጋትን ዕፀ ሕይወትን ዛሬ አልሰጥህም፤ አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም አንተ፣ ሔዋን፣ ዘሮችህ ምእመናንም ሕያው ሆነህ ለዘለዓለም ትኖር ዘንድ ከዕፀ ሕይወት እንድትበላ እሰጥሃለሁ እንጂ። ይህ አርባ ሦስቱ ቀን ሕግ የመተላለፍህን ዋጋ አይከፈልም። አዳም ሆይ! በውስጧ የተሰወርህባት ዕፀ ሕይወትን ትበላ ዘንድ ሰጠሁህ፤ አንተም ሔዋንም ከእርሷ ብሉ፤ እኔ ልመናህን ችል አልልም። ተስፋህንም ያለ ዋጋ አልመልስም፤ የገባሁልህ ቃል ኪዳን እስኪፈጸም ድረስ ልቡናህን አጽና፤ እግዚአብሔርም ከአዳም ጋር ንግግሩን አቆመ።

አዳምም ወደሔዋን ተመለከተ፤ ተነሺ የአንቺን የበለስ ፍሬ ውሰጂ። እኔም ሌላውን እወስዳለሁ፤ ወደ ቤታችንም እንሂድ አላት። አዳምና ሔዋንም ተነሥተው ወደ ቤታቸው ሄዱ።፡የፀሐይ መግቢያው ሰዓትም ነበር። ከእርሷ ይበሉ ዘንድም አስቸኩለቻቸው /አጓጓቻቸው/። አዳምም ሔዋንን ከዚህ የበለስ ፍሬ እበላ ዘንድ እፈራለሁ፤ እርሷን ከመብላቴ የተነሣ የሚደርስብኝን

አላውቅምና አላት፡፡ አዳምም አለቀሰ፤ እንዲህ እያለ ይጸልይ ዘንድም በእግዚአብሔር ፊት ቆመ፡፡ አቤቱ ጌታችን ሆይ! ከዚህ የበለስ ፍሬ እንዳልበላ ሆዴን ሙሉ አድርገው፡፡ ከእርሷ በበላሁ ጊዜ ምን ትጠቅመኛለች፡፡ ከእርሷ እኛ ዘንድ እኔ ምን እፈልጋለሁ፡፡ አቤቱ ፈጣሪ ሆይ! ባለቀች ጊዜ እርሷን እፈልግ ዘንድ ለምን እሻለሁ፡፡ ዳግመኛ ከእርሷ ብበላ በእርሷ ምክንያት የሚመጣበኝን አላውቅምና አለ፡፡

የእግዚአብሔር ቃልም ወደ አዳም እንዲህ ሲል መጣ፡፡ አዳም ሆይ! ይህ ጥበቃ፣ ይህ ድካም፣ ይህ ትጋት፣ ይህ ፍርሃት ሕጌን ከመተላለፍ አስቀድሞ ለምን አልነበረም? ነገር ግን አዳም ሆይ! በዚህች ኃላፊት ምድር በምትኖርበት ዘመን እንስሳዊ ባሕርይ ያለው ሰውነትህ በርትቶ በኃይል እስኪቆም ድረስ ያለምድራዊ ምግብ መኖር አይችልም አለው፡፡ እግዚአብሔርም ከአዳም ጋር መነጋገሩን አቆመ፡፡

አዳምም የበለስን ፍሬ ወሰደ፣ በወርቅ ብትሮች ላይ አስቀመጣት፡፡ ሔዋንም የበለስን ፍሬ ወስዳ በዕጣን ላይ አስቀመጠቻት፡፡ ከፍሬዎቹ እያንዳንዱም ሚዛኑ በአንተ ዘንድ እንዳለው ሆነ፤ ከዚህች ምድር ፍሬ በገነት ያለው ፍሬ እጅግ ታላቅ ነውና፡፡ አዳምና ሔዋን ግን እንዳስለመዱ እስኪነጋ ድረስ ሌሊቱን ሙሉ ቁመው ቀኑ፡፡ ፀሐይ በወጣ ጊዜም ጸሎታቸውን ጨረሱ፡፡ ከጸሎቱ ፍጻሜ በኋላ አዳም ሔዋንን ሔዋን ሆይ! ከገነት በስተሰሜን በኩል ነይ፡ ለአራት የሚከፈል ባሕር፣ የሚመነጭ ምንጭ ወዳለበት ቦታም እንሂድ አላት፡፡

የሕይወት ውኃን ይሰጠን፣ ከእርሱም ያጠጣን ዘንድ እግዚአብሔርን እንለምነው፡፡ ሕያው እንዳንሆን እግዚአብሔር ከዕፀ ሕይወት አላበላንምና፡፡ በምድር ውኃም ያረካን ዘንድ፤ ከሕይወት ውኃ ይሰጠን ዘንድም እርሱን እንለምን፡፡ ሔዋንም ይህን ቃል ከአዳም በሰማች ጊዜ እሺ አለችው፡፡ ከገነት ትንሽ ከምትርቅ የውኃ ምንጭ ድንበር ወደ ገነት ጫፍ ተነሥተው መጡ፡፡ በእግዚአብሔር ፊት ይጸልዩ ዘንድም ቆሙ፡፡ ወደ እነርሱ ይመለከት፤ ይቅር

ይላቸው የልመናቸውንም ዋጋ ይሰጣቸው ዘንድ ለመኑት፡፡

ከሁለቱ ጸሎት በኋላም አዳም እንዲህ በሚል ቃል በእግዚአብሔር ፊት ጸሎት ጀመረ፡፡ አቤቱ አምላክ ሆይ! በገነት በነበርሁ ጊዜ ከዕፀ ሕይወት ሥር ሲፈስሱ ውኃዎችን ዐይ ነበር፡፡ ልቤም አይመኛቸውም ነበር፡፡ ሥጋዬም ከእነርሱ ይጠጣ ዘንድ አይሻም፤ ጽምንም አያውቅም ነበር፡፡ ዛሬ ከምንኖርባት ይልቅ እኔ ሕያው ነበርሁና፡፡ ሕያውን ደግሞ የሕይወት ምግብ አያስደንቀውም፡፡ አቤቱ ዛሬ ግን ሥጋዬ ከመጠማቱ የተነሣ ደረቀ፡፡ የሞተ ሰውም ሆንሁ፡፡ እድን ዘንድ የሕይወት ውኃን ስጠኝ፡፡ አቤቱ በምሕረትህ ከዚህ ፈተና፣ ስቃይ/ግርፋት/ አድነኝ፡፡ በገነትህ ምድር የምትኖረን ከሆነ ከዚህ ምድር ወደ ሌላ ምድር አውጣን አለው፡፡

የእግዚአብሔር ቃልም ወደ አዳም እንዲህ ሲል መጣ፡፡ አዳም ሆይ! ዕረፍት ወዳለባት ሌላ ምድር አውጣን የምትለው ከዚህች ምድር ሌላ ምድር የለም፡፡ ዕረፍት ያለባት መንግሥተ ሰማያት እንጂ፡፡ ወደ እርሷ መግቢያህ ደግሞ በአሁኑ ጊዜ አይደለም፡፡ የመከራው ጊዜ ከተፈጸመ በኋላ ነው እንጂ፡፡ እኔ አንተን ጻድቃን ዘሮችህንም ወደ ሰማይ ዐሳርጋለሁ፡፡ አንተ ዛሬ የምትፈልጋትን ለአንተም ለእነርሱም ዕረፍትን እሰጣለሁ፡፡ ጠጥተህ ሕያው ትሆን ዘንድ የሕይወት ውኃን ስጠኝ ማለትህም በዚህ ዕለት የሚሆን አይደለም፡፡ ወደ ሲኦል በምወርድበት፣ የብረት በሮችንም በምሰብርበት፣ የብረት ሰንሰለቶችንም በምቀጠቅጥበት ጊዜ ነው እንጂ፡፡ በገነት ታርፍ ዘንድም በቸርነቴ የጻድቃንን የአንተንም ነፍስ አድናለሁ፡፡ ይህም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ነው፡፡

ዳግመኛም የምትሻው የሕይወት ውኃ ዛሬ በዚህ ዕለት የሚፈጸምልህ አይደለም፡፡ በጎልጎታ ምድር በአንተ ራስ ላይ ደምን በማፈስስበት ዕለት ነው እንጂ፡፡ በዚያ ጊዜ ደሜ የሕይወት ውኃ ይሆንልሃል፡፡ ለአንተ ብቻ አይደለም ከዘሮችህ የሚያምኑብኝ ሁሉ ነው እንጂ፡፡[43] እርሱ ሕይወትም፡ እረፍትም

[43] ማቴ.፳፮፥፳፮

ይሆንላቸዋልና።

ዳግመኛም እግዚአብሔር አዳምን አለው። አዳም ሆይ! በገነት በነበርህ ጊዜ ይህ መከራ በአንተ ላይ አልደረሰብህም። ትእዛዜን በተላለፍህ ጊዜ ይህ ሁሉ መከራ ደረሰብህ እንጂ። ዛሬ ግን ሥጋህን መብል መጠጥ የሚያስጨንቀው ሆነ። በአንተ ዘንድ ከመሬት የሚፈልቀውን ውኃም ጠጣ አለው። እግዚአብሔርም ከአዳም ጋር ንግግሩን አቆመ።

አዳምና ሔዋንም ለእግዚአብሔር ሰገዱ፡ ወደ ውኃው ምንጭም ተመለሱ። ወደ ቤትም ሄዱ፡ ቀትር/የቀን እኩሌታም/ ሆነ። ወደ ቤት በቀረቡ ጊዜ ታላቅ እሳትን ተመለከቱ፡ አዳምና ሔዋንም ያን ጊዜ ፈርተው ቆሙ። አዳምም ሔዋንን በቤታችን ያለው እሳት ምንድን ነው? አላት። እኛ ሥራ እንሠራምና የምንጋግርበት፡ ወጥም የምንሠራበት፤ ሁብት የለንምና የዚህችን እሳት ምሳሌዋን ስሟንም አናውቅም። እግዚአብሔር ሱራፌን የእሳት ሰይፍ አስይዞ በላከው ጊዜ ነው እንጂ። እርሱ ያብረቀርቃል፤ ያበራል። ከመፍራታችን የተነሣም ወደቅን፤ እንደ ሞተ ሰውም ሆንን። ዛሬም ሔዋን ሆይ! እግዚአብሔር በእኛ ላይ ይቆጣ ዘንድ ወድዷል፤ ከእርሷም አባረረን አላት።

ሔዋን ሆይ! ዳግመኛም ከዚህ ሌላ ቤት ሳለን ትእዛዙን ተላለፍን፤ እርሱም ቤታችንን ትዞራት ዘንድ እሳትን እስከመላክ ደረሰ። ወደውስጧም እንገባ ዘንድም አንችልም፤ ከእግዚአብሔር ፊትስ የት እንሸሻለን? በገነት ውስጥ አያሳድረንም፤ ከጥሩ ነገሯም ሁሉ ከልክሎናል። በዚህች ቤትም አኖረን፤ እስከንጽናና ድረስ በውስጧ መከራውን ጨለማውንና ፈተናውን ታገሥን። ዛሬም ወደ ሌላ ምድር ከወጣን በውስጧ የሚሆነውን ማን ያውቃል? ምድር ምን እንደሆነች፡ ከዚህች ጨለማም ፈጽማ የጨለመች እንደሆነች ማን ያውቃል? በዚህች ምድር ቀን ይሁን ጨለማ ማን ያውቃል? ሩቅ ወይም ቅርብ እንደሆነችስ ማን ያውቃለ? ሔዋን ሆይ! እግዚአብሔር ከገነት ወደየት ያርቀን ዘንድ ይሻል?

ሔዋን ሆይ! እግዚአብሔር ትእዛዙን በመተላለፋችን ይህን ማየት ቢከለክለን ሁል ጊዜ እርሱን እንለምናለን:: እግዚአብሔር ከተጽናናንባት ከዚህች ምድር ወደ ሌላዋ ኃላፊ ምድር ያወጣን ዘንድ ይፈልጋል:: ነፍሳችንም ይገድል፣ ከምድር ገጽም ያጠፋን ዘንድ ይሻል:: ሔዋን ሆይ! ከገነት በራቅን ጊዜ ዳግመኛ እግዚአብሔርን የት እናገኘዋለን? ወርቁን፣ ዕጣኑን፣ ከርቤውን፣ የበለሱንም ፍሬ ይሰጠን ዘንድ እንለምነው:: ዳግመኛ ያጽናናን ዘንድ የት እናገኘዋለን:: በገባልን ቃል ኪዳን ባሰበን ጊዜ የት እናገኘዋለን? አላት:: አዳምም ዝም አለ::

አዳምና ሔዋንም ወደ ቤታቸው ይመለከቱ ነበር:: እሳትም በዙሪያዋ ትወጣ ነበር:: ይህች እሳትም ከሰይጣን ነበረች:: እርሱ ከዕፀዋት የደረቁ ሳሮችን ሰብስቦ ተሸክሞ ወደ ቤት አምጥቷልና:: ቤቱን ያቃጥል ዘንድም በውስጣቸው እሳትን ጨምሮባቸዋልና:: ይኸን የሚያደርገው አዳምና ሔዋን እንዲያዝኑ፣ በእግዚአብሔርም ተስፋ እንዲቆርጡ፣ እንዲክዱትም ያደርጋቸው ዘንድ ነው:: ነገር ግን በእግዚአብሔር ቸርነት ቤቱን ያቃጥል ዘንድ አልቻለም:: እግዚአብሔርም በቤቱ ዙሪያ መልአኩን ላከ:: እሳቷ እስክትጠፋ ቤቷን ይጠብቃት ዘንድ ከቀኑ የጀመረች እሳት እስኪነጋ ድረስ ትነድ ነበርና:: ቀኑም አርባ አምስተኛው ቀን ነበር:: አዳምና ሔዋንም ቁመው እሳቱን ይመለከቱ ነበር:: ከእሳቱ ፍርሀት የተነሣም ወደ ቤት መቅረብ አልቻሉም:: ሰይጣንም የእሳቱ ነበልባል ፈጽሞ ከፍ እስኪል ድረስ ዕንጨት እየተሸከመ ወደ እሳት ይወረውር ነበር:: ቤታቸውም ተሰወረች:: ከእሳቱ ብዛት የተነሣ ቤቷ ትቃጠላለች ብሎ አስቦ ነበርና፡ነገር ግን የእግዚአብሔር መልአክ ይጠብቃት ነበር:: ሰይጣንም ይራገም ዘንድ አልቻለም:: በእርሱ ላይ የሠለጠነ ይሆን ዘንድ አልከፋበትም::

ከእርሱ በሚወጣው ቃልም አላዘኑም:: በዚህም ልቡናውን ያፀና ነበር:: የእግዚአብሔር ቃል እስኪመጣ ድረስም ክፉ ነገር አልተናገረውም::

አገልጋዮቼን ያሳትህ ሰይጣን ሆይ! ወግድ፤ እስኪለው ድረስ:: አንተ መጥፋታቸውን ትሻለህና:: ምሕረቴ ባትከለክለኝ አንተንም ሰራዊትህንም ከምድር ገጽ ባጠፋሁህ ነበር:: እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ታገሥሁህ እንጂ አለው:: ሰይጣንም ከእግዚአብሔር ፊት ሸሸ:: እሳቷም በቤቱ ዙሪያ ቀኑን ሁሉ ትነድድ ነበር:: ይህም አዳምና ሔዋን ከገነት ከወጡ አርባ ሰባት ቀን ነው::

የእሳቱ ነበልባል ትንሽ እንደ ቀዘቀዘ ባዩ ጊዜ እንዳስለመዱ ይገቡ ዘንድ ወደ እርሷ መሄድን ጀመሩ:: ነገር ግን ከእሳቱ ነበልባል የተነሣ አልቻሉም:: አዳምና ሔዋንም በቤታቸውና በመካከላቸው ካለው የእሳት ነበልባል የተነሣ ማልቀስ ጀመሩ:: የእሳቱ ነበልባልም ወደ እነርሱ ቀረበ፤ እነርሱም ፈሩ::

አዳምም ሔዋንን በመካከላችን ያለች ይህችን እሳት ተመልከቺ፤ ከዚህ ቀድሞ እሺ ትለን ነበር:: ሕጉን ከተላለፍን በኋላ ግን እንደ ቀድሞው እሺ አትለንም:: እኛ የተፈጥሮን ድንበር ተላልፈናልና:: አካላችን ጠባያችንም ተለወጠ:: የእሳት ግን ጠባያዊ ተፈጥሮዋ አልተለወጠም:: ስለሆነም በእኛ ላይ ኀያል ሆነች:: ወደ እርሷ በቀረብን ጊዜ ሥጋችንን አቃጠለችን:: አዳምም በእግዚአብሔር ፊት እንዲህ ሲል ቆመ፤ እናድርባት ዘንድ ባዘዝኸን በቤታችንና በእኛ መካከል የለየችን ይህችን እሳት ተመልከት፤ እነሆ መግባት አንችልምና::

እግዚአብሔርም አዳምን ሰማው፤ ቃሉንም ወደ እርሱ ላከ:: አዳም ሆይ! ይህን እሳት ተመልከት፤ ከምታስደስት ካማረች ከገነት ይልቅ ነበልባሏ፣ ላቧ ምንድን ነው? አንተ በሕጌ ጥላ ሥር ሳለህ ፍጥረታቱ ሁሉ ይሰግዱልህ ነበር:: ትእዛዜን በተላለፍህ ጊዜ ግን ፍጥረታት ሁሉ በአንተ ላይ አመጹ /ጸኑ/:: ዳግመኛም አዳም ሆይ! ተመልከት፤ እንደ እኔ በመለኮታዊ ክብር ከፍ ከፍ ያደርግህ ዘንድ ቃል የገባልህ ሰይጣን ቃሉን አልፈጸመልህም:: ጠላት ሆነህ እንጂ:: ሊያቃጥልህ ወድዶ ይህን እሳት ያዘጋጀው እርሱ ነው:: አዳም ሆይ! አንድ ቀን ስንኳ ቃሉን ለምን አልፈጸመልህም? ትእዛዙን በሰማህ ጊዜ በአንተ ላይ የነበረው ክብር ተገፈፈ እንጂ:: አዳም ሆይ! ከአንተ ጋር ይህን ቃል ኪዳን

በማድረጉ አንተን የወደደህ ይመስልሃልን? ወይም ወደ ላይ ለማውጣት የሚሻ መስለህን? ይህን የሚያደርግ አይደለም፡፡

አዳም ሆይ! በአንተ ላይ ስላለው ፍቅሩ አይደለም፡፡ ከብርሃን ወደ ጨለማ፣ ከታላቅነት ወደ ታናሽነት፣ ከክበር ወደ ኀሳር፣ ከደስታ ወደ ኃዘን፣ ከዕረፍት ወደ ፍጹም ድካም ሊያወጣህ ይወዳል እንጂ፡፡ ዳግመኛም እግዚአብሔር አዳምን አለው፡፡ ሰይጣን በዚህ መልክ በቤትህ ዙሪያ ያደረገውን ይህን እሳት ተመልከት፡፡ ቃሉን ከሰማችሁ እርሱ አንተንም ዘርህንም ይዞርሃል /ይፈትንሃል/፡፡ በእሳትም ይገዛሃልና፡፡ ከሞታችሁም በኋላ ወደ ሲኦል ትወርዳላችሁ፡፡ የእሳት ነበልባልንም ታያላችሁ፤ በአንተና በዘርህ ላይም ይከባል፡፡ ከእርሱም መድኀኒት አይገኝላችሁም፤ ቃሌ [ወልደ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ] እስኪመጣ ድረስ ከእሳቱ ብዛት የተነሣ ዛሬ ወደ ቤትህ መግባት እንዳልቻልህ፡፡

በቃል ኪዳኑ የመጨረሻ ዕለት መንገዱን ይለይልሃል፡፡ ፈጥነህ ወደ እርሷ ትገባ ዘንድ አይደለም፡፡ ቃሌም በውስጧ ነው፡፡ መንገድህንም ይለይልሃል፡፡ ወደ ዕረፍትም ትገባለህ፡፡ እግዚአብሔርም አዳምን በእሳቷ ላይ ጠራው፡፡ አዳም ወደ ቤቱ እስኪሻገር ድረስም በእግዚአብሔር ትእዛዝ እሳቷ ተከፈለች፡፡

ለአዳምም መንገድ ሆነችው፡፡ እግዚአብሔርም ከአዳም ጋር ንግግሩን አቆመ፤ አዳምና ሔዋንም ወደ ቤታቸው መሄድ ጀመሩ፡፡ ከእሳቱ መንገድ በደረሱ ጊዜ ሰይጣን በአውሎ ነፋስ አምሳል እሳቱን እፍ አለባቸው፡፡ በአዳምና በሔዋን ላይም የእሳት ፍም አደረገባቸው፡፡ ሰውነታቸው ከልብስ የተራቆተ ነበረና የእሳቱ ፍም ሥጋቸውን አቃጠለው፡፡ ከእሳቱ ነበልባል /ማቃጠል/ የተነሣም አዳምና ሔዋን አለቀሱ፡፡ አቤቱ ጌታችን ሆይ! አድነን፤ አታቃጥለን፤ በዚህ በሚያስጨንቅ ሥቃይም አትግረፈን፤ ትእዛዝህን እንደመተላለፋችንም አትቅጣን እያሉ አለቀሱ፡፡

እግዚአብሔርም ሰይጣን በእሳት ያቃጠለውን ሥጋቸውን ተመለከተ። ሌላውን መልአኩን ላከ። የእሳቱን ፍምም ከእነርሱ አስወገደ። በሥጋቸው የቀረ እሳት ግን ነበር። እግዚአብሔርም አዳምን አለው። ለአንተ አምላክነትን፣ ትዕቢትን ይሰጥህ ዘንድ የወደደ የሰይጣንን ወዳጅነት ተመልከት፤ እነሆ! በእሳት አቃጠለህ። ከምድር መጥፋትህንም ይሻል። አዳም ሆይ! ወደ እኔ ተመልከት፤ የፈጠርሁህ እኔ ከእርሱ ስንት ጊዜ አዳንሁህ። እርሱ ቢሆን ኖሮ ባጠፋህ ነበር።

ዳግመኛም ሔዋንን አላት፤ በገነት ውስጥ ቃል የገባልሽ እነሆ! ይህ ነው። ከዕፀ በለስ በበላችሁ ጊዜ ዐይናችሁ ይገለጣል። አማልክትም ትሆናላችሁ፤ ከፉና በጐውንም ታውቃላችሁ አለሽ።[44] እነሆ! ሥጋችሁን በእሳት አቃጠለው። ከገነት ጣዕም ይልቅም የእሳትን ጣዕም አቀመሳችሁ። ከፉ የሆነ የእሳትን መቃጠልም አሳያችሁ፤ ዐይኖቻችሁም መልካምን አላዩም። በእኔ ዘንድ በውስጧ እያላችሁ ገነትን ዐያችኋት። ከሰይጣን የደረሰባችሁን ከፉ ነገር ሁሉ አያችሁ። አምላክነትንም ለእናንተ ሊሰጣችሁ አይችልም። የሚያስደስት ቃል ኪዳንም አይፈጽምላችሁም። ለእናንተ ከእናንተ በኋላ ለሚመጣው ዘራችሁም መራራ ሆነባችሁ እንጂ። እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ንግግሩን አቆመ።

አዳምና ሔዋንም ወደ ቤት ገቡ። ሥጋቸውን ካቃጠለው ከእሳቱ የተነሣም ፈርተው ነበር። አዳምና ሔዋንን በዚህ ዓለም አሁን ሥጋችንን ያቃጠላት እሳት በሞትን ጊዜማ ሰይጣን ነፍሳችንን እንዴት ያቃጠለው ይሆን? እነሆ! ድኅነታችን ሩቅ ነውና ወዮልን። ይቅር ይለን ዘንድ፤ ቃል ኪዳኑንም ይፈጽምልን ዘንድ፣ እግዚአብሔር ካልመጣ አሉ።

ከዚህ በኋላ አዳም እና ሔዋን ቤቱን ዞሩ። ዳግመኛ ወደ እርሷ በመግባታቸውም ከእርሷ ሊባረኩ ፈለጉ። በዐሳባቸው ሁለተኛ ፈጽሞ ወደ እርሷ የማይገቡ መስሏቸው ነበርና። የፀሐይን መግባት በተመለከቱ ጊዜ የእሳቱ ዋዕይ ወደ አዳምና ወደ ሔዋን ወደ ቤታቸውም ውስጥ ገባ። በውስጧ ይተኙ ዘንድም አልቻሉም። ፀሐይ ከገባች በኋላም ከቤት ወጡ። ከገነት ከወጡ

44 ዘፍ. ፫÷፩

በኋላም ዕለታቱ አርባ ሰባት ነበሩ፡፡ አዳምና ሔዋንም እንዳስለመዱት ወደ ገነት ተራራ ራስ ሥር በዚያ ይተኙ ዘንድ፣ በደላቸውንም ይቅር ይላቸው ዘንድ፣ ወደ እግዚአብሔር ቁመው ጸለዩ፡፡ በተራራው ራስ ግርጌም ተኙ፡፡

የመልካም ነገር ጠላት ሰይጣንም በሕሊናው እንዲህ ይል ነበር፡፡ እግዚአብሔር ለአዳም የድኅነት ቃል ኪዳን ገብቶለታል፡፡ ከሚደርስበት ጾዋትወ መከራ ሁሉ ያድነው ዘንድ፡፡ ለእኔ ግን ቃል ኪዳን አልገባልኝም፤ ከመከራም አላዳነኝም፡፡ የነበርሁበትን መንግሥቱንም እርሱን፡ ዘሩንም ያኖረው ዘንድ ቃል ኪዳን ገብቶለታል፡፡ እኔ አዳምን ልግደለው፡፡ ከእርሱ የተነሣ መሬት ትከለከል ዘንድ፣ ለእኔ ብቻም ትሆን ዘንድ በሞተ ጊዜም መንግሥተ ሰማያትን የሚወርስ ዘር አይቀርለትም /አይገኝም/፡፡ መንግሥቴም ለእኔ ሆና ትቀራለች፡ እግዚአብሔርንም ያስጨንቀዋል፡፡ እኔንም፣ ሰራዊቴንም ወደ እርሷ ይመልሰኛል አለ፡፡

ከዚህ በኋላም ሰይጣን ሰራዊቶችን ጠራቸው፡፡ ሁሉም መጥተው ከእርሱ ዘንድ ደረሱ፡፡ አቤቱ ጌታችን ሆይ! ምን ታደርግ ዘንድ ትወዳለህ? አሉት፡፡ እናንተ ታውቃላችሁ፤ ይህ አዳምን ከመሬት የፈጠረ እግዚአብሔር ነው፡ መንግሥታችንን የወረሰ እርሱ ነው፡ ኑ ተሰብስበን እንግደለው፡፡ ወይም ድንጋይ በላያቸው ጥለን እርሱንም ሔዋንንም እንግደል፡ ኑ አላቸው፡፡ እነርሱም ሰሙት፡፡ አዳምና ሔዋን ወደ ሚገኙበት ተራራማ ቦታም መጡ፡፡ እነርሱ ግን ተኝተው ነበር፡፡

ሰይጣንም ከሰራዊቱ ጋር ታላቅ ድንጋይ አንሥቶ ሳያዘንፍ በትክክል ጣላት፡፡ ቦታው ድንጋያማ፣ ገደላማ ስለሆነ ድንጋዩ በላያቸው በወደቀ ጊዜ ድንጋይ ከእነርሱ ወደ ጉድጓድ ይገባል፡ እነርሱም ይድናሉ እንጂ አይሞቱም፣ ብሎ በሕሊናው አሰቧልና፡፡ ሰይጣንም "ይህችን ድንጋይ በትክክልም በላያቸው ጣላት፤ ከእነርሱም ወደ ሌላ አቅጣጫ እንዳትሄድ በላያችሁ በጣላችኋት ጊዜም ሽሹ እንጂ አትቁሙ" አላቸው፡፡ እነርሱም እንዳዘዛቸው አደረጉ፡፡

ድንጋይቱ ወደ አዳምና ወደ ሔዋን ስትወርድም እግዚአብሔር በአዳምና በሔዋን ላይ እንደድንኳን ትሆንላቸው ዘንድ እንዳትጎዳቸውም አዘዛት። በእግዚአብሔር ትእዛዝም እንዲሁ ሆነች። ድንጋይዋም በወደቀች ጊዜ ከእርሷ የተነሣ ምድር ተናወጠች። ከታላቅነቷም የተነሣ ታወከች። መሬት ከመናወጧ፣ ከመታወኳ የተነሣም አዳምና ሔዋን ከእንቅልፋቸው ነቁ። ለእነርሱም ድንጋዩ እንደ ድንኳን ሆኖላቸው አገኙት። እነርሱም ከሰማይ በታች እንደሆኑ አላወቁም፤ እነርሱ በድንኳኑ ሥር አልነበሩምና ዐይተው ፈሩ።

አዳምም ሔዋንን ይህ ተራራ ስለምን ዝቅ አለ? መሬትስ ለምን ተነዋወጠች? /ታወከች?/ ይህች ድንጋይስ በእኛ ላይ እንዴት ተጋረደች? እግዚአብሔር ሊመታን፣ በሥር ቤትም ሊያስረን ይወዳልን? አላት። ያለትእዛዙ ከቤት በመውጣታችን በእኛ ላይ ሊቆጣ መሬትንም ሊያስምጥብን? ነውን? አላት። እኛ በፈቃዳችን አድርገናልና። ከቤት በወጣን ጊዜም አልመረመርነውም /ልብ አላደረግነውም/። ወደዚህች በታም መጣን አላት። ሔዋንም ምድር ስለእኛ የምትናወጽ ከሆነ አዳም ሆይ! ወዮልን፡ ግርፋታችን በዛ፤ ነገር ግን ወደ እግዚአብሔር እንጸልይ ዘንድ ተነሥ፤ በእኛ ላይ ስለተከለለች /ስለተጋረደች/ ያሳውቀን ዘንድ አለችው።

አዳምም ይህን ተጋድሎ ያሳውቀው ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ቆሞ ጸለየ። አዳምም እስኪነጋ ድረስ ለጸሎት ቆሞ ነበር። አዳም ሆይ! ከቤት በመውጣትህ ማን አሰወገደህ? ወደዚህም በታ እንዴት መጣህ? የሚል የእግዚአብሔር ቃል መጣ። አዳምም እግዚአብሔርን ወደ ቤት በሚገባው የእሳት ነበልባል ምክንያት እኛ ወደ ዚህች በታ መጣን አለው። እግዚአብሔርም አዳምን አዳም ሆይ! የአንዲትን ቀን የእሳት ዋዕይ አትፍራ። በሲኦል ብትኖርስ እንዴት በሆንህ? አዳም ሆይ! አትፍራ፤ እመታህም ዘንድ ይህን ድንጋይ እኔ እንደጋረድሁብህ በልብህ አታስብ። አምላክ ለመሆን ቃል የተግባባኸው ሰይጣን እንዳይመታህ ነው እንጂ፤ ሕይወታችሁን ከምድረ ገጽ ያጠፋችሁ ዘንድ

በአንተና በሔዋን ላይ የወረደው ይህ ድንጋይም ታላቅ ነው፡፡ ነገር ግን በቸርነቴ ይህች ደንጊያ በላያችሁ ትኖር፣ ትጋረድም ዘንድ አዘዝኳት አለው፡፡

በቦታችሁ ያለ ይህ ድንጋይም ምልክት ነው፡፡ አዳም ሆይ! ይህ ምልክትም ወደዚህ ምድር በመጣሁ ጊዜ ሰይጣን እኔን ለመግደል የአይሁድን ሕዝቦች ያስነሣል፡፡ በድንጋይ ውስጥም ይጨምሩኛል፡፡ ታላቅ ድንጋይም ይገጥሙብኛል፡፡[45] በድንጋይ ውስጥም ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት እቆያለሁ፡፡ በሦስተኛው ቀንም እነሣለሁ፡፡[46] ለአንተም ለሚያምኑብኝ ዘሮችህም ድኅነት ይሆናል፡፡ አዳም ሆይ! ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት እስኪፈጸም ድረስ ግን ከድንጋዩ አላወጣህም አለው፡፡ እግዚአብሔርም ከአዳም ጋር ንግግሩን አቆመ፡፡

አዳምና ሔዋንም ጌታችን እንደነገረው ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በድንጋዩ ታች ቆዩ፡፡ ዳግመኛም ከቤት ስለመውጣታቸው፣ ያለ እግዚአብሔር ትእዛዝም ወደ አሉበት ቦታ ስለመምጣታቸው አዘኑ፡፡ ከሦስት መዓልት ከሦስት ሌሊት በኋላም እግዚአብሔር ድንጋዩን ፈታው /ለቀቀው/፡፡ ከውስጧም አወጣቸው፤ ሥጋቸውም የደረቀ ሆነ፡፡ ከለቅሶ፤ ከኃዘን የተነሣም ዐይኖቻቸው ታወኩ /ፈዘዙ/፡፡ አዳምና ሔዋንም ወደ ቤታቸው /ዕቃ ቤት/ ሄደው ገቡ፡፡ በዚህች ዕለትም እስከ ምሽት ድረስ ይጸልዩ ዘንድ ቆሙ፡፡ ይህም አዳምና ሔዋን ከገነት ከወጡ ከዓምሳ ቀን በኋላ ነበር፡፡ ዳግመኛም አዳምና ሔዋን ወደ እግዚአብሔር ይጸልዩ፣ በዚህች ዕለትም ምሕረትን ከእግዚብሔር ይለምኑ ዘንድ ከቤታቸው ተነሡ፡፡

በነጋ ጊዜም አዳም ሔዋንን ለሥጋችን ሥራ እንሠራ ዘንድ ነይ እንሂድ አላት፡፡ ከቤትም ወጡ፡፡ ሥጋቸውን የሚሸፍኑበት ይፈልጉ ዘንድ ከደቡብ ወደ ገነት ጫፍ ደረሱ፡፡ ነገር ግን ሥራን አያውቁም ነበርና አላገኙም፡፡ ሥጋቸውም በደም የታለለች /የተሸፈነች/ ሆነች፡፡ ከቅዝቃዜውና ከሙቀቱ የተነሣ ዲዳ ሆኑ፡፡ አዳምም ሥጋቸውን የሚሸፍኑበትን ያሳያቸው ዘንድ ፈልጎ በእግዚአብሔር ፊት ቆመ፡፡ የእግዚአብሔር ቃልም እንዲህ ሲል መጣለት፡፡ አዳም ሆይ! ሔዋንን

[45] ማቴ. ፳፯+፶፱-፷፩

[46] ማቴ. ፳፰+፩

ይዘህ ከዚህ ቀደም ወደ ጾማችሁበት ባሕር ኑ። በዚያም አንበሶች ሥጋቸውን የበሏቸው
የበጐችን ቆዳ ታገኛላችሁ፣ የቀረውን ቆዳቸውንም ውሰዱ፤ ልብስ አድርጋችሁም ልበሱት አለው።

አዳምም ይህን ቃል ከእግዚአብሔር በሰማ ጊዜ ሔዋንን ይዞ ከደቡብ ጫፍ ይጾሙበት ወደ ነበረው የውኃ ምንጭ ወዳለበት ወደ ሰሜናዊው የገነት ጫፍ ተመለሰ። በመንገዱ ሲሄድም ከቦታው ከመድረሳቸው በፊት ከፉ ሰይጣን ከአዳም ጋር ስለልብሱ፣ ስለስቃዩ ሲነጋገር የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰማ።

ሰይጣንም የበጐች ቆዳ ካለበት ቦታ ፈጥኖ ሄዶ ይወስደው ዘንድ ወደደ። አዳምና ሔዋን እንዳያገኟቸው በእሳት ያቃጥላቸው፣ ወደ ባሕርም ይጥላቸው ዘንድ ወደደ። ይህን በወደደ ጊዜም የእግዚአብሔር ቃል ከወደ ሰማይ መጣ። አዳምና ሔዋን ወደ እርሱ እስኪመጡ ድረስም በእነዚህ ቆዳዎች /ሌጦዎች/ ገመድ አሰረው። ወደ እርሱ በቀረቡ ጊዜም ከመልኩ የተነሣ ፈሩ። የእግዚአብሔር ቃልም ወደ አዳምና ሔዋን እንዲህ ሲል መጣ። በእባብ ተሰውሮ ያሳታችሁ ይህ ነው። የብርሃን ልብሳችሁንም የገፈፋችሁ፣ የነበራችሁን ክብርም ያስቀረባችሁ እርሱ ነው።

አዳም ሆይ! ታላቅ ስለሆነች አምላክነት ቃል ኪዳን የገባላችሁ እርሱ ነው። በእርሱ ዘንድ መልካም የት አለ? እነሆ ዛሬ መልኩ የከፋ በመላእክት ዘንድ የሚያስጸይፍ ሰይጣን /ጽኑ ጠላት/ የሚሰኝ ሆነ። አዳም ሆይ! እርሱ የእንስሳትን ምድራዊ ልብስ ወስዶ ያጠፋ ዘንድ ወድዷልና፤ ትለብሰው ዘንድም አልተወህም። የተከተላችሁት የዚህ /የሰይጣን/ ደግነቱ ምንድን ነው? ስለታዘዛችሁለት የጠቀማችሁስ ምንድን ነው? የሰይጣን ስራዊቶቹንም አስተውሉ፤ፈጣሪያችሁ እኔንም ተመልከቱ፣ የሚደረግላችሁን፣ ጥሩ ሥራዬንም አስተውሉ። እነሆ! እኔ እስከትደርሱ፣ እስኪታዩትም ድረስ አስርሁት፣ ደካማነቱንም ተመለከታችሁ፤ ኀይልም አልነበረውም አላቸው። እግዚአብሔርም

ሰይጣንን ከእስራቱ ፈታው።

ከዚህ በኋላ አዳምና ሔዋን ተደነቁ። በመፈጠራቸውም በእግዚአብሔር ፊት አለቀሱ፤ ሥጋቸው ምን እንደሆነች አሰቡ፤ ምድራዊ ልብስም ስለቸገራቸው አለቀሱ። አዳምም ሔዋንን ሔዋን ሆይ! የምንለብሰው የእንስሳት ቆዳ ይህ ነው። በለበስነው ጊዜ የሞት ምልክት በእኛ ላይ ገባ። የእነዚህ ቆዳ /ሌጦ/ በገ**ች እንደሞቱ፣ እንዳረጁም እኛም ዳግመኛ እንደ እነርሱ እናረጃለን፤ እንሞታለንም አላት። አዳምና ሔዋንም ቆዳውን /ሌጦውን/ ይዘው ወደ ቤታቸው ተመለሱ። ወደ እርሷ በተመለሱ ጊዜም እንዳስለመዱ ቆመው ጸለዩ፤ እንዴት አድርገው ልብስ እንደሚያደርጉት ተቀምጠው እያሰቡም ነበር። ጥበብ አልነበራቸውምና። እግዚአብሔርም እንዴት እንደሚያደርጉት ያስረዳቸው ዘንድ መልአኩን ወደ እነርሱ ላከ።

መልአኩም አዳምን ከተምር እሾህን አምጣ አለው። አዳምም የእግዚአብሔር መልአክ እንዳዘዘው አመጣ። መልአኩም በፊታቸው ቀሚስ በሚሰፋ አምሳል ያደርገው ጀመር። እየተመለከተም እሾሁን ይዞ በውስጡ ተከለው፤ ዳግመኛም መልአኩ እሾሆቹን በሌጦው /በቆዳው/ ውስጥ የተሰወሩ እንደአንድ ወጥ ልብስም የተሰፉ ይሆኑ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ። እንደ እግዚአብሔር ትእዛዝም እንዲሁ ሆኑ። ልብስም ሆነላቸው፤ እነርሱንም አለበሳቸው፤ ያን ጊዜም እርስ በርሳቸው ከመተያየት የሥጋቸው ራቁትነት ተሰወረላቸው። ይህም በሃምሳ አንደኛው ቀን መጨረሻ ሆነ።

አዳምና ሔዋንም ሥጋቸው በተሸፈነ ጊዜ ይቅር ካላቸው፣ እርቃናቸውንም ከሸፈነላቸው ከእግዚአብሔር ምሕረትን ሽተው ይጸልዩ ዘንድ ቆሙ። በዚህች ዕለት በእግዚአብሔር ፊት በጸሎት ኢያሉ አልታወኩም / አልተረበሹም/። ንጋት በሆነ ጊዜ እንዳስለመዱት ፀሐይም ሲወጣ ጸሎታቸውን ጸለዩ። ከቤትም ወጡ። አዳምም ሔዋንን ከቤት የምዕራቡን ጫፍ አናውቅምና ዛሬ እናየው ዘንድ እንሒዳለን አላት። እነርሱም ወደ ምዕራቡ ጫፍ ይሄሔዱ

ዘንድ ወጡ፡፡ ከቤት በራቁ ጊዜም ሰይጣን ወደ እነርሱ መጣ፡፡ ከሦስት ቀን ጀምረው እንደተራቡ እንደ ሁለት አንበሶችም ተመስሉ በቤታቸውና በእነርሱ መካከል ተሰወሩ፡፡ እነዚህም ሰባብረው ይበሏቸው ዘንድ ወደ አዳምና ወደ ሔዋን ደረሱ፡፡

አዳምና ሔዋንም ከእጆቻቸው ያድናቸው ዘንድ ፈልገው ወደ እግዚአብሔር አለቀሱ፡፡ የእግዚአብሔር ቃልም ወደ እነርሱ መጣ፡፡ ከእነርሱም አስወገዳቸው፡፡ እግዚአብሔርም አዳምን አለው፡፡ አዳም ሆይ! የምሥራቅን ጫፍ ትተህ በምዕራብ ጫፍ ምን ትሻለህ? መኖሪያህ በዚህ ነው፡፡ ዛሬም ወደ ቤትህ ተመለስ፡፡ ሰይጣን እንዳያስትህ፣ መከራም እንዳያመጣብህ በዚያው ተቀመጥ፡፡ አዳም ሆይ! በምዕራብ ጫፍ ከአንተ ዘር ይወጣል፡፡ ከእነርሱ የተነሣም ይመላል፡፡ የሰይጣንን ትዕዛዝ በመስማታቸው፣ ሥራዎቹን በመከተላቸው፣ በበደላቸውም ያረክሱታል፡፡

እኔም በእነርሱ ላይ የጥፋት ውኃን አመጣለሁ፡፡ ሁሉንም አሰጥማቸውለሁ፡፡ ከእነርሱ ውስጥ የሚቀሩ ጻድቃንን አስቀራለሁ እንጂ፡፡ ከዚህች ምድር እስከ ምትርቀዋ ምድር ድረስ አወጣቸዋለሁ፡፡ አንተ ዛሬ የምትኖርባት ይህች ምድርም ያለ አንድ ሰው ምድረ በዳ ሆና ትቀራለች፡፡[47]

እግዚአብሔር ይህን ነገር ካላቸው በኋላ ወደ ቤታቸው ተመለሱ፡፡ ሥጋቸውም ደረቀች፡፡ ከጾም፣ ከጸሎት፣ ከኃዘን ብዛት፣ እግዚአብሔርን ካለመስማታቸው /ከመደፋፈራቸው/ የተነሣም ኀይላቸው ደከመች /አለቀች/፡፡ አዳምና ሔዋንም እስኪነጋ ድረስ ሌሊቱን ሁሉ ይጸልዩ ዘንድ በቤታቸው ቆሙ፡፡ ፀሐይ በወጣ ጊዜ አዳምና ሔዋን ከኃዘኑ ስሜት የተነሣ ወደየት እንደሚሄዱም አላወቁም፤ ቤታቸውን ዞሩት፡፡ ከሰሜን ወደ ገነት ጫፍ ይራመዱ ነበር፡፡ ወደጫፍም ይወጡ ዘንድ ጀመሩ፡፡ ሰፋት ወደ ሌለው የምሥራቅ ጫፍ እስኪደርሱ ድረስ፡፡ ጸሎታቸው፣ ልመናቸው ከሊቃነ ጳጳሳቱ አለቃ ከአባ ባስልዮስ ከንጉሣችን ኀይለ ሥላሴ፣ ከጌታችን ከአርአያ ዮሐንስ፣ ከሁላችንም የጥምቀት ልጆች ጋር ይሁን፡፡ አሜን፡፡

47 ዘፍ.፮÷፲፩-፲፰

## ምዕራፍ አራት

## ገድለ አዳም ዘሐምሌ

አንድ አምላክ በሆነ በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም ሐምሌ ስድስት ቀን የሚነበብ የአባታችን የአዳም፣ የእናታችን ሔዋን የገድላቸው ዜና ይህ ነው፡፡ ጸሎታቸው፣ በረከታቸው፣ የይቅርታ ልመናቸው በጳጳሳቱ አለቃ ባስልዮስ በንጉሣችን ኀይለ ሥላሴ፣ በእኛም ላይ ለዘለዓለሙ ጸንቶ ይኑር፤ አሜን፡፡

ኪሩብም በምዕራብ በር ቆሞ አዳምና ሔዋን ወደ ገነት እንዳይገቡ የገነትን በር ይጠብቅ[48] ነበር፡፡ ኪሩብም እግዚአብሔር እንዳዘዘው አላጠፋቸውም፡፡ አዳምና ሔዋን ግን ከምሥራቅ ወደ ገነት ጫፍ በደረሱ ጊዜ ኪሩብ እንደሌለ ያስቡ ነበር፡፡ ሊገቡ ፈልገው በበር ላይ ቆመው ሳለ ያን ጊዜ ኪሩብም የተሳለ ሰይፍ ይዞ ሊገድላቸው መጣ፡፡ ገነት በመግባታቸው እግዚአብሔር እንዳያጠፋው ፈርቶ ነበርና፡ ነበልባሉ ከሩቅ የሚወጣ /የሚታይ/ ሰይፍም በኪሩብ ዘንድ ነበር፡፡

በአዳምና በሔዋን ላይ በተነሣ ጊዜም ነበልባሉ አልወጣለትም ነበር፡፡ ኪሩብም እግዚአብሔር ይቅር እንደሚላቸው፣ ወደገነትም እንደሚመልሳቸው አሰበ፡፡ ኪሩም ወደ መንግሥተ ሰማያት ስለመግባታቸው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ /ፈቃድ/ ያውቅ ዘንድ እያደነቀ ቆመ፡፡ ወደ ሰማይ መውጣት ግን አልቻለም፣ ወደ እነርሱ ቀርቦ ቆሞ ቀረ፡፡ ከእነርሱ ይለይ ዘንድም አልቻለም፡፡ ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ወደ ገነት እንዳይገቡ እንዳያጠፋውም ፈርቶ ነበርና፡፡

አዳምና ሔዋንም የሚያንጸባርቅ የእሳት ሰይፍ በእጁ ይዞ ወደ እነርሱ ሲመጣ ባዩት ጊዜ ከመፍራታቸው የተነሣ በግንባራቸው ወደቁ፤ እንደ ሞተ ሰውም ሆኑ፡፡ ያን ጊዜ ሰማይና ምድር ተነዋወጡ፡ ሌሎችም የኪሩቤል ሰራዊትም ገነትን ወደ ሚጠብቅ ወደ ኪሩብ ወደ መሬትም ወረዱ፡፡ በመገረም፣

---

[48] ዘፍ.፫፥፳፬

በመደመምም ተመለከቱት፡፡ ዳግመኛም ሌሎች አዳምና ሔዋን ባሉበት አትራቢያ ወረዱ፡፡እነርሱም ልዩ በሆነ ኃዘንና ደስታ ውስጥ ነበሩ፡፡ደስታቸውም አዳምን ይቅር እንዳለው የእርሱ ወደ ሆነው የደስታ ቦታ ገነትም እንደሚመልሰው ስላሰቡ ነበር፡፡

ስለ አዳም ማዘናቸውም የወደቀ /የተጣለ/ ስለነበር፤ እርሱም ሔዋንም እንደሞተ ሆነው ስለነበር ነው፡፡ በልባቸውም አዳም በዚህ ቦታ የሞተ አይደለም፤ ከዚህ ቦታ በመውጣቱ እግዚአብሔር ገደለው እንጂ ብለው አስበው ነበር፡፡ ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ወደ ገነት ሊገባ ወድዷልና፤ የእግዚብሔር ቃልም ወደ አዳምና ወደ ሔዋን መጣ፡፡ ከሞታቸው /ከወደቁበትም/ አነሣቸው፡፡ እንዲህም አላቸው፡፡ ወደዚህ ለምን መጣችሁ? ከእርሷ ወደ አወጣኋችሁ ወደ ገነት መግባት ትሻላችሁን? ይህ ዛሬ አይሆንም፤ የገባሁላችሁ ቃለ ኪዳን እስኪፈጸም ድረስ ታገሡ እንጂ አላቸው፡፡

አዳምም የእግዚአብሔርን ቃል እንደሰማ የመላእክትንም ድምፅ በጆሮው ይሰማ ነበር እንጂ አያያቸውም ነበር፡፡ አዳምና ሔዋንም መላእክትን ለእግዚአብሔር የምትታዘዙ መላእክት ሆይ! ቀድሞ የነበረኝን ብርሃን ተመልከቱልኝ፤ እናንተን አያችሁ፣ እንደ እናንተም አመሰግን ነበር፡፡ ልቤ / አሳቤም/ ትልቅ /ገናና/ ነበር፡፡ ዛሬ ግን ትእዛዙን በመተላለፌ ብርሃኔ ተገፈፈች፡፡ ከዚህች ችግርም ደረስሁ፡፡ እናንተን ካለማየት ደረጃም ደረስሁ፡፡ እንደ ጥንቱም አትታዘዙኝም፡፡ እንስሳዊ ሥጋን ገንዘቤ አድርጌያለሁና የእግዚአብሔር መላእክት ሆይ! ዛሬም ወደቀድሞ ቦታዬ ይመልሰኝ ዘንድ ከእኔ ጋር እግዚአብሔርን ለምኑልኝ፡፡ ከዚህ ድካም ያድነኝ፣ እርሱን በመበደሌ በእኔ ላይ የፈረደብኝ ይህን የሞት ጽዋም ያስወግድልኝ ዘንድ ለምኑልኝ አያለ፡፡

መላእክትም ከአዳም ይህን ቃል በሰሙ ጊዜ ስለአዳም ሁላቸውም አዘኑ፡፡ ከገነት ወደ ድካም ከሕይወት ወደ ሞት፣ ከዕረፍት ወደ ጽኑ ድካም፣ ከደስታዋ ቦታ ወደ ኃላፊዋ ምድር፣ እስኪወጣ ያታለለው ሰይጣንንም ረገሙት፡፡

መላእክትም አዳምን አሉት፡፡ አንተ ሰይጣንን ሰማህ፣የፈጠረህ የእግዚብሔርን ትእዛዝም ተውህ፤ የገባልህን ቃል ኪዳን እንደሚፈጽምልህም በሰይጣን አመንህ፡፡ አዳም ሆይ! ዛሬም ከሰማይ ከመውደቁ በፊትም ከእርሱ የተነሣ በእኛ ላይ የደረሰውን እናሳውቅሃለን፡፡ እርሱ ሰራዊቱን ሰበሰበ፡፡ ሸነገላቸውም፡፡ ታላቅ መንግሥት ይሰጣቸው ዘንድም ቃል ገባላቸው፡፡ ለእነርሱ ያሰበውን አምላክነትን ይሰጣቸው ዘንድ፤ ሰራዊቱም ቃሉ እውነት እንደሆነ አመኑ፤ ሰገዱለትም፡፡ እግዚአብሔርን ማመስገንም እምቢ አሉ፡፡ እንደ ሥርዐታችን ሳለንም በእርሱ ትእዛዝ ሥር እንሆን ዘንድ፣ ቃል ኪዳኑንም አምነን እንቀበል ዘንድ ላከብን፡፡ ምክሩን /ዐሳቡንም/ አምነን አልተቀበልንም፤ ከእግዚአብሔር ጋር በተጣላ፣ እርሱንም በወነጀለ ጊዜም ሰራዊቱን ሰበሰበ፡፡ ከእኛ ጋርም ተጣላ፡፡ ከእኛ ጋር የነበረው የእግዚአብሔር ኀይል ስለነበረም በእርሱ ላይ ተበረታታንበት፤ ከሰማያትም ጣልነው[49]፤ ያን ጊዜ ከእኛ ወደቀ /ተለየ/፡፡ ከእኛ ተለይቶ በመውረዱም በሰማያት ታላቅ ደስታ ሆነ፡፡ እርሱ ከሰማይ ቀርቶ ቢሆን አንድ መልአክም ቢሆን በውስጧ ባልቀረ ነበርና፡፡

ነገር ግን የእግዚአብሔር ቸርነት ከእኛ እስከጨለማዋ ምድር አስወገደው፡፡ ስለዚህም ከሥራው የተነሣ ጨለማ፣ ክፉም ሆነ፡፡ አዳም ሆይ! እስኪያታልልህ ይፈትንህ ዘንድ እርሱ ቀረበ፡፡ ከገነት እስከኃላፊዋ ምድርም አወጣህ፤ እኒህ ሁሉ መከራዎችም ደረሱብህ፡፡ እግዚአብሔርም በእርሱ ላይ ያመጣበትን ሞት በአንተም ላይ አመጣብህ[50]፡፡ አዳም ሆይ! ለእርሱ በመታዘዝህ እግዚአብሔርንም ባለማመስገንህ ነው፡፡ ሁላቸው መላእክትም ተደሰቱ፤ እግዚአብሔርንም አመሰገኑት፡፡ አዳም ከዚህች ዓለም እንዳይጠፋም ለመኑ፡፡ ይኸውም ወደ ገነት ሊገባ በመፈለጉ ነው፡፡ ቃል ኪዳኑ እስኪፈጸም ድረስ እንዲታገሥ በዚህ ዓለም ከሰይጣን ፈተና እንዲወጣ ይረዳው ዘንድ ነው፡፡

የእግዚአብሔር ቃልም እንዲህ ሲል ወደ አዳም መጣ፡፡ አዳም ሆይ! ይህችን የደስታ ምንጭ ገነትን ተመልከታት፤ ይህችን አድካሚ ምድርም

[49] ራእ.፲፪÷፯-፱

[50] ዘፍ.፫÷፲፯-፲፱

አስተውላት፤ በገነት የሚኖሩ እኒህ መላእክትንም ተመልከት። ከእነርሱ የተነጣ የመላች ናት። አንተ ግን በዚህች ምድር ብቻህን ነህ።የታዘዝህለት ሰይጣንም እንዲሁ ነው። ቃሌን ብትጠብቅ፤ በትእዛዜም ብትጸና ከመላእክቶቼ ጋር በገነት በኖርህ ነበር። ሕጌን በተላለፍህ፣ ሰይጣንንም በሰማህ ጊዜ ከፋትን ከተሞሉ መላእክትና ከእርሱም ጋር የምትኖር ሆንህ። በውስጧም እሾህና አሜከላ ወደ ምታበቅል ወደ ዚህች ምድር ወረድህ። አዳም ሆይ! አምላክነትን ይሰጥህ ዘንድ ሰይጣንን ለምነው።

እኔ እንዳደረግሁልህ ገነት ያስገባህ ዘንድ ቃል ኪዳን የገባልህን ወይም እኔ ሥጋን እንዳደረግሁልህ ያደርግልህ ዘንድ፤ እኔ የዕረፍት ቀን እንደሰጠሁህ ይሰጥህ ዘንድ፣እኔ እንደፈጠርሁልህ ለባዊት ነፍስን ይፈጥርልህ ዘንድ ለአንተ ከሰጠኋት ከዚህች ምድር ወደሌላ ምድር ያወጣህ ዘንድም ለምነው። አዳም ሆይ! ቆጥሬ ከነገርሁህ ከእነዚህ ሁሉ የፈጸመልህ የለም። አዳም ሆይ! በአንተ ላይ ከፍጥረቶቼም ላይ ያለውን ቸርነቴን ዕወቅ። እኔ ትእዛዜን እንደመተላለፍህ አልከፍልህም። አምስት ቀን ተኩል ሲፈጸም በቸርነቴ አድንሃለሁ እንዳልሁህ መጥቼ አድንሃለሁ።

ዳግመኛም አዳምና ሔዋን ሆይ የእሳት ሰይፍ በእጁ የያዘ ኪሩብ እንዳያጠፋችሁ ተነሡ፤ ከዚህ ሂዱ አላቸው። አዳምም በእግዚአብሔር አነጋገር /ቃል/ ልቡ ተረጋጋ፤ በፊቱም ሰገደለት። እግዚአብሔርም አዳምን በደስታ እስከቤቱ ይሸኙት ዘንድ መላእክትን አዘዛቸው። በእነርሱ ላይ ስለደረሰው መከራም ፍርሀት ነበረባቸውና። ያን ጊዜም አዳምንና ሔዋንን ይዘው ቤታቸው እስኪያስገቧቸው ድረስ በማኅሌት፣ በዝማሬ ከገነት ራስ /ተራራ/ ላይ አወረዷቸው። መላእክትም ሊያጽናኗቸው፣ ሊያበረታቷቸው ጀመሩ፤ ከእነርሱም ወደ ላካቸው ወደ ፈጣሪያቸው ወደ ሰማይ ሄዱ።

መላእክት ከአዳምና ከሔዋን ተለይተው ከሄዱ በኋላም ያፈረው ሰይጣን መጣ። በአዳምና በሔዋን ቤት በርም ቆመ። አዳምንም እንዲህ አያለ

ጠራው፤ አዳም ሆይ! ነገርን እነግርህ ዘንድ ና አለው። አዳምም ከቤት ወጣ። ከእግዚአብሔር መላእክት ወገን የሚሆን መልአክ እንደሆነ በጥሩ ምክርም ሊያጽናናው እንደመጣ አሰበ። ወጥቶ ባስተዋለ ጊዜም ከመላእክት አምሳል የተለወጠ፤ የከፋም ሆኖ ዐየ። አዳምም አንተ ማን ነህ? አለው። እንዲህ ብሎም መለሰለት። በአባብ የተሰወርሁ፣ ሔዋንንም ያናገርኋት፣ ትእዛዙን እስከትሰማ ድረስም የሸንገልኋት እኔ ነኝ። በእኔ ምክር አንተም አሷም ከዕፀ በለስ ፍሬ እንድትበሉ፣ እንድትሸነግልህም የላክኋት እኔ ነኝ፤ ከእግዚአብሔር ትእዛዝም ወጣችሁ አለው።

አዳምም ይህን ቃል ከእርሱ በሰማ ጊዜ እግዚአብሔር እንዳዘጋጀልኝ አንተም ገነትን ልታዘጋጅልኝ ትችላለህን? ወይስ እግዚአብሔር እንዳለበሰኝ ብርሃናዊ ልብስን ልታለብሰኝ ትችላለህን? ትሰጠኝ ዘንድ ቃል የገባህልኝ አምላክነት የት አለች? በገነት እያለን የተናገርሽው መልካም ነገር ሁሉ የት አለ? አለው። ሰይጣንም አዳምን አለው: ለአንዱ የተናገርሁትን የምፈጽምለት ይመስልሃልን? አይደለም። እኔ በልቡና የፈለግሁትን አደርሻለሁ /ፈጽሜያለሁ/ ። እኔ በዚህ ወደቅሁ። እናንተንም በዚህ ጣልኋችሁ። ምክሬን የሚቀበል ሁሉ ይወድቃል። አዳም ሆይ! ዛሬም አንተ እንደወደቅህ ፈጣሪህን አቃለልህ። እኔን በመስማትህ በፍርድ ውስጥም በመሆንህ እኔ በአንተ ላይ ንጉሥ ነኝ። አምላክ ቃል ኪዳን እስከ ገባልህ ቀን ድረስ ከእጄ የሚያድንህ የለም። ዳግመኛም የምትድንበትን ሰዓት፣ ቃል ኪዳን የገባልህንም ዕለት አናውቅም አለ።

ስለዚህም እኛ መከራን በአንተ፣ ከአንተም በኋላ ለሚነሣው ዘርህም ሞትን እናበዛለን። ይህም ፍጹም ፈቃዳችን ነው። ከሰው ልጆች ወገን አንዱ ስንኳን በሰማይ ያለ ርስታችንን ይወርስ ዘንድ አንተወውም። አዳም ሆይ! እኛ ቤታችን በሚቃጠል እሳት ውስጥ ነው። ከቶ ሥራን አንተውም። አዳም ሆይ! ወደ ምታድርባት ቤት በምትገባበት ጊዜ እሳትን የበተንሁብህ እኔ ነኝ አለው።

አዳምም ይህን በሰማ ጊዜ ፈጽሞ አለቀሰ። ሔዋንንም ሔዋን ሆይ!

ነገሩን ስሚ፡፡ በገነት እያለን የተናገረውን አንዱን ስንኳን እንደማይፈጽምልን አስተውዪ፡፡ በእውነት በእኛ ላይ ነገሠ፡፡ ነገር ግን የፈጠረን እግዚአብሔር ከእጁ ያድነን ዘንድ እንለምነው አላት፡፡ አዳምና ሔዋንም እጃቸውንም ወደ እግዚአብሔር ዘረጉ፡፡ ከእነርሱም ያስወግደው ዘንድ ይጸልዩ ነበር፡፡ ምክንያቱም ከእነርሱ ላይ እንዳይበረታታ፤ ድልም እንዳይነሣቸው፣ እግዚአብሔርንም እንዳይክዱት፡፡ ያን ጊዜም እግዚአብሔር መልአኩን ፈጥኖ ወደ እነርሱ ላከ፡፡ በእነርሱም አስወገደው፡፡ ይህም ፀሐይ በገባ ጊዜ፣ ከገነት ከወጡም ሃምሳ ሦስቱ ቀን ከተፈጸመ በኋላ ተደረገ፡፡

አዳምና ሔዋንም ወደ ቤት ገቡ፡፡ ወደ እግዚአብሔር ይጸለዩ ዘንድም ፊታቸውን ወደ ምሥራቅ መልሰው ቆሙ፡፡ ከመጸለያቸው በፊትም አዳም ሔዋንን አላት፤በምድር ሳለን ያደረሰብንን መከራ እነሆ! ተመለከትሁ፡፡ ነይ፤ የሠራናትን ኃጢአት ይቅር ይለን ዘንድ ከእግዚአብሔር ምሕረትን እንፈልግ፤ እንቁምም አላት፡፡ ዳግመኛም አርባው ቀን እስኪፈጸም ድረስ፣ አንወጣም፤ በውስጧ ብንሞትም እርሱ ያድነናል አላት፡፡

አዳምና ሔዋንም በአንድነት ተስማምተው ከእግዚአብሔር ምሕረትን በመሻት ተነሥ ተው ይጸልዩ ዘንድ ቆሙ፡፡ ከቤታቸውም በቀንም፣ በሌሊትም ጸሎታቸው እንደእሳት ነበልባል ከአፋቸው እስኪታርግ ድረስ አልወጡም፡፡ የበጐ ጠላት ሰይጣንም ጸሎታቸው ይፈጸም ዘንድ አልተዋቸውም፤ ሰራዊቱን ጠራቸው እንጂ፡፡ ሁሉም ወደ እርሱ ደረሱ፡፡ ያሳትናቸው አዳምና ሔዋን ሌሊትም፣ ቀንም ወደ እግዚአብሔር ይጸለዩ ዘንድ ተስማሙ፡፡ ከእርሱ ድኅነትን ፈልገው አርባ ቀን እስኪፈጸም ድረስ ከቤታቸው እንደማይወጡ ተስማሙ፡፡ እነርሱም እንደተስማሙ ጸሎታቸውን ይጨርሳሉ፡፡ እግዚአብሔርም ከእጃችን ያድናቸዋል፡፡ ወደ ሥራቸው /ወደ ነበሩበትም/ ይመልሳቸዋል፡፡ አስተውሉ! ምን እናድርግባቸው አላቸው፡፡

ሰራዊቱም ጌታችን ሆይ! ሥልጣኑ አለህ፤ የምትሻውን አድርግ አሉት፡፡

ያን ጊዜ ሰይጣን ከብዙ ሰራዊቱ ጋር ተነሣ፤ በሌሊትም ወደ ቤት ውስጥ ገባ፡፡ ዳግመኛም አርባ መዓልት፣ አርባ ሌሊት አዳምና ሔዋንን ደበደባቸው፡፡ እንደሞቱ አድርጐም ተዋቸው፡፡ የእግዚአብሔር ቃልም ወደ አዳምና ሔዋን መጣ፡፡ ከሕማማቸውም አነሣቸው፡ እግዚአብሔርም አዳምን ጽና፤ ከደረሰብህ ፈተና የተነሣም አትፍራ፡ አለው፡፡ አዳምም አለቀሰ፡ እንዲህም አለ፡፡ ጌታዬ ሆይ! ግርፋት እስኪገርፉኝ ድረስ የት አለህ? ይህ ሕማም በእኔ በባርያህ፤ በሔዋንም ደረሰብን፡፡

እግዚአብሔርም አዳምን አለው፤ አምላክነት እሰጥሃለሁ ያለህ የገንዘብህ አለቃ ይህ ነው፡፡ ለአንተ ያለው ፍቅሩ የት አለ? እንደሚቻለው ቃል ኪዳን የገባልህ ሀብቱስ የት አለ? አዳም ሆይ! ይምጣና ያጽናናህ፤ ያበርታህ፣ ከአንተ ጋርም ይደሰት፤ ይጠብቅህ ዘንድም ሰራዊቱን ይላክልህ፡፡ አንተ እነርሱን ሰማህ፤ በምክራቸውም የተማረከህ ሆንህ፤ ሕጌን ተላለፈህ፤ ሕጋቸውንም ተከተልህ፡፡ አዳምም በእግዚአብሔር ፊት አለቀሰ፡፡ አቤቱ ፈጣሪዬ ሆይ! በትንሽ ጥፋት ለብዙ መከራ ትሰጠኛለህ? አቤቱ ጌታዬ ሆይ! ከሰይጣን እጅ ታድነኝ ዘንድ፣ ይቅርም ትለኝ ዘንድ እለምንሃለሁ፡፡ በዚህች ኃላፊት ምድር ያለች ነፍሴንም ከሥጋዬ አትለያት፡፡

እግዚአብሔርም አዳምን አለው፤ መጀመሪያ የምትሻው ይህ ከሆነ ከመተላለፍህ በፊት በሆነ ነበር፡፡ አንተ ካለህበት ሕማምም ባረፍህ ነበር፡፡ እግዚአብሔርም አዳምን ታገሠው፡፡ አዳምና ሔዋንም አርባው ዕለት እስኪፈጸም ድረስ ይቆሙ ዘንድ፡፡ ለአዳምና ለሔዋንም ኀይላቸው ቀነሰች፡፡ ሥጋቸውም ከጾም፣ ከጸሎት፣ ከረኀብ፣ ከጽም የተነሣ ከሳች፡፡ እነርሱ ከገነት ከወጡ በኋላ ምግብ፣ ውኃ አልቀመሱምና፡፡ ለጭካኔያቸውም መውጫ አልነበረውም፡፡

ዳግመኛም አርባው ቀን እስኪፈጸም ድረስ ከረኀቡ የተነሣ ለጸሎት ይቆሙ ዘንድ ኀይል አልነበራቸውም፡፡ በቤት የተጣሉ ነበሩ፡፡ ነገር ግን የምስጋና

ነገር ብቻ ከአንደበታቸው ይወጣ ነበር። ሠላሳ ዘጠኝ ቀን በሆነ ጊዜም ሰይጣን ወደ ቤት መጣ። በላዩም ብርሃናዊ ልብስ ነበር። የብርሃን ዝናርም ታጥቆ ነበር። በእጆቹም የብርሃን በትሮች ነበሩ። በእርሱ ላይም ታላቅ ታላቅ ጽሕም፤ መልካም አነጋገርም ነበረው። ይህንንም በምትሐት አደረገ[51]።

አርባ ቀን ከመፈጸሙ በፊት አዳምና ሔዋንን ያስታቸው ዘንድ አሰበ፤ እነርሱ አርባውን ዕለት በጾም በጸሎት በፈጸሙ ጊዜ እግዚአብሔር ወደ ሥራቸው /ቦታቸው/ ይመልሳቸዋል፤ ከመለሳቸውም እርሱ ይቅር ይላቸዋል፤ ይቅር ባይላቸውም ከገነት ሥራ ይሰጣቸዋል፤እነርሱም እንደቀድሞው ሁለተኛ ጊዜ ይረጋጋሉ ብሎ አስቧልና። ሰይጣንም በመልካም ምሳሌ በቤት ቀደመ። አዳምንም አንተና ሔዋን ተነሥታችሁ ቁሙ፡ እስከ መልካሟ ምድር ድረስም ከእኔ ጋር ሂዱ። እኔ እንደ እናንተ ሥጋና ዐፅም ያለኝ ነኝና። በፈጠረኝ ጊዜም የዓለም ጫፍ በሆነች በደቡባዊዋ ገነት አስቀመጠኝ፤ በዚህም ኑር አለኝ። እንደቃሉም በዚያ ኖርሁ፤ ትእዛዙንም አላፈረስሁም። ዳግመኛም በእኔ ላይ እንቅልፍን አመጣ። አዳም ሆይ! ከጐኔ አንተን አወጣህ፤ በእኔ ዘንድም አልነበርህም፤ እግዚአብሔር በመለኮታዊት እጁ ተሸከመህ በምሥራቃዊቷ ገነትም አስቀመጠህ።

ከጐኔ በወጣህ ጊዜም ስለ አንተ አዘንሁ። በእኔ ዘንድ አላሳደረህም / አላኖረህምና/። እግዚአብሔርም አገልጋዬ ሆይ! ከገነት ስላወጣሁት ስለ አዳም አትዘን፤ ከፉ አላገኘውም፤ ከጐኑም ረዳት ፈጠርሁለት አለኝ። ከእግዚአብሔር አነጋገር የተነሣም በዚህ ነገር ደስ ተሰኘሁ። ዳግመኛም እኔ በዚህች ቤት እንደሆናችሁ አላውቅም ነበር። በእናንተ ስለደረሰው መከራም አላውቅም ነበር። ከጐንህ የፈጠርሁት አዳም ሕጌን ተላለፈ። ከጐኑ የፈጠርኋት ሔዋንም ሕጌን ስላፈረሰች ከገነት አስወጣኋቸው። በምታሳዝን፣ በምታደክም ምድር አኖርኋቸው ብሎ እግዚአብሔር እስኪነግረኝ ድረስ አለ። ሰይጣንንም ሰሙት። እነርሱም እስከዚህች ሰማንያ ቀን በስቃይ ነበሩ።

---

51 ፪ቆሮ.፲፩+፲፬

እግዚአብሔር ተነሥተህ ወደ እርሱ ሂድ ወደ በታህም አድርሳቸው አለኝ፡፡ ሰይጣን ወደ እነርሱ ቀርቦ እንዳይመታቸው አትተዋቸው፡፡ እነርሱ ዛሬ ቢታላቅ ድካም ናቸው፡፡ ከረኀቡም የተነሣ ወድቀዋል፡፡ ወደ አንተ በወሰድሃቸው ጊዜም ከዕፀ ሕይወት ፍሬ አብላቸው፤ ከሕይወት ውኃም አጠጣቸው፤ የብርሃን ልብስም አልብሳቸው፤ እነርሱ ከአንተ ተገኝተዋልና፡፡ ታዝንላቸው፣ ስለደረሰባቸው መከራም ንስሐ ትገባላቸው ዘንድ ይገባል አለኝ፡፡ ይህን በሰማሁ ጊዜም አዘንሁ፤ ልቡናዬንም ስለ እናንተ ይታገሥ ዘንድ አልቻለም፡፡

ልጆቼ አዳምና ሔዋን ሆይ በሰማሁ ጊዜ ሰይጣንን ስለ ፈራሁ በልቤ ዳግመኛ እንደልጆቼ አዳምና ሔዋን እንዳያስተኝ አልሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በምሄድበት ጊዜ ሰይጣንን በመንገድ ያገኘኝ ይሆንን? እንደ እነርሱም ይጣላኝ ይሆንን? አልሁ፡፡ እግዚአብሔርም ሰይጣንን ባገኘኸው ጊዜ አትፍራው፡ በእጅህ ባለው ምርኩዝም ምታው አለኝ፡፡ እኔ ሽማግሌ ነኝ፡ መሄድም አልችልም፣ ያመጧቸው ዘንድ መላእክትን ላክ አልሁት፡፡ እግዚአብሔርም መላእክትስ እንደ እነርሱ አይደሉም፤ ከእነርሱ ጋርም አምነው አይመጡም፡፡ እኔ አንተን መረጥሁህ፤ እነርሱም በአምሳልህ ትእዛዝህን ይሰሙ ዘንድ ከአንተ ተፈጥረዋልና፡፡

ዳግመኛም እግዚአብሔር ለመሄድ ኀይል ካጣህ ትሸከምህ ዘንድ ደመናን እልክልሃለሁ፤ ከቤታቸውም ታኖርሃለች/ ታደርስሃለች/! አለኝ፡፡ ደመናዋም ትታህ ትመለሳለች፤ ከአንተ ጋር ሊመጡ ከወደዱ አንተንም እነርሱንም የምትሸከም ደመና እልካለሁ አለኝ፡፡ ያን ጊዜም ደመናን አዘዛት፡ ከእናንተ ዘንድም አድርሳኝ ተመለሰች፡፡ ልጆቼ አዳምና ሔዋን ሆይ! ዛሬም ሽበቴን፣ ከሩቅ በታ መምጣቴን ተመልከቱ፡ ወደ ዕረፍቷ በታ እንሄድ ዘንድ ከእኔ ጋር ኑ፤ በማለት በአዳምና በሔዋን ፊት ማልቀስ ጀመረ፡፡ እንባውንም እንደውኃ በመሬት ላይ አፈሰሰ፡፡

አዳምና ሔዋንም ዐይኖቻቸውን ባነሡ ጊዜ ጽሕሙን ተመለከቱ፡ የሚጣፍጥ ነገሩንም አዳመጡ፡፡ ልቡናቸውም ተዳመጸለት /ለሰለሰለት/፡፡ ቃሉንም ሰምተው እውነት እንደሆነ አመኑት፤ እነርሱ ከቤታቸው የወጡትም እውነት ስለመሰላቸው ነበር፡፡ ፊቱን በተመለከቱት ጊዜም እነርሱን ይመስል[52] ስለነበር አመኑት፡፡ እርሱም የአዳምንና የሔዋንን እጅ ያዘ፡፡ ከቤታቸውም ያወጣቸው ጀመር፡፡ ከእርሱ ጥቂት ወደ ውጪ በደረሱ ጊዜ እግዚአብሔር ሰይጣን ድል እንደነሣቸው፣ አርባ ቀን ከመፈጸሙ በፊትም እንዳስወጣቸው፣ ሩቅ ወደሆነ ቦታ ያጠፋቸው ዘንድ እንደሚወስዳቸው ዐወቀ፡፡

ዳግመኛም የእግዚአብሔር ቃል ወደ አዳም መጣ፡፡ ሰይጣንንም ረገመው፡ ከእነርሱም አስወገደው፡፡ እግዚአብሔርም አዳምና ሔዋንን ያነጋግራቸው ጀመር፡፡ ከቤት እስከዚህ ምን አወጣችሁ? አላቸው፡፡ አዳምም እግዚአብሔርን አቤቱ! ከእኛ አስቀድመህ ሌላ ሰው ፈጠርህን? እኛ በቤት እያለን ያን ጊዜ ያማረ ሽማግሌ መጣ፡፡ ወደ እኛም ገባ፡፡ እኔ ወደ ዕረፍት ቦታ እመልሳችሁ ዘንድ ከእግዚአብሔር ወደ እናንተ የተላክሁ ነኝ አለ፡፡ አቤቱ አምላክ ሆይ! እኛም ከአንተ የተላከ እንደሆነ አመንን፤ ከእርሱ ጋርም መጣን፡፡ ከእርሱ ጋር የት እንደምንሔድም አናውቅም አለው፡፡

ዳግመኛም እግዚአብሔር አዳም ሆይ! እነሆ ይህ የምክንያት የሐሰት[53] አባት ነው፡፡ ለመጾም፣ ለመጸለይ የተስማማችሁ አንተን ሔዋንንም ያወጣችሁ እርሱ ነው፡፡ አርባው ቀን እስኪፈጸም ባልወጣችሁ፤ ቃላችሁን ይለውጥ፣ ማሰሪያችሁን ይቆርጥ፣ ተስፋም ያስቆርጥ ዘንድ ወድዷልና ያጠፋችሁ ዘንድ አስወጣችሁ፡፡ በእናንተ አምሳል ባይገለጥ እናንተን ማሳት ባልቻለም ነበርና፡፡ ስለዚህ እናንተን መስሎ ወደ እናንተ መጣ፡፡ እነርሱ እውነተኞች እንደሆኑ ትምህርት ይሰጣችሁ ጀመር፡፡ እኔም በቸርነቴ፣ በይቅርታዬ ያጠፋችሁ ዘንድ አልተውሁም፡፡ ከእናንተ አስወገድሁት እንጂ፡፡

አዳም ሆይ! ዛሬም ሔዋንን ይዘህ ወደ ቤታችሁ ተመለሱ፡፡ በእርሱም እደሩ/ኑሩ/፡፡ እስከማግስትም የአርባው ቀን ፍጻሜ ነው፡፡ በወጣችሁ ጊዜም ወደ ምሥራቃዊቱ የገነት በር ኑ አላቸው፡፡ አዳምና ሔዋንም ለእግዚአብሔር

52 ፪ቆሮ ፲፩፥፲፬

53 ዮሐ ፰፥፵፬

ሰገዱ፡፡ በእርሱ ስለተደረገላቸው ድኅነትም ፈጽመው አመሰገኑት፡፡ ወደ ቤትም ተመለሱ፡፡ የሠላሳ ዘጠነኛው ቀን ፍጻሜ ምሽት በሆነ ጊዜም አዳምና ሔዋን ወደ እግዚአብሔር ይጸለዩ ዘንድ በታላቅ ድካም ቆሙ፡፡ ከኀይለኛ /ከጽኑ/ ችግር ይወጡ ዘንድ ከረኀቡ፣ ከጾሙ፣ ከጸሎቱ የተነሣ ሌሊቱን ሁሉ እስኪነጋ ድረስ በነበራቸው ትጋት ኀይላቸው አልቆ ነበርና፡፡ አዳምም ሔዋንን እግዚአብሔር እንዳዘዘን ወደ ገነት በር እንሄድ ዘንድ ነይ አላት፡፡

እነርሱም እንደልማዳቸው ቀኑን ሁሉ ጸሎታቸውን ጸለዩ፤ ከቤትም ወጡ፤ ምሥራቃዊት ወደ ሆነች ገነት በር አቅራቢያም ሂደው ደረሱ፡፡ አዳምና ሔዋንም ያበረታቸው፣ ከረኀባቸው የሚጠግቡበትንም ወደ እነርሱ ይልክ ዘንድ ፈልገው በእግዚአብሔር ፊት ሊጸልዩ ቆሙ፡፡ አዳምና ሔዋን ጸሎታቸውን በጨረሱ ጊዜም በደከመ ኃይላቸው ነበሩ፡፡

ዳግመኛም የእግዚአብሔር ቃል መጣ፤ እንዲህም አላቸው፡፡ አዳምና ሔዋን ሆይ! ተነሥታችሁ ሂዱና ሁለት የበለስ ፍሬ ወደዚህ አምጡ፡፡ አዳምና ሔዋንም ወደ ቤት እስኪቀርቡ ድረስ ተነሥተው ሄዱ፡፡ ክፉ ሰይጣንም እግዚአብሔር ስላረጋጋቸው ቀና፡፡ ቀድሟቸውም ወደ ቤት ውስጥ ገባ፡፡ ሁለት የበለስ ፍሬዎችንም ያዘ፡፡ አዳምና ሔዋን እንዳያገኟቸውም ከቤት ውጪ ቀበራቸው፡፡ በሰይጣን አስተሳሰብ የሚያጠፋቸው መስሎት ነበርና፡፡ በደረሱ ጊዜም ሁለት የበለስ ፍሬዎች በእግዚአብሔር ቸርነት በመሬት ላይ ነበሩ፡፡ እግዚአብሔርም ክፉ ያሰበባቸው የሰይጣንን ዐሳብ ለወጠበት፡፡ እግዚአብሔርም ሁለቱንም ዕፀዋት እንዲያፈሩ አደረገ፡፡ ቤቱንም ጋረዱት፣ ሰይጣን የቀበራቸው ከቤቱ በስተምሥራቅ በኩል ነበርና፡፡

ሁለቱም ዕፀዋት ፍሬን በተመሉ ጊዜ ሰይጣን አዘነ፤ አለቀሰም፡፡ እንዲህም አለ፡፡ ከዚያም እንዳሉ በተውኋቸው ነበር፡፡ እነሆ! ዛሬ ግን ሁለቱ ዕፀዋት ፍሬያማ ሆኑላቸው፡፡ አዳምም ሕይወቱን ሙሉ ከእነርሱ የሚመገብ ሆነ፡፡ በዐሳቤ የቀበርኋቸው ፈጽመው ይጠፋ ዘንድ ነውና፡፡ እግዚአብሔርም

ዐሳቤን ለወጠብኝ፤ ይህች ልዩ ፍሬ ትጠፋ ዘንድ እግዚአብሔር አልፈለገምና፡ በግልጽ ግልጽ አደረጋት እንጂ። በአገልጋዮቹ አደርገው ዘንድ የወደድሁት ዐሳቤም ጠፋ አለ። ሰይጣንም የፈለገውን ስላላገኘ አፍሮ ተመለሰ።

አዳምና ሔዋንም ወደ ቤት በተቃረቡ ጊዜ ፍሬን የተመሉ ሁለት የበለስ ዕፀዋትን ተመለከቱ፡ በቤቱም ተጠልለው /ተጋርደው/ ነበር። አዳምም ሔዋንን እኛ ዟሪዎች ነን መሰለኝ፤ እነኚህ ሁለት ዕፀዋት መቼ በቀሉ? ጸላኢ ሰይጣን ሊያዞረን ይሻል መሰለኝ፤ ሰይጣን ያዞረን ዘንድ ይሻል ትያለሽን? በመሬት ከቤታችን ሌላ ቤት አለ ትያለሽን? አላት። ሔዋን ሆይ! ነገር ግን በውስጧ ሁለት የበለስ ፈሬዎችን እናገኝ ዘንድ ወደ ቤት እንግባ፤ በውስጥ ያለችው ቤታችን ናትና። በውስጧ በለሶችን ካላገኘን ግን ይህች ቤታችን አይደለችም። ወደ ቤትም ገቡ፣ በአራቱም ማዕዘኖች ተመለከቱ፡ የበለስን ፍሬ ግን አላገኙም። አዳምም አለቀሰ፤ ሔዋንንም ሔዋን ሆይ! እኛ ቤቱን ዞርን፤ እኔ ግን እነዚህ ሁለት የበለስ ዕፀዋት ፍሬ በቤቱ ያሉ ይመስለኛል አላት። ሔዋንም እኔ አላውቅም አለች፤ አዳምም ይጸልይ ዘንድ ቆመ። እንዲህም አለ። እግዚአብሔር ሆይ! ወደ ቤት እንመለስ፣ የበለስ ፍሬንም እንወስድ፣ ወደ አንተም እንመለስ ዘንድ አዘዝኸን። ዛሬ ግን አላገኘናቸውም። አቤቱ ፈጣሪያችን ሆይ! አንተ ወሰድሃቸውን? የእነዚህን ሁለት ዕፀዋት ምሥጢር ግለጥልን አለ።

የእግዚአብሔር ቃልም እንዲህ ሲል ወደ አዳም መጣ። አዳም ሆይ! የበለስን ፍሬ ታመጣ ዘንድ ላክሁህ፤ ሰይጣንም ከቤት ቀድሞህ የበለሱን ፍሬ ወሰደ። ከቤትም በምሥራቅ በኩል በውጪ ቀበረው። እርሱ በዐሳቡ ያጠፋቸው ዘንድ አስቧልና፤ በመልካምም አልዘራቸውም። እነኚህ ዕፀዋት ፈጥነው የበቀሉትም በንጽሕናው አይደለም። እኔ በቸርነቴ ይበቅሉ ዘንድ አዘዝኋቸው። ሁለቱም ታላላቅ ዕፀዋት ሆኑ። እናንተ በሥሮቻቸው ትጠለሉ / ታርፉ/ ዘንድ ኀይሌን፣ ድንቅ ሥራየን፣ ዳግመኛም የሰይጣንን ድኸነት /

ደካማነት/ ክፉ ሥራዎቹንም አሳያችሁ ዘንድ ነው፡፡ እርሱ ከገነት ካወጣችሁ ጊዜ ጀምሮ ከሚያደርግባችሁ ክፉ ተግባር አንድ ቀን ስንኳን ከእናንተ አልተወገደም፡፡ እኔ ግን ኀይልን አልሰጠሁትም፡፡

እግዚአብሔርም አዳም ሆይ! ስለ እነዚህ ዕፀዋት አንተም፣ ሔዋንም ዛሬ ደስ ይበላችሁ፤ ተጠለሉባቸው፤ በተጠለላችሁ ጊዜም ከፍሬያቸው አትብሉ፡፡ አትቅረቧቸውም አለ፡፡ አዳምም አለቀሰ፡፡ እንዲህም አለ፡፡ አቤቱ ጌታዬ ሆይ ፈጽመህ ልትገድለን ትወዳለህን? ከፊትህ ትጥለን ዘንድስ ሕይወታችንም ከምድር ገጽ ትቆርጥ /ታጠፋ/ ዘንድ ትሻለህን? አቤቱ ጌታችን ሆይ! በውስጣቸው ሞት እንዳለ ካወቅህ ወይም እንደቀድሞው ክፉ ነገር እንዳለባቸው ካወቅህስ ንቀላቸው፡፡ ከቤታችንም አድርቃቸው፤ እኛንም ከሐሩሩ /ከሙቀት/፣ ከረኀብ፣ ከጽም፣ የተነሣ እንሞት ዘንድ ተወን፡፡ አቤቱ ጌታችን ሆይ! እኛ ግን ተአምርህ ብዙ እንደሆነ ዕናውቃለን፤ ሳይወድም ከፍጥረት ላይ ፍጥረትን ታወጣለህ፤ ድንጋዮችንና ዕፀዋቱን የሚፈጥር ኀይልህ ሁሉን ቻይ ነው አለሉ፡፡

እግዚአብሔርም አዳምን የዐሳቡን ታላቅነት በረኀብ፣ በጽም፣ በሐሩር የጸና ትዕግሥቱን ተመለከተ፤ ሁለቱን ዕፀዋት እንደቀድሞው ወደ ሁለት የበለስ ፍሬዎች ለወጣቸው፤ እግዚአብሔርም አዳምና ሔዋንን ከእናንተ አንዱ የበለስን ፍሬ ይውሰድ አላቸው፡፡ እግዚአብሔር እንዳዘዛቸውም ወሰዱ፤ እግዚአብሔርም ወደ ቤት ግቡ፤ ትጠግቡ ዘንድም ሁለቱን የበለስ ፍሬዎች ብሉ፤ በተራባችሁ ጊዜ እንዳትጠፉ፤ አላቸው፡፡ እግዚአብሔር ባዘዛቸው ጊዜም ወደ ቤት ገቡ፡፡ ሰዓቱም የፀሐይ መግቢያ ነበር፡፡ ፀሐይ ስትገባም አዳምና ሔዋን ይጸልዩ ዘንድ ቆሙ፡፡ የበለስን ፍሬ ይበሉ ዘንድም ተቀመጡ፡፡ ይበሉ ዘንድም አላወቁበትም፤ በምድራዊቷ መብል ለእነርሱ ልማድ አልነበራቸውምና፡፡

ዳግመኛም በሚበሉበት ጊዜ ሆዳቸው የምትከብድ ሥጋቸውም፣ ልባቸውም የምትገዘፍ፣ ምድራዊውንም ምግብ የሚወድዱ ስለመሰላቸው

ፈርተው ነበር። አዳምና ሔዋንም ተቀምጠው እያለ እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ በነበረው ይቅርታ በረኀብ፣ በጽምም እንዳይጠፉ መልአኩን ላከ። መልአኩም አዳምና ሔዋንን እግዚአብሔር እንዲህ ይላችኋል። እስከሞት ከመጾማችሁ የተነሣ ኀይል አልቀረላችሁም፣ ነገር ግን በልታችሁ ሥጋችሁን አጽኑት /አበርቱት/። እናንተ እንስሳዊ ሥጋ የለበሳችሁ ናችሁና ያለመብል፣ ያለመጠጥ አትበረቱም አላቸው። አዳምና ሔዋንም ወሰዷቸው፣ ከእነርሱ ይበሉ ዘንድም ጀመሩ። በእነርሱ ዘንድም እንደሚጣፍጥ ኅብስት አደረገላቸው። መልአኩም ከእነርሱ ዘንድ ሄደ። አዳምና ሔዋንም ከረኀባቸው እስኪጠግቡ ድረስ ከበለሱ ፍሬ ተመገቡ። የተረፈውንም አስቀመጡ። በእግዚአብሔር ኀይልም ፍሬዎቹ ሙሉ ሆኑ።

እግዚአብሔር ባርኳቸዋልና ጸሎታቸው፣ ልመናቸው፣ ከጻጻሳቱ አለቃ ከአባ ባስልዮስ፣ ከንጉሣችን ኀይለ ሥላሴ፣ ከንግሥና ወራሽ አምኃ ሥላሴ፣ ከንግሥታችን ከወለተ ጊዮርጊስ፣ ከአርዓያ ዮሐንስ ነፍስ ከሁላችንም የጥምቀት ልጆች ጋር ይሁን። ለዘለዓለሙ አሜን።

## ምዕራፍ አምስት

## ገድለ አዳም ዘነሐሴ

አንድ አምላክ በሆኑ በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም ነሐሴ ስድስት ቀን የሚነበብ የአባታችን የአዳም፣ የእናታችን የሔዋን የገድላቸው ዜና ይህ ነው። ጸሎታቸው፣ በረከታቸው እና የይቅርታ ልመናቸው ከጳጳሳቱ አለቃ ከአባ ባስልዮስ፣ ከንጉሣችን ከኀይለ ሥላሴ፡ ከንግሥታችን ከወለተ ጊዮርጊስ ነፍስ ጋር ይሁን፡ ለዘለዓለሙ አሜን።

ከዚህ በኋላ አዳምና ሔዋን ከልብ በመደሰት በጽኑዕ ኀይል ይጸልዩ ዘንድ ተነሡ። ለእግዚአብሔርም ሌሊቱን ሁሉ ጸሎት አቀረቡ። ደስታንም አበዙ። የስማንያኛው ዕለት መጨረሻ በነጋ ጊዜም እንደልማዳቸው ተነሥተው

ጸለዩ፤ ከቤትም ወጡ። ሆዳቸው በከበዳቸው ጊዜ ሊጸዳዱ /ወደመኪነ ምኩሳህ ሊወጡ/ ፈለጉ። ይጸዳዱ ዘንድም ከእርሷ መውጫ አልነበረምና ከደረሰባቸው ጭንቀት የተነሣም የቤቱን አካባቢ ይዞሩ ነበር። እርስ በርሳቸው እንድንበላ ያስገደደን ማን ነው? እያሉ አለቀሱ። ይህ ችግር ደርሶብናልና ከምንበላ ሞት በተሻለን ነበር። ወዮልን ዛሬ ከምንሞት ከመብላታችን በፊት ብንሞት በተሻለን ነበር። ሆዳችንም ንጽሕት በሆነች ነበር። ዛሬ ግን ሆዳችን ጐሰቆለች።

አዳምም ሔዋንን "ይህ ክብደት በገነት እያለን አልደረሰብንም፤ ይህን ከፉ ምግብ አልበላንም፤ ትያለሽን" አላት። "እግዚአብሔር በሆዳችን ባለው በዚህ ምግብ ይቀጣናልን?። ወይስ አንጀታችን ይወጣ ዘንድ ይሻልን? ወይስ ቃል ኪዳኑ ሳይፈጸም ሊገድለን ይሻልን?" አላት። አዳምም ከእግዚአብሔር ዘንድ ምሕረትን ፈለገ። አቤቱ አምላክ ሆይ! በሆዳችን ባለው በዚህ መከራ አታጥፋን። አቤቱ ፈጣሪ ሆይ! እንደቸርነትህ መጠን አድርግልን እንጂ አትቅጣን፤ የገባህልን ቃል ኪዳን እስኪፈጸም ድረስም አትተወን አለ።

እግዚአብሔርም ወደ እነርሱ ተመለከተ። በእነርሱ ይጸዳዱ ዘንድም ቦታዎችን ፈጠኖ ፈታላቸው /ከፈተላቸው/። እስከዚህች ሰዓት በእነርሱ ቢጨከን እንዳይጠፉ ነው። አዳምና ሔዋንም በሆዳቸው ያለውን አስወገዱ። እያዘኑ እያለቀሱም ወደ ቤታቸው ገቡ፤ ከሆዳቸው ከወጣው ሐሰር /ቆሻሻ/ የተነሣም አዳምና ሔዋን ከዚህች ሰዓት ጀምሮ እንደ ተለወጡ ዐወቁ። ገነትን በመፈለግ ይገቡ ዘንድ እንደማይችሉም ተስፋ ቆረጡ። ኃላፊቷ ምድር ለሥጋቸው ብቻ ሆናለችና።

ሥጋ ሁሉ ደግሞ መብላት፣ መጠጣት፣ መጸዳዳት ይሻል። ያለዚያ ግን መኖር የሚቻል አይደለም። አዳምም ሔዋንን አላት፤ እነሆ! ተስፋችን ተቆረጠ፤ ወደ ገነት የመግባት እምነታችንም መነመነ። የገነት ሰዎችም አንሆንም። ዛሬ ከምድር የተገኘን ምድራውያን ሆነናልና። ወደ ገነት አንመለስም፡ ዳግመኛ እግዚአብሔር ወደ ገነት እንደሚያስገባን እንደሚያድነንም ቃል ኪዳን እስከ

ገባበት ቀን ድረስ አላት። ይቅር ይላቸው ዘንድም ወደ እግዚአብሔር ጸለዩ። ከዚህ በኋላ ሕሊናቸው ጸጥ አለች። ልባቸውም ተሰበረች። ምኞታቸውም ቀዘቀዘች። በዚህ ዓለም እንደ ስደተኛ /መጻተኛ/ ሆኑ። አዳምና ሔዋንም በዚህች ዕለት አደሩ። ከመብሉ የተነሣ ሆዳቸው ስለከበደ ብዙ እንቅልፍ ደረሰባቸው።

ሲነጋም አዳምና ሔዋን በቤታቸው ውስጥ ዳግመኛ ጸለዩ። አዳምም ሔዋንን እነሆ! ከእግዚአብሔር ዘንድ ምግብን ፈለግን፤ ሰጠንም፤ ዳግመኛም መጠጥን ከእርሱ እንሻለን አላት። ተነሥተውም በሰሜን ከገነት ጫፍ እስካለው እስከ ውኃው ምንጭ ድረስ ሄዱ። አስቀድመውም ሰውነታቸውን በዚህ ጣሉ። ከውኃው ይጠጡ ዘንድ እንዲያዝዛቸውም /እንዲፈቅድላቸውም/። በውጪም ወደ እግዚአብሔር ይጸልዩ ዘንድ ቆሙ። የእግዚአብሔር ቃልም እንዲህ ሲል መጣ። "አዳም ሆይ! ሥጋ እንስሳዊ ነው። በውኃ ታረካው ዘንድ ይሻል። አንተም ሔዋንም ወስዳችሁ ጠጡ፡ ፈጽማችሁም አመስግኑ" አላቸው።

አዳምና ሔዋንም ወደ ውኃው ቀርበው ሥጋቸው እስኪረካ ድረስ ጠጡ። ከጠጡ በኋላም እግዚብሔርን አመሰገኑት። አስቀድሞ እንዳስለመዱት ወደ ቤታቸው ተመለሱ። ይህም በሰማንያ ሦስተኛው ዕለት መጨረሻ ነበር። ዘወትር ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን፡ እስከ ዘለዓለሙ ድረስ አሜን።

አራት ቀን በሆነ ጊዜም ሁለት የበለስ ፍሬዎችን ወሰዱ። በእግዚአብሔር አጋዥነት ምልክት ይሆናቸው ዘንድ ከቅጠላቸው ጋርም ወደ ቤታቸው ወሰዷቸው። ፍሬ እስኪይዙ ድረስም አኖሯቸው። ያደረገላቸውን የእግዚአብሔርን ተአምርም አስተዋሉ። ዳግመኛም አዳምና ሔዋን በቤት ውስጥ ነበሩ። ምግብን ያሳያቸው ዘንድ ሽተው፣ ሥጋቸውንም ያሳድጉ ዘንድ ፈልገው ነበርና። የእግዚአብሔር ቃልም እንዲህ ሲል ወደ አዳም መጣ። "ከቤት ወደ ምዕራብ እስከ ጭቃማው ጥቁር ምድር ድረስ ውረዱ፡ በዚያም ምግብ ታገኛላችሁ" አላቸው። አዳምም የእግዚአብሔርን ቃል ሰማ፤ ሔዋንን

ይዞ ወደ ጥቁሩ ምድር ወረደ:: የበቀለች፣ የጎመራች፣ አሸት የሆነች ስንዴንም አገኘ::

ለመበላትም በስላ ነበር:: አዳምም ተደሰተ:: ዳግመኛም የእግዚአብሔር ቃል መጣ፤ አዳም ሆይ! ከዚህ ስንዴ ውሰድ:: ለአንተም ምግብ አድርግ፡ ሥጋህን ታሳድግ ዘንድም ተመገብ አለው:: እግዚአብሔርም ስንዴውን ኅብስት ያደርገው ዘንድ ለአዳም ማስተዋልን ጥበብን ሰጠው:: አዳምም ይህን ሁሉ ፈጸመ:: ብዙ ድካምም ደከመ:: ወደ ቤቱም ተመለሰ:: የስንዴውንም አሠራር በመማሩ /በማወቁ/ እርሱ ደስተኛ ነበር:: በእጭር እንተወው እንጂ ስለ እርሱ የሚናገር የድርሳኑም ብዛት ታላቅ /ብዙ/ ነው::

በስንዴ ምክንያት ከሰይጣን ጋር ለአዳም የተደረገለት የመጀመሪያ ተአምር ይህ ነው:: አዳምና ሔዋን ወደ ጥቁሩ ምድር በወረዱ ጊዜ እግዚአብሔር ወደ አሳያቸው ስንዴ ደረሱ፤ ደርቃም አዩዋት:: ለማጨድም ደርሳ ነበር:: አዳምና ሔዋንም ታጠቁ:: የሚያጨዱበት ማጭድ ግን አልነበራቸውም፡ እስኪጨርሷት፣ ከምርም እስኪያደርጓት ድረስ ስንዴዋን ይነቅሉ ጀመር:: ከደረሰባቸው ከበረኀው፣ ከረኀቡ፣ ከጽሙ፣ ከድካሙ የተነሣም ከጥላዋ ይጠለሉ ዘንድ ወደ ዛፏ መጡ:: ነፋስም መታቸው ተኙም:: ሰይጣንም አዳምና ሔዋን ያደረጉትን ተመለከተ:: ሰራዊቱንም ጠራቸው፡ እንዲህም አላቸው:: ለአዳምና ለሔዋን እግዚአብሔር ይህን ስንዴ አሳያቸው:: ሥጋቸው ተመግበ ይኖር ዘንድ እነርሱም መጥተው ከእርሷ /ከስንዴዋ/ ሥራ የተነሣ ስለደከሙ ተኝተው ነበር:: ኑ እንሂድ በእርሷም እሳትን እንጨምርባት፣ እናቃጥላትም፣የውኃውን መንቀል /የውኃ መቅጃቸውን/[54] ከእነርሱ እንውሰድ:: የሚጠጡትን እንዳያጡም እንድፋው:: በረኀብና በጽምም እንግደላቸው አለ::

ከመኝታቸው በተነሡ ጊዜም ወደ ቤት ይመለሱ ዘንድ ይወዳሉ፡ በመንገድ እንደርስባቸው ዘንድ በረኀብ፣ በጽምም ይሞቱ ዘንድ እንበረታታባቸው፡ እግዚአብሔርን ከካዱም ከምድር ያጠፋቸዋል:: ከእነርሱም



[54] መንቀል የውኃ መያዣ ነው::

እናርፋለን አለ፡፡ ሰይጣንና ሰራዊቱም በስንዴው ላይ እሳትን ጨመሩ፡ አቃጠሏትም፤ አዳምና ሔዋንም ከእሳቱ ዋዕይ /ማቃጠል/ የተነሣ ከእንቅልፋቸው ተነሡ፡፡ ስንዴዋ ተቃጥላ፣ በእነርሱ ዘንድ የነበረ ውኃቸው ተደፍቶ ተመለከቱ፡ እያለቀሱም ወደ ቤት ተመለሱ፡፡ ወደ ተራራው ቢወጡም ሰይጣንና ሰራዊቱ መላእክትን መስለው ወደ እነርሱ ደረሱ፡፡ ሰይጣንም አዳምን አዳም ሆይ! በረኀብና በጽም የምታዝነው ምን ሆነሃል? ስንዴህን ሰይጣን ያቃጠለብህ ይመስለኛል አለው፡፡ እርሱም አዎን፤አለው፡፡

አዳም ሆይ! ወደ እኛ ተመልከት፡፡ እኛ የእግዚአብሔር መላእክት ነን፡፡ ሌላ ከእርሷ የሚሻል የስንዴ እርሻ እናሳይህ ዘንድ እግዚአብሔር ላከን፡፡

በአማረች የውኃ ምንጭ፡ ብዙ ዕፀዋት ባለበት በእርሷ ትኖራለህ፤ በተቃጠለው ፋንታ በስንዴዋ እርሻ ታመርታለህ አለው፡፡ አዳምም እውነት እንደሆነ ዐወቀ፡ መላእክት ያነጋግሩት ነበርና፡፡ ከእነርሱ ጋርም ተመለሰ፡፡ ሰይጣንም እሱንና ሔዋንን ለስምንት ቀን ይበረታታባቸው ጀመረ፡፡ አዳምና ሔዋንም ከረኀብ፣ ከጽም፣ ከድካምም የተነሣ በመሬት እስኪወድቁ፡ የሞቱም እስኪመስሉ ድረስ፡፡ ሰይጣንና ሰራዊቱም ትተዋቸው ሸሹ፡፡

እግዚአብሔርም ወደ አዳምና ወደ ሔዋን ተመለከተ፡፡ ከሰይጣን የደረሰባቸውን፣ ጥፋታቸውንም አስተዋለ፡፡ እግዚአብሔርም ቃሉን ላከ፡፡ ከመሞታቸው፡ ከመውደቃቸውም አስነሣቸው፡፡ አዳም በተነሣ ጊዜም አቤቱ ጌታችን ሆይ! ለእኛ የሰጠኸንን ስንዴ አቃጠልህ፡፡ መላእክትህንም ላክህ፣ ወደ ስንዴ እርሻም አዞሩን፤ ትገድለን ዘንድ ትሻለህን? ይህ ከአንተ ከሆነ ነፍሳችንን ውሰድ፤ አታሰቃየን አለ፡፡ እግዚአብሔርም አዳምን እኔ ስንዴህን አላቃጠልሁም፤ የመንቀልንም [የበራድህንም] ውኃ አልደፋሁም፤ አዞርህ ዘንድም መላእክቴን አላከኋቸውም፤ የስገድህለት አለቃህ ከትእዛዜም የወጣ ሰይጣን ስንዴውን ያቃጠለው፣ ውኃውንም የደፋው፣ ያዞረህም እርሱ ነው፡፡ የገባላችሁ ቃል ኪዳን ምትሐት ፍጹም ሐሰትም ነው፡፡ አዳም ሆይ! ዛሬ ከአንተ

ጋር ያሉ መልካም ሥራዎችን ታውቃለህ እንጂ አለው።

መላእክትንም አዘዛቸው። አዳምና ሔዋንንም ተሸከሟቸው፣ ወደ ስንዴው ቦታም አመጧቸው። እንደ ቀደመውም አገኙት። የውኃው መያዣያ /መንቀልም/ ሙሉ ነበር። ዕንጨቱንም ተመለከቱ፤ በላይዋም መና ተቀምጦ ነበር። ከእግዚአብሔር ኃይል የተነሣም አደነቁ። በተራቡ ጊዜም ከመናው ይበሉ ዘንድ መላእክት አዘዟቸው። እግዚአብሔርም ሰይጣንን የስንዴውን እርሻ ተመልሶ እንዳያጠፋ ረገመው። አዳምና ሔዋንም ከስንዴው ወሰዱ። ከእርሷም መሥዋዕት አዘጋጁ። መጀመሪያ ደማቸውን ለመሥዋዕት ወደ አቀረቡበት ተራራማ ቦታ ወስደውም ዐሳረጉት /ሠውት/። ዳግመኛም አስቀድሞ በተሠሩት በመሠውያው ላይ ቍርባንን አቀረቡ። አዳምና ሔዋንም እንዲህ እያሉ ይጸልዩ ዘንድ ቆሙ።

አቤቱ አምላክ ሆይ! በገነት እያለን እንደቍርባን ምስጋናችን ለአንተ ነበር። ንጽሕናችንም እንደ ዕጣን ወደ አንተ ታርግ ነበር፤ ዛሬም አቤቱ ጌታችን ሆይ! ይህን ቍርባን ከእኛ ተቀበል። ከቸርነትህ ባዷችንን አትመልሰን። እግዚአብሔርም አዳምና ሔዋንን ይህን ቍርባን እንዳቀረባችሁልኝ፤ ለእኔም እንዳደረጋችሁልኝ እኔ ወደ ምድር በወረድሁ ጊዜ ሥጋ አደርገዋለሁ። አድናችሁማለሁ። በሚገባ ለሚቀበሉት ለምሕረት፡ ኀጢአትንም ለማስተስረይ በመሠውያው ዘወትር እንዲሠውት አደርገዋለሁ አላቸው።

እግዚአብሔርም ወደ አዳም ቍርባን የምታበራ እሳትን ላከ። አካባቢውም በጸዳል ተሞላ። በቍርባኑ የወረደውም መንፈስ ቅዱስ ነው። እግዚአብሔርም በማንኪያ አምሳል የእሳት ጉጠት ይይዝ ዘንድ መልአኩን ቍርባኑን ይይዝና አዳምና ሔዋንንም ያቀርባቸው [ከመሥዋዕቱ ይሰጣቸው] ዘንድ አዘዘው። መልአኩም እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ። ለአዳምና ለሔዋንም ከመሥዋዕቱ ሰጣቸው። ልቡናቸውም ፍጹም ደስታን ተሞላች።

እግዚአብሔርም አዳምን ኃዘን፣ ችግር በሚደርስባችሁ ጊዜ ይህ

ልማድ ይሆንላችኋል፡፡ መዳናችሁ፣ ወደ ገነት መግባታችሁ ግን በእናንተና በእኔ ያሉት ቀናት በሚፈጸሙበት ጊዜ ነው፡፡[55] ምሕረቴ እና ይቅርታዬ በእናንተ ላይ ቢሆን ኖሮ በስሜ ስላቀረባችሁት መሥዋዕት /ቊርባን/ ወደ ገነት /ወደ ክብሬ/ በመለስኋችሁ ነበር፡፡ አዳምም በእግዚአብሔር ዘንድ በሰማው በዚህ ቃል ተደሰተ፡፡ እርሱም ሔዋንም በመሥዋዕቱ ፊት ሰገዱ፡ እጅ ነስተውትም ወደ ቤታቸው ተመለሱ፡፡ ይህም ከገነት ከወጡ ከሰማንያ ቀን በኋላ በዐሥራ ሁለተኛ ቀን ፍጻሜ ነበር፡፡

ሌሊቱን ሁሉ እስኪነጋ ድረስ ቆሙ፡፡ ከቤትም ወጡ፡ አዳምም ልቡናው ደስ ስለተሰኘ ለእግዚአብሔር ስላቀረቡት ቊርባንም፡ ከእርሱም ስለ ቀረቡ ሔዋንን በሳምንት ሦስት ጊዜ ባለ ሕይወታችን ሁሉ ይህን እናድርግ እነዚህም ረቡዕ፣ ዐርብ፣ ሰንበት ናቸው አላት፡፡ በዚህ ቃልም እርስ በእርሳቸው ተስማሙ፡፡ እግዚአብሔርም በዐሳባቸው፡ በጽንአታቸውም ተደሰተ፡፡ የእግዚአብሔር ቃልም እንዲህ ሲል ወደ አዳም መጣ፡፡ አዳም ሆይ! ሰው በሆንሁ ጊዜ በእኔ ላይ የሚመጣውን መከራ የምቀበልበትን ዕለት አንተ አስቀድመህ ወሰንህ፡፡ እነዚህም ረቡዕ፣ ዐርብ ናቸው፡፡ እሑድ ግን እኔ ሁሉን ፈጠርሁበት፡ ሰማያትንም እንዲሁ ከፍ አደረግሁበት፡፡

ዳግመኛም በምነሣበት ዕለት ደስታን አደርጋለሁ፡፡[56] የሚያምኑብትንም ከፍ ከፍ አደርጋቸዋለሁ፡፡ አዳም ሆይ! ይህን ቊርባን በሕይወትህ ሙሉ አቅርብ፡፡ እግዚአብሔርም ከአዳም ጋር መነጋገሩን አቆመ፡፡ አዳምም ሰባት ሱባኤ እስኪፈጸም ድረስ እንደታዘዘው ከሳምንት ሦስት ጊዜ መሥዋዕት ያቀርብ ነበር፡፡ በዕለተ እሑድ ይህም የኀምሳው ቀን መጨረሻ ነው፡፡ አዳም እንደልማዱ ቊርባንን አዘጋጀ፡፡ እርሱ እና ሔዋንም ይዘው እንዳስለመዱ በእግዚአብሔር ፊት መሥዋዕቱ ወደ ሚሠዋበት መጡ፡፡

የመልካም ነገርጠላት ሰይጣን ግን በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስን /ባለሟልነት/ ባገኙበት በቊርባኑ ምክንያት በአዳምና በሔዋን ቀና፡፡ በዚህም

---

[55] አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

[56] ግሉ. ፳፰+፭: ፳+፩

የተነሣ በሰው አምሳል በሚታይበት ገንዘብ ስለት ከሆኑ ድንጋዮች መካከል ስለት /የሚቆርጥ/ ደንጊያን ፈጥኖ ያዘ:: ሄዶም በአዳምና በሔዋን ዘንድ ቆመ:: አዳምም ከመሠውያው ላይ ወጥቶ ነበር:: ጸሎትም ጀምሮ ነበር::

እርሱም እጁን ወደ እግዚአብሔር ዘረጋ:: በእርሱ ዘንድ ባለ በስለት ደንጊያ መምታቱንም አፋጠነ:: የአዳም ቀኝ ጎኑንም ወጋው:: ከጎኑም ደም፣ ውኃ ወጣ:: አዳምም እንደሞተ ሰው ሆኖ ከመሠውያው ላይ ወደቀ:: ሰይጣንም ሸሸ:: ሔዋን መጥታም አነሣችው፤ ከመሠውያው በታችም አስቀመጠችው:: በእርሱ ላይም ታለቅስ ነበር::

አዳም ቍርባኑን በመሠውያው ላይ ባሳረገ ጊዜ ከጎኑ የወጣ ደሙ በቍርባኑ ላይ ፈሰሰ:: እግዚአብሔርም የአዳምን መሞት/መውደቅ/ ዐየ:: ቃሉንም ላከ፡ አነሣውም:: ቍርባንህንም ፈጽም አለው:: በጣም አስደስቶኛል፡ ምንም ጉድለት የለበትምና:: እግዚአብሔርም አዳምን አለው:: ዳግመኛ እኔ በዚህች ምድር እንደዚህ ይደርስብኛል:: እወጋለሁ፤ ከጎኔም ደምና ውኃ ይወጣል::[57] በሥጋዬም ይፈሳል::[58] ይህም እውነተኛ ቍርባን ነው:: በቍርባኑ መሠውያ ላይም ፈጽሞ ያርጋል::

እግዚአብሔርም አዳምን ቍርባኑን ይፈጽም ዘንድ አዘዘው:: ቍርባኑን አቅርቦ ከፈጸመ በኋላም በእግዚአብሔር ፊት ሰገደ:: ለእርሱ ስላሳየው ምልክትም አመሰገነው:: እግዚአብሔርም አዳምን በዕለተ እሑድ ፈወሰው:: ይህም አምሳኛው ቀን የሰባተኛው ሱባኤ መጨረሻ ዕለት ነው:: አዳምና ሔዋን ግን ወደ ተራራው ተመለሱ:: እንደልማዳቸውም ወደ ቤተ መዛግብት /ዕቃ ቤት/ ተመለሱ:: አዳም ከገነት ከወጣ መቶ አርባ ሁለት ቀን ተፈጸመ::

በነጋ ጊዜም አዳምና ሔዋን ከቤታቸው ወጡ:: ከቤት ወደ ሰንዶአቸው በታ ወደ ምዕራብ ጫፍ ወረዱ:: እንደልማዳቸውም በዛፍ ሥር ~~ተመለሱ:: በዘ አራዊት~~ መጥተው ከበቧቸው:: ሰይጣንም በክፋቱ ይህን

57 ዮሐ ፲፱፥፴፬
58 በዕለተ ዐርብ ይህን ታሪክ የፈጸመው የሮማ ወታደር ለንጊኖስ ነው:: ይህ ሰው የጌታ ሰው የክርስቶስን ደም ሲፈሰስም ብሎ ከአይሁድ በመለየት ወይጣሪ ሄዷል:: ሌላው ለመለስ ክርስቶስ ጐኑ አገኘው:: ከአይሁድ አንድንት እንዲያወጣ ከምተም አይለግውም በግለት ቀኝ ጐኑን በጦር ወጋው:: ውኃና ደም ለጥምቀታችን ደሙ ለመጠጣችን ሆኗል:: በመጨረሻም ይህ ሰው የክርስቶስ ተከታይ በመሆን በሰማዕትነት ሙቷል::

ያደርግ ነበር።

አዳምን በግቢ /በግብረ ሥጋ ግንኙነት/ ምክንያት ድል እስኪነሣው ድረስ። ከዚህ በኋላ የመልካም ጠላት ሰይጣን መልአክ መሰለ። በእርሱ አምሳልም ሌሎች ሁለት ነበሩ። ለአዳም ወርቅ፣ ዕጣን እና ከርቤን እንዳመጡለት መላእክት ሦስት ነበሩ። በአዳምና በሔዋን ፊት አለፉ። እነርሱም በዛፍ ሥር ነበሩ። ሽንገላን በተመላ ጥሩ ነገር ከአዳምና ከሔዋን ጋር እጅ ተነሣሱ። አዳምም ፊታቸውን፣ መልካም ነገራቸውን በተመለከተ ጊዜ ቁሞ ተቀበላቸው። ወደ ሔዋንም አመጣቸው። ሁሉም ተቀመጡ፡ የአዳም ልቡናም ደስተኛ ነበር።

እርሱ/አዳም/ ወርቅ፣ ዕጣን፣ ከርቤ ያመጡለት መላእክት እንደሆኑ በልቡ አሰበ። እነዚያ መላእክት አስቀድሞ ወደ አዳም በመጡ ጊዜም ከእነርሱ የተነሣ ዕረፍት፣ ደስታ በእርሱ ላይ ነበር። መልካም የሆኑ ምልክቶችን ይሰጡት ዘንድ እንደመጡ አሰቧልና። ሰይጣን እንደሆነም አላወቀም። ስለዚህም በደስታ ተቀብሎ ከእነርሱ ጋር ተቀመጠ።

ከእነርሱ ታላቁ ሰይጣንም እንዲህ አለ። አዳም ሆይ! ፈጽሞ ደስ ይበልህ። እነሆ! እግዚአብሔር አንዲት ነገርን እንነግርህ ዘንድ ወደ አንተ ልኮናልና+አለው።

አዳምም ምንድን ነው? አለ። ሰይጣንም ነገሩ /ቃሉ/ ቀላል ነው። እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው። ካልሰማህ እኛ ወደ እግዚአብሔር እንመለሳለን። ቃላችንን እንዳልተ ቀበልህም እንነግረዋለን። ዳግመኛም ሰይጣን አዳም ሆይ! ከእኛ የተነሣ አትፍራ። መንቀጥቀጥም አይድረስብህ። አታውቀንምን አለው። አዳምም አላውቃችሁም አላቸው።

ሰይጣንም እኔ ወርቅን እስከ ቤትህ ተሸክሜ ያመጣሁልህ፣ ይህ ሁለተኛው ደግሞ ዕጣን፣ ይህ ሦስተኛው ደግሞ ከርቤን ያመጣልህ ነው። ከተራራው እስከ ቤትም የተሸከሙህ ናቸው አለው። እስከ ቤት ያደረሷችሁን

ጓደኞቻችንን ግን እግዚአብሔር ከእኛ ጋር አልላካቸውም፤ እናንተ ትጠቀሙባላችሁና አላቸው።።

አዳምም ይህን ቃል ከእነርሱ በሰማ ጊዜ አመናቸው። እግዚአብሔር የተናገረውን ቃል ተናገሩ፤ እኔም እቀበለዋለሁ አላቸው። ሰይጣንም እንደምትቀበለው ማልልኝ፤ ቃል ኪዳንም ግባልኝ አለው። አዳምም እኔ መሐላ እና ቃል ኪዳን አላውቅም አለው። ሰይጣንም እጅህን አውጣት፣ በእጄ ላይም አስቀምጣት። የእግዚአብሔር እውነት ሕያው ሆኖ የሚኖር፣ ከአርያም ወደ ሰማይ ያረገ፣ መሬትን በውኆች ላይ ያጸና እና ከአራቱ ባሕርያት የፈጠረኝ እኔ ቃል ኪዳኔን አላረክስም፤ ቃሌንም አልለውጥም፤ /አላቆሽሽም/ በል አለው፤ አዳምም እንዲሁ ማለ።

ሰይጣንም እነሆ! አንተ ዘመን አለህ። ከገነት ከወጣህ ጀምሮ ፈጽሞ ከፉን አታውቅም፣ እግዚአብሔር ከጎንህ የወጣች ሔዋንን ትወስዳት ዘንድ የምትጽናናበት ልጅ ለመውለድም ታገባት ዘንድ አዝዟል፤ ችግርም ኃዘንም ከአንተ ዘንድ ይርቃል። ይህ ሥራም ከባድ አይደለም፤ መሰናከልም አይሆንብህም አለው።

አዳምም ይህን ከሰይጣን በሰማ ጊዜ ስለመሐላው ከባድ ኃዘንን አዘነ። አዳምም ሰይጣንን አለው፤ እኔ በዕድሜዬ በሥጋዬ እንዴት እዘሙታለሁ / አበድላለሁ/። ተቸግሬ ከመሐላዬ ብመለስ እግዚአብሔር ያጠፋኛል፤ ከምድር ገጽም ይደመስሰኛል። እኔ ቀድሞ ከዕፀ በለስ በበላሁ ጊዜ ከገነት ወደ ዚህች ኃላፊት ምድር አውጥቶኛልና። በሌላም በኩል በእኔ ላይ ሞትን አመጣ፤ ዳግመኛም ይህን ካደረግሁ ሕይወቴን /ነፍሴን/ ከዚህች ምድር ይወስዳል፤ ወደ ሲኦልም ያወርደኛል፤ እጅግም ያሰቃየኛል። የምትለኝን ይህን ቃል እግዚአብሔር አልነገረኝም፣ እናንተም የእግዚአብሔር መላእክት አይደላችሁም።

እናንተ ሰይጣናት ከእርሱ ወደ እኔ የተላካችሁም አይደላችሁም፤

ናችሁ። በምትሐትም መላእክትን መሰላችሁብኝ እንጂ ከእኔ ወግዱ፤ እግዚአብሔር ይርገማችሁ አላቸው። ሰይጣናትም ከአዳም ፊት ሸሹ። አዳምና ሔዋን ተነሥተው ወደ ቤታቸው ተመለሱ። ወደ ውስጥም ገቡ። አዳምም ሔዋንን የማደርገውን ታያላሽን? አትናገሪምን? በታላላቅ ስሞቹ ስለመማሌ በእግዚአብሔር ዘንድ ይቅርታን አጣሁ። እጄንም ዳግመኛ በሰይጣን እጅ ላይ አደርጋለሁ አላት።

ሔዋንም አዳም ከነገራት የተነሣ ዝም አለች። አዳምም ተነሥቶ እጁን ወደ እግዚአብሔር ዘረጋ። ይቅር ይለው ዘንድ ከእርሱ ይቅርታን ፈልጓልና። ያደረገውን ይቅር ይለው ዘንድም ያለቅስ ነበር። አዳምም እንዲሁ ለጸሎት ቆሞ ነበር። ለአርባ ቀንና ለአርባ ሌሊት ያህል እጁን በመዘርጋት ከረኀቡ፣ ከጽሙ የተነሣ በምድር እስከሚወድቅ ድረስም አልበላም፡ አልጠጣም።

እግዚአብሔርም ቃሉን ወደ አዳም ላከ፤ ከወደቀበትም አነሣው። አዳም ሆይ! በስማዮች ለምን ማልህ? ሁለተኛስ ከሰይጣን ጋር ለምን ተማማልህ? አለው። አዳምም አለቀሰ። አቤቱ ጌታዬ ሆይ! ይህን ሳላውቅ አድርጌዋለሁና ይቅር በለኝ አለ። የእግዚአብሔር መላእክት እንደሆኑ አምኜ ነበርና አለ። ይቅርም አለው፤ ከሰይጣንም ተጠንቀቅ፡ አለው። እግዚአብሔርም ከአዳም ጋር ንግግሩን ፈጸመ። አዳምም ልቡናው ተጽናና፡ ሔዋንንም ወሰዳት። እንደልማዳቸው ለሥጋቸው ምግብ ያዘጋጁ ዘንድ ከቤት ወጡ።

ከዚያች ሰዓት ጀምሮ አዳም ሔዋንን በሩካቤ ሥጋ ያውቃት ዘንድ ሕሊናው ይፈታተነው ነበር። ይህን ያደርግ ዘንድ ግን ይፈራ ነበር። እግዚአብሔር እንዳይቆጣው አዳምና ሔዋንም ወደ ውኃው ምንጭ ሄዱ። በሚደሰቱ ሰዎች አምሳልም በዚያ ተቀመጡ።

ሰይጣንም በእነርሱ ቀና። እርሱ ከሰራዊቱ ዐሥሩ እንደ እነርሱ ያለ ደም ግባት የሌለ ደናግልን መሰሉ። ከውኃውም ወደ አዳምና ወደ ሔዋን ወጣ። እርስ በርሳቸውም ዓለምን የመላች የአዳምና ሔዋንን መልክ ገጽ

እንመልከት፡ መልካቸው ከእኛ የተለየ እነርሱም ከእኛ ያማሩ ናቸውና ተባባሉ፡፡

አዳምና ሔዋንም ወደ ጫፍ ደረሱ፤ አጅም ነሷቸው፡፡ ከእነርሱ የተነሣም እያደነቁ ቀሩ፡፡ አዳምና ሔዋንም ከደም ግባታቸው የተነሣ በማድነቅ ወደ እነርሱ ተመለከቱ፡፡ እኛ ከምንኖርባት ምድር ታች መልካም ፍጥረት ያለባት ሌላ ዓለም አለችን? አሉ፡፡ እኒህ ደናግልም ለአዳምና ለሔዋን እውነት ነው፡፡ ፍጥረታችንም ብዙ ነው አሉ፡፡ አዳምም የምትባዙት በምንድን ነው? አላቸው፡፡

እኛ የሚያገቡን ባሎች አሉን፤ ከእነርሱም እንፀንሳለን፡፡ ልጅ እንወልዳለን፡፡ ልጆችም ያድጋሉ፤ በዚህም እንባዛለን፡፡ አዳም ሆይ! የማታምነን ከሆነ እኛ ባሎቻችን፣ ልጆቻችንን እናሳይሃለን አሉት፡፡ ልጆቻቸውን፣ ባሎቻቸውን እንደሚጠሩም በባሕር ላይ ነበሩ፡፡ ከባሕሩም ሰዎች እና ሕፃናት ወጡ፡፡ ከእነርሱ እያንዳንዱ ሁሉም ወደ ሚስቱ ወደ ልጆቹም ይደርስ ነበር፡፡

አዳምና ሔዋንም ባዩአቸው ጊዜ ሄዱ፡፡ ከእነርሱ የተነሣም አደነቁ፡፡ እነርሱም አዳምና ሔዋንን እነሆ! ባሎቻችን፣ ልጆቻችን ተመልከታችሁ፤ ፅንስ ሲሆን ግን አታውቁም፡፡ አዳም ሆይ! ሥራውን መጀመርን አንተ በሔዋን ላይ እንዴት እንደምታደርግ እናሳይሃለን ብለው፡፡ አንዱም ሌላውም በአዳም ፊት ከፉ ማድረግን/ሩካቤ ሥጋ መፈጸምን/ ጀመረ፡፡ ከዚህ በኋላ አዳምን አንተም በሔዋን ላይ እንዲህ አድርግ፤ አሉት፡፡ ልጅ ትወልዳለህ፤ ዘር ትተካለህ፡ ትባዛለህም አሉት፡፡ ሰይጣን ይሸነግለው ዘንድም በአዳም ፊት ይህን ያደርግ ነበር፡፡

ዳግመኛም፣ ሰይጣን በዐሳቡ እንዲህ አለ፡፡ በመጀመሪያ እግዚአብሔር አዳምን ስለዕፀ በለስ "ከእርሱ አትብላ፤ ከበላህ ሞትን ትሞታለህ" ብሎ አዝዞታልና፡፡ ግርፋት፣ መከራም ከሥጋው እስኪወጣ ድረስ ዛሬም ይህን ነገር ያደርግ ዘንድ ባታለልሁት ጊዜ፣ ወደ ሔዋንም በቀረበ፣ በወደቀም ጊዜ ያለ እግዚአብሔር ትእዛዝ በሆድዋ ይፀነሳል፣ እርሱም ይገድለዋል፡፡

በዚያን ጊዜም ሰይጣን በአዳም ፊት ይህን ምትሐት አደረገ፤ ሊገድለው ከምድረ ገጽም ሊያጠፋው ፈልጎ አዳምንም የነጠለአት እሳት በሰውነቱ ተቀላቀለበት /ተስማማው/፡፡ ያደርጋት /ፍላጐቱ ሥጋ ይፈጽም/ ዘንድም አሰበ፡፡ ነገር ግን ሰውነቱን ይገታ ነበርና እግዚአብሔር ይገድለው ዘንድ ይህን ምክር ለማድረግ /ዝሙትን ለመፈጸም/ ይፈራ ነበር፡፡ አዳምና ሔዋንም ወደ እግዚአብሔር ይጸልዩ ዘንድ ተነሡ፡፡ ሰይጣንና ሰራዊቱ ግን ከአዳም ፊት ወደ ባሕር ወረዱ፡፡ እነርሱ ወደ መሬት ሲመለሱ ያዩአቸው ነበር፡፡

አዳምና ሔዋንም እንደልማዳቸው ወደ ቤት /ቤተ መዛግብት/ ተመለሱ፡፡ ይህ የሆነውም ምሽት ነው፡፡ አዳምና ሔዋንም በሌሊት ወደ እግዚአብሔር ይጸልዩ ዘንድ ተነሡ፡፡

ጸሎታቸው፣ አማላጅነታቸው ከሊቃነ ጳጳሳቱ አለቃ ከአባ ባስልዮስ፣ ከንጉሣችን ኀይለ ሥላሴ፣ ከጥምቀት ልጆች ከእኛ ጋርም ይሁን፡፡ ለዘለዓለሙ አሜን፡፡

## ምዕራፍ ስድስት

## ገድለ አዳም ዘመስከረም

አንድ አምላክ በሆኑ በአብ፣ በወልድ፣ በንፈስ ቅዱስ ስም፤ መስከረም ስድስት ቀን የሚነበብ የአባታችን የአዳም፣ የእናታችን የሔዋን ገድል ይህ ነው፡፡ ጸሎታቸው፣ በረከታቸው፣ አማላጅነታቸው ከሊቃነ ጳጳሳቱ አለቃ ከአባ ባስልዮስ፣ ከንጉሣችን ኀይለ ሥላሴ፣ ከሁላችንም ጋር ይሁን፤ ለዘለዓለሙ አሜን፡፡

አዳምም ይጸልይ ዘንድ ቆሞ ነበር፡፡ ሔዋንን ስለመገናኘት በልቡናው ውስጥ ካለው ዐሳብ የተነሣ እንዴት እንደሚጸልይ አላወቀም፡፡ እስኪነጋም እንዲህ ሆነ፡፡ በነጋ ጊዜም አዳም ሔዋንን ነይ፤ ወርቅ ወደ ሰጠን ተራራ ተነሽ እንሂድ፡፡ ስለዚህ ምክር ወደ እግዚአብሔር እንለምን ዘንድ አላት፡፡ ሔዋንም

አዳም ሆይ! ምክሩ ምንድን ነው? አለችው፡፡ እግዚአብሔር ስለጋብቻ /ግንኙነት/ ያለትእዛዙ እንዳልፈጽም ያስረዳኝ ዘንድ አሻለሁ፤ አንቺንም እኔንም እንዳያጠፋን ሰይጣናት በምትሐት ኅጢአትን ሲያደርጉ ስለታዩኝ ልቦናዬ ተቃጥሏልና አላት፡፡

ሔዋንም አዳምን ወደ ምድር ታች ለምን እንሄዳለን፤ በቤታችን ቁመን ይህን ምክር ያስረዳን ዘንድ ወደ እግዚአብሔር እንጸልይ እንጂ፤ መልካም ከሆነም፣ ካልሆነም አለችው፡፡ አዳምም ለጸሎት ተነሣ፡፡ እንዲህም አለ፤አቤቱ ፈጣሪያችን ሆይ! እኛ እንደተደፋፈርንህ አንተ ታውቃለህ፡፡ በተደፋፈርንህ ጊዜም ብርሃናዊት ጸጋችን ተገፈፈችብን፡፡ ሥጋችን መብልን፣ መጠጥን እና እንስሳዊት ፍትወትን /ምኞትን/ የምትሻ ሆነች፡፡ አቤቱ ጌታችን ሆይ! ያለ ትእዛዝህ እንዳንሠራ እዘዘን፤ እንዳታጠፋን፡፡ ካላዘዝኸን ግን እኛ እንሸነፋለን፡፡ ትእዛዝህን ወደ መተላለፍም እንመለሳለን፤ አንተም ታጠፋናለህ፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ነፍሳችንን ተቀበል፤ ከዚህ እንስሳዊ ፍትወትም አንረፍ፡፡ ይህ ተግባር የማይፈቀድልን ከሆነ ሔዋንን ከእኔ ለያት፤ እኔንም ከእርሷ ለየኝ፡፡

ከእኛም አንዳችንን ከአንዳችን ውሰድ፤ አርቀንም፡፡ አቤቱ ጌታችን ሆይ! እርስ በርሳችን በለየኸን ጊዜም አጋንንት ምትሐት ያደርጉብናል፡፡ ልባችንንም ያስጠፉናል፡፡ እርስ በርሳችንም አእምሮአችንን ያስጨንቁታል፡፡ እርስ በርሳችን ካልሆነ በማይታዩን ሁኔታ በፊታቸው ነን፤ አዳምም ንግግሩን አቆመ፡፡ እግዚአብሔርም እውነት እንደሆነ፤ ከሰይጣን ፈተና የተነሣ መታገሥ እንደማይችል፡፡ ወደ አዳም ቃል ተመለከተ፡፡ እግዚአብሔርም አዳም ስላሰበው፣ ስለጸለየውም ጸሎት አዳምን አመሰገነው፡፡

የእግዚአብሔር ቃልም ወደ አዳም እንዲህ ሲል መጣ፡፡ አዳም ሆይ! ይህ ጥንቃቄ ከገነት ወደ ኃላፊዋ ምድር ከመውጣትህ በፊት ቢሆን ኖሮ መልካም ነበር አለው፡፡ ከዚህ በኋላም እግዚአብሔር ወርቅ ያመጣውን መልአክ፣ ዕጣን ያመጣውን መልአክ እና ከርቤ ያመጣውን መልአክ የመጋባትን

ተግባር ያስረዱት ዘንድ ወደ አዳም ላከ።

መላእከትም አዳምን ወርቅን ውሰድ፤ ለማጫ ይሆናት ዘንድም ለሔዋን ስጣት። እርሷና አንተ አንድ አካል ትሆኑ ዘንድ ቃል ኪዳንም አድርግላት፤ የእጅ መንሻ ዕጣን፣ ከርቤም ስጣት አሉት። አዳምም ከመላእከት ይህን ሰማ። ወርቅንም ወሰደ፤ ለሔዋን ጭንም ልብስ አደረገው። በእጃቸውም ቃል ተግባቡ። መላእከትም አዳምና ሔዋንን አርባ ቀን፣ አርባ ሌሊት ይጸልዩ ዘንድ አዘዟቸው። ከዚያም በኋላ ወደ ሚስቱ ይቀርብ ዘንድ፤ ንጹሕ ይሆን ዘንድ፤ ርኩስም እንዳይሆን፡ ልጅም ትወልድለት ዘንድ፤ ዘርን ይዘሩ ዘንድ፣ የዘሩትንም ከመሬት ይነቅሉ /ይሰበስቡ/ ዘንድ አስተማሩት።

አዳምና ሔዋንም የመላእክትን ቃል ተቀበሉ። መላእከትም ከእነርሱ ሄዱ። አዳምና ሔዋንም አርባው ቀን እስኪፈጸም ድረስ ጾሙ። አዳምና ሔዋንም መላእከት እንዳዘዟቸው ተኙ። አዳምም ከወጣበት ቀን ጀምሮ ሔዋንን እስካገባበት ድረስ ሁለት መቶ ሦስት ቀን ሆነው። ይህም ስድስት ወር ከሃያ ሦስት ቀን ነው። ለአዳምና ለሔዋንም የሰይጣን ጦርነት በእነርሱ ላይ ጠፋላቸው። በመሬትም እንደ ሥጋ መጠናቸው ይኖሩ፣ ይሠሩም ነበር። የሔዋን ፅንስ ዘጠኝ ወር እስኪሆን ድረስ እንዲሁ ነበር።

የመውለጃዋ ጊዜም ተቃረበ፤ ሔዋንም አዳምን አለችው። ይህች ቤት ንጹሕ ቦታ ናት። በገነት ያሉ ምልክቶች በውስጧ ስላሉ፤ ዳግመኛም እኛ በውስጧ እንጸልያለን፤ ሰይጣን በእኛ ላይ ወደ ጣላት የድንጋይ ድንኳን ቤት እንሂድ እንጂ። በእርሷ ሊገድለን ፈልጎ በእግዚአብሔር ትእዛዝም ተያዘች፤ ተከለለችልን፤ ቤትም ሆነችልን። አዳምም ሔዋንን ወደ ዚያች ቤት ወሰዳት፤ የመውለጃዋ ጊዜ ሲደርስ በሕማም ትፀንሻለሽ፤ በኃዘንም ልጅ ትወልጃለሽ ያለው የእግዚአብሔር ቃል ይፈጸም ዘንድ ሔዋን በምጥ ተጨነቀች፤[59] ለሞትም ደረሰች፤ አዳምም አዘነ፤ ልቡ ታወከ፣ ለሞትም ደረሰች።

አዳምም በውስጧ ያለውን የሔዋንን መጨነቅ በተመለከተ ጊዜ

ተነሥቶ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ:: አቤቱ አምላክ ሆይ! በዚህ ጭንቅ ውስጥ ባሪያህ ሔዋንን ተመልከት:: በገነት በነበረችበት ጊዜ የፈረድኸውን /የተናገርኸውን/ በእርሷ ላይ አታምጣ፡ አታጥፋትም:: አቤቱ ፈጣሪያችን ሆይ! በምሕረት ዐይን ተመልከታት፡ ከዚህች ጭንቅም አውጣት::

እግዚአብሔርም ወደ አገልጋዩ ወደ ሔዋን ተመለከተ፡ አጸናትም:: የበኵር ልጇንም ወለደች:: ከእርሱ ጋርም ሴት ልጅ ወለደች፡ አዳምም በሔዋን መዳን ተደሰተ:: ዳግመኛም በተወለዱለት ሕፃናት ተደሰተ:: አዳምም በቤት ውስጥ እስከ ስምንት ቀን ድረስ ለሔዋን ይላክ ነበር:: የልጁን ስምም ቃኤል አለው፤ ሴት ልጁንም ሉልዋ[60] አላት::

የቃኤል ትርጓሜም ጠላት ማለት ነው:: ከመውጣቱ በፊት በእናቱ ማሕፀን ሳለ እኅቱን ጠልቷልና:: ስለዚህም አዳም ቃኤል ብሎ ሰየመው:: የሉልዋ ትርጓሜም ያማረች /መልከ መልካም/ ማለት ነው:: እርሷ በደም ግባት ከእናቷ ትበልጣለችና:: አዳምና ሔዋንም ለቃኤልና ለእኅቱ አርባ ዕለት እስኪሞላ ድረስ ታገሡ:: አዳምም ሔዋንን ስለ ሕፃናቱ ቍርባን እናቀርብ ዘንድ እሻለሁ አላት::

ሔዋንም መጀመሪያ ለወንዱ ልጅ ቍርባን እናቅርብ፤ ከዚያ በኋላ ደግሞ ለሴቷ ልጅ እናቅርብ አለችው:: አዳምም ቍርባንን አዘጋጀ:: እርሱም፣ ሔዋንም፣ ልጆቻቸውም ወዳዘጋጁት ወደ መሠውያው መጡ::

አዳምም ቍርባኑን በመሠውያው ላይ አቀረበ፤ እግዚአብሔርም ቍርባኑን ይቀበልለት ዘንድ ፈለገ:: እግዚአብሔርም የአዳምን መሥዋዕት ተቀበለ፡፡ አዳምም ከቍርባኑ ተቀበለ፤ ልጁም ተቀበለ:: ሔዋንና ሴቷ ልጅ ግን አልቆረቡም /ከመሥዋዕቱ አልተቀበሉም/:: አዳምም ወረደ ልጆችም፤ እነርሱም ደስተኞች ነበሩ::

የሴቷ ልጅ ቀን እስኪፈጸም ድረስም አዳምና ሔዋን ታገሡ:: አዳምም ቍርባንን አዘጋጀ፤ ሔዋንን፣ ሕፃናቱንም ይዞ ወደ መሠውያው ሄዱ::

እንደልማዱም ቍርባንን ዐሳረገ። እግዚአብሔርም ቍርባኑን ይቀበልለት ዘንድ ፈለገ። እግዚአብሔርም የአዳምና የሔዋንን ቍርባን ተቀበለ። አዳም፣ ሔዋን እና ሕፃናቱም ተቀበሉ፤ ከተራራውም ወረዱ፤ እነርሱም ደስተኞች ነበሩ። ወደ ወለዱበት ቤት የሄዱ አይደለም። ወደ አልወለዱባት ቤታቸው /ቤተ መዛግበት/ ሄዱ እንጂ። ሕፃናቱን በውስጧ ያዞሯቸው ዘንድ ከገነት በነበሩት ምልክቶች ይባረኩ ዘንድ። በምልክቶች ከተባረኩ በኋላም ወደ ወለዱበት ቤት ተመለሱ።

ሔዋን ቍርባን ከማቅረቧ በፊት አዳም ይዟት ወደ ውኃው ምንጭ ከእርሷ ጋር ሄደ። ሰውነታቸውንም ወደዚያ ጣሉት፤ እርሷም እርሱም ታጠቡ። ይህችም አዳም በመጀመሪያ ሥጋውን የታጠበባት ናት። ከደረሰባቸው ድካም የተነሣ አዳምና ሔዋንም ከንስሐቸው፣ ከቍርባናቸው በኋላ ሌሊቱን ሁሉ ይጸልዩ ዘንድ ወደ ቤት /ቤተ መዛግበት/ ይመጡ ነበር። ይባረኩም ዘንድ ወደ ቤታቸው ተመለሱ።

አዳምና ሔዋንም ሕፃናት ጡት እስኪጠቡ ድረስ እንዲሁ ነበር። ጡት ባስጣሏቸው ጊዜም አዳም ከሰባት ቀን ሦስት ጊዜ ከሚያደርገው ሌላ ስለነፍሳቸው ቍርባን ለልጆቹ አዘጋጀ። ካስጣሏቸው /ጡት ካስተዋቸው/ በኋላም ሔዋን ፀነሰች። የመፅነስ ዘመኗንም ጨረሰች። ወንድና ሴት ልጅንም ወለደች። ወንድ ልጁን አቤል ብሎ ሰየመው። ሴቷንም አቅሌምየ ብሎ ሰየማት። አርባ ቀን ከተፈጸመ በኋላ ስለወንድ ልጁ ቍርባን አዘጋጀ። በመጀመሪያም አቀረበ።

ዕለቱ በተፈጸመ ጊዜም ስለሴት ልጁ እንደገና አዘጋጀ። በመጀመሪያ ለቃኤልና ለእኅቱ እንዳዘጋጀው ቍርባን ለእነርሱም አቀረበላቸው። ወደ ቤታቸው /ቤተ መዛግብትም/ ይባረኩ ዘንድ አመጣላቸው፤ ወደ ወለዱበት ቤትም ተመለሱ። ዳግመኛም አዳም በመኝታ ወደ ሔዋን ይቀርብ ዘንድ አልተመለሰም። ከዚህ በኋላ ሕፃናቱ በቁመት ፈጽመው ያድጉ ጀመር።

ቃኤልም በታናሽ ወንድሙ የሠለጠነ፣ ልቡም የጨከነ ሆነ። አባቱ

ቊርባን ሲያቀርብ ብዙ ጊዜ ይቀር ነበር፡፡ ቁርባን ይቀበል ዘንድም ከእነርሱ ጋር አይሄድም ነበር፡፡ አቤል ግን የዋህ፣ ገር ልቡና ነበረው፡፡ ለአባቱም፤ ለእናቱም ይታዘዝ ነበር፡፡ ቊርባንን ስለመቀበልም አያስተምረውም ነበር፡፡ ቊርባንም ይወድ ነበር፤ ብዙ ይጾም፣ ይጸልይ ነበር፡፡ ይህችም ለአቤል ትምህርት ሆነች፡፡ እርሱ ወደ ቤት /ቤተ መዛግብት/ መጥቷልና፡፡

በውስጧም የወርቅ፣ የዕጣን፣ የከርቤ በትሮችን ተመለከተ፡፡ በእርሱ ዘንድም ተሣለ፡፡ እነዚህን እንዴት አገኛችኋቸው አለ፡፡ አዳምም የደረሰባቸውን ሁሉ አስረዳው /አመለከተው/፡፡ ቃኤልም በአቤል ቀና፤ አባቱ አዳም ስለነገረው፣ አምላካዊ ስለሆኑ ተግባራትም፣ ከአባቱ ከአዳም በኋላም በቤት / ቤተ መዛግብት/ ሌሊቱን ሙሉ ቀረ፡፡ በዚህች ሌሊትም በሰው አምሳል ሰይጣን ታየው፡፡ እንዲህም አለው፡፡ ቊርባን በማሳረግ ጊዜ ሲጾም፣ ሲጸለይ አንተ አባትህን ብዙ ጊዜ ታውከዋለህ፤ እኔም እገድልሃለሁ፤ ሕይወትህንም ከዚህ ዓለም አጠፋለሁ አለው፡፡

አቤል ግን ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፡፡ ከእርሱም አስወገደው፤ በዲያብሎስ አነጋገርም አላመነም፡፡ በነጋ ጊዜም የእግዚአብሔር መልአክ ተገለጠለት፤ እንዲህ ሲልም አዘዘው፡፡ ከጾም፣ ከጸሎት፣ ለአምላክህ ቊርባንን ከማቅረብ አትቆጠብ፡፡ እነሆ! እግዚአብሔር ጸሎትህን ተቀብሏል፣ በሌሊት ካሳየህ መልኩ የተነሣም አትፍራ፡፡ እኔ ረግሜዋለሁ አለው፡፡

መልአኩም ከእርሱ ሄደ፡፡ በነጋ ጊዜም አቤል ወደ አዳምና ወደ ሔዋን መጣ፡፡ በራእይ የታየውን አስረዳቸው፡፡ በሰሙም ጊዜ አዘኑ፡፡ ሊተረጉሙለት አልቻሉም፤ ልቡን ደስ አሰኙት እንጂ፡፡ ልቡ በደነደነ በቃኤል ግን ሰይጣን ወደ ልቡ ገባ፤ ወንድምህ አቤልን ወላጆቹ አዳምና ሔዋን ከአንተ ይልቅ ብዙ ይወዱታል፡፡ ከፍቅራቸው ጽንዓት የተነሣም ለአቤል መልከ መልካሟን ሊያጋቡት ይሻሉ፤ እነሆ! እኔ ይህን እመክርሃለሁ፤ ወንድምህን ግደለው፤ ያን ጊዜም ለአንተ ትቀርልሃለች፤ እኅቱም ቈማ ትቀራለች አለው፡፡

ሰይጣንም ከእርሱ ሄደ፤ ከፉ ነገርም በልቡ ቀረ /ተቀረጸ/፡፡ ብዙ ጊዜም የወንድሙን መግደያ ይፈልግ ነበር፡፡ አዳምም ታናሹን እንደሚጠላው በተመለከተ ጊዜ ልቡን ለማለዘብ ፈለገ፡፡ አዳምም ቃኤልን ልጄ ሆይ! ካየሃቸው ፍሬዎች ውሰድ፤ ለአምላክህም ቊርባንን ዐሳርግ፤ በደልህን ኀጢአትህንም ይቅር ይልህ ዘንድ አለው፡፡

ዳግመኛም አቤልን ከዘርህ ቊርባንን ውሰድ፤ ለአምላክህም ቊርባንን ዐሳርግ፤ ኀጢአትህንና በደልህን ይቅር ይልህ ዘንድ አለው፡፡ አቤልም የአባቱን ቃል ተቀበለ፤ ከዘሩም ወሰደ፤ ቊርባንም አደረገ፡፡ አባቱ አዳምንም ከእኔ ጋር እንሂድ እንዴት ቊርባን እንደማቀርብ ታስተምረኝ ዘንድ አለው፡፡ አዳምና ሔዋንም ከእርሱ ጋር ወጡ፡፡ በመሠውያው ላይ ቊርባን እንዴት እንደሚቀርብም አስረዱት፡፡ ከዚህ በኋላም የአቤልን መሥዋዕት ይቀበል ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ጸለዩ፡፡

እግዚአብሔርም ወደ አቤል ወደ ቊርባኑም ተመለከተ፡፡ እግዚአብሔርም በአቤል ከቊርባኑ መበጀት /ማማር/ የተነሣ ስለየዋህ ልቡናው፣ ስለሥጋው ንጹሕነት ፈጽሞ ተደሰተ፡፡[61] በውስጡ የሸንገላ ተግባር አልነበረበትም ነበርና፡፡ ከመሠውያው ወርደውም ወደሚኖሩበት ቤት ሄዱ፡፡ አቤልም በቊርባኑ ስለተደሰተ ከሰባቱ ቀን ሦስት ቀን መሥዋዕት ያሳርግ ነበር፡፡

ቃኤል ግን ቊርባንን የሚወድ አልነበረም፡፡ በአባቱ ከብዙ ቁጣ በኋላ አንድ ጊዜ ያሳርግ ነበር እንጂ፡፡ ቊርባን በሚያቀርብበት ጊዜም ዐይኑ በሚያሳርገው ቊርባን ትሆን ነበር፡፡ ለመሥዋዕት ይሆነው ዘንድ ከበጎቹ ትንሹን ይወስድ ነበር፡፡ ዳግመኛም ዐይኑ በዚያ ነበር፡፡ ስለዚህም እግዚአብሔር መሥዋዕቱን አልተቀበለም፡፡[62] ልቡናው ጥፋትን /በደልን/ የተሞላ ነውና፡፡ በተወለዱባት ቤትም ሁላቸውም እንዲህ በአንድነት ኖሩ፡፡ ለቃኤል ዐሥራ ዐምስት ዓመት፤ለአቤልም ዐሥራ ሁለት ዓመት እስኪሆነው ድረስ፡፡

አዳምም ሔዋንን አላት፤ ሕፃናቱ እነሆ! አደጉ፤ እናጋባቸው ዘንድ

61 ዘፍ.፬፥፪-፭

62 ዘፍ.፬፥፭

ይገባል አላት፡፡ ሔዋን ቃኤልን ማጋባት እንዴት ይሆናል? አለችው፡፡ አዳምም የአቤልን እኅት /መንትያ/ ለቃኤል እናጋባው፡፡ ሔዋንም አዳምን ቃኤል አይፈልግም፤ እርሱ ልበ ጠማማ ነውና፤ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት እስከሚያሳርጉ ድረስ ተዋቸው አለችው፡፡ አዳምም ዝም አለ፡፡

ሰይጣን ግን በጦርነት ያለ ሰውን መስሎ ወደ ቃኤል መጣ፡፡ አዳምና ሔዋን ስለጋብቻችሁ ተማክረዋል፤ ያንተን እኅት ለአቤል፣ የአቤልን እኅትም ለአንተ ሊያጋቡ ተስማሙ አለው፡፡ ባልወድህ ኖሮ ይህን ነገር ባልነገርሁህም ነበር፡፡ ምክሬን ብትቀበልስ፣ ብትሰማኝም በምታገባበት ዕለት ያማረ ብዙ ወርቀ ዘቦ ልብስ አመጣልሃለሁ፡፡ ዘመዶቼም ይረዱሃል አለው፡፡

ቃኤልም በደስታ ዘመዶችህ የት አሉ? አለው፡፡ ዘመዶቼስ አባትህ አዳምን በመጀመሪያ እወስደው ዘንድ ከፈለግሁ ከደቡባዊው ገነት ውስጥ ናቸው አለው፡፡ እርሱ ግን አልተቀበለኝም፡፡ አንተ ብትቀበለኝ፣ ብትፈልግ ከገባህ በኋላ ወደ እኔ ትመጣለህ፤ አንተ ታርፋለህ፤ ከአባትህ ከአዳም ሥራም ትድናለህ አለው፡፡

የቃኤል ጆሮዎችም ተከፈቱ፣ ወደ አነጋገሩም አዘነበሉ፣ በበረሃም አልቆመም፤ ወደ እናቱ ሔዋን መጣ፤ መታት፣ ረገማትም፡፡ እኅቴን ለወንድሜ ታጋቡ ዘንድ ለምን ትወስናላችሁ? እኔ ሙቻለሁን? አላት፡፡ እናቱ ግን ሸነገለችው /አባበለችው/፡፡ ወደሚኖሩባቸው ላከችው፡፡ አዳምም ሔዋንን ቃኤል ስላደረገው ያለችውን በሰማ ጊዜ ፈጽሞ አዘነ፤ ዝምም አለ፤ ምንም አላለም፡፡

በነጋታው አዳም አቤልን ልጄ አቤል ሆይ! ከበጎችህ ጥሩ ጠቦት ውሰድ፤ ለአምላክህም ቁርባንን ዐሳርግ፡ ለወንድምህም በስንዴ ፍሬ ቁርባንን ለአምላኩ ያሳርግ ዘንድ እኔ እነግረዋለሁ አለው፡፡ እነርሱም ከአባታቸው ከአዳም ይህን ሰሙ፤ ሁለቱም ቁርባናቸውን ያዙ፡፡ መሠውያው ወዳለበት ተራራም ወጡ፤ ቃኤል ግን በወንድሙ በአቤል ታበየበት፡፡ ከመሠውያውም ገፋው፡፡ ቁርባንን ያሳርግ ዘንድም አልታገሠውም፡፡ እርሱም ቁርባኑን

ሸንገላን፣ ትዕቢትን በተሞላ ልቡና ዐሳረገ፡፡

አቤል ግን ከመሰውያው አጠገብ ድንጋዮችን ሠራለት፡፡ በዚያም ላይ ትሕትናን በተሞላ ልቡና መሥዋዕቱን አቀረበ፡፡ የሸንገላ ተግባርም አለነበረበትም፡፡ ቃኤልም መሥዋዕቱን ባቀረበበት መሠውያ ላይ ቆሞ ነበር፡፡ እርሱም ቊርባኑን ይቀበል ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ይጮህ ነበር፤ ቊርባኑን ግን አልተቀበለውም፡፡ ከአምላክ የታዘዘች እሳትም ቊርባኑን ታቃጥል ዘንድ አልወረደችም፡፡

በመሠውያው ላይም ቆሞ ቀረ፤ ፊጽሞም ተቆጣ፡፡ እግዚአብሔር ቊርባኑን ይቀበለውም፣ አይቀበለውም እንደሆነ ወደ ወንድሙ ወደ አቤልም ይመለከት ነበር፡፡

አቤልም እግዚአብሔር ጸሎቱን ይቀበለው ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፤ አምላካዊት እሳትም ወረደች፡፡ የአቤልን መሥዋዕትም አቃጠለች፤ እግዚአብሔርም የመሥዋዕቱን መዓዛ አሸተተ፡፡ እርሱ ወዶታል፤ ተደስቶበታልምና፡፡ በሰው አምሳልም መላእክተ ብርሃንን ላከለት፡፡ እርሱ ካሸተተው የመሥዋዕት መዓዛ ይቀበሉ ዘንድ /ይቆርቡ ዘንድ/፡፡ እነርሱም አጽናኑት፣ ልቡንም አበረታቱት፣ ቃኤልም በወንድሙ ቊርባን ላይ የሆነውን ሁሉ ያይ ነበር፡፡

ስለዚህም ተቆጣ፤ አፉንም ቊርባኑን ያልተቀበለለት እግዚአብሔርን ለመሳደብ ከፈተ፡፡ እግዚአብሔርም ቃኤልን ለምን ፊትህን አጠቆርህ?[63] ቊርባንህን እቀበል ዘንድ ጻድቅ/እውነተኛ/ ሁን፡፡ በእኔ ማንጐራጐር አይጠቅምም፤ በአንተ ነው እንጂ፤ በእርሱ ሁኔታ እየሳቀ እግዚአብሔር ለቃኤል ይህን ነገረው፡፡ ቊርባኑንም ተጸየፈው፡፡ ወደ አባቱና ወደ እናቱም ወረደ፡ የደረሰበትን ሁሉም ለአዳም አስረዳው፡፡ እርሱም ተቆጥቶ ነበር፡፡ የቃኤልን ቊርባን ስላልተቀበለውም ቃኤል አዘነ፡፡ አቤል ግን በፍጹም ደስታ ወደ አባቱና ወደ እናቱ ወረደ፡፡ ቁርባኑን እግዚአብሔር እንደተቀበለለትም ነገራቸው፤

ተደሰቱ፤በፊቱ እጅ ነሡት፤ አቤልም አባቱ አዳምን ቃኤል ከመሠውያው ላይ ገፋኝ፣ በእርሱ ቍርባን ዐሳርግ ዘንድም አልታገሠኝም /አልፈቀደልኝም/፡፡ እኔ ሌላ መሠውያ ሠራሁ፡ ቁርባኑንም በዚያ ላይ አቀረብሁለት /ሠዋሁት/ አለው፡፡

አዳምም ይህን በሰማ ጊዜ በጣም አዘነ፡፡ ይህ መሠውያ በመጀመሪያ አዳም መሥዋዕትን ይሠዋበት የነበረ ነውና፡፡ ቃኤልም ከቁጣው /ከንዴቱ/ የተነሣ ወደ ሜካ ሄደ፡፡ ሰይጣንም ወደ እርሱ /ወደ ቃኤል/ ደረሰ፡፡ ወንድምህ አቤል አንተ ከመሰውያው ላይ እንደገፋኸው በአባትህ በአዳም ዘንድ ከሰሃል አለው፡፡ እርሱን /አቤልን/ እነሆ! እጅ ነሡት፤ ተደሰቱም አለው፡፡ ቃኤልም በጣም ተቆጣ፡፡ አንዱን እስከ ሚያውቅም አልተወውም፡፡ በቤት እስኪሰበሰቡ ድረስ ወንድሙን ይጠብቅ ነበር፡፡

ቃኤልም አቤልን ወንድሜ ሆይ! ጥሩ በረሃ አለ፤ በውስጡም ያማሩ የሚያስደስቱ ዕፀዋት አሉበት፤ ለሚመለከታትም ታሳሳለች/ታስጐመጃለች/፡፡ ወንድሜ ሆይ! አንተ አንድ ቀን ስንኳ ትደሰት ዘንድ ወደ በረሃው ፊጽመህ መጥተህ አታውቅም፡፡ ዛሬም ከእኔ ጋር ወደ በረሃው ትሄድና ትደሰት ዘንድ እሻለሁ፤[64] በረሃችንንና በጐቻችንን ትባርክ ዘንድ አለው፡፡ አንተ ጻድቅ ነህና፤ ወንድሜ ሆይ! እኔም በጣም እወድሃለሁ፣ አንተ ከእኔ ትርቀኛለህ እንጂ አለው፡፡

አቤልም ወደ በረሃ ይሄድ ዘንድ ወንድሙ ቃኤልን ተቀበለው፡፡ /እሺ አለው/፡፡ ከመውጣታቸው በፊትም ቃኤል አቤልን ብትር እይዝ ዘንድ ቆምልኝ /ቆየኝ/ አለው፡፡ አቤልም በይውህናው ቆመ /ጠበቀው/፡፡ ሽንጋይ / ደበኛ/ ቃኤል ግን በአራዊት ምክንያት በትር ይዞ ወጣ፡፡ እርሱና ወንድሙም መንገድ ይሄዱ ዘንድ ጀመሩ፡፡ ከእርሱ ጋር እየተነጋገረ፣ እያዘናጋው ሥራውንም ያስረሳው ነበር፡፡ ሥራ፣ በጐችም ከሌሉበት ምድረ በዳ እስከሚደርሱ እንዲህ ይለው ነበር፡፡

አቤልም፣ ቃኤልን ወንድሜ ዕፀዋትን፣ ፍሬያትን፣ ልምላሜዎችን፣ በጐችን ያልኸኝንም ተግባራት ሳናይ በመሄድ /በጉዞ/ ደከምን፡፡ አባርካቸው



64 ዘፍ.፬+፰

ዘንድ ያልገዥኝ በጉቾህ የት አሉ? አለው:: ቃኤልም ወንድሜ ሆይ! ዛሬ በፊታችን ብዙ መልካም ነገሮችን ታያለህ:: እስካደርስህ ድረስ በፊቴ ሂድ እንጂ አለው:: አቤልም ቀደመው፤ ቃኤልም በኋላው ቀረ:: አቤልም ያለተንኮል በይውሀና ይሄድ ነበር:: ወንድሙ እንደሚገድለውም አያውቅም ነበር::በደረሰ ጊዜም ወንድሙ ቃኤል በነገር አጽናናው:: እርሱ በኋላው ትንሽ ርቆ ይሄድ ነበር:: ፈጥኖም እስኪጥለው ድረስ በብትር[65] ደጋግሞ መታው:: ከመሬት በወደቀ ጊዜ ወንድሙ ይገድለው ዘንድ እንዳለው ተረዳ::

አቤልም "ወንድሜ ቃኤል ሆይ! ስለጠባናቸው ጡቶች ተወኝ፤ አትምታኝ:: ስለተሸከሙችን ማሕፀን፣ ስለ ፈጠረን አምላክ በዚህ በሚገድል ብትር አትምታኝ:: የምትገድለኝ ከሆነ ከእነዚህ ታላላቅ ድንጋዮች ውሰድ:: ፈጥነህም ግደለኝ" አለው::

ልቡናው የገዘፈ፣ የደነደነ ቃኤልም ታላቅ ደንጊያ ይዞ ናላውን እስኪያወጣው ድረስ የወንድሙን ራስ መታው፤ ወንድሙም ፊቱ በደም ተነክሮ ነበር፤ ባደረገውም አልተጸጸተም:: የጻድቁ አቤል ደም የወደቀባት ምድርም ተነዋወጸች:: ደሙ ቃኤልን ትውጠው ዘንድም እንዲህ ሆነች፤ የአቤል ደምም የገደለውን ይበቀልለት ዘንድ በምሥጢር ወደ እግዚአብሔር ጮኸ::[66] ቃኤል ግን ለወንድሙ መሬት መቆፈር ጀመረ:: መሬት ሲንቀጠቀጥ በተመለከተ ጊዜ በእርሱ ላይ ስለደረሰበት ፍርሃት ይንቀጠቀጥ ነበር::

ወንድሙንም በጉድጓዱ /በመቃብሩ/ ጨመረው፤ በመሬትም ደፈነው /ቀበረው/:: መሬትም ትቀበለው ዘንድ አልፈቀደችም፤ ወደላይ ተፋችው እንጂ:: ቃኤልም እንደገና መቃብር ቆፈረ፤ ወደላይም ተፋችው:: እስከ ሦስት ጊዜ እንዲህ አደረገ:: መሬት ግን የአቤልን ሥጋ ወደ ላይ ትተፋው ነበር:: በመጀመሪያ ጊዜ ጭቃማዋ መሬት የተፋችው ለፍጥረቱ ሁሉ በሞት የመጀመሪያ በመሆኑ ነው:: ዳግመኛ የተፋችው፡ ያልተቀበለችው ጻድቅ፣ ቸር / ገር/፣ በከንቱም የተገደለ በመሆኑ ነው:: ሦስተኛ የተፋችው ወይም

ያልተቀበለችውም በወንድሙ ፊት ምስክር ይሆን ዘንድ፣ የእግዚአብሔር ቃል ወደ ቃኤል በመጣ ጊዜ መፈራረጃ ይሆነው ዘንድ ነው።

በወንድሙ ላይም እግዚአብሔር ተቆጣ፤ በአቤል መገደልም ተጸጸተ። ሰማይም ተነዋወጸ፤ መባርቅትም በፊቱ ወጡ። የእግዚአብሔር ቃልም ከሰማይ ወደ ቃኤል መጣ። ቃኤል ሆይ! ወንድምህ አቤል የት አለ?[67] አለው።

ቃኤልም በጸና፣ በደነደነ ልብ እንዴት? ጌታዬ ሆይ! የአቤል ጠባቂው እኔ ነኝን? አለ። እግዚአብሔርም ቃኤልን የወንድምህን የአቤልን ደም የጠጣች ምድር የተረገመች ናት፤ አንተም የምትፈራ፣ የምትንቀጠቀጥ ሁን። ይህም ምልክት ይሆንልሃል። ያገኘህ ሁሉ ይገድልሃል[68] አለው።ቃኤልም እግዚአብሔር ስለተናገረው ስለዚህ ቃል አለቀሰ። ቃኤልም እግዚአብሔርን የሚያገኘኝ ሁሉ ይገድለኛል። ከምድረ ገጽም እጠፋለሁ አለ። እግዚአብሔር ግን ቃኤልን ያገኘህ ሁሉ ይገልሃልህ ያለው አልነበረም። ከዚህ ሁሉ ነገር በፊት ቃኤልን የገደለው ሰባት ጊዜ በቀልን ይቅር እለዋለሁ ይል ነበር እንጂ። የእግዚአብሔር ቃል ቃኤልን ያለው ግን ወንድምህ የት አለ? ነው። እግዚአብሔር በቸርነቱ የቃኤልን መመለስ /ንስሐ/ ስለፈለገ ይህን አደረገ። እርሱም በዚያን ጊዜ ተጸጸተ። አቤቱ ጌታ ሆይ! ወንድሜን ስለገደልሁት ኀጢአቴን ይቅር በለኝ አለ። እግዚአብሔርም ኀጢአቱን ይቅር አለው። እግዚአብሔር ቃኤልን ያለው ግን የወንድምህን ደም የጠጣች ምድር የተረገመኝ ትሁን ነበር። ይህም ከእግዚአብሔር በቃኤል ላይ የተደረገ ይቅርታ ነው።

እርሱ መሬትን ረገማት እንጂ እርሱን አልረገመውምና። ምድር ግን የገደለች፣ ኀጢአትንም የሠራች አልነበረችም። ርግማን የሚገባ በገደለው ሰው ነበር። እግዚአብሔር ከምሕረቱ የተነሣ ዐሳቡን እንደማያውቅ እንደአንድ ሰው አደረገ እንጂ። ወደ ቃኤልም ተመለሰ። ወንድምህ የት አለ? አለው። መልሶ አላውቅም፣ አለ። ቃኤልም የሚፈራ የሚንቀጠቀጥም ሆነ፡ እግዚአብሔርም በዚህች መልከት የታወቀ አደረገው። በፍጥረቱ ሁሉም ወንድሙን ገዳዩ

እንደሆነ ታወቀ፡፡

ዳግመኛም በመጀመሪያ የነበረውን ጸጥታ ያስተውል ዘንድ ፍርሀትን፣ መንቀጥቀጥን አመጣበት፡፡ በኋላ የመጣበትን መንቀጥቀጥ፡ ፍርሀት አስተዋለ፡፡ በእግዚአብሔር ይድን ዘንድ፡ ስለኀጢአቱም ይጸጸት ዘንድ፡ በመጀመሪያ የነበረውን ጸጥታ ይፈልግ ዘንድ፡፡

የእግዚአብሔር ቃል ቃኤልን የሚገድለውን ሁሉ ሰባት እጥፍ ይቅር እለዋለሁ፤ ማለቱ ግን እግዚአብሔር በሰይፍ ይሞት ዘንድ የሚሻ አይደለም፡፡ እርሱን በጾም፣ በጸሎት፣ በለቅሶ፣ በከባድ ቀኖና ከኀጢአቱ እስኪድን ድረስ የሚገድለው /የሚቀጣው/ ይፈልግ ነበር እንጂ፡፡ ሰባት እጥፍ የተባለውም በዘመኑ ሁሉ እግዚአብሔር ቃኤልን የታገሠው ሰባት ትውልድ ነው፡፡

ወንድሙን የገደለ ግን በየቦታው ጸጥታ /መረጋጋት/ የቀረለት አይደለም፡፡ ወደ አዳምና ወደ ሔዋንም ተመለሰ፡፡ የሚፈራ፣ የሚንቀጠቀጥ፣ እጁም በደም የተነከረ ነበር፡፡ በተመለከቱት ጊዜም አለቀሱ፤ አዘኑ፤ ፍርሀቱ፣ መንቀጥቀጡ በደም መነከሩ፣ በምን ምክንያት እንዳገኘው አላወቁም፤ ቃኤልም ከእርሱ ጋር መንታ ወደ ተወለደችቱ እኅቱ እየሮጠ ገባ፡፡ ባየችው ጊዜም ፈራች፡፡ ወንድሜ ሆይ! ይህ ዐይነት መንቀጥቀጥ /መፍራት/ በምን ምክንያት አገኘህ? አለችው፡፡ እርሱም ወንድሜ አቤልን በበረሀ ገደልሁት አላት፡፡ እኅቱ ይህን ነገር በሰማች ጊዜም አለቀሰች፡፡ እየጮኸችም ወደ አባቷና ወደ እናቷ ሄደች፡፡

ቃኤል ወንድሙ አቤልን እንደገደለው አስረዳቻቸው፡፡ ቃላቸውን /ድምፃቸውን/ ከፍ አድርገውም ጮኹ፤ ፊታቸውንም መቱ፤ በራሳቸውም ትቢያ ነሰነሱ፤ ልብሳቸውንም ቀደዱ፡፡ አቤል ወደ ተገደለበት ቦታ ይሄዱ ዘንድም ወጡ፡፡ ተገድሎ ከመሬት ላይም ተጥሎ አገኙት፡፡ አራዊትም ከበውት ነበር፡፡ ስለ እውነተኛው አቤል እያለቀሱ እየጮሁም ነበሩ፡፡ ሥጋውም ከንጽሕናው የተነሣ በጐ መዓዛን ይሸት ነበር፡፡

አዳምም ተመለከተው፤ አንባውም በፊቱ ይፈስ ነበር። ወደ ቤተ መዛግብት /ዕቃ ቤት/ ሄደ። በዚያችም አስቀመጠው። በአፈው /በሽቱ/ በከርቤም ገነዘው። አዳምና ሔዋንም በብዙ ኃዘን፣ ለቅሶ ፣በመገነዘም መቶ ቀን ያህል ቆዩ። አቤልም የዐሥራ አራት ዓመት ከመንፈቅ ልጅ ነበር። ቃኤልም የዐሥራ ሰባት ዓመት ከመንፈቅ ልጅ ነበር። ቃኤልም የወንዱምን ግንዘት ከፈጸመ በኋላ እኅቱ ሉልዋን ወደዳት፤ ያለ አባቱና ያለእናቱ ትእዛዝም ወስዶ አገባት። ስለ ልቡናው ከፋት እነርሱ እርሷን ሊያስተውት አልቻሉምና። ለገነት ወደ ምትቀርብ፣ ወንድሙንም ወደ ገደለበት ቦታ /ተራራ ግርጌ/ ወረደ። በታውም ብዙ ዕፀዋት፣ ብዙ ዛፎችም በውስጡ ነበሩ። ቃኤልም ከእኅቱ ልጅን ወለደ።

ልጆቹም ይባዙ ጀመሩ፤ አዳምና ሔዋን ግን አቤል ከተገነዘ /ከሞተ በኋላ ሁለት ዐሥር ዓመት እርስ በርሳቸው ሳይቀራረቡ /ሩካቤ ሥጋ ሳይፈጽሙ/ ኖሩ። ከዚህ በኋላ አዳም ሔዋንን በግብር ዐወቃት ፤ፀነሰችም። በፅንሷ ወራትም አዳም ነይ፤ ቊርባን እንውሰድ፤ ለእግዚአብሔርም እናሳርግ፤ የሚያጽናና መልካም ልጅን ይሰጠን ዘንድም እንለምነው፤ እኅቱንም እናጋባው አላት። ቊርባን አዘጋጁ። ወደ መሠውያም አኖሩት። በእግዚአብሔር ፊትም አቀረቡት።

ቊርባናቸውን ይቀበላቸው፣ ደግ ዘርን /ፍሬንም/ ይሰጣቸው ዘንድ ከእግዚአብሔር ይፈልጉ ጀመር። እግዚአብሔርም አዳምን ሰማው፣ ቊርባኑንም ተቀበለው። አዳምና ሔዋን፣ ልጃቸውም ከመሥዋዕቱ ተቀበሉ። ወደ ቤተ መዛግብት ወረዱ፤ በአቤል ሥጋ ፊትም ሌሊትም፣ ቀንም ይበራ ዘንድ ቀንዲል አደረጉ /አዘጋጁ/። አዳምና ሔዋንም በቤት ውስጥ ይጾሙ ይጸልዩ ነበር። የሔዋንም የፅንሷ ወራት ተፈጸመ። የመውለጃዋ ጊዜም ደረሰ። ሔዋንም አዳምን እወልድ ዘንድ ወደ ዐለቱ ለመሄድ እፈልጋለሁ አለችው።

አዳምም ከአንቺ ጋር ሴት ልጅሽን ትላላከሽ ዘንድ ይዘሽ ሂጂ። እኔ ግን

ከቤተ መዛግብት በልጇ በአቤል ሥጋ ፊት እቆማለሁ አላት፡፡ ሔዋንም ከአዳም ይህን ሰማች፤ እርሷም ሄደች፤ ሴት ልጇም እንዲሁ፤ አዳምም በቤተ መዛግብት ከልጁ ጋር ብቻውን ቀረ፡፡ ሔዋንም መልኩ ፍጹም ያማረ ልጅ ወለደች፡፡ ፊቱ፤ ደም ግባቱ እንደ አባቱ አዳም ያምር ነበር፡፡ ሔዋንም ባየችው ጊዜ ተጽናናች፡፡ በቤትም ስምንት ቀን ያህል ቆየች፤ ሴት ልጇንም ያየው፣ ስምም፣ ያወጣለት ዘንድ እስኪመለስ ድረስ ቆየች፡፡ እንደታዘዘችውም አደረገች፡፡

አዳምም በደረሰና ሕፃኑንም የተፈጥሮውን ደም ግባት በተመለከተው ጊዜ ተደሰተበት፣ ስለአቤልም ተጽናና፡፡ ሕፃኑንም "ሴት" ብሎ ጠራው፡፡ ትርጓሜውም እግዚአብሔር ልመናየን ሰማኝ፤ ከችግሬም አዳነኝ ማለት ነው፡፡ ሌላው ትርጓሜው ኀይለኛ፣ ጽኑዕ ማለት ነው፡፡[69] ከሰየመው በኋላ ወደ ቤተ መዛግብት ተመለሰ፡፡ ሴቲቱ ልጅም ወደ እናቷ ተመለሰች፡፡ ሔዋንም አርባውን ቀን እስከትጨርስ ድረስ በዚህ ቤት ተቀመጠች፤ ወደ አዳምም መጣች፡፡ ከሕፃኑ ከሴት ልጁም ጋር ተቀበላት፡፡

ወደ ውኃው ምንጭም ወጡ፤ አዳምና ሴት ልጁም በአቤል ስለነበራቸው ኀዘን ታጠቡ፡፡ ሔዋንና ሕፃኑም ስለመንጻት ታጠቡ፡፡ ተመልሰውም ቍርባንን ያዙ፤ ወደ ተራራውም ሄዱ፤ ስለ ሕፃኑም መሥዋዕቱን ዐሳረጉ፡፡ እግዚአብሔርም ቍርባናቸውን ተቀበላቸው፡፡ እነርሱንና ልጆቻቸውንም ባረከ፤ ወደ ቤተ መዛግብትም ተመለሱ፡፡

አዳም ግን በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ወደ ሚስቱ ወደ ሔዋን ይቀርብ ዘንድ አልተመለሰም፡፡ ሌላ ዘር ከእነርሱ ይወለድ ዘንድ ዳግመኛ አልተገናኙም፡፡ እኒህ ዘሮች የተወለዱትም ቃኤል፣ ሉልዋ፣ አቤል፣ አቅሌምያ፣ ሴት ብቻ ናቸው፡፡[70] ሴትም በቁመቱ ፈጽሞ አደገ፡፡ በጾም፣ በጸሎት፣ ቢታላቅ ድካም መመራት ጀመረ፡፡ አባታችን አዳምም ከሚስቱ ከሔዋን ከተለየ ሰባት ዓመት

[69] በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፬÷፳፭ ላይ "ቃኤል በገደለው በአቤል ፈንታ እግዚአብሔር ሌላ ዘር ተክቶልኛል ስትል ሴት አለችው" የሚለውን ልብ ይሏል፡፡

[70] ገድለ አዳም ዋና ዋናዎቹን ቁጥር ለአዳም አምስት ልጆች እንዳሉት ቢያስረዳም ከአምስት በላይ መሆናቸውን ቅዱሳት መጻሕፍት የሚመሰክሩት እና ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንም የሚያረጋግጡት እውነታ ነው፡፡ /ኩፋሌ ፭÷፲፩፣ ቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ ገጽ ፩፻፱ ተመልከት/

ሲሆነው ሰይጣን ከእርሱ ተለይቶ ባየው ጊዜ ቀናበት፡፡ ከእርሷ ጋር ይተኛ ዘንድም ይፈትነው ነበር፡፡ አዳምም ተነሥቶ ወደ ቤተ መዛግብት ወጣ፡፡ ሌሊት ሌሊት በእርሷ ውስጥ ይተኛ ነበር፡፡ በነጋ ጊዜም ዘወትር ወደ ቤት ይወርድ ነበር፤ ከእርሷም ይባረክ፣ ይጸልይ ነበር፡፡

ጨለማው ሲመጣም ወደ ማደሪያው ድንኳን ይወጣ ነበር፡፡ ለብቻውም ይተኛ ነበር፤ ሰይጣን ድል እንዳያደርገውም ይፈራ ነበር፡፡ ሠላሳ ዘጠኝ ቀንም እንዲህ ተለይቶ ቆየ፡፡ የመልካም ጠላት ሰይጣንም አዳም እንደተለየ፣ እርሱም እንደሚጾም፣ እንደሚጸልይ በተመለከተ ጊዜ በምትሐት ያማረች ሴት መስሎ ታየው፡፡ በአርባኛው ቀን ሌሊት መጥታም በፊቱ ቆመች፡፡ አዳም ሆይ! በዚህች ቤት ካደራችሁበት ጊዜ ጀምሮ ከእናንተ የተነሣ እኛን ታላቅ ዕረፍትን አግኝቶናል፡፡ ታላቅ ጸሎታችሁም ወደ እኛ ደርሳለች፡፡ ታረጋጋናለች /ታጽናናናለች/ ፤ ዛሬም አዳም ሆይ! ወደ ማደሪያው ድንኳን በወጣህ ጊዜ ትተኛ ዘንድ ከአንተ የተነሣ ተጠራጠርን፡፡ ከሔዋን በመለየትህ ምክንያትም ታላቅ ኃዘን ደረሰብን፡፡ ዳግመኛም ወደዚህች የማደሪያ ድንኳን በምትሆንበት ጊዜ ጸሎትህ ትፈስ ነበር፤ ልቡናህም ከደም ግባት የተነሣ ተቅበዘበዘች፡፡ በቤት ውስጥ በነበርህ ጊዜ ጸሎትህ የተሰበሰበች፣ ወደ እኛም የምትወርድ /የምትደርስ/ ዕረፍትም የሚገኝባት ናት፡፡

ዳግመኛም እኔ ከአንተ በተለዩ ልጆችህ አዘንሁ፡፡ ታላቁ ኃዘን ግን ስለልጅህ ስለአቤል ሞት ነው፡፡ እርሱ ጻድቅ ነበርና፡፡ ለጻድቅ ሰው ሁሉም እያንዳንዱ ይጸጸታልና፡፡ እኔ ስለልጅህ ስለሴት መወለድም ተደሰትሁ፡፡ ነገር ግን በሔዋን ምክንያት ትንሽ /ከባድ/ አዘንሁ፡፡ እኅቴ ናትና፤ እግዚአብሔር ከአንተ ላይ እንቅልፈን ባመጣ ጊዜ ከጐንህም በአወጣት ጊዜ ከእርሷ ጋር እኔንም አውጥቶኛልና፡፡ ከአንተም እርሷን ታላቅ አደረጋት፤ እኔን ወደታች አወረደኝ፡፡ በአንተ ዘንድ ስላለችዋ እኅቴም እኔ ደስተኛ ነኝ፤ እግዚአብሔርም ያጽናናኝ ነበር፡፡ አዳም ወደ ቤተ መዛግብት ድንኳን በወጣ ጊዜ አትዘኚ፤

ከሔዋንም በላይ እኔ /እንቺን/ ወደ እርሱ እልካለሁና እርሱም ያገባሻል፤ ሔዋን አምስት ልጅ እንደወለደች አንቺም ከእርሱ አምስት ልጅ ትወልጃለሽ አለኝ::

ቃል ኪዳኑም እነሆ! ዛሬ ተፈጸመልኝ:: ወደ አንተ የላከኝም እንጋባ ዘንድ ነው፤ አንተ እኔን በምታገባኝ ጊዜ ከሔዋን ልጆች ይልቅ ደም ግባቱ ያማረ ልጅን ትወልዳለህና:: ዳግመኛም አንተ እስከ ዛሬ ገና ጐልማሳ ነህ:: ቀሪ ዘመንህን በኃዘን አትጨርስ፤ መከራህም የበዛ አይሁን:: በዚህ ዓለም ዘመንህን በደስታ ትጨርሰው ዘንድ ጽና:: እኔም ብርሃን በሌለበት በዚህ ተግባር አደሰትብሃለሁ:: የአምላክህን ትእዛዝ ተነሥ ፈጽም እንጂ አለች:: ወደ አዳም ቀርባም አቀፈችው::

ከእርሷ የተነሣ ድል እንደሚነሣ ያወቀ አዳምም ከእርሷ ያድነው ዘንድ በተቃጠለ ልብ ወደ ፈጣሪው ጸለየ:: እግዚአብሔርም ቃሉን ወደ አዳም እንዲህ ሲል ላከ:: አዳም ሆይ! ይህች መልክ ስለ አምላክነት፣ በትዕቢት የማለልህ ናት:: አንተን ይቅር አትልም፤ አንድ ጊዜ በሴት መልክ፣ ሌላ ጊዜ በመልአክ አምሳል፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ በሽማግሌ አምሳል ትታይሃለች እንጂ:: ይህን ሁሉ የሚያደርገው ነፍስህን /ሰውነትህን/ ለማጥፋት ነው:: አዳም ሆይ! ዛሬም አስተውል:: ብዙ ጊዜ ከእጁ እንዳዳንሁህ፤ እኔ ይቅር ባይ አምላክ እንደሆንሁ እስካስረዳህ ድረስ፣ እኔ አንተን ይቅር እላለሁ፤ የአንተን መጥፋትም አልሻም አለው::

እግዚአብሔር ሰይጣንን ለአዳም በከፋ መልኩ በግልጽ ይታየው ዘንድ አዘዘው:: አዳምም በተመለከተው ጊዜ ፈራ፤ ተንቀጠቀጠ፤ እግዚአብሔርም አዳምን አለው፤ ፊቱ የከፋ ዲያብሎስን ተመልከተው፤ እስከ ዛሬ ድረስ ከብርሃናዊት ቦታህ ወደ ጨለማው፤ ከዕረፍት ወደ ድካም ያወረደህ እርሱ እንደሆነ ዕወቅ:: አዳም ሆይ! አስተውል:: እርሱ አምላክ እንደሆነ የሚናገር አምላክ ጨለማ ይሆናልን? አምላክ የሴት መልክ ይመስላልን? በሌላውስ ላይ ይበረታታልን? አምላክ ይሸነፋልን? አዳም ሆይ! አስተውል:: በፊትህ ያለ ይህ

ከፉ /ሰይጣን/ ወደ አየር /ሰማይ/ ይወጣ ዘንድ አይችልም፡፡ እኔም ከእርሱ የተነሣ አትፍራ! ከዛሬ ጀምሮ በአንተ ላይ የሚያደርገውን ሁሉ ዕወቅ፤ ልብም አድርግ እልሃለሁ፡፡

እግዚአብሔርም ሰይጣንን ከአዳም ፊት አስወገደው፤ እግዚአብሔርም አዳምን አበረታ ታው፤ ልቡንም አጽናናው፤ ወደ ቤተ መዛግብት ወረደ፡፡ ከሔዋንም አትለይ፤ እኔ ከአንተም ከእርሷም እንስሳዊት ፍትወትን /ምኞትን/ አጠፋለሁ አለው፡፡ ከዚያች ቀን ጀምሮ ፍትወት /ምኞት/ ከአዳምና ከሔዋን ተወገደች፡፡ በእግዚአብሔር ትእዛዝም ዐረፉ፡፡ ይህን ተግባር እግዚአብሔር ከአዳም ዘር ለአንዱ ስንኳን አላደረገም፡፡ ለአዳምና ሔዋን ብቻ ነው እንጂ፡፡

አዳምም ስላጸናቸው ፊቲውንም ስላጠፋላቸው በእግዚአብሔር ፊት ሰገደ፤ ከቤቱ ወርዶ መጀመሪያ እንደ ነበሩት ከሔዋን ጋር ተቀመጠ፡፡ አርባ ቀንም ተፈጸመለት፤

ልመናቸው፣ አማላጅነታቸው ከሊቃነ ጳጳሳቱ አለቃ ከባስልዮስ፣ ከንጉሣችን ኀይለ ሥላሴ፣ ከንግሥታችን ከወለተ ጊዮርጊስ፣ ከመንግሥቱ ወራሽ አምኃ ሥላሴ፣ ከሁላችንም ጋር ለዘለዓለሙ ጸንቶ ይኑር፤ አሜን፡፡

## ምዕራፍ ሰባት

## ገድለ አዳም ዘጥቅምት

አንድ አምላክ በሆኑ በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም ጥቅምት ስድስት ቀን የሚነበብ የአባታችን የአዳም፣ የእናታችን የሔዋን የተጋድሏቸው ዜና ይህ ነው፡፡ ጸሎታቸው፣ በረከታቸው ከሊቃነ ጳጳሳቱ አለቃ ከባስልዮስ፣ ከንጉሣችን ኀይለ ሥላሴ፣ ጋር ይሁን፡፡ ለዘለዓለም አሜን፡፡

ሴትም ሰባት ዓመት በሆነው ጊዜ መልካሙንና ከፉውን ዐወቀ፡፡ በጾምና በጸሎት ተወስኖ ይኖር ነበር፡፡ ከእግዚአብሔር ምሕረትን፣ ይቅርታን ያገኝ ዘንድ ስለፈለገም ሁል ጊዜ ለጸሎት ይቆም ነበር፡፡ ብዙ ጊዜም ከአባቱ

አዳም ጋር መሥዋዕት በማሳረግ ይደክም ነበር፡፡ እርሱ መልኩ ያማረ፣ ልቡም ገር፣ የነፍሱን /የሰውነቱን/ ባሕርይ የሚጠብቅ ነበርና፡፡ ስለሆነም ሁል ጊዜ መሥዋዕት ያሳርግ ነበር፡፡ እግዚአብሔርም በቍርባኑ ተደሰተ፤ በንጽሐናውም ተደሰተበት፡፡

ሰባቱ ዓመት እስኪፈጸም ድረስም አባቱና እናቱ በእግዚአብሔር ፈቃድ ነበሩ፡፡ ከመሠውያው ከወረደ ቍርባኑንም ካከናወነ በኋላ መልኩ ባማረ መልአክ አምሳል ሰይጣን ታየው፡፡ ብርሃንም በእርሱ ላይ ያብለጨልጭ ነበር፡፡ በእጁም የብርሃን በትር ይዞ ነበር፡፡ በብርሃን ዝናርም የታጠቀ ነበር፡፡

ሴትንም በጥሩ ሰላምታ እጅ ነሣው፡፡ በጣፋጭ አነጋገርም ይሸነግለው ጀመር፡፡ ሴትንም ከዚህ ተራራ ለምን ትቀመጣለህ? ይህ ተራራ ከባድ፣ በድንጋይ፣ በጠጠር፣ መልካም ፍሬ በሌለው ዛፍ የተመላ ነውና፡፡ ቤት የሌለው በረሃ ነው፤ ጥሩ መኖርያ ሀገርም፣ አይደለም፤ በረሃ /ፀሐያማ/፣ ድካም፣ ኃዘን ያለበት ነው እንጂ፡፡

እኛ በጥሩ ቦታዎች እንኖራለን፤ ከዚህ ዓለም የተለየ ሌላ ዓለም አለ፡፡ ያማረች ዓለም ናት፤ ሥርዐቶቻችንም ያማሩ ሥርዐቶች ናቸው፡፡ ከሚስቶቻችንም ከእነርሱ የሚያምር የለም፡፡ ሴት ሆይ! እኔ ከእነርሱ ላጋባህ እሻለሁ፡፡ አንተ መልካም እንደሆንህ አያለሁና፡፡ በዚህ ምድር ለአንተ የምትሆን ጥሩ ሴትም የለችም፤ በዚህች ዓለም የምትኖሩ ሁላችሁም አራት ናችሁ፤ እኛ ግን በዓለም ብዙ ነን፡፡ ደናግሎቻችም ብዙዎች ናቸው፡፡ አንዲቱ ከሌላኛይቱ ታምራለች፡፡ ዘመዶችን ታይ ዘንድ ልወስድህ እሻለሁ፡፡ የፈለግሃትን፣ የወደድሃትንም አጋባሃለሁ፡፡ በእኔ ዘንድም አኖርሃለሁ፤ አሳርፍሃለሁም፡፡ እንደ እኛም በፍጹም ብርሃን ትሞላለህ፡፡ እኛ በምንኖርበት ዓለምም ትቀራለህ፤ ከዚህ ዓለም ከድካሙም ታርፋለህ፤ ወደ ድካምም አትመለስም፡፡ ቁርባንን አታሳርግም፤ ምሕረትን አትሻም፤ ኀጢአትንም አታደርግም፤ እንስሳዊ ፈቲውን / ዝሙትንም፤ አትፈጽምም፡፡ እኔ የምልህን ብትሰማኝ ከልጆቼ አጋባሃለሁ፡፡

ይህም በእኛ ዘንድ ኀጢአት አይደለም፤ እንስሳዊ ፍትወትም አይደለም።

እኛ በምንኖርበት ዓለም አምላክ የለንም፤ ሁላችንም አማልክት ነን እንጂ። ሁላችንም ብርሃናውያን ነን፤ ሰማያውያን፣ ኀያላን፣ ጽኑዓን፣ ክቡራን ነን አለው። ሴት፡ ይህን ነገር በሰማ ጊዜ ተደነቀ። ልቡናውም ወደ ሽንገላ /የተንኮል/ አነጋገሩ አዘነበለ። ሴትም ሰይጣንን አለው፥ ሌላ ዓለም ተፈጠረ ትላለህን? ከዚህ ፍጥረት፣ ከዚህ ዓለም የሚያምር ሌላ ፍጥረት አለን? አለው፤ አዎ! እነሆ! ስለ እነርሱ ለአንተ የነገርሁህን ሁሉ ሰማህ አለው።

ሴትም አነጋገርህ ያማረ ነው፤ ማጽናናትህም አስደነቀኝ። ነገር ግን ወደ አባቴ ወደ አዳም፣ ወደ እናቴ ወደ ሔዋን እስከምሔድ ድረስ ዛሬ ከአንተ ጋር መምጣት አልችልም፤ ያልኸኝን ሁሉ እነግራቸዋለሁ፤ ከአንተ ጋር እሄድ ዘንድ ከፈቀዱልኝ እመጣለሁ። ዳግመኛም ያለ አባቴና እናቴ ፈቃድ ይህን አደርግ ዘንድ እፈራለሁ አለው። እንደ ወንድሜ እንደ ቃኤልም እጠፋለሁ፤ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እንደተደፋፈረ እንደ አዳምም እጠፋለሁ፤ አንተ ግን ቦታውን እነሆ! ዐወቅኸው፤ ነገ መጥተህ ጐብኘኝ አለው።

ሰይጣንም ይህን ነገር በሰማ ጊዜ ሴትን አንተ የነገርሁህን ለአባትህ አዳም ካሳወቅኸው ከእኔ ጋር ትመጣ ዘንድ አይፈቅድልህም፤ ነገር ግን እኔን ስማኝ፤ ከእኔ ጋርም ሂድ፤ ይህን ነገርም አትንገራቸው። ይህም ባይሆን አንተ በእኔ ዘንድ ክቡር ነህ፤ ይህን ያልሁህን ነገር ባትፈጽምም ነገር ግን ወደ እኛዋ ዓለም ከእኔ ጋር እንሂድ፤ ማማሯንም ተመልከታት፤ በውስጧም ደስ ይበልህ፤ ዛሬም በልጆቼ ዘንድ ተሸለም፤ እያቸውም፤ ፈቃድህንም ፈጽም፤ ደስም ይበልህ፤ በነጋው እኔ ወደዚህች ቦታ እመልስሃለሁ፤ መኖር ከፈለግህም ከእኔ ጋር ትኖራለህ አለው።

ሴትም የአባቴ መንፈስ በእኔ አድሯል። አንድ ቀን ከእነርሱ ከተለየሁ ይሞታሉ፤ በዚህም እግዚአብሔር ይወቅሰኛል። ወደዚህች ቦታ እንደምመጣ፣ ቍርባንም እንደማሳርግ የሚያውቁ ካልሆነ አንድ ሰዓት ስንኳ ከእኔ አይለዩም።

ወደ ሌላ ቦታ እንድሄድም አይፈቅዱልኝም፡፡ እኔ በፍጥነት ወደ እነርሱ በመመለሴ ልቡናቸው በእኔ ይደሰታል አለው፡፡

ሰይጣንም አንድ ቀን ከእነርሱ ብትሰወር በአንተ ላይ ምን ይደርሳል? አንተ ወደ እነርሱ ትመለሳለህ አለው፡፡ ሴትም በእርሱ ላይ የበዛ ነገሩን ባስተዋለና፤ እርሱም እንዳልተወው ባየ ጊዜ ሩጦ ወደ መሠውያው ወጣ፡፡ ከእርሱ መድኀኒትን /ድኅነትን/ ፈልጐ እጁን ወደ እግዚአብሔር ዘረጋ፤ እግዚአብሔርም ቃሉን ላከ፡፡ ሰይጣንንም ረገመው፤ ከእርሱም ሸሸ፤ ሴት ወደ መሠው ያው መውጣቱም በልቡናው እንዲህ ስላሰበ ነው፡፡ መሠውያው የቍርባን ማሳረጊያ ቦታ ነው፡፡ እግዚአብሔርም በውስጡ አለበት፡፡ መለኮታዊት እሳትም ትከበዋለች፤ ሰይጣንም ሊከፋብኝ /ድል ሊነሣኝ/ ከዚህም ሊወስደኝ አይችልም በማለት ነው፡፡

ሴትም ከመሠውያው ወርዶ ወደ እናቱና ወደ አባቱ ሄደ፡፡ ነገሩን ይሰሙ ዘንድ ሲፈልጉም በመንገድ አገኛቸው፡፡ እነርሱ ይጠባበቁት ነበር፡፡ መልአክ መስሎ ከታየው ከሰይጣን የደረሰበትን ሁሉ ይነግራቸው ጀመር፡፡ አዳምም ይህን ነገር በሰማ ጊዜ እጅ ነሣው፡፡ ለእርሱም የታየው ሰይጣን እንደሆነ አሳወቀው፤ አስገነዘበውም፡፡ ይዘውትም ወደ ቤተ መዛግብት / ወደሚኖሩበት/ ሄዱ፡፡ እነርሱም በእርሱ ደስተኞች ነበሩ፡፡ ከዚህች ቀን ጀምሮ በሚሔድበት ቦታ፣ በቍርባኑ ማሳረጊያም ቢሆን ከእርሱ አይለዩም ነበር፡፡ ይህችም ለሴት ምልክት ሆነችው፡፡ እርሱም የሰባት ዓመት ልጅ ነበር፤ አባታችን አዳምም ልቡ ፍጹም የሆነ፤ ሴትን በተመለከተው ጊዜ ያጋባው ዘንድ ወደደ፡፡

ዳግመኛም ፀላኢ /ሰይጣን/ እንዳይታየው ድልም እንዳይነሣው /አሰበ/፡፡ አዳምም ልጁ ሴትን ልጄ ሆይ! የአቤልን እኅት ልያን ታገባ ዘንድ እፈልጋለሁ፤ ከእርሷ ዘርን ታገኝ ዘንድ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን እንደገባ ምድርን ትሞላ ዘንድ፤ ልጄ ሆይ! ይህ ጥፋት /በደል/ አይደለምና አትፍራ፡፡ እኔ ፀላኢ /ሰይጣን/ ድል እንዳይነሣህ ከመፍራቴ የተነሣ አጋባሃለሁ አለው፡፡ ሴት ግን ሊያገባ

የሚወድ አልነበረም፤ ነገር ግን አባትና እናቱን ስለሚሰማ /ስለሚታዘዝ/ አይሆንም አላላቸውም።

አዳምም ለሴት ልያን አጋባው። እርሱም የዐሥራ አራት ዓመት ልጅ ነበር። ሃያ ዓመት በሆነው ጊዜ ልጅ ወለደ። ልጁንም "ሔኖስ" አለው። ዳግመኛም ሌሎችን ልጆች ወለደ። ሄኖስም አደገ፤ አጋባውም፤ ቃይናንንም ወለደ፤ ቃይናንም አደገ፤ አጋባውም፤ መላልኤልንም ወለደ እነዚህ አባቶች /አበው/ አዳም በሕይወተ ሥጋ እያለ ተወለዱ። እነርሱም በቤተ መዛግብት ነበሩ። አዳምም ዕድሜው ሰባት መቶ ሃምሳ ሆነ።

ለመላልኤልም መቶ ሠላሳ ዓመት ሆነው። መላልኤል ባደገ ጊዜም ጾምን፤ ጸሎትን፤ ተጋድሎን ወደደ። የአባታችን አዳም የዘመኑ ፍጻሜ እስኪቀርብ ድረስ። ይኸውም ዘጠኝ መቶ ሠላሳ ዓመት ነው።[71] አባታችን አዳምም የዘመኑ ፍጻሜ እንደ ተቃረበ በተመለከተ ጊዜ ልጁ ሴትን ጠራው። ከቤተመዛግብት /ዕቃ ቤት/ ወደ እርሱ ቀረበ። ልጄ ሴት ሆይ! ልጆችህን ሳልሞት እባርካቸው ዘንድ ወደ እኔ አቅርብ አለው። ሴትም ይህን ቃል ከአዳም በሰማ ጊዜ ከእርሱ ወጣ። እንባዎቹም በጉንጮቹ ፈሰሱ፤ ልጆቹንና የልጅ ልጆቹን ሰበሰበ፤ ወደ አባቱ ወደ አዳምም አመጣቸው።

አባታችን አዳምም ሲዞሩ ባያቸው ጊዜ ከእነርሱ በመለየቱ አለቀሰ፤ ሲያለቅስ በተመለከቱት ጊዜም ሁላቸውም አለቀሱ። አባታችን አዳም ሆይ! ከእኛ ትለይ ዘንድ እንዴት ይሆናል? እያሉም በፊቱ ወደቁ። መሬትስ እንዴት ትውጥሃለች? ከዐይናችንስ እንዴት ትሰወራለህ? /ትታጣለህ/ እነርሱም ይህንን የመሰለውን ቃል አበዙ።

አባታችን አዳምም ሁሉንም ባረከ፤ ሴትንም ከባረከው በኋላ ልጄ ሴት ሆይ! አንተ በኃዘን፣ በድካም የተመላ ይህን ዓለም፣ በዓለም የደረሰብንን መከራም ታውቃለህ። እኔ ንጹሕናህን የምትጠብቅ ትሆን ዘንድ አዝዝሃለሁ። ለእግዚአብሔር ታማኝ፣ ንጽሕና ጻድቅ ትሆን ዘንድ ለሰይጣን አትገዛ፤



[71] ዘፍ.፭፥፭

ለሚያሳይህ ምትሐትም እንዳትንበረከክ፡፡ ዛሬ የማዝዝህን ትእዛዜን ጠብቅ፤

ልጅህ ሄኖስንም እንዲህ እዘዘው፡፡ ሄኖስም ልጁ ቃይናንን ይህን ትእዛዝ ይዘዘው፣ ቃይናንም ልጁ መላልኤልን ይህን ትእዛዝ ይዘዘው፣ ይህ ትእዛዝም በልጆቻችሁ ሁሉ የጸና ይሁን፡፡ ልጄ ሴት ሆይ በምሞትበት ቀን ሥጋዬን ወስዳችሁ ከርቤ፣ ሰሊክ፣ ሜዓ[72] በሚባሉ ሽቶዎች ገንዙት፡፡ እንደዚህ አድርጋችሁም ከገነት እግዚአብሔር የሰጣቸው ምልክቶች ባሉበት በቤተ መዛግብት ተውኝ፡፡ ልጄ ሆይ! በኋለኛው ዘመን ጥፋት ይመጣል፤ ፍጥረትን ሁሉ ያሰጥመዋል፡፡ ከስምንት ሰው በቀር አይተርፍም (አይቀርም)፡፡ ልጄ ሆይ! ከልጆቻችሁ የሚቀሩት እነሀ በዚህ ዘመን ከዚህ ቤት ሥጋዬን ከእነርሱ ጋር ይወስዱታል፡፡

ከእነርሱ ጋር በወሰዱት ጊዜም ከእነርሱ ወገን የሆነ ሽማግሌ ልጆቹን ያዝዛቸዋል፡፡ ከጥፋት ውኃ ከዳኑ በኋላ ሥጋዬን በመሬት ውስጥ ያስቀምጡ ዘንድ፡፡ ሥጋዬ የሚቀመጥበት ቦታ የምድር መካከል ነውና፡፡[73] እግዚአብሔርም ከዚህ ይመጣል፡ ወገኖቻችንንም ሁሉ ያድናል፡፡ ልጄ ሴት ሆይ! ዛሬም ለሕዝቦችህ የቆምህ ሁን፡ እግዚአብሔርን በመፍራትም ጠብቃቸው፡ ወደ ጥሩው መንገድ ምራቸው፣ ለእግዚአብሔር ይደክሙ ዘንድ እዘዛቸው፡ ሰይጣንን እንዳይሰሙት፡ እንዳያጠፋቸውም አስረዳቸው፡፡

ዳግመኛም ልጆችህን፣ የልጅ ልጆችህን ከቃኤል ልጆች ጋር ይቀላቀሉ ዘንድም ፈጽመህ አትተዋቸው፡፡ በሥራም፡ በነገርም አይቅረቧቸው፡፡ አዳምም ሴትን፡ ልጆቹን፣ የልጅ ልጆቹን ሁሉ ባረከ፡፡ አዳምም ወደ ልጁ ወደ ሴት፡ ወደ ሚስቱ ሔዋንም ተመለሰ፡፡ እግዚአብሔር ለእኛ ለምልክት የሰጠን ይህን ወርቅ፣ ዕጣን፣ ከርቤ ጠብቁት አላቸው፡፡ ጥፋት በሚመጣበት ዘመን ፍጥረቱን ሁሉ ያጠፋልና /ያሰጥማልና/፡፡ ወደ መርከቡ የሚገቡትም ከእነርሱ ጋር ወርቁን፡ ዕጣኑን ከርቤውን፡ ሥጋዬንም ይውሰዱ፡፡ ወርቅ፣ ዕጣን ከርቤ ግን ከሥጋዬ /ከበድኔ/ ጋር ወደ መሬት ይመለሳሉ /ይቀበራሉ/፡፡

72 በዘመኑ የነበሩ የሽቶ ዓይነቶች ናቸው፡፡

73 መዝ.፸፫+፲፫

ከረዥም ዘመን በኋላ ከሥጋዬ ጋር ወርቁ፣ ከርቤው፣ ዕጣኑ በውስጧ ያለባት ሀገር ትማረካለች፡ ሀገሯ ስትማረክም ወርቁ፣ ዕጣኑ ከርቤው ከምርኮኛው፡ ጋር ይማረካል፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ክርስቶስ እስኪመጣ ድረስም አይጠፉም፤ ይጠበቃል እንጂ፡፡ ሰው በሆነ ጊዜ ነገሥታት ወስደው እጅ መንሻ ያቀርቡለታል፡፡

ወርቁ የሰማይና የምድር አምላክ የመሆኑ ምልከት ነው፡፡ ከርቤውም የመከራ ምልከት ነው፡፡ ዳግመኛም ወርቅ የሰይጣንን፣ የአጋንንትንም ሁሉ ፈተና ድል መንሻ ምልከት ነው፡፡ ዕጣኑም እርሱ /ክርስቶስ/ ከሙታን ተለይቶ የመነሣቱ ምልከት ነው፡፡ እርሱም በሰማያውያንና በምድራውያን ዘንድ ልዑል /ታላቅ/ ነውና፡፡ ዳግመኛም ከርቤ እርሱ /ክርስቶስ/ ከሰይጣን መራራ መከራን፣ ሞትን የመቀበሉ ምልከት ነው፡፡ ልጄ ሴት ሆይ! ዛሬም ለእኔ የገለጣቸውን ስውር የሆኑ ምሥጢራትን እነሆ! ለአንተ ገለጥሁልህ፡፡ ትእዛዜ ለአንተም ለሕዝቦችህም ጠባቂ ይሆን ዘንድ አለው፡፡

አዳም ሴትን አዝዞ ከፈጸመ በኋላ መለያያው ተፈታ፡፡ እጁ፣ እግሩም ዛለ፣ አፉም ዲዳ ሆነ፤ አንደበቱም ፈጽሞ አልተናገረም፡፡ ዐይኖቹንም ከደነ፣ ነፍሱንም ሰጠ፡፡ በመጨረሻም ልጆቹ እርሱ እንደሞተ አስተዋሉ፡፡ ሰውነታቸውንም በእርሱ ላይ ጣሉ፤ ወንዶችም፣ ሴቶችም፣ ታላቆችም፣ ታናሾችም ያለቅሱ ነበር፡፡

የአዳም ሞትም ዘጠኝ መቶ ሠላሳ ዘመን በዚህ ምድር ከኖረ በኋላ ነው፡፡ በፀሐይ አቆጣጠር ሚያዚያ ዐሥራ አራት ቀን፣ ዐርብ ቀን በዘጠኝ ሰዓት ሞተ፡፡ ይኸውም ዕለት የተፈጠረበት ቀን ነው፡፡ በዚሁም ዐረፈ፡፡ የሞተባት ሰዓትም ከገነት የወጣባት ሰዓት ናት፡፡ ሴትም በጥሩ ሁኔታ ገነዘው፡፡ ከደብር ቅዱስ በሚገኙ በብዙ ዕፀዋት ሽታም አጠነው፡፡ ሥጋውንም ከቤቱ በስተምሥራቅ በኩል አስቀመጠው /ቀበረው/፡፡ ልጆቹም እስኪነጋ ድረስ ሌሊቱን ሁሉ እያለቀሱ በፊቱ ቆሙ፤ በፊቱም የሚያበራ መቅረዝ አደረጉ፡፡ ሴት

እና የሄኖስ ልጅ ቃይናን ወጡ። ወደ እግዚአብሔር ያቀርቡ ዘንድም ጥሩ የሆነ ቊርባንን ወሰዱ። ይሠው ዘንድም አዳም ለእግዚአብሔር ያቀርብበት ወደ ነበረው መሠውያ ወጡ። ሔዋንም መጀመሪያ ቊርባናችንን ይቀበል ዘንድ እግዚአብሔርን እስከምንለምነው ድረስ ታገሡ አለቻቸው።

የባሪያው የአዳምንም ነፍስ ይጠብቅ፣ ወደ ዕረፍትም ያሳርጋት፤ ዘንድ ሁላቸውም ቆመው ጸለዩ፤ጸሎታቸውን በጨረሱ ጊዜም የእግዚአብሔር ቃል መጣ። ስለ አባታቸው አዳምም አጽናናቸው፤መላእክትም ወደ እነርሱ ወረዱ አጽናኗቸውም። ከዚህ በኋላ ስለ እነርሱና ስለ አባታቸው አዳም መሥዋዕታቸውን ወደ እግዚአብሔር አቀረቡ፡ ቊርባኑን ከፈጸሙ በኋላም የእግዚአብሔር ቃል ከእነርሱ ወደ ታላቁ ሰው ወደ ሴት እንዲህ ሲል መጣ። ከአባትህ ጋር እንደነበርሁ እንዲሁም ከአንተ ጋር ነኝ፤ ለአባትህ የገባሁለት ቃል እስኪፈጸም ድረስ ቃሌን እልካለሁ። አንተንም፣ ዘርህንም አድናለሁ፤ የአባትህን የአዳምን ትእዛዝ ግን ጠብቅ። ዘርህንም ከወንድምህ ከቃኤል ዘር ጠብቅ አለው። እግዚአብሔርም መነጋገሩን አቆመ።

ሴት፣ ሔዋን፣ ልጆቹም ከደብር /ከተራራ/ ወደ ቤተ መዛግብት ወረዱ። አዳም በመጀመሪያ በኤደን ምድር በቤተ መዛግብት ነፍሱ ከሥጋው የሞተችበት ነበር። በመሞትም አንድ ስንኳን አልቀደመውም፤ በበቀል የሞተ ልጁ አቤል ነው እንጂ። የአዳም ልጆችም ስለ አባታቸው አዳም ያለቅሱ ዘንድ፣ መቶ አርባ ቀን ቊርባንንም ያቀርቡ ዘንድ ቆሙ።

አዳም ከሞተ በኋላም ሴት ከቃኤል ልጆች የእርሱን ልጅ ፣የልጅ ልጆቹን ለየ። ቃኤልና ዘሩም አቤልን በገደለበት በስተምዕራብ ጫፍ ወረዱ። ሴትና ልጆቹ ግን በቤተ መዛግብት በሚገኘው ተራራ ደቡባዊ ክፍል ተቀመጡ። ለአባታቸው የቀረቡ ይሆኑ ዘንድ። ሴትም ሽማግሌ፣ ታላቅ፣ የሰውነቱ ደም ግባት ያማረ፣ በአስተሳሰቡም የጸና ነበረና። በንጽሕና፣ በንስሓ፣ በገርነት ጠበቃቸው። ከእነርሱ /ከልጆቹ/ አንዱ ስንኳን ወደ ቃኤል ልጆች

ይወርድ ዘንድ አልፈቀደም፤ ስለ ንጽሕናቸው ስለወደቁት ሰራዊተ መላእከት ፈንታ የእግዚአብሔር ልጆቹ ተባሉ።

እነርሱ በቤታቸው ፈጽመው እግዚአብሔርን ያመሰግኑት ነበርና፤ ይህችም /ቤታቸውም/ ቤተ መዛግብት ናት። ሴትም በአባቱ በአዳም ሥጋ ፊት ቆመ። ምሕረት ለእርሱ፣ ለልጆቹም ፈልጎ ሌሊትም ቀንም ይጸልይ ዘንድ ቆመ። ልጆቹ ሲመካከሩበት በሰማ ጊዜ ሴትና ልጆቹም ምድራዊውን ሥራ የማይወዱ ነበሩ። ስለ ሰማያዊው ይደክሙ ነበር እንጂ። ዐሳብም ድርጊትም አልነበራቸውም። ምስጋናን ክብርን፣ ዝማሬን ለእግዚአብሔር ያቀርቡ ነበር እንጂ።

- *በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስንክሳር መሠረት የአባታችን የአዳም መታሰቢያ /ክብረ በዓል/ ሚያዝያ ሲድስት ቀን መሆኑ ይታወቃል። በዚህ ዕለት የመታሰቡ ምክንያትም ዕለተ ሞቱ በዚህ ቀን በመሆኑ ነው። ገድለ አዳም ደግሞ በየወሮቹ መግቢያ በስድስት፣ በስድስት ቀን እንደሚታሰብ ከገለጠ በኋላ ዕለተ ዕረፍቱ ሚያዝያ /፲፬/ ቀን መሆኑን ያስረዳል። ይኸ የሰምንት /፰/ ቀናት ልዩነት ሊመጣ የቻለው ገድሉ ዕለተ ዕረፍቱን በጎርጎርዮሳውያን ዘመን አቆጣጠር በመግለጡ ነው። በአማካይ በጎርጎርዮሳውያን የዘመን አቆጣጠር እና በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር መካከል ከፈረንጆቹ አዲስ ዓመት እስከ ነሐሴ ወር ድረስ የሰምንት /፰/ ቀናት ልዩነት መኖሩን ልብ ይሏል። በተለይም ዘመኑ ዘመነ ማርቆስ በሚሆንበት ዓመት ሚያዝያ ወር ላይ ከጎርጎርዮሳውያን ጋር ያለን የቁጥር ልዩነት ስምንት /፰/ ቀን ብቻ ነው። አዳም ያረፈው ደግሞ በዘመነ ማርቆስ ሚያዝያ ወር ነው። ይህም ዘጠኝ መቶ ሠላሳውን*

*የአዳም ዕድሜ ለአራቱ ወንጌላውያን ስናካፍላቸው ሁለት መቶ ሠላሳ ሁለት ደርሶ ሁለት ይቀራል። ቀሪው ቁጥር የሚያመለክተውም አዳም ያረፈው በዘመነ ማርቆስ መሆኑን ነው። ስለዚህ ገድሉ አዳም ሚያዝያ /፲፩/ ቀን ዕለተ ዕረፍቱ ነው ማለቱ ከሚያዝያ ስድስት ጋር ምንም ዐይነት የእውነት / facl/ ተቃርኖ የለበትም።*

ስለዚህም እነርሱ ሁል ጊዜ የመላእክትን ቃላት ይሰሙ ነበር። እነርሱም በገነት መንገድ ያመሰግኑ፣ ያከብሩም ነበር። ለተልእኮ ሲላኩ፣ ወደ ሰማይም ሲወጡ ከሴት፣ ከልጆቹ ንጽሕና የተነሣ ይሰሟቸው፣ ያስተውሏቸውም ነበር። ዳግመኛም ገነት ከእነርሱ ሩቅ አልነበረችም። በመንፈሳዊ /በመልአክ/ ክንድ ዐሥራ ዐምስት ክንድ ነው። ይህም ማለት አንዱ ክንድ በሰው ሦስት ክንድ ነው። ይህም አርባ አምስት ክንድ ይሆናል። ሴትና ልጆቹም በተራራው ላይና በተራራው ታች ይኖሩ ነበር። አይዘሩም፤ አይለቅሙም። ሥጋዊ ምግብም ስንዴም አያዘጋጁም። ቊርባን ብቻ ነው እንጂ።

ከማደርያቸው ተራራም ከሚጣፍጡ ዕፀዋት ፍሬ ይመገቡ ነበር። ሴትም በየአርባ ቀኑ ብዙ ጊዜ ይጾም ነበር። አረጋውያን ልጆቹም እንዲሁ ነበሩ። የሴት ዘሮች ነፋስ በነፈሰ ጊዜ የገነትን ዕፅ ሽታ /መዓዛ/ ያሸቱ ነበር። ከድንጋጤ የተለዩ፣ ቅንዓት የሌላቸው ብፁዓን ፣ንጹሐን ነበሩ። ክፋት፣ እርስ በርስ መጣላት፣ እንስሳዊት ጾር፣ ዝሙት የለባቸውም፤ ከአንደበታቸውም በደል፣ እርስ በእርስ መረጋገም፣ ክፉ ምክር፣ እንደ ዓለሙ ሰው መሸንገል፣ መሐላ ፈጽሞ የለም። በከበዳቸው ጊዜም በጻድቁ በአቤል ደም ይምሉ ነበር።

በልጆቻቸው፣ በሚስቶቻቸው ላይ ሁል ጊዜም በማደሪያቸው ለልዑል እግዚአብብሔር ጾም፣ ጸሎት፣ ስግደት በማቅረብ ድንቆች ነበሩ። በአባታቸው በአዳም በድንም ይባረኩ፤ያሻሹት ነበር። እስከ ሴት ዕድሜ ፍጻሜ ድረስ

እንዲህ ያደርጉ ነበር። ጻድቅ ሴትም ልጆቹ ሄኖስን፣ ቃይናንን፣ የሄኖስን ልጅ የቃይናንን ልጆች ጠራቸው። የዘመኑ ፍጻሜ ደርሷል።

ቊርባን በማደርግበት በመሠውያው ላይ ድንኳን ልሠራ እወዳለሁ። ትእዛዙንም ሰሙ፣ ታናናሾችም፣ ታላላቆችም ሁሉም ወጡ፤ በዚህም ደከሙ። በመሠውያው ላይ ያማረች ድንኳንን ሠሩ።

የሴት ዐሳብም ከተራራው በልጆቹ ላይ በረከት ይሆን ዘንድ ነው። ከመሞቱ በፊት ስለ እነርሱ መሥዋዕት ያሳርግ ነበር። የድንኳን ሥራ በተከናወነ ጊዜ በደከሙበት በዚህ ቦታ ቊርባን ያቀርቡበት ዘንድ አዘዛቸው። ወደ አባታቸውም አመጣቸው። ሴትም ይዞ ወደ ተራራው አወጣቸው። ቊርባኖቻቸውን ይቀበላቸው፣ የልጆችን ነፍስ ይቅር ይል ዘንድ፣ ከሰይጣን እጅ /ፈተና/ ይጠብቃቸው ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፣ እግዚአብሔርም ቊርባኑን ተቀበለ፤ ልጆቹንና እርሱንም ባረከ።

እግዚአብሔር ለሴት እንዲህ ሲል ቃል ኪዳን ገባለት። ለአባትህ የገባሁለት የቃል ኪዳን ዘመን ዐምስት ቀን ተኩል ሲፈጸም ቃሌን እልካለሁ፡ አንተንም ዘርህንም አድንሃለሁ። ሴት መሥዋዕቱን ተቀበለ፤ ልጆቹም እንዲሁ ከመሠውያው ወረዱ፤ ወደ ቤተመዛግብት ወጡ፤ በውስጧም ጸለዩ። ከአባታችን ከአዳም ሥጋም ተባረኩ፤ ተሻሹበትም።

ሴትም ትንሽ ቀኖችን በቤት ውስጥ ተቀመጠ፤ ታመመ፤ ሕመሙም ለሞት ነበር። የበኩር ልጁ ሄኖስ፣ የሄኖስ ልጅ ቃይናን፣ የቃይናን ልጅ መላልኤልም ወደ እርሱ መጡ። የመላልኤል ልጅ ያሬድ፣ የያሬድ ልጅ ሄኖክ፣ ሚስቶቻቸው፣ ልጆቻቸውም ከሴት ይባረኩ ዘንድ ወደ እርሱ መጡ። ሴትም በእነርሱ ላይ ጸለየ፤ ባረካቸው፤ በጻድቁ በአቤል ደምም እንዲህ ሲል አማላቸው፤ ልጆቼ ሆይ! እኔ እለምናችኋለሁ። ከዚህ ከተቀደሰና ንጹሕ ተራራ /ደብር ቅዱስ/ ከእናንተ አንዱ ስንኳ ይወርድ ዘንድ አትተውት። ወንድሙን ከገደለው ከኀጢአተኛው ቃኤል ልጆች ጋር እንዳትቀላቀሉ። ልጆቼ ሆይ!

ከእነርሱና ከኀጢአት ሁሉ እንደምንሸሽ፡ እናንተ ታውቃላችሁ፡፡

ወንድሙ አቤልን ስለመግደሉ በሚቻለን ሁሉ ከእርሱ እንሸሽ፡፡ በዚህ ነገርም ሴት የበኵር ልጁ ሄኖስን ባረከው፡፡ ዘመኑን በሙሉ ንጹሕ ሆኖ በአባታችን በአዳም ሥጋ /በድን/ ፊት ያገለግል ዘንድ አዘዘው፡፡ ዳግመኛም ሴት ወደ ሠራው መሠውያ ይመለስ ዘንድ የሕይወት ዘመኑን ሁሉ፣ በእውነት፣ በፍርድ እና በንጽሕና ሕዝቡን ይጠብቅ ዘንድም አዘዘው፡፡

ሴትም መለያያው ተፈታ፤ እጁና እግሩም ዛለ፡፡ አፉም ከመናገር ዲዳ ሆነ፤ ነፍሱንም ሰጠ፤ በዘጠኝ መቶ ዐሥራ ሁለት ዓመቱ[74]፣ ኅዳር ሃያ ሰባት ሰኞ ቀን ዐረፈ፡፡ ለሄኖስም ሃያ ዓመት ሆነው፡፡ ሴትንም በመልካም አገናነዝ ገነዙት፤ ሽቱንም ቀቡት፤ሥጋውንም ከአዳም ጐን በቀኝ በኩል በቤተ መዛግብት አስቀመጡት፤ አርባ ቀንም አለቀሱለት፣ እንደ አባታቸው አዳምም ስለ እርሱ /ስለ ሴት/ ቍርባንን ዐሳረጉ፡፡ ሴት ከሞተ በኋላም ሄኖስ ለሕዝቡ ቆመላቸው፤ አባቱ እንዳዘዘውም በእውነተኛ ፍርድ ጠበቃቸው፡፡

ለሄኖስ ስምንት መቶ ኻያ ዓመት በሆነው ጊዜ የቃኤል ዘሮች ብዙ ሆኑለት፡፡ እነርሱ ብዙ ያገቡ ነበርና እንስሳዊት ፍትወትን ይወዱ ነበርና ከገነት ተራራ በታች የምትገኝ ምድር እስከትሞላ ድረስ፡፡ በዚህ ዘመንም ከቃኤል ልጆች ወገን የሚሆን ዕውሩ ላሜህ ነበር፡፡ ብዙ እንስሳትም ነበሩት፡፡ ከሚጠብቃቸው ትንሽ እረኛ ጋር ይልካቸው ነበር፡፡

ትንሹ እረኛ ምሽት ሲሆን በመጣ ጊዜም በአያቱ በላሜህ ፟እናቱና ከአባቱ ጋር ያለቅስ ነበር፡፡ እነዚህን እንስሳት የእንስሳት ሌቦች እንዳይወስዱ እጠብቅ ዘንድ አልችልም፡፡ እኔን ስለ እነርሱ ወይም ስለ እንስሳቱ ይገድሉኛል፡፡ በቃኤል ልጆች ውስጥ መስረቅ፣ መግደል፣ ኀጢአት መሥራት በዝቷልና፡፡ ላሜህም በእርሱ ላይ ልቡናው ራራ፡፡ እውነት ነው፤ እርሱ ለብቻው በእነርሱ ይሸነፋል አለ፡፡ ላሜህም ተነሣ፡፡ ከመታወሩ በፊት የነበረውን ወንጭፉንም ከሕፃኑ ወሰደ፡፡ ታላላቅ ገብሶችን፣ የተለመዱ መጠምጠሚያዎችን ለእርሱ

---

74 ዘፍ.፭+፰

የነበረ መገለጫውን /ምርኩዙን/ ያዘ:: ከትንሹ እረኛ ጋርም ወደ በረሃ ይሔድ ነበር፤በከብቶች ኋላም ተቀመጠ::

ትንሹ እረኛ እንስሳቱን ይጠብቅ ነበር:: ላሜህም ብዙውን ጊዜ እንዲህ ያደርግ ነበር:: ቃኤልም እግዚአብሔር ከተጸየፈውና ከረገመው ጊዜ ጀምሮ በመፍራት፣ በመንቀጥቀጥ ይኖር ነበር::[75] በቦታውም በመረጋጋት አይኖርም ነበር፤ ከቦታ ወደ ቦታ ይቅበዘበዝ ነበር እንጂ:: ቃኤልም ወደ ላሜህ ሴቶች ደርሶ ጠየቃቸው፤ እነርሱም ከእንስሳት ጋር በበረሃ እንደሆነ ነገሩት:: ቃኤልም ላሜህን ይፈልገው ዘንድ መጣ:: ከበረሃውም ደረሰ፤ ትንሹ እረኛም ሲንቀሳቀስ ድምፁን ሰማው፤ ላሜህንም ይህ አውሬ ነው? ወይስ ሌባ አለው::

ላሜህም በወጣ ጊዜ አቅጣጫውን አመልክተኝ አለው:: ላሜህም ወንጭፉን ዘረጋ፤ ቀስቱንም አዘጋጀ፤ አቅጣጫውንም ለወጠ:: ቃኤል ከበረሃ በወጣ ጊዜ እረኛው ላሜህን እነሆ! ወጥቷልና ውጋ /ወርውር/ አለው:: በጦርም ወጋው፤[76] በግንባሩም ወደቀ፤ ድንጋይ ባለበት ወንጭፍም ወነጨፈበት፤ በበረሃም ወደቀ፤ ሁለት ዐይኖቹም ተነቀሉ፤ በዚያን ጊዜም ሞተ:: ትንሹ እረኛም ጌታዬ ሆይ! የገደልኸው ቃኤል ነው አለው:: እጁን በእጁ የቆረጠ ላሜህ ከመጸጸቱ የተነሣ ጠፋ፤ ቢታናሹ እረኛ ራስም በመካከለኛ እጁ ችግር አደረሰበት፤ እንደሞተም ወደቀ::

ላሜህም አሰቦ ድንጋይ አንሥቶም መታው፤ ራሱንም ሰበረው ሞተም፤ ነገሩም ብዙ ነው:: ሄኖስም ዘጠኝ መቶ ዓመት በሆነው ጊዜ የበኩር ልጁ የቃይናን ልጆች ሁላቸውም ወደ እርሱ ተሰበሰቡ:: ሴቶቻቸውም ልጆቻቸውም ከእርሱ በረከትን ፈልገው ያገኙ ዘንድ/በእነርሱ ላይም ጸለየ፤ ባረካቸውም፤ በጻድቁ በአቤል ደምም እንዲህ ብሎ አማላቸው:: ከዚህ ከተቀደሰው ተራራ ከልጆቻችሁ አንዱ ስንኳ ይወርድ ዘንድ አትተዉ፤ ከገዳዩ ከቃኤል ልጆች ጋርም

---

[75] ዘፍ. ፬፥፲፪-፲፬

[76] ትርጓሜ አራት ቃኤል የሞተው በድንጋይ ተወግሮ እንደሆነ የስረዳል /ዘፍ.፬፥፳፫ትርጓሜውን ተመልከት/ ገድለ አዳም ደግሞ በጦርም እንደተወጋ ያስገነዝባል:: ይህም መጀመሪያ በጦር ተወግቶ ከወደቀ በኋላ እርሱ ወንድሙን በገደለበት መሣሪያ /ድንጋይ/ መግደሉን ያሳያል:: መጽሐፈ ኩፋሌን ስንመለከት ደግሞ የነበረበት የድንጋይ ቤት ተንዶ እንደገደለው ያስረዳል:: /ኩፋሌ ፮፥፩/

አትቀላቀሉ።

ቃይናን ልጁን ጠራው። ልጄ ሆይ! ተመልከት፤ ልብህንም ወደ ሕዝቦችህ አድርግ፤ በጽድቅ /በእውነት/ በንጽሕና አጽናቸው። በዘመንህ ሁሉ በአባታችን በአዳም ሥጋ ፊት ታገለግል ዘንድ የጸናህ ሁን አለው፤ ከዚህ በኋላም ሄኖስ በዘጠኝ መቶ ዐምስት ዓመቱ ዐረፈ፤ ቃይናንም ገነዘው፤ በቤተ መዛግብትም በአባቱ በአዳም በግራ በኩል አስቀመጠው፤ እንደ አባቶቹ ልማድም ስለ እርሱ ቍርባንን ዐሳረገ።

ሄኖስ ከሞተ በኋላ ቃይናን አባቱ እንዳዘዘው ለሕዝቡ በእውነት ቆመ፡ በቤተመዛግብትም የአዳምን ሥጋ ያገለግል ነበር። ቃይናንም ዘጠኝ መቶ አንድ ዓመት ኖረ፤ በእርሱ ላይም ሕማም ችግር ደረሰበት። የሚያርፍበት በደረሰ ጊዜ አበው ከሴቶቻቸው ከልጆቻቸው ጋር መጡ፤ ባረካቸው። በጻድቅ በአቤል ደምም እንዲህ ብሎ አማላቸው፤ ከዚህ ከተቀደሰው ደብር /ተራራ/ ከእናንተ አንዱ ስንኳን ይወርድ ዘንድ አትተውት፤ ከገዳዩ ከቃኤል ልጆች ጋርም አትቀላቀሉ።

የበኵር ልጁ መላልኤልም የአባቱን ትእዛዝ ተቀበለ፤ እርሱን ባረከው፤ ሞተም። ልጁ መላልኤልም በሽቱ ገነዘው፤ በአባቶቹ በኩልም በቤተ መዛገብት አስቀመጠው /ቀበረው/። እንደ አባቶቻቸው ልማድም ስለ እርሱ ቍርባን ዐሳረጉ። መላልኤልም ለሕዝቡ ቆመ፤ በእውነት፣ በቅንነት፣ በንጽሕና እንዲጸኑ አደረጋቸው። ከቃኤል ልጆች ጋር እንዳይቀላቀሉም ጠበቃቸው፤ እርሱም በቤተ መዛግብት ውስጥ ቆመ። በአባታችን በአዳም አጠገብ ይጸልይ ዘንድ፣ ለእርሱም ለሕዝቡም ምሕረትን ያገኝ ዘንድ ስምንት መቶ ዘጠና አምስት ዓመት እስኪሆነው ድረስ እንዲህ አደረገ፤ ከዚህ በኋላ ታመመ። ልጆቹ ሁሉ ያዩት ዘንድ ወደ እርሱ ተሰበሰቡ። ከዚህ ዓለም ከመውጣት /ከመሞት/ በፊት ሁላቸው ከእርሱ በረከትን ፈልገዋልና፤ መላልኤልም ተነሥቶ ከአልጋው

ተቀመጠ፤ እንባውም በጉንጮቹ /በፊቱ/ ይፈስ ነበር፤ የበኵር ልጁ ያሬድንም ወደ እርሱ ጠራው፤ ፊቱንም ሳመው፡፡ ልጄ ያሬድ ሆይ! ሕዝብህን ትጠብቅ ዘንድ በእውነት፣ በንጽሕናም ትመራቸው ዘንድ ሰማይና ምድርን በፈጠረው አምልሃለሁ አለው፡፡

ከዚህ ከተቀደሰው ተራራም ከእነርሱ አንዱ ስንኳን ወደ ቃኤል ልጆች ይወርድ ዘንድ አትተወው፡፡ ልጄ ሆይ! ስማ፣ ከእርሱ ጋር እንዳትጠፋ፡፡ በኋለኛው ዘመን በእነርሱ ምክንያት በመሬት ላይ ታላቅ ጥፋት ይሆናል፤ እግዚአብሔር በአዳም /በፍጥረቱ/ ላይ ይቆጣል፤ በውኃም ያጠፋቸውል፡፡[77] ዳግመኛም ዘርህ አንተን እንደማይሰሙ አውቃለሁ፡፡ ከዚህ ተራራም ይወርዳሉ፤ ከቃኤል ልጆች ጋርም ይቀላቀላሉ፤ ከእነርሱ ጋርም ይጠፋሉ፡፡

ልጄ ሆይ! ይቅር በላቸው፤ ጠብቃቸውም፤ በእነርሱ ኀጢአት የመጣው ለአንተም እንዳይተርፍህ፡፡ መላልኤልም ልጁ ያሬድን በሞትሁ ጊዜ ሥጋዬን ገንዘ፤ ያባቴ ሥጋ ባለበት በቤተ መዛግብትም አኑረው፡፡ አንተም በሥጋችን አጠገብ ቁም፤ ወደ እግዚአብሔርም ጸልይ፤ ጠብቃቸውም፤ አንተ እስከታርፍ ድረስም አገልግሎታቸውን ፈጽም አለው፡፡

መላልኤልም ልጆቹን ሁሉ ባረከ /መረቀ/፤ በአልጋው ላይም ተኛ፤ እንደ አባቶቹም ዐረፈ፡፡ ያሬድም መላልኤል አባቱ እንደ ሞተ በተመለከተ ጊዜ አለቀሰ፤ አዘነ፤ አቅፎም እጁንና እግሩን ሳመው፡፡ ልጆቹ ሁሉ እንዲህ አደረጉ፤ መልካም አገናነዘንም ገነዙት፡፡ በአባቶቹ ሥጋ /መቃብር/ አጠገብም አኖሩት፤ አርባ ቀንም እያለቀሱ ቆዩ፤ ያሬድም የአባቱን ትእዛዝ ተቀበለ፡፡ ሕዝቦቹን በእውነት፣ በንጽሕና ይጠብቃቸው ዘንድም እንደ አንበሳ ጸና፤ ከከፋት በቀር ሥራን ይሠሩ ዘንድም አዘዛቸው፡፡ ወደ ቃኤል ልጆች እንዳይሄዱ ስለ እነርሱ ይፈራ ነበርና፤ ስለዚህም ብዙ ያዝዛቸው ነበር፡፡

ያሬድም ስድስት መቶ ስልሳ ዐምስት ዓመት እስኪፈጸም ድረስ ሕይወቱን ሁሉ ያዝዛቸው ነበር፡፡ ዳግመኛም ባሰብናቸው በዓመታቱ ፍጻሜ

[77] ዘፍ.፮፥፯ ይመልከቱ፡፡

ምልከት ሆነለት፡፡ ሕዝቡን ያስተምር፤ ይጸልይላቸውም ዘንድ በአባቶቹ ሥጋ ፊት እንደ አንበሳ የጸና ነበርና፡፡ ሰይጣንም በእርሱ ላይ ቀና፤ እርሱ ለልጆቹ ባለመፍረዱ ያለ ፈቃድ ይሁኑ ዘንድ፡፡

ሰይጣንም በመልካም ሰው አምሳል ተገለጠ፤ እርሱና ከሰራዊቱ ዐምስት ነበሩ፡፡ ከእነርሱም ያማረ ጽሕም ያለው፣ ቁመቱም ከቤቱ በር የሚደርስ ነበር፡፡ ያሬድንም ከውስጧ ጠሩት፤ ያሬድም ወጣ፡፡ እንደመልካም ሰዎች ደም ግባታቸው ያማረ ሆነው አገኛቸው፡፡ ከመልካቸው፣ ከደም ግባታቸው የተነሣ አደነቀ፡፡ ከቃኤል ልጆች እንዳይሆኑ በልቡ አሰበ፡ልና፡፡

ዳግመኛም በልቡ የቃኤል ልጆች ወደ ዚህች ተራራ ይወጡ ዘንድ አይችሉም አለ፡፡ በውስጣቸውም እነዚህን የሚመስሉ መልከ መልካሞች የሉም፡፡ ከእነዚህ ሰዎች ከዘመዶቼ አንድ ስንኳን የለም፡፡ እነዚህ የተሰደዱ ናቸው እንጂ፡፡ ያሬድም ከእነርሱ ጋር እጅ ተነሣሣ፤ ከእነርሱ ጋር ያለ ሽማግሌንም አለው፡፡ አባቴ ሆይ! ምልክትህን አስረዳኝ፤ ከአንተ ጋር ያሉ እነዚህም እነማን እንደሆኑ ንገረኝ፤ እኔ እንደ ስደተኛ አይሃለሁና አለው፡፡

ሽማግሌውም ያለቅስ ዘንድ ጀመረ፤ ሌሎችም ከእርሱ ጋር አለቀሱ፡፡ አረጋዊውም ልጄ ሆይ! አታውቀኝምን? አለው፤ አላውቃችሁም አለው፡፡ ሽማግሌውም እኔ እግዚአብሔር በመጀመሪያ የፈጠረው አዳም ነኝ፤ ይህም አቤል ልጄ ነው፤ ሰይጣን ባደረበት በወንድሙ በቃኤልም ተገደለ፡፡ ይህ ሴትም ከእግዚአብሔር የለመንሁት ለእኔም የሰጠኝ ልጄ ነው አለው፤ በአቤል ፈንታም አጽናናኝ ይህ የሴት ልጅ ሄኖስም ልጄ ነው፡፡ ይህ ሌላውም የሄኖስ ልጅ ቃይናን ነው፤ ይህም የቃይናን ልጅ መላልኤል ነው፤ ይህንም አባትህ አመለከተኝ፡፡

ያሬድም ከመልካቸውና ከሽማግሌው የተነሣ አደነቀ፡፡ አረጋዊው /ሽማግሌውም/ ልጄ ሆይ! አታድንቅ፡፡ እኛ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እግዚአብሔር በፈጠራት በገነት ደቡባዊው ምድር እንኖራለን፤ እናንተ በታቹ በምትኖሩበት በገነት ግን ያኖረን ዘንድ አልወደደም፡፡ ትእዛዙን በተላለፍሁ ጊዜ

ከእርሱ አስወጣኝ፤ በዚህች ቤት የምኖር ሆኜ ቀረሁ። ከባድ የሆኑ ችግሮችም ደረሱብኝ፤ ዕለተ ሞቴ በተቃረበ ጊዜም በመልካም ሥነ ምግባር ሕዝቡን ይጠብቅ ዘንድ ልጄ ሴትን አዘዝሁት፤ ትእዛዙም ከአንዱ ወደ አንዱ እየተላለፈ ቆየ።

ልጄ ያሬድ ሆይ! እኛ በጥሩ ቦታዎች ውስጥ ነን፤ እናንተ ግን አባትህ መላልኤል በዚህ እንዳላችሁ እንዳስረዳኝ በድካም ውስጥ ናችሁ። ብዙ ጥፋት ይመጣል፤ ሁሉንም ምድር ያስጥመዋል አለኝ። ስለ እናንተ በመፍራቴም ልጄ ሆይ! ተነሣሁ።

ልጆቼንም ከእኔ ጋር ይገኙ አንተንም፣ ልጆችህንም እናይ ዘንድ ወደዚህ መጣሁ። እኔም በዚህች ቤት ቁመህ ስታለቅስ አገኘሁህ፤ ልጆችህም በዚህ ተራራ ተበትነው በበረሃ በድካም ናቸው። ልጄ ሆይ! እኛ በመንገድ እስከዚህ ድረስ በመጣን ጊዜ ከዚህ ደብር ግርጌ ሌሎች ሰዎችን አገኘን። እነርሱም ባማረች፣ ዕፀዋት፣ ፍሬያት በበዙባት፣ ብዙ ልምላሜም ባለባት ምድር ናቸው። ይህችም የገነት አምሳል ናት። ባገኘናቸው ጊዜ እናንተም እንደ እነርሱ ናችሁ፤ ብለን አመሰገንን። አባትህ መላልኤል እነርሱ እንደ እነርሱ አይደሉም እስኪለን፤ ድረስ።

ልጄ ሆይ! ዛሬም ምክሬን ስማ፤ አንተም ፣ዘርህም ካላችሁበት ከዚህ ሕማም ታርፉ ዘንድ ወደ እነርሱ ውረዱ። ወደ እነርሱ መሄድ ካልፈለጋችሁ ተነሥተህ ወገኖችህን ያዝ፤ ከእኛ ጋር ወደ ገነት ና። በአማረች ምድርም ተቀመጥ፣ አንተና ወገንህ ከምትኖሩበት ከዚህ ስቃይ ታርፉላችሁ አለው። ያሬድም ይህን ነገር ከሽማግሌው በሰማ ጊዜ አደነቀ፤ ወዲያና ወዲህም ተመላለሰ። በዚህች ቀን ከልጁ አንድ ስንኳ አላገኘም፤ ሽማግሌውም መልሶ እስከዚያች ቀን ድረስ መሸሸጊያችሁ የት ነበር? አለው።

ሽማግሌውም አባትህ ባያመለክተን ባላወቅን ነበር፤ አለው። ያሬድም ነገሩ እውነት እንደሆነ አመነ። ሽማግሌውም ያሬድን ነገሩ እውነት ከሆነ ለምህ

ተመለስህ? አለው። ያሬድም ከአንተ ጋር ስለመምጣት ወደ ነገርከኝ ሰዎች ስለመውረድም ከልጆቼ አንዱን አማክረው ዘንድ እሬልጋለሁ አለው። ሽማግሌውም ምክሩን በሰማ ጊዜ ዛሬ መማከሩን ይተው ዘንድ ያሬድን አለው፤ ከእኔ ጋር ና፤ ምድሪቷንም እንያት፤ እኛ የምንኖርባት ምድር ካላስደሰተችህ ትኖራለህ፤ወገንህንም ከእኛ ጋር እናመጣለን። ደስ ካላችህም ወደ ቤታህ ትመለሳለህ አለው።

ያሬድም ከልጆቹ አንዱን ስንኳን ያማክረው ዘንድ ሳይመጣ እንዲወጣ፤ አጓጓው። ያሬድም ከቤት ወጣ፤ ከእነርሱ ጋር በመካከላቸው ሄደ። እነርሱም የቃኤል ልጆች መኖሪያ ወደሆነው ወደ ተራራው ራስ እስከሚደርስ ድረስ ያረጋጉት ነበር። ሽማግሌውም ከጓደኞቹ አንዱን አለው፤ እኛ የአገሌን ሥራ ይዘናል፤ ያሬድን እናለብሰው ዘንድ ምርጥ ልብስን ወደቤት አመጣን።

ከእነርሱ አንዱንም አገሌ ሆይ! ተመለስ አለው። እኛ እስክትመጣ ያሬድንም እስክናለብሰው ከዚህ እንቆያለን። እንደ እኛም ደም ግባቱ ያማረ ይሁን፤ ወደ ምድራችንም ይገባ ዘንድ የተገባው ይሁን አለ። ከእነርሱም አንዱ ተመለሰ። ትንሽ ራቅ እንዳለ ሽማግሌው ጠራው። መጥቼ እስክነግርህ ታገሥ አለው። እርሱ ቆመ፤ ሽማግሌውም ወደ እርሱ ሄደ፤ እንዲህም አለው፤የረሳነው ተግባር ይህ ነው፤ በቤት ውስጥ ቡሥጋዎች /በዐጽመ አበው/ የሚያበራውን ቀንዲል አጥፋ፤ ፈጠንህም ድረስብን አለው።

ሽማግሌውም ሄደ፤ ወደ ጓደኞቹ እና ወደ ያሬድም ተመለሰ። እነርሱም ከተራራው ወረዱ፤ያሬድም ከእነርሱ ጋር ወረደ፤ በቃኤል ልጆች ቤት አካባቢ በሚገኘው ውኃ አጠገብም ተቀመጡ። ልጆቻቸው፣ ጓደኛቸውም ልብሱን እስኪያመጣ ይጠብቁት ነበር። ይህ የተመለሰውም ቀንዲሉን አጠፋ፤ ደርሰውም ምትሐትን አመጣ፤ አሳያቸውም። ያሬድም በተመለከተ ጊዜ ከመልኩ፣ ከደምግባቱ የተነሣ አደነቀ፤ በልቡም ተደሰተ፤ እውነት እንደሆነም አመነ። እነርሱ ተቀምጠው እያለም ከእነርሱ ሦስቱ ተነሡ፤ ወደ ቃኤል ልጆች

ቤትም ገቡ። ዛሬ እኛም ጓደኞቻችንም እንበላ ዘንድ ወደ ውኃው አምጡልን።

የቃኤል ልጆችም በተመለከቷቸው ጊዜ ከእነርሱ የተነሣ አደነቁ። በሀሳባቸውም እነዚህ መልከ መልካሞች ናቸው፤ እነርሱን የሚመስል ፈጽሞ አላየንም አሉ። ተነሥተውም ከእነርሱ ጋር ጓደኞቻቸውን ያዩ ዘንድ ወደ ውኃው አካባቢ ወጡ፤ መልካምንም አገኙ፤ ይሰበሰቡ ዘንድም እርስ በርሳቸው ተጠራሩ። እነዚህን መልከ መልካሞችም ያዩ ዘንድ ወንዶችም ሴቶችም ወደ እነርሱ ተሰበሰቡ።

ሸማግሌውም እኛ በዚህች ምድራችሁ ስደተኞች ሰዎች ነን፤ ከእናንተ ጥሩ ሙብል መጠጥን፣ ሴቶችንም አምጡ፤ በእናንተ ዘንድም ዕንረፍ አላቸው። እነርሱም ይህን የሽማግሌ ነገር በሰሙ ጊዜ ሁሉም ከቃኤል ልጆች እያንዳንዱ ሚስቱን በሌላም በኩል ሴት ልጁን ያመጣ ነበር። ወደ እነርሱም ብዙ ሴቶች ደረሱ። ከእነርሱም እያንዳንዱ ያሬድን ለራሱ ወይም ለሚስቱ ይፈልገው ነበር። ሁሉም እንደዚህ ያደርጉ ነበር። ያሬድም ይህን ሲያደርጉ በተመለከተ ጊዜ ከእነርሱ የተነሣ ሰውነቱ ተመሰጠች /ተጨነቀች/። ከምግባቸውም አልተመገበም፤ ከመጠጣቸውም አልጠጣም። ሽማግሌውም ነፍሱ እንደተመሰጠች /እንደተጨነቀች/ ተመለከተ። ያሬድንም አትዘን፤ እኔ ታላቅ ሽማግሌ ነኝ አለው። የምሠራውን ሥራ እንዳየህ እንዲሁ እንደ እኔ አድርግ፤ እጆችህን ዘርጋ፤ ከእነርሱም አንዷን ውሰድ አለው።

ሌሎች ከእነርሱ አምስት ጓደኞችም በያሬድ ፊት እንዲሁ አደረጉ። እርሱ እንደ እነርሱ ያደርግ ዘንድ ያሬድም መጥፎ ሲያደርጉ በተመለከታቸው ጊዜ አለቀሰ። በሕሊናውም አባቶቼም እንዲህ አደረጉ? አለ። በዚያን ጊዜም ያሬድ እጁን ዘረጋ። በተቃጠለ ልቡና፣ በብዙኀ ለቅሶም ለመነ። ከእጃቸው ያድነው ዘንድም ከእግዚአብሔር ምሕረትን ፈለገ። ያሬድ በጸለየ ጊዜም ሽማግሌውም ጓደኞቹም ሸሹ። በጸሎቱ ቦታ ይቆሙ ዘንድም አልቻሉም። ያሬድም ተመለሰ፤ አላያቸውምም፤ ነገር ግን ሰውነቱ በቃኤል ልጆች መካከል

ቆሞ አገኘ፤ አለቀሰ። እንዲህም አለ። አቤቱ ጌታዬ ሆይ! አባቶቼ ካስረዱኝ ከነዚህ ጋር እንዳታጠፋኝ። ዛሬም ጌታዬ አምላኬ ሆይ! እኒህ ያሳዩኝ አባቶቼ እንደሆኑ አስቤ ነበር። ዛሬ ግን በዚህ ጥሩ ሁኔታ ምትሐት የሆኑብኝ ሰይጣናት ሆነው አገኘኋቸው። እኔ አውቄባቸዋለሁና፤ ዛሬም ጌታዬ ሆይ! ከእነዚህ ሰይጣናት እንዳዳንኸኝ እኔ በመካከሉ ከቆምሁበት ከዚህ ዘር /ወገን/ አድነኝ፣ ከመካከላቸው ያወጣኝ ዘንድም መልአክህን ላክ። ከመካከላቸው እሸሽ ዘንድ ኀይል የለኝምና አለ። ያሬድም ጸሎቱን በፈጸመ ጊዜ እግዚአብሔር መልአኩን ወደ እርሱ ላከለት። ከመካከላቸውም ወሰደው። ከተራራው ላይም አስቀመጠው፤ መንገዱንም አሳየው፤ አስረዳውም፤ ከእርሱም ጋር ሄደ።

የያሬድ ልጆችም ከሰዓት በኋላ ይጎበኙት ዘንድ ልማድ ነበራቸው። ከእርሱም ይባረኩ /ይመረቁ/ ነበር። በሚሠሩት ሁሉ ይማከሩ ነበር፤ ሥራ ሲኖርም ይሠሩለት ነበር፤ በዚህ ሰዓት በመጡ ጊዜም ያሬድን አላገኙትም። ቀንዲሉ ጠፍቶ፣ የአበው ሥጋ /አጽምም/ ወድቆ አገኙት፣ በእግዚአብሔር ኀይልም ከእነርሱ ቃል ትወጣ ነበር። እነርሱም ልጆችን ቃኤልን እንዳጠፋው ያጠፋው ዘንድ ፈልጎ ሰይጣን በልጆችን ምትሐት አደረገበት አሉ። እነርሱም የሰማይና የምድር አምላክ ሆይ! ከሰይጣን እጅ ልጃችንን አድነው፤ ሰይጣን በፊቱ ታላቅ ምትሐትን አድርጓልና ይሉ ነበር። በእግዚአብሔር ኀይልም ብዙ ሥነ ምግባራትን ይነጋገሩ ነበር።

የያሬድ ልጆችም ይህን ቃል በሰሙ ጊዜ ፈሩ፤ ስለ አባታቸውም አለቀሱ። በእርሱ ላይ የደረሰበትን እነርሱ አያውቁሙ ነበርና። በዚህች ዕለት ፀሐይ እስኪገባ ድረስ ስለ እርሱ ያለቅሱ ነበር። ያሬድም መጣ፣ ፊቱም የከፋ ነበር፤ ወደ ቤት በቀረበ ጊዜም ከአባቶቹ በመለየቱ ዐሳቡ ደከም፣ ሥጋውም አዝኖ ልጆቹ አዩት። ወደ ቤትም ፈጠኑ፤ በአንገቱም ተጠምጥመው አለቀሱ። አቤቱ አባታችን ሆይ! እስከ ዛሬ የት ትተኸን ሄድህ? ይህ ልማድህ አይደለምና አሉት። ዳግመኛም አባታችን ሆይ! ከዚህ ቦታ በተሰወርህ ጊዜ ከአባቶቻችን

በድኖች ቀንዲሉ /መብራቱ/ ጠፍቷል፡፡ ወድቀውም ቀርተዋል፡፡ ድምፅም ከእነርሱ ይወጣ /ይሰማ/ ነበር አሉት፡፡

ያሬድም ይህን በሰማ ጊዜ አዘነ፡፡ ወደ ቤትም ገባ፤ በድኖችንም ወድቀው፣ መብራቱም ጠፍቶ አገኛቸው፡፡ እነርሱም ከሰይጣን እጅ የሚድንበትን ይሹለት ነበር፡፡ ያሬድም በበድኖቹ ላይ ወደቀ፤ እጅም ነሣቸው፡፡ አለም፤ አባቶቼ ሆይ! እናንተን በምፈልግበት ጊዜ እግዚአብሔር ከሰይጣን እጅ አዳነኝ፡፡ አኔም እግዚአብሔርን ትለምኑት ዘንድ እለምናችኋለሁ፤ እስከምሞትባት ቀን ድረስ ከእርሱ /ከሰይጣን/ ይጠብቀኝ፣ ይሰውረኝም ዘንድ አለ፡፡

ልመናቸው አማላጅነታቸው ከሊቃነ ጳጳሳቱ አለቃ ከባስልዮስ፤ ከንጉሣችን ከኀይለ ሥላሴ፣ ከወራሴ መንግሥት ከአምኃ ሥላሴ ጋር ለዘለዓለም ይኑር፤ አሜን፡፡

## ምዕራፍ ስምንት

## ገድለ አዳም ዘኀዳር

አንድ አምላክ በሆኑ በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም ኀዳር ስድስት ቀን የሚነበብ የአባታችን አዳም፣ የእናታችን ሔዋን የገድላቸው ዜና ይህ ነው፡፡ ጸሎታቸው፣ በረከታቸው፣ ከሊቃነ ጳጳሳቱ አለቃ ከባስልዮስ ከንጉሣችን ኀይለ ሥላሴ፣ ከወራሴ መንግሥተ አምኃ ሥላሴ፣ ከንግሥታችን ከወለተ ጊዮርጊስ ነፍስ፣ የጥምቀት ልጆች ከሆንን ከሁላችንም ጋር ይሁን፡፡ አሜን፡፡

ድምፆችም ዝም አሉ፡፡ የአባታችን የአዳም ቃል በእግዚአብሔር ኀይል ወንድም ከወንድሙ ጋር እንደሚነጋገር ያሬድን እንዲህ ብሎ አነጋገረው፡፡ ልጄ ያሬድ ሆይ! ከሰይጣን እጅ ላዳነህ ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን ዐሳርግ፤ ቍርባን በምታሳርግበት ጊዜም እኔ በማሳርግበት መሠውያ ላይ ሁን፤ በእርሱም ቍርባኑንን ዐሳርግ፡፡ ከሰይጣን የተነሣም ልብ የምትል ሁን፤ ጥፋቱን ስለሚሻ

በምትሐት ብዙ ጊዜ በሙሽራ ተመስሏልና፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ከእጁ አዳነኝ። ሕዝቦችንም ከእርሱ የተነሣ ያስተውሉ ዘንድ አዘዛቸው፤ ለእግዚአብሔርም ቍርባን ማሳረግን አትተው፤ ከዚህ በኋላ የአዳም ቃልም ዝም አለ።

ያሬድና ልጆቹም ከዚህ ሁኔታ የተነሣ አደነቁ። በድኖችን እንደ ነበሩት አስቀመጡ። ያሬድም ሌሊቱን ሁሉ እስኪነጋ ድረስ ይጸልይ ዘንድ ከልጆቹ ጋር ቆመ። ቍርባንንም አዘጋጀ፤ አዳም እንዳዘዘውም በመሠውያው ላይ ዐሳረገው። ያሬድ ከእግዚአብሔር ዘንድ ምሕረትን፣ የኀጢአትንም ሥርየት፣ ስለጠፋውም ቀንዲል ከመሠውያው ላይ ቆሞ ሳለ እግዚአብሔር ያሬድን በሠውየው ላይ ታየው፤እርሱንም፣ ልጆቹንም ባረከ /መረቀ/፤ መሥዋዕታቸውንም ተቀበለ፤ በመሠውያው ላይ ካለች መለኮታዊት እሳት ይወስድ ዘንድም አዘዘው። ከእርሷም ከአባታችን ከአዳም ሥጋ ፊት ያበራ የነበረ መብራትን ያበራ ዘንድ።

ዳግመኛም እግዚአብሔር ለአባታችን ለአዳም የገባለትን ቃል ኪዳን ገለጠለት። አምስት ሺህ አምስት መቶውን ዘመን፣ ወደ መሬትም የመምጣቱን ምሥጢር ገለጠለት። እግዚአብሔርም ያሬድን አለው። ከመሠውያው የወሰድሃት ይህች እሳት በሥጋዎቹ /በድኖች/ ፊት የምታበራ ብርሃን ትሁንህ፤ ከእርሱ የአዳም ሥጋ እስኪወጣ ድረስ ከቤት አትውጣ። ያሬድ ሆይ! በቀንዲሉ የምታበራዋን እሳትም ጠብቅ፤ ከቤት ትወጣ ዘንድም አትመለስ፤ በታዩህ ጊዜ ምትሐትን ያይደለ በጎ ማየትን እስከትቀበል ድረስ።

እኔ እግዚአብሔር ጠብን፣ ክፉ ሥራንም አልወድምና ፤ምግባራቸውንም እንዳይማሩ፣ ዳግመኛም ከቃየል ልጆች ጋር እንዳይቀላቀሉ፤ ሕዝቦችህን እዘዛቸው በማለት እግዚአብሔር ያሬድን አዘዘው። እርሱም ልጆቹም ቀረቡ፤ እሳትን ወስዶ፤ ወደ ቤትም ወርዶ በአዳም ሥጋ ፊትም መብራትን አበራ፤ ሕዝቡንም አዘዛቸው።

ይህች ምልክትም በያሬድ ዕድሜ በአራት መቶ ሃምሳ ዓመት በቀረች

እሳት የሆነች ነበረች። ዳግመኛም ድርስቱ እንዳይረዝም ቃሉን እናሳጥረው እንጂ ከእነርሱ የማናስባቸው መንከራት /ድንቆች/ ብዙዎች ናቸው፤ ነገር ግን ይህች ከብዙዎቹ እጅግ ድንቅ ናት። ያሬድም ስምንት ዓመት ያህል ልጆቹን ሲያስተምር ቆየ፤ ልጆቹም ያዘዛቸውን ትእዛዝ ይተላለፉ ጀመሩ። ያለፈቃዱም ብዙ ሥራዎችን ይሠሩ ነበር። ከደብር ቅዱስም ከአንዱ በኋላ አንዱ /ተከታትለው/ ይወርዱ ጀመር፤ ከቃኤል ልጆች ርኩሳን ማኅበራት ጋርም ተቀላቀሉ።

በዚህ ሥራም የያሬድ ልጆች ከደብር ቅዱስ ይወርዱ ነበር። እኛስ በፈቃዳችን እንገለጥላትኋለን፤ ይህ ቃኤል ወደዚህች ጥቁር ጭቃማ ምድር በወረደ ጊዜ ዘሮቹ በዙ። ከእነርሱ አንዱም ቃኤልን የገደለ የዕውሩ የላሜህ ልጅ ስሙም ግኑን ነው። ግኑንም ከታናሽነቱ ጀምሮ በውስጡ ሰይጣን ያደረበት ነበር። በነጋሪት፣ በአውታር፣ በጸናጽል፣ በዝማሬ፣ በመሰንቆ፣ በከበሮ፣ ብዙ ተግባራትን ያደርግ ነበር፤ ይመታባቸውም ነበር። በሚመታባቸው ጊዜም በውስጣቸው ሰይጣን ያድርባቸው ነበር። በመካከላቸውም የሚያምሩ፣ የሚጣፍጡ፣ ልብንም የሚስቡ ቃላትን ይሰሙ ነበር።

ይመቱባቸው ዘንድም ማኅበራትን ሁሉ ይሰበስብ ነበር። በሚመቱባቸው ጊዜም በቃኤል ልጆች ዐይን ፊት መልካም ይሆን ነበር። እርስ በርሳቸውም በኀጢአት ይቃጠሉ ነበር። እንደ እሳትም ይገለባበጡ ነበር። ሰይጣንም እርስ በርሳቸው ልባቸውን ያቃጥላቸው ነበር። በውስጣቸውም ፍትወት /ዝሙት/ የበዛባቸው ነበሩ።[78] ሰይጣንም የሚያሰክር መጠጥ መጥመቅን፣ መድኀኒት ማዘጋጀትን፣ ለግኑንን አስተማረው። ይህ ግኑንም ማኅበራቱን ወደ መጠጫዎቹ ሰበሰበ፤ በየእጃቸውም አትክልቱን ሁሉ አደረሰ፤ ይጠጡባቸውም ነበር።

ይህ ግኑን ግን ኀጢአትን ያበዛ፣ ትዕቢትንም ያደርግ ነበር። የቃኤል ልጆችም የማያውቋትን ኀጢአት እንዲሠሩ ያስተምራቸው ነበር። የማያውቋትን



[78] ኩፋሌ ፯+፰፤ዘፍ.፯+፱-፲

ሥርዓትም ሠራላቸው። ሰይጣንም ባያቸው ጊዜ ይገዙለት፣ ያላቸውንም ሁሉ ይሰሙት ነበር። ግኑንም ደስ ተሰኘ። እርሱ ብረትን ወሰደ፣ ከእርሱ ዕቃ /የጦር መሣሪያ/ እስኪያዘጋጅ ድረስም የልቡናው ሐሳብ በዛ። ይኸም የሆነው በሰከሩ ጊዜ እርስ በርሳቸው መጣላት፣ መጋደል ይበዛ ስለነበር ነው። በኋደኛው ላይ የሚበረታም ይማርከው፣ ሴት ልጆቹንም ወስዶ በፊቱ ኀጢአትን ይሠራባቸው ነበር። ሰዎቹ እንደ ተሸነፉ በተመለከቱ ጊዜም ያልተሸነፉቱ ሌሌሎቹ መጡ። የተሸነፉትም ወደ ግኑን መጥተው ከሰሱ፤ በመካከላቸውም ቆመ። ወደ ኃጢአትም እንዲያዘነብሉ አደረጋቸው፤ በውስጣቸው ኃጢአት በዛ። እያንዳንዱም እኅቱን፣ ልጆቹን፣ እናቱንም ይወስድ ነበር፤ ሌሎችም የአባታቸውን እኅት ልጅ ወሰዱ። አንዱ ከአንዱ ተለይቶ አልቀረም ነበር።

ከፉውን ዐያውቁም ነበር። /የሴት ወገኖች/ እንዴት ሰነፉ? /አበዱ/?፣ ከኀጢአታቸው የተነሣም መሬትን አረከሱ። የፈጠራቸው እግዚአብሔርንም አስቆጡት። ግኑንም ማኅበራቱን /ሰራዊቱን/ ሰበሰበ። ከበሮም ይመቱ ነበር፣ በደብር ቅዱስ አስቀድመን እንደተናገርነው ሁሉ ያደርጉ ነበር። ይህን ያደረገውም በደብር ቅዱስ የሚኖሩ የሴት ልጆች ይሰሙ ዘንድ ነው። የሴት ልጆች ይህንን በሰሙ ጊዜም ያደንቁ ነበር። ማኅበራቱ /ሰራዊቱም/ ወደ እነርሱ ይመጡ፣ ወደ እነርሱ ይመለከቱ ዘንድም በተራራው ራስ ይቆሙ ነበር፤ ለአንድ ዓመትም እንዲህ አደረጉ።

ዓመቱ በተፈጸመ ጊዜ ሰይጣን እነርሱ ትንሽ እንደሆኑ ተመለከተ፤ በግኑንም አደረበት። በመከፋፈል የተለያዩ ሥራይን ያደርግ ዘንድ አስተማረው። የቃኤል ልጆችም ይህን ሁሉ ያደርጉ ነበር። በደም ግባት፣ በልብስ ያንጸባርቁ ነበር። በከበሮ፣ በነጋሪትም ወደ ተራራው ራስ ይሰበሰቡ ነበር። ያማሩ ልብሶችን በመልበስ፣ ፈረሶችን በመጋለብ፣ ብዙ መጥፎ ተግባራት ያደርጉ ነበር።

በተራራው ላይ የነበሩ የሴት ልጆችም ስለወደቁት ሰራዊት

እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ይጸልዩ ነበር፡፡ እግዚአብሔርም መላእክት /ልጆቼ/ አላቸው፤ ታላቅ ደስታንም ተደሰተባቸው፡፡ ከዚህ በኋላ ትእዛዙን አልጠበቁም፣ አባቶቻቸው የተከተሉትን የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳንም አልያዙም፣ ከጾማቸው፣ ከጸሎታቸው፣ ከአባታቸው ከያሬድ ምክርም ተለዩ እንጂ፡፡ የቃኤልን ልጆች የለበሱትን ልብስ፣ ያደረጉትን ጌጣጌጥም ያዩ ዘንድ ከጠዋት እስከ ምሽት ድረስ በተራራው ራስ ይሰበሰቡ ነበር፡፡

የቃኤል ልጆችም ከታች ሆነው የሴትን ልጆች ያዩአቸው ዘንድ ወደላይ ይመለከቱ ነበር፡፡ ማኅበራቱ /ሰራዊቱም/ ከተራራው ላይ ቆመው ወደ እነርሱ ይወርዱ ዘንድ ይጠሯቸው ነበር፡፡ የሴት ልጆችም ከተራራው ላይ ሁነው እኛ መንገዱን አናውቅም የላሜህ ልጅ ግኑንም እነርሱ መንገዱን እንደማያውቁ ሰማ፡፡ እንዴት እንደሚያስወርዳቸውም አሰበ፤ ሰይጣናትም ማታ ተገለጡለት፣ እንዲህም አሉት፡፡ እነርሱ የቆሙበት ይህ ተራራ መንገድ የሌለው ነውና ከእርሱ ይወርዱ ዘንድ በነጋታው ሲመጡ ከተራራው ጫፍ በስተምዕራብ በኩል ኑ በዚያም የውኃ ምንጭ መንገድ ታገኛላችሁ፤ ይህችም በሁለት ተራሮች መካከል ወደ ውኃው ታች ታወርዳለች በላቸው አለው፡፡

በነጋ ጊዜም ግኑን እንደልማዱ ነጋሪት እና ከበሮ መታ፡፡ የሴት ልጆችም ሰሙ፤ እንደልማዳቸው መጡ፡፡ ግኑንም በምዕራብ በኩል ወደታች ኑ፣ የምትወርዱበትን መንገድ ታገኛላችሁ አላቸው፡፡ የሴት ልጆች ከእርሱ ይህን በሰሙ ጊዜም የሰሙትን ሁሉ ለያሬድ ይነግሩት ዘንድ ወደ ቤት ተመለሱ፡፡ ያሬድም ይህን በሰማ ጊዜ አዘነ፤ እነርሱ እንደሚተላለፉ ዐወቀ፤ ከዚህ በኋላ ከሴት ልጆች መቶ ሰዎች ተሰበሰቡ፡፡ እርስ በርሳቸው ወደ ቃኤል ልጆች ኑ፤ እንውረድ፤ የሚያደርጉትን ሥራቸውንም እንመልከት፤ ከእነርሱ ጋርም እንደሰት፣ ተባባሉ፡፡

ዳግመኛም ያሬድ ይህን ነገር ከመቶ ሰዎች በሰማ ጊዜ ሰውነቱ ተናወጸ፣ ልቡም አዘነ፤ በታላቅ ንዴትም ተነሥቶ በመካከላቸው ቆመ፡፡

ከተቀደሰ፣ ንጹሕም ከሆነ፣ አባቶቻችን በውስጡ እንኖር ዘንድ ካዘዙን ከዚህ ተራራ አንዱ ስንኳን እንዳይወርድ ሲል በጻድቁ በአቤል ደም አማላቸው:: ያሬድም እነርሱ እንዳልተቀበሉት በተመለከተ ጊዜ የተቀደሳችሁ፣ ንጹሐን፣ ርኅሩኃን የምትሆኑ ልጆቼ ሆይ! ከዚህ ከደብር ቅዱስ በወረዳችሁ ጊዜ እግዚአብሔር ዳግመኛ ትወጡ ዘንድ አይፈቅድላችሁም፤ አላቸው::

ዳግመኛም እኔ በአባታችን በአዳም ሞት፣ በጻድቁ በአቤል ደምም አምላችኋለሁ:: ልጆቼ ሴት፣ ሄኖስ፣ ቃይናን፣ መላልኤል ሆይ! እኔ የምነግራችሁን ትሰሙ ዘንድ፣ ከዚህ ከደብር ቅዱስም እንዳትወርዱ አምላችኋለሁ:: እናንተ ከዚህ በወረዳችሁ ጊዜ ሕይወት፣ ይቅርታ ከእናንተ ይወገዳል/:: የዲያብሎስ ልጆች እንጂ የእግዚአብሔር ልጆች አትባሉምና አላቸው፤ እነርሱ ግን ነገሩን አልሰሙም::

በዚህ ዘመን የሸመገለ ሄኖክ ነበር:: ለእግዚአብሔር በመቅናትም ተነሣ:: እኔ ከእናንተ ነኝ፣ እኔን ስሙኝ፣ የአባቶቻችንን ትእዛዝ በተላለፋችሁ፣ ከዚህ ከደብር ቅዱስም በወረዳችሁ ጊዜ ከባድ ነው:: ዳግመኛ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ፈጽሞ የምትወጡ አይደለም፤ አላቸው:: እነርሱም በሄኖክ ላይ ተነሡበት፤ ነገሩንም አልሰሙትም፤ ከደብር ቅዱስ ወረዱ እንጂ:: የቃኤልን ልጆች ያማሩ ሆነው እጃቸውም፣ እግራቸውም በጌጣጌጥ አምሮ በተመለከቱ ጊዜ የኃጢአት እሳት በልባቸው ነደደ:: በሴት ልጆች ዘንድም ታላቅ ደም ግባት እንዳላቸው አደረጋቸው:: የሴት ልጆችንም ሰይጣን በሴቶች ዘንድ ፈጽመው ያማሩ እንዲሆኑ አደረጋቸው:: የቃኤል ልጆችም በሴት ልጆች ፊት እንደነጣቂ አራዊት ይዘሉ ነበር:: የሴት ልጆችም በቃኤል ልጆች ዘንድ እንዲሁ ነበሩ፤ ከእነርሱ ጋርም ረከሱ::

በርኩሰት ከወደቁ በኋላ በወረዱባት መንገድ ተመለሱ፤ ወደ ተራራው ይመለሱ ዘንድም ወደዱ፤ ነገር ግን አልተቻላቸውም:: የደብር ቅዱስ ድንጋዮች በፊታቸው እንደምትንበገበግ እሳት ሁነውባቸዋልና:: ስለሆነም ዳግመኛ ፈጽሞ

መውጣት አልተቻላቸውም:: ዳግመኛም እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ ተቆጣ፤ በእነርሱም ከምስጋና ሕይወት ስለወረዱ ተጸጸተ:: ከእነርሱ ወገን ንጽሕናቸውን እንዴት ተው? በኃጢአት ርኩሰትም እንዴት ወደቁ?

እግዚአብሔርም ቃሉን እንዲህ ሲል ወደ ያሬድ ላከ፤ ለእኔ ልጆች ብለህ የጠራሃቸው እነኚህ ልጆችህ እነሆ! ትእዛዜን ተላለፉ፤ ወደ ጥፋት፣ ወደ ኃጢአት ምድርም ወረዱ፤ ወደዚህ ወርደው እንዳይጠፉ ወደ ቀሩት ዞር /ተመለስ/ አለው:: ያሬድም በእግዚአብሔር ፊት አለቀሰ፤ ከእርሱም ምሕረትን ይቅርታን ፈለገ፤ያሬድም ሥጋው ከነፍሱ ትለይ ዘንድ ይፈልግ ነበር:: ከደብር ቅዱስ ስለልጆቹ መውረድም የእግዚአብሔርን ቃል አይሰማም ነበር:: ያሬድም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ሰማ፤ እንዳይወርዱም ወደ እነርሱ ተመለሰ፤ ነገሩን እየሰሙትም ምክሩን አይቀበሉትም ነበር::

ከዚህ በኋላ ሌሎች ማኅበራት ተሰበሰቡ፣ ወንድሞቻቸውን ይፈልጉ ዘንድ ወረዱ፣ ዐብረው /በአንድነትም/ ጠፉ:: ከእነርሱ አንዱ ስንኳ ሳይቀር በአንድነት ካሉት ከታናናሾቹ በቀር አንዱም ከሌላው ጋር እንዲህ ሆኑ፣ ያሬድም ከደረሰበት ሃዘን የተነሣ ታመመ:: ዕለተ ሞቱ እስኪደርስም እንዲሁ በሕማሙ ነበር:: የበኩር ልጁ ኖኅንም ጠራው::

ከእርሱ ዘንድ በደረሱ ጊዜም ጸለየላቸው፣ ባረካቸው:: አላቸውም፣ እናንተ የጻድቃን፣ የንጹሐን ልጆች ከዚህ ከደብር ቅዱስ አትውረዱ:: የወለዳችኋቸው ልጆቻችሁ ከዚህ ደብር ቅዱስ ወርደዋልና፤ ሰውነታቸውንም በምታስጸይፍ ፍጽታታቸው /ዝሙታቸው/ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ከመተላለፋቸው የተነሣ ከደብር ቅዱስ እንደ እንግዳ /መጻተኛ/ አደረጉ:: እኔም በእግዚአብሔር ኀይል በደብር ቅዱስ እንደማይተዋችሁ አውቃለሁ:: ልጆቻችሁ ትእዛዙን፣ የቀደሙ አባቶቻችንን ትእዛዝም ተላልፈዋልና::

ነገር ግን ልጆቼ ሆይ! እግዚአብሔር ከኃላፊዋ ምድር ያውጣችሁ፤ ይህን ደብር ቅዱስን በዐይኖቻችሁ ታዩ ዘንድ አትመለሱ:: ልጆቼ ሆይ!

ልቡናችሁን በነፍሳችሁ አድርጉ፤ከእናንተ ጋር ያለ የእግዚአብሔርን ትእዛዝም ጠብቁ፡፡ ከዚህ ከደብር ቅዱስ በወጣችሁ ጊዜ ወደዚህች ወደ ኃላፊዋና ወደማታውቋት ምድር ትገባላችሁ፤ ከእናንተ ጋርም የአባታችንን የአዳምን ሥጋ፣ ሦስቱን ያማሩ ቊርባናት እጅ መንሻ ውሰዱ፤ እነዚህም ወርቅ፣ ዕጣን፣ ከርቤ ናቸው፡፡ እነዚህም የአባታችን የአዳም ሥጋ በሚቀመጥበት ቦታ ይሁኑ፡፡

ልጆቼ ሆይ! ከእናንተ ለሚቀረው የእግዚአብሔር ቃል ወደ እርሱ ይመጣል፡፡ ከዚህ ምድርም ይወጣል፤ ከእርሱ ጋርም የአባታችን የአዳምን ሥጋም ይወስዳል፡፡ መድኀኒት በሚደረግበት ምድር /በቀራንዮም/ ያስቀምጠዋል፡፡[79] ኖኅም ከእኛ የሚቀረው ማን ነው? አለው፡፡ ያሬድም የምትቀረው አንተ ነህ አለው፤ የአባታችን የአዳምን ሥጋ /አጽም/ ከቤት ትወስዳለህ የጥፋት ውኃ በሚመጣበት ጊዜ ከአንተ ጋርም በመርከቡ ታስቀምጠዋለህ፡፡ ድኅነት ወደሚደረግባት ቦታ /ቀራንዮ/ የአባታችንን ሥጋ የሚወስደውም ከአብራክህ የሚወጣው ልጅህ ሴም ነው አለው፡፡

ያሬድም ወደ ልጁ ወደ ሄኖክ ተመለሰ፤ አንተ ልጄ ሆይ! በዚህች በአት ጽና፡፡ በዘመንህ ሁሉ የአባታችን የአዳምን ሥጋ አገልግል፡፡ ሕዝብሕንም በእውነት፣ በቅን ሆነህ አገልግል አለው፡፡ ያሬድም ዝም አለ፡፡ እጆቹም ዛሉ፡፡ ዐይኖቹም ተከደኑ፡፡ እንደ አባቶቹም ዐረፈ፡፡ የያሬድ ሞትም በዘጠኝ መቶ ስልሳ ሁለት ዓመት ነበር፡፡

የኖኅ ዕድሜም ዘጠኝ መቶ አምሳ ዓመት ሲሆን ታኅሣሥ ዐሥራ ሁለት ዐርብ ቀን ሞተ፡፡ እንባውም በዘመኑ ስለወደቁ ስለሴት ልጆች ከባድ ኃዘን ከማዘኑ የተነሣ በጉንጮቹ ይፈስ ነበር፡፡ ሄኖክ፣ ማቱሳላ፣ ላሜህ፣ ኖኅ አራቱም ለእርሱ አለቀሱለት፤ በጥሩ አገናነዘም ገነዙት፡፡ በቤተ መዛግብት /ዕቃ ቤትም/ አስቀመጡት፤ አርባ ቀንም አለቀሱለት፡፡ ልቅሷቸው በተፈጸመ ጊዜም ሄኖክ፣ ማቱሳላ፣ ላሜህ፣ ኖኅ ከእነርሱ በተለየው በአባታቸው ልባዊ ኃዘን አደረባቸው፤ ማየትም አልቻሉም፡፡

[79] ይህ ቦታ የአዳም አፅም የነበረበት በኋላ ላይ ደግሞ ክርስቶስ የተሰቀለበት፣ በቅዱሳት መጻሕፍትም የራስ ቅል በመባል የሚታወቀው ቀራንዮ ነው፡፡ ማቴ.፳፯+፴፱-፴፭

ሄኖክም የእግዚአብሔርን፣ የአባቱ የያሬድንም ትእዛዝ ጠበቀ፤ በቤቱም ለእግዚአብሔር ይገዛ ነበር። ሄኖክም ብዙ የሚያስደንቁ ነገሮች ነበሩት፣ የታወቀ መጽሐፍም አለው። በዚህ ቦታ መንከራቶቹን /ተአምራቶቹን/ ማሰብ አይቻልም። የሴት ልጆቹ ካዘነበሉ በኋላ እነርሱም ልጆቻቸውም፤ ሴቶቻቸውም ወደቁ። ሄኖክ፣ ማቱሳላ፣ ላሜኅ፣ ኖኅ ባዩአቸው ጊዜም ከሕደትን በተሞላ በዚህ ጥርጥር /ኃጢአት/ በመውደቃቸው ልቡናቸው ታመመ። ከዚህ ከጠማማ ትውልድ ያወጣቸው፣ ይጠብቃቸውም ዘንድ ከእግዚአብሔር ምሕረትን ፈልገው አለቀሱ።

ሄኖክም ሦስት መቶ ስልሳ አምስት ዓመት በእግዚአብሔር ፊት በማገልገል ቆመ። ይህ ከተፈጸመ በኋላ በውስጡ ባለው /በተሰጠው/ ጸጋ እግዚአብሔር ከዚህች ምድር እንደሚወስደው ዐወቀ። ልጆቹንም ልጆቼ ሆይ! እግዚአብሔር ከዚህች ምድር የጥፋት ውኃን እንደሚያመጣ ፍጥረትንም እንደሚያጠፋ እኔ ዐውቃለሁ። በዚህች ምድር በዚህ ሕዝብ ላይ የመኳንንቱ /የሹማምንቱ/ መጨረሻ እናንተ ናችሁ። ከዚህ ከደብር ቅዱስ ከምትወልዷቸው አንድ ስንኳ እንደማይቀር እኔ ዐውቃለሁ። በሕዝቡ ልጆች ላይም ገዢ አይሆንም። በዚህ ደብር /ተራራ/ ላይ ብዙ ማደሪያ አይቀርላችሁም። ዳግመኛም ስለ ሰውነታችሁ ተጠንቀቁ፤ ለእግዚአብሔር በመገዛት፣ እግዚአብሔርንም በማምለክ ጽኑ። በቀናች ሃይማኖት፣ ለእውነት በመገዛት፣ በንጽሕና በቅን ፍርድ፣ በንስሐ አምልኩት አላቸው።

ዳግመኛም ጮኸ። ሄኖክም እነርሱን ማዘዙን ከፈጸመ በኋላ እግዚአብሔር ከዚህ ደብር /ተራራ/ የቸሮች እና የእውነተኞች ማደሪያ ወደሆነችው ወደ ሕይወት ምድር /ብሔረ ሕያዋን/ ዐሳረገው።[80] ይህም ብርሃኑ እስከ ሰማይ የሚደርስ ደስታ የሚገኝበት የገነት አደባባይ ነው። ይህ ብርሃንም ከዚህ ዓለም ብርሃን ውጪ ነው። ዓለምን ሁሉ የመላ የእግዚአብሔር ብርሃን ነው፤ ቦታም አይወስነውም። በእግዚአብሔር ብርሃን ውስጥ በመኖሩም



[80] ዘፍ.፭+፳፪-፳፬

እግዚአብሔር ሞትን እስከሚፈቅድለት ጊዜ ከሞት ሥልጣን /መገዛት/ ወጣ።

በዚህ በደብር ቅዱስ ከአባቶቻችን፣ ከልጆቻቸውም አንዱ ስንኳ አልቀረም። ከሦስቱ ከማቱሳላ፣ ከላሜህ፣ ከኖኅ በቀር። እነርሱ ከደብር ቅዱስ /ከተራራው/ በአንድነት ወርደዋልና። ከቃኤል ልጆች ጋርም በኃጢአት ወድቀዋልና። ስለዚህም ከእነርሱ የተነሣ ተራራው ተከለከለ። በእርሱ ላይም ከሦስት ሰዎች በቀር አልቀረም።

ኖኅም ከታናሽነቱ ጀምሮ ኃጢአት እንደበዛ፣ ክፋትም እንደበረታ፣ የሰው ልጆችም እንደጠፉ፣ ኃዘን እንደበዛ፣ ጻድቃንም እንዳነሱ፣ ያስተውል ነበር። ነፍሱን /ሰውነቱን/ አደከመ፤ ድንግልናውንም ጠበቀ፤ የሰው ልጆች ስላደረጉት ጥፋትም አዘነ። ኖኅም ፈጽሞ የሚያለቅስ፤ ፊቱንም የሚቋጥር ነበር። ስለዚህም ሰውነቱን በድካም አጸና፤ ሰይጣንም ወደ እርሱ ይቀርብ ዘንድ አልቻለም። ኖኅም ከአባቶቹ ጋር ሕፃን እያለ አላስቆጣቸውም፣ ፈጽሞ ትእዛዝን አልተላለፈም፤ ያለ ምክራቸውም /ፈቃዳቸው/ አላደረገም።

ከአባቶቹ በራቀ ጊዜም ጸሎትን ያደርግ ዘንድ ይሻ ነበር፤ ወይም ሥራን ይሠራ ነበር፤ በእርሱ በማመንም እግዚአብሔርን ይለምነው ነበር። ስለዚህም እግዚአብሔር ጠበቀው። በተራራው ሳለ በአንዲት በደል /ኃጢአት/ ስንኳን እግዚአብሔርን አላሳዘነም፤ በራሱ ፈቃድም ከእግዚአብሔር ፈቃድ አልወጣም፤ እግዚአብሔርንም አላስቆጣውም፤ ከእርሱም ከሚቀድሙት ከአባቶቹ የበለጠ ተአምራት ያደርግ ነበር፤ በጥፋት ውኃ ዘመን የተደረገውም በቂ ነው።

ኖኅም ድንግልናውን የሚጠብቅ፣ አምስት መቶ ዓመትም እግዚአብሔርን የሚሰማ ነበር። ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ዘርን ያስነሣለት ዘንድ ወደደ። እግዚአብሔርም እንዲህ ሲል አነጋገረው። "ኖኅ ሆይ! ተነሥና ሚስት አግባ፤ ከእርሷ የሚያጽናናህ ልጅ ይወለድልህ ዘንድ። ብቻህን ትቀራለህና ከዚህች ኃላፊቷ ምድርም ትወጣለህ። ከዘርህም መሬትን የሚያንጽ ይወለዳል አለው።

ኖኅም ይህን ከእግዚአብሔር በሰማ ጊዜ ትእዛዙን አልተላለፈም:: ወደ ጥፋት የሄዱ ከሄኖስ ወገን የሚሆን የአቦረዝን ልጅ ሐይከል[81] የተባለችዋን ሴት አገባ:: ሦስት ጊዜ በሩካቤ ሥጋ ተዋወቃት:: ሴምን፣ ካምን፣ ያፌትንም ወለደች::[82] ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ለኖኅ የጥፋት ውኃ በዚህች ምድር እንደሚመጣ ነገረው:: /ይህ የጥፋት ውኃ/ ፍጥረትን ያጠፋል፣ ከፍጥረቱም አንዱ ስንኳ በምድር አይታይም፤ /አይድንም/ አለው:: ዳግመኛም እግዚአብሔር ኖኅን ልጆችህን ጠብቅ፤ ከቃኤል ልጆች ጋር ተቀላቅለው እንዳይጠፉ እዘዛቸው፤ አስረዳቸውም አለው::

ኖኅም የእግዚአብሔርን ቃል ሰማ፤ ልጆቹንም በተራራው ጠበቀ:: ወደ ቃኤል ልጆች ይወርዱ ዘንድም አልተዋቸውም /አልፈቀደላቸውም/:: ዳግመኛም እግዚአብሔር ኖኅን ለአንተም ከአንተ ጋር ላሉ ቤተሰቦችህም መዳኛ ይሆንህ ዘንድ ከማይነቅዘ ዕንጨት መርከብን ሥራ::[83] ይህንንም በታችኛው የኤዳን ምድር በመጀመሪያ በቃኤል ፊት ትሠሩ ዘንድ ያስፈልጋል:: እነርሱም አንተ የምትኖርባትን ያዩ ዘንድ ነው:: በዚህም ይመለሱ ንስሐ ይገቡ ዘንድ ነው:: ካልወደዱ ግን እነርሱ ይጠፋሉ፤ እንቅፋትም በእነርሱ ላይ ይሆናል:: የምትሠሩባቸውን ዕንጨቶችንም ከደብር ቅዱስ ቁረጡ፤ የመርከቡ ርዝመትም ሦስት መቶ ክንድ ይሁን፤ አግድሙ አምስት መቶ ክንድ ይሁን፤ ቁመቱም ሠላሳ ክንድ ይሁን::

ይህን ሠርተህ ከፈጸምህ ወደ ላይ አንድ በር ይሁን፤ ሦስት ክፍል ይሁን፤ ከክፍሎቹ እያንዳንዳቸውም ቁመቱ ዐሥር ክንድ ይሁን:: የመጀመሪያዋ ቤት የአናብስት፣ የአራዊት፣ የሰጎኖች ሁሉ ይሁን፤ ሁለተኛውም ለወፎች፣ ለተሐዋስያን ይሁን፤ ሦስተኛዋ ቤትም ለአንተ፣ ለቤተሰቦችህ፣ ለልጆችህ፣ ለሚስቶቻቸውም ይሁን፤ በመርከቡም የውኃ ጉድጓድ ሥራ፤ በርም አድርግላቸው::

81 በመጽሐፈ ኩፋሌ ደግሞ "አምዛራ" ተብላ ተጠርታለች ለአንድ ሰው ሁለት ስም እንዳለው እንበለው ያስተውል ኩፋሌ ፮፥፩

82 ዘፍ ፮፥፲

83 ዘፍ ፮፥፲፬

ከእነርሱ ውኃ ይገኝ ዘንድ ለአንተ፣ ከአንተ ጋር ላሉት መጠጥ ይሁን። ጉድጓዱንም በውስጥና በውጪ በቆርቆሮ ለብጠው። በመርከቡ ውስጥም አንተም ከአንተ ጋር ያሉትም ትመገቡ ዘንድ የስንዴ ማጠራቀሚያ ሥራ። ዳግመኛም አብኑስ[84] ከተባለው ዕንጨት መጥቅዕ/ደወል/ ሥራ፤ ርዝመቱ ሦስት ክንድ፤ አግድሙ አንድ ክንድ ተኩል ይሁን። መምቻው /መደወያውም/ ከእነዚህ ዕንጨቶች ይሁን። የሚደወለውም በቀን ሦስት ጊዜ ይሁን። መጀመሪያ በነጋ ጊዜ የመርከቡን አሠራር ያዩ ዘንድ ለሥራም ይሰበሰቡ ዘንድ።

የሁለተኛውንም ደወልም ድምፁን በሰሙ ጊዜ ለምግብ ይሰበሰቡ ዘንድ፤ ሦስተኛውም ምሽት በሆነ ጊዜ ሄደው ከድካማቸው ያርፉ ዘንድ ነው።

እግዚአብሔርም ኖኅን አለው፤በሕዝቡ በመካከላቸው ዞር፤ /ተመላለስ/ ጥፋት መጥቶ እንደሚያስጥማቸውም አስረዳቸው። በፊታቸውም መርከብን ሥራ። ስለ መርከቡ አሠራር ከለመኑህ /ከጠየቁህ/ እንዲህ ብለህ አስረዳቸው። እግዚአብሔር እኔንም ልጆቼንም ከጥፋት ውኃ እንድን ዘንድ ወደ መርከቡ እንድንገባ አዘዘኝ።

ኖኅ በመካከላቸው በተመላለሰ፣ ባስረዳቸውም ጊዜ ዘማውያን፣ ዘፋኞችም ከመሆናቸው የተነሣ ሳቁበት። ይህ ሽማግሌ ይሳሳታል /አእምሮውን አጥቷል/ አሉ። ውሆች ወደ ተራራው ላይ ይመጡ ዘንድ እንዴት ይቻላል? ወደ ተራራው ላይ የሚወጣ ውኃ ፈጽሞ ዐላየንም። ይህ ሽማግሌ ግን የጥፋት ውኃ ይመጣል ይላል አሉ።

ኖኅ ስለ እነርሱ እግዚአብሔር ያዘዘውን ተግባራት ሁሉ አደረገ። ኖኅም እነዚህን ሦስት ልጆች ወለደ። በመጀመሪያ መቶ ዓመት ታቦት[85] የሠራባት ነው። በዚህች መቶ ዓመት ደም የሚወጣበትን ፈጽሞ አልተመገበም። የእግሩ ጫማም አልተለወጠም፤ አልተበጠሰም፤ /አላረጀምም/ ዳግመኛ በዚህ መቶ ዓመት ልብሶችን ከእርሱ አልለወጠም፤ ከእነርሱም ሥራው አልተቆረጠም።

[84] “አብኑስ” ለደወል አገልግሎት የሚውል ጠንካራ እንጨት ነው።



[85] በዚህ አግባብ ታቦት ያለው መርከቡን ነው።

በእጁ የተያዘች በትርም አልተለወጠችም፡፡ በራሱ ያለ መጠምጠሚያውም አላረጀም፤ የራስ ጠጉሩም አልበዛም፤ አልጎደለምም፡፡ ሰብዐ ሁለቱ መተርጉማን፣ (ጥበበኞች) እንዳስረዱን፡፡ አስቀድሞም በዮናናውያን መጽሐፍ እንደተጻፈ፡፡ እኒህ ሦስቱ የኖኅ ልጆችም ከእነርሱ የመጀመሪያው ሴም፣ካምና ያፌት ናቸው ከማቱሳላ ልጆችም ሚስት አገቡ፡፡

ዳግመኛም የኖኅ አባት የላሜህ ዕድሜ ሰባት መቶ ሃምሳ ዓመት ሆነ፤ ዳግመኛም ላሜህ ለሞት ተቃረበ፤ አባቱ ማቱሳላን፣ ልጁ ኖኅንም ጠራ፡፡ ላሜህም በማቱሳላ ፊት አለቀሰ፤ እንዲህም አለው፤ አባቴ ሆይ! ባርከኝ፣ ነጻም የወጣሁ አድርገኝ፤ ማቱሳላም ልጁ ላሜህን ባረከ፡፡ እንዲህም አለው፦በሁሉም በአባቶቻችን ጊዜ ከእነርሱ አንዱ ስንኳን ከአባቱ በፊት አልሞተም፡፡ ልጁ ይቀብረው ዘንድ አባት ከልጁ በፊት ነው እንጂ፡፡ ልጄ ሆይ! ዛሬ ግን አንተ ትሞታለህ? እኔም ከዚህ ሥጋ ከመለየቴ በፊት ኃዘንህን እቀምሳለሁ፡፡

ልጄ ሆይ! ዛሬ እነሆ ዓለም ተለወጠ፡፡ አሟሟታቸውም ተቀየረች፤ ከዛሬ ጀምሮ ልጅ ከአባቱ በፊት የሚሞት ይሆናል፤ በልጁም አይደሰትም፣ ከእርሱም የተነሣ አይጠግብም፡፡ እንደዚሁም ሁሉ ልጁ በአባቱ አይረካም፤ አይደሰትበትምም፡፡[86] ላሜህም ሞተ፤ ገነዙትም፤ ከቤተ መዛግብትም አደረጉት፡፡ የላሜህ ሞትም የጥፋት ውኃ ከመምጣቱ ከዐሥራ ሰባት ዓመት በፊት ነበር፡፡ አባቱ ማቱሳላ፣ ልጁ ኖኅም በደብር ቅዱስ ለብቻቸው ቀሩ፡፡ ኖኅም ሁል ጊዜ ወደ መርከብ ይወርድ ነበር፡፡ ልጆቹን፣ ሚስቶቻቸውንም ያስተምር ዘንድ፤ ስለነፍሳቸው ይደከሙ፣ ይጸልዩም ዘንድ ለማስተማር ሲመሽ ወደ ተራራው ይወጣ ነበር፡፡

ከቃኤል ልጆች ጋር እንዳይቀላቀሉ፣ ይከተሏቸው ዘንድም እንዳይወርዱ፣ ይጠበቁ ዘንድ ኖኅ ስለ ልጆቹ ይፈራ ነበርና፡፡ በዐሳቡም እኒህ ጎልማሶች ይሸነፉሉ ይል ነበር፡፡ በሌሊት ከእነርሱ በወረደ ጊዜም ሽማግሌው ማቱሳላን በእነርሱ ላይ ያዝዘው ነበር፡፡[87] ኖኅም በቃኤል ልጆች ላይ ስብከትን /

[86] ማቴ.፲፥፳፩
[87] ሄኖ.፬፥፲፫

ትምህርትን/ ያበዛ ነበር:: የሴት ልጆች ከደብር ቅዱስ በወረዱ ጊዜም ከቃኤል ልጆች ጋር ሆኑ፤በርኵሰታቸውም ረከሱ:: ከእነርሱም ገርሳኒ ረዓይት የሚባሉ ልጆችንወለዱ:: እነርሱም በኀይላቸው ጽኑዓን የሆኑ ናቸው:: ሌላውም እንደ እነርሱ ራዓይታይ ነው::

ጥበበኞች ሆኑ፤ ቀዳማውያንም ስለ እነርሱ ጽፈዋል:: መላእከት ከሰማይ እንደወረዱ፣ ከቃኤል ልጆች ጋርም እንደተቀላቀሉ፣ ከእነርሱም ረዓይትን እንደወለዱ በአነጋገራቸውም እንደሳቱ ተናገሩ:: ከዚህ የተነሣም በእግዚአብሔር ዘንድ ሐሰት ነው:: ረቂቃን መላእከት ቢሆኑ ሰው በሌለበት በኃጢአት ይገኙ ነበር? ይህ ግን አይደለም:: ይህ ተግባር የመላእከት / የመናፍስት/ ባሕርይ ቢሆን ያልረከሰች አንድ ሴትም በመሬት ባልተውም ነበር:: ሰይጣናት እጅግ ክፉዎች ናቸውና:: ነገር ግን አስተሳሰባቸው ጠባያቸውም ሴትም፣ ወንድም አይደለም::[88]

እነርሱ ረቂያን መናፍስት ናቸው እንጂ:: ሕጉን በተላላፉ ጊዜም ጥቁሮች ሆኑ:: ብዙ ሰዎችም መላእከት ከሰማይ ወርደው ከሴቶች ጋርም ተገናኝተዋል፤ ልጅም ወልደዋል ይላሉ:: ይህ ግን እውነት አይደለም:: ከተራራው ላይ ወጥተው የነበሩ የአዳም ልጆች ናቸው እንጂ:: ድንግልናቸውን፣ ንጽሕናቸውን፣ በመላእከት አምሳል ምስጋናቸውን በመጠበቃቸው የእግዚአብሔር መላእከት/ልጆች/ ይባሉ ነበርና:: ሕጉን በተላለፉ ጊዜ ግን ከቃኤል ልጆች ጋር ተቀላቀሉ፤ ልጅም ወለዱ::

የማያውቁት ግን መላእከት ከሰማይ ወረዱ፤ ከሰው ልጆች ጋርም ግንኙነትን አደረጉ፤ ከእነርሱም ረዓይትን ወለዱ ይላሉ::

የአዳምና የሔዋን ልመናቸው፣ አማላጅነታቸው ከሁላችንም ጋር ጸንቶ ይኑር:: ለዘለዓለሙ አሜን::

---

[88] በመላእክት ዘንድ የወንድና የሴት ግብር አለመኖሩን ለመገለጽ መሆኑን ልብ ይሏል:: ማቴ.፳፪፥፴

## ምዕራፍ ዘጠኝ

## ገድለ አዳም ዘታኅሣሥ

አንድ አምላክ በሆኑ በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም ታኅሣሥ ስድስት ቀን የሚነበብ የአባታችን የአዳም እና የእናታችን የሔዋን የገድላቸው ዜና ይህ ነው፡፡ ጸሎታቸው፣ በረከታቸው እና የይቅርታ ልመናቸው ከሊቃነ ጳጳሳቱ አሊቃ ባስልዮስ ከንጉሣችን ከኀይለ ሥላሴ ከምንሰማው፣ ከምናነበው እና ከሁላችንም ጋር ይሁን፡፡ አሜን፡፡

ታላቁ ሽማግሌ ማቱሳላም ከኖኅ ልጆች ጋር በደብር ቅዱስ ቀረ፡፡ ዘጠኝ መቶ ስልሳ ዓመት ከኖረ በኋላም ታመመ፤ ሕማሙም የሚሞቱበት ነበር፡፡ ልጆቹ ኖኅ፣ ሴም፣ ካም፤ያፌትም ዐወቁ፤ ከሚስቶቻቸውም ጋርም ወደ እርሱ መጡ፤ በፊቱም አለቀሱ አሉም፡፡ አቤቱ ሽማግሌ አባታችን ሆይ፤ ባርከን፤ከእኛ በተለየህ ጊዜ ይቅር ይለን ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ለምንልን አሉት፡፡ ባዘነ ልብም የተወደዳችሁ ልጆቼ ሆይ፤ ስሙ አላቸው፡፡ ከሁሉም አባቶቻችን አንዱ ስንኳን አልቀረም፤ እናንተ ስምንቱ ነፍስ ናችሁ እንጂ፡፡ እግዚአብሔር የፈጠራቸው አባታችን አዳምንና እናታችን ሔዋንን ነው፡፡ ከእነርሱ የተነሣም የገነት ጐረቤት ምድር ሞላች፤ ዘራቸውንም አበዛው፤እነርሱ ሕጉን አልጠበቁም እንጂ፡፡ እርሱም ያጠፋቸው ዘንድ ይሻል፤ ትእዛዙን ቢጠብቁ ግን ሰማይንም፣ ምድርንም ይመሉ ነበሩ፡፡

ነገር ግን እኔ እግዚአብሔር አምላኬን እለምነዋለሁ፤ በምትሄዱባት በዚህች በኃላፊዋ ምድር ዘራችሁን ያበዛው፣ ይባርካችሁም ዘንድ ፤ልጆቼ ሆይ፤ ዘሬም ፈጽማችሁ ወዳልገባችሁባት ምድር እግዚአብሔር በመርከብ ይወስዳችኋል፡፡ ንጹሐን የሆኑ የአባቶቻችን አምላክ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሆን ዘንድ በተባረከች ቤተ መዛግበት /ዕቃ ቤት/ ውስጥ ለአባታችን አዳም፣ ለእናታችን ሔዋን ክብርን የሰጣቸው እግዚአብሔር ለእናንተም እኒህን ሦስት ክብራት ይስጣችሁ፡፡

እግዚአብሔር ለአዳምና ለሔዋን የሰጣቸው ክብርም ይህ ነው፡፡ የመጀመሪያው ክብር እግዚአብሔር አዳምን ንጉሥ አድርጎ የሾመላት መንግሥት ሰማይ ናት፡፡[89]

ሁለተኛ ክብርም ክህነት ናት፡፡ እግዚአብሔር የሕይወት እስትንፋስ እፍ ብሎበታልና፡፡ ሦስተኛዋ ክብርም ትንቢት ናት፡፡ አዳም እግዚአብሔር በሚያስበው ነገር ይናገር ነበርና፤ እኔም ለዘራችሁ እነዚህን ሦስት[90] ክብሮች /ማዕራጋት/ ይሰጣችሁ ዘንድ አምላኬን እለምንዋለሁ፡፡

ዳግመኛም ማቱሳላ ኖኅን አለው፡፡ኖኅ ሆይ! እኔ ከእግዚአብሔር የተባረኩሁ ነኝ፤ እኔ አዝዝሃለሁ፤ እንደቀደሙኝ እንደ አባቶቼ ሁሉ እኔ ከአንተ እለያለሁ፤ ከልጆችህ ጋር የምትቀር አንተ ነህ፡፡ ትእዛዜን ለራስ ጥቅም ጠብቅ፣ የምልህን ሁሉ አትዘንጋ /አትተወው/፡፡ እነሆ! አምላኬ በምድር ላይ ጥፋትን ያመጣል፤ ሥጋዬን ፈጥነህ ገንዘ፤ በዕቃ ቤቱም አድርገው፡፡ ሚስትህን፣ ልጆችህን፣ ሚስቶቻቸውንም ይዘህ ከዚህ ከደብር ቅዱስ ተራራ ውረድ፡፡ የአባታችን የአዳምን ሥጋ ይዘህ ወደ መርከቡ ግባ፡፡

በምድር ላይ የጥፋት ውኃ ወቅት እስኪፈጽምም በዚያ አኑረው፤ ልጄ ሆይ! በምትሞትበት ጊዜ የቃይናንም ልጅ መልከ ጼዴቅን ይወስደው ዘንድ የበኩር ልጅህን ሴምን እዘዘው፡፡ ይህም የአርፋክስድ የልጁ ልጅ መልከ ጼዴቅ[91] ነው፡፡ እርሱም የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነው፡፡ የአባታችን የአዳምን ሥጋ ወስደው በመርከብ ውስጥ ያስቀምጡት ዘንድ መልከ ጼዴቅም እስከ ዘለዓለሙ ድረስ በአባታችን በአዳም ሥጋ ፊት በዚህች ደብር /ተራራ/ ለእግዚአብሔር አገልጋይ ይሁን፡፡

ኖኅ ሆይ! በዚህች ቦታ ወይም ሀገር የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ለአዳምና ለዘሩ፤ በእግዚአብሔር ለሚያምኑ ሁሉ መድኀኒትን ያደርጋል፤

89 [illegible]

90 [illegible]

91 [illegible]

የእግዚአብሔር መልአከም ከልጆችህ ጋር ይሄዳል፡፡

ከዚህች ቦታ እስኪያደርሳችሁ፤ ይህችም የምድር ማእከል ናት አለው፡፡ ማቱሳላም ኖኅን ልጄ ሆይ! በአባታችን በአዳም ሥጋ ፊት ለእግዚአብሔር የሚገዛ፣ ልብሱ የሚሸት፣ ወገቡን የታጠቀ እና ጌጣጌጥንም ለእርሱ ያላደረገ ይሁን፡፡ የደሃ ልብስ ለብሶ ብቻውንም ይቁም እንጂ፡፡

የአባታችን የአዳምን ሥጋ ይጠብቅ ዘንድም አምላክ ለሆነ ለእግዚአብሔር ይጸልይ፡፡ ይህ ሥጋ በእግዚአብሔር ዘንድ ታላቅ ነውና፡፡ ይህን የልዑል እግዚአብሔር ካህንም በንጹሕ፣ ባማረም ልብ እግዚአብሔርን ያገለግል ዘንድ የቆመ ይሆናል አለው፡፡

ከዚህ በኋላ ማቱሳላ ኖኅን በእነዚህ ትእዛዛት ሁሉ አዘዘው፡፡ እንግዲህ ዕወቅ፤ ትእዛዜንም ጠብቅ አለው፡፡ በዚህን ጊዜም ማቱሳላ እጁ ዛለ፤ ከመናገርም ዝም አለ፡፡ ዐይኑንም ከደነ፣ እንደሁሉም አባቶቹ ዐረፈ፡፡ እንባውም በፊቱ ይፈስ ነበር፡፡ በመለየቱም ልቡ አዝኖ ነበር፡፡ አንዱ ስንኳን በውስጧ ስላልቀረባት ስለ ደብረ ገነት /ደብር ቅዱስ/ እግዚአብሔር ፍጥረቱን ሁሉ ሊያጠፋው ፤ከምድር ገጽም ሊደመስሰው ስለ መውደዱ ያዝን ነበር፡፡

የማቱሳላ ዕረፍትም በዘጠኝ መቶ ስልሳ ዘጠኝ ዓመቱ መጋቢት ሁለት እሑድ ቀን ነበር፡፡ ኖኅም ከልጆቹ ጋር በብዙ ለቅሶና ኃዘን ገነዙት፡፡ በቤተ መዛግብትም አስቀመጡት፡፡ አርባ ቀን ያህልም ከሚስቶቻቸው ጋር የሚያስደንቅ ለቅሶን አለቀሱለት፡፡ ስለማቱሳላ የነበራቸው ኃዘንና ለቅሶ ከተፈጸመ በኋላ፣ ኖኅ፣ ልጆቹም ማቱሳላ እንዳዘዛቸው ያደርጉ ዘንድ ጀመሩ፡፡

ማቱሳላ ከሞተ በኋላ ልጆቹ ሚስቶቻቸውም እንደ አባቶቻቸው ሥርዓት መጡ፤ ከእነርሱም ተባረኩ፡፡ እነርሱም በታላቅ ለቅሶና ኃዘን ላይ ነበሩ፤ ኖኅም መርከቡን ሠርቶ ጨረሰ፡፡[92] የሚሠራውም አልቀረውም ነበር፤ ኖኅና ልጆቹም የመዳን መንገድ በየት እንዳለች ይመራቸው ዘንድ እግዚአብሔርን ለመኑት፡፡ ጸሎታቸው በተፈጸመ ጊዜ እግዚአብሔር ኖኅን



92 ዘፍ. ፮-፯

አለው፡፡ ወደ ቤተ መዛግብት ግባ፣ አንተም ልጆችህም የአባታችሁ የአዳምን ሥጋ ውሰዱ፣ በመርከቡም አድርጉት፡፡

ዳግመኛም ወርቁን፣ ዕጣኑን፣ ከርቤውን ውሰዱ፤ ከሥጋው /ከአፅሙ/ ጋርም በታቦቱ /በመርከቡ/ አኑሩት፡፡ ኖኅም ይህን ትእዛዝ ከእግዚአብሔር ዘንድ ሰማ፤ እርሱዋም ልጆቹም ገቡ፡፡[93] የአባታችንን ሥጋም አጅ ነሱ፡፡ የአባታችን የአዳምን ሥጋም አንሥቶ በእግዚአብሔር ኀይል ተሸከመው፡፡ ከእርሱ ጋር ካለውም አንዱ ስንኳ ይረዳው ዘንድ አልወደደም፡፡

ልጁ ሴምም ወርቁን ያዘ፣ ካም ከርቤውን፣ ያፌትም ዕጣኑን ተሸከመ፤ ከቤተ መዛግብትም አወጧቸው፡፡ እንባቸውም በፊታቸው ትፈስ ነበር፡፡ አዳም በመካከላቸው የነበረላቸው በድኖችም ባወጧቸው ጊዜ ጮሁ፡፡ አባታችን አዳም ሆይ፤ ከአንተ መለየታችን ምንኛ ጭንቅ ነው? አሉ፡፡ የአባታችን የአዳም ሥጋም እንዲሁ ልጆቼ ሆይ፤ ከእናንተ፣ ከዚህ ከደብር ቅዱስ መለየት እንደምን ያለ ጭንቅ ነው? ነገር ግን ልጆቼ ሆይ፤ ዳግመኛ ሲመጣ እግዚአብሔር ሥጋችንን እንደሚሰበስብ እኔ አምላለሁ፡፡[94] መድኃኒታችን ይቅር እስኪለን ታገሡ እንጂ አለ፡፡

በድኖችም በእግዚአብሔር ኀይል እርስ በርሳቸው ይነጋገሩ ነበር፡፡ አዳምም በድኖች ዳግመኛ እስከሚነሡ ድረስ በልጆቹ ፊት የምታበራ ከእግዚአብሔር የተላከች እሳት ትቀር ዘንድ ፈለገ፡፡ እግዚአብሔርም በእነርሱ ላይ ታበራ ዘንድ መለኮታዊት እሳትን አስቀረ፤ በእነርሱ ላይም እግዚአብሔር ቤቱን ዘጋ፡፡ ሁሉንም በበድኖች አምሳል እስከሚያስነሣበት ዕለት ድረስ ምልክቷ ይታወቅ ዘንድ አልተዋትም፤ ይህ ነገርም አዳም ይናገረው የነበረው ነው፡፡ እርሱ የሞተ ነበር፤ ነገር ግን እግዚአብሔር በሕያዋንና በሙታን ዘንድ ተአምራቱን ያሳይ ዘንድ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ይህ ሆነ፡፡

ሰይጣን በአዳም ነፍስ ላይ ገገር ነው የሚል ቢኖር እግዚአብሔር የሙታንን ነፍሶች ከእጁ ይወጡ ዘንድ አዘዛቸው፡፡ በድን ሆነው ሳሉ የእግዚአብሔርን ተአምር ይናገራሉ፡፡ ሁሉንም በእውነት እስከሚያወጣበት

93 ዘፍ.፯+፯
94 ዳን. ፲፪+፪

እስከመዳን ቀን ድረስም ወደ ቦታቸው መለሳቸው::

ኖኅና ልጆቹ ከሁሉም ሙታን በድን ይህን በሰሙ ጊዜ ፈጽመው አደነቁ፤ በእግዚአብሔር የነበራቸው ሃይማኖትም በረታች፤ ከቤትም ወጡ:: በተቃጠለ ልብ የለቅሶ ቃላትን እየደረደሩም ከደብር ቅዱስ ይወጡ ጀመር፤ ከአባቶቻቸው ቤት /ማደሪያ/ ከደብር ቅዱስ በመለየታቸው አለቀሱ፤ ኖኅና ልጆቹም ቤት ይፈልጉ ዘንድ ተመለሱ፤ ነገር ግን አላገኙም::

በእነርሱ ላይ ለቅሶና ኃዘን ጸናባቸው፤ በዚህን ጊዜ መኖርያ ቤት እንዳልቀረላቸው ዐወቁ:: ዳግመኛም ዐይኖቻቸውን አነሡ፤ ገነትን ዛፎቿንም ተመለከቷት፤ በታላቅ ለቅሶና በኃዘን ድምፆቻቸውን አንሥተው በሰላም እጅ እንነሳሻለን አሉ:: የደስታ ገነት፣ የብርሃናውያን ማደርያ፣የቅዱሳን ቦታ ሆይ! እጅ እንነሳሻለን፣ የፍጥረቱ ሁሉ መጀመሪያ የሆነ የአዳም ማደሪያ የሆንሽ የደስታ ቦታ ሆይ! ሕግን በተላለፈ ጊዜ አፍሮ በሕይወቱ ከአንቺ ወደቀ፤ እነሆ እኛም በውስጡ እንዳንኖር ከአንቺ በታች ካለ ከደብር ቅዱስ እነሆ! ራቅን፤ በሕይወታችንም ዐናይሽም::

እግዚአብሔር እስከምንሄድባት ምድር ድረስ ከእኛ ጋር ያፈልስሽ ዘንድ እንሻለን:: ነገር ግን ወደዚህች ወደ ተረገመችዋ ምድር እግዚአብሔር ያፍልስሽ:: እኛን ግን እግዚአብሔር አንሥቶ ከልጆቻችን ጋር ወደዚች ምድር ይወስደናል፤ ትእዛዙን በመተላለፋችን ግርፋትን እስከንቀበል ድረስ::

ኖኅና ልጆቹም የንጹሐን የአባቶቻችን በድን ማደሪያ ቤት ሆይ! ሰላም እንልሻለን አሉ:: በውስጥህ በድኖቹ ይቀመጡ ዘንድ የተገባህ ንጹሕ ቦታ ሆይ! ሰላም እንልሃለን:: ስለ አባቶቻችን ሥጋ /በድን/ እግዚአብሔር አምላክ ይጠብቅህ፤ ዳግመኛም ንጹሐን፣ ገዢዎች አባቶቻችን ሆይ! ሰላም እንላችኋለን፤ ከዚህ ከኃላፊው ዓለምም ያድነን ዘንድ ለምኑልን አሉ::

ከዘራችሁ ስለቀረነው ስለ እኛ ትጸልዩ ዘንድ እንለምናችኋለን፣ በሰላም እጅ እንነሳችኋለን፤ በአበው ዘንድ ታላቅ ሊቀ የሆንህ ሴት ሆይ በሰላመ እጅ

እንነሳሃለን የአባቶቻችን የቅዱሳን ማደሪያ ደብር ቅዱስ ሆይ! እያሉ ኖኅና ልጆቹ አለቀሱ፡፡ ወዮልን የቀረን እኛ ስምንቱ ነፍሳት ነንና ገነትን ከማየት እነሆ! ራቅን ይሉም ነበር፡፡

ከደብር ቅዱስ ሲያወጣቸው ድንጋዮችን እጅ ይነሱ ነበር፡፡ በእጃቸው በትከሻቸው ይይዙ ነበር፡፡ ከዕፀዋትም ይሳለሙ ነበር፡፡ ከመርከቡ በር እስኪደርሱ ድረስም እንዲህ እያለቀሱ ወረዱ፡፡ ኖኅና ልጆቹም ፊታቸውን ወደ ምሥራቅ መለሱ፡፡ ከእግዚአብሔርም የሚመራቸውን፣ የአባታችን የአዳምን ሥጋም እንዴት እንደሚያስቀምጡ የሚያዝዛቸውን ፈለጉ፡፡

የእግዚአብሔር ቃልም እንዲህ ሲል ወደ ኖኅ መጣ፡፡ ኖኅ ሆይ! የአዳምን ሥጋ ወደ ሦስተኛዋ ቤት /ክፍል/ አውጣ፤ በምሥራቅ በኩል አስቀምጠው፤ ወርቁም፣ ዕጣኑም፣ ከርቤውም ከእርሱ ጋር ይሁን፡፡ አንተና ልጆችህም ስትጸልዩ በፊቱ የምትቆሙ ሁኑ፡፡ ሚስትህም ሴቶች ልጆችህም ከርመከቡ በስተምዕራብ በኩል ይሁኑ፤ ከእነርሱ ጋርም አይቀላቀሉ አለው፡፡

ኖኅም ይህን ቃል ከእግዚአብሔር በሰማ ጊዜ እሱም ልጆቹም ወደ መርከቡ ገቡ፡፡ የአዳምን ሥጋም በምሥራቅ በኩል፣ ሦስቱን እጅ መንሻም ከእርሱ ጋር አስቀመጠው፡፡ ይህም ግንቦት ሃያ ሰባት ቀን ዐርብ በሁለት ሰዓት ነበር፡፡ እግዚአብሔርም ኖኅን አለው፤ ወደ መርከቡ ራስ ውጣ፣ አራዊቱም ወደ መርከቡ ይሰበሰቡ ዘንድ ሦስት ጊዜ ደውል ምታ አለው፡፡

ኖኅም የዚህ ደውል ድምፅ አዕዋፉ፣ አራዊቱ ይሰሙ ዘንድ እስከ ዓለም ዳርቻ ይደርሳልን? አለ፡፡ እግዚአብሔርም ኖኅን አለው፣ የዚህ ደውል ድምፅ ብቻ የሚወጣ /የሚሰማ/ አይደለም፡፡ በአዕዋፉ፣ በአራዊቱ ጆሮ እስኪደርስ ድረስ ከድምፁ ጋር የእኔ ኀይል ይወጣል እንጂ፡፡ ይህን ነጋሪት /ደውሉን/ በመታኸው ጊዜ ነጋሪት ይመታ ዘንድ ከሰማይ መለአኬን እልካለሁ፤ ሁሉም አራዊት ወደ አንተ ይሰበሰባሉ፡፡

ኖኅም እግዚአብሔር እንዳዘዘው ደወሉን ፈጥኖ መታ፤ መልአኩም

መሬት እስከትነዋወጽ ድረስ ነጋሪቱን መታ፤ በእርሷ ያሉ ፍጥረታትም ታወኩ:: አራዊቱ፣ እዕዋፉ፣ ተሐዋስያኑ፣ አንበሶቹ እና ሰጎኖቹ ሁሉ ዐርብ በሦስት ሰዓት ተሰበሰቡ:: ከቀኑ ሦስት ሰዓት ተኩልም ወደ ታችኛይቱ ቤት /ክፍል/ ገቡ:: አዕዋፋቱ፣ ተሐዋስያኑም ወደ ሦስተኛዋ ቤት /ክፍል/ ገቡ:: ከቀኑ በዘጠኝ ሰዓትም ኖኅ፣ ሚስቱ፣ ልጆቹ፣ ሚስቶቻቸውም ወደ ላይኛይቱ አዳራሽ /ክፍል/ ገቡ:: ኖኅም ሴቶችን በምዕራብ በኩል እንዲቀመጡ አዘዛቸው፤ኖኅና ልጆቹም ከአባታችን ከአዳም ዐፅም ጋር በምሥራቅ በኩል ነበሩ::

ኖኅም ከጥፋት ውኃ ያድነው ዘንድ ከእግዚአብሔር ምሕረትን ፈልጎ ነበርና ቁሞ ቀረ:: እግዚአብሔርም ኖኅን አነጋገረው፤ እንዲህም አለው:: ከአዕዋፍ ወገን፣ ከሴትም፣ ከወንድም ሁለት ሁለት ውሰድ:: ዳግመኛም ከንጹሐን ከሴትም ከወንድም ሰባት፣ ሰባት ውሰድ አለው:: ኖኅም ይህን ሁሉ አደረገ::[95] ወደ መርከቡ በገባ ጊዜም እግዚአብሔር የመርከቡን በር በአምላካዊ ኃይሉ ዘጋባቸው::

እግዚአብሔር በእነርሱም የሰማይ በሮች ይከፈቱ እና የውኃ ጎርፍ ይወርድ ዘንድ አዘዘ:: በእግዚአብሔር ትእዛዝም እንዲህ ሆነ:: እግዚአብሔርም ምንጮቹ ሁሉ ይከፈቱ ዘንድ አዘዘ:: ጥልቆች /ጉድጓዶችም/ ውኃዎችን ያስገፉ ዘንድ:: እንደሚዞር ባሕርም በዓለሙ ሁሉ ከፍ ከፍ አለ፤ ጮኸ፣ ድምፁንም አሰማ:: የጥልቆችን መዛግብት /በሮች/ በከፈቱ ጊዜ የነፋሳት ጎርፎች ጎረፉ / ተከፈቱ/:: አውሎ ነፋስ /ጥቅል ነፋስ/፣ ጉም፣ ጭጋግ፣ ጨለማ ተከሠተ:: ከጨረቃ ከከዋክብት ጋር ፀሐይም ብርሃኑን ነሣ፤ዕለቱም ፈጽሞ የሚመስለው የሌለ የፍርሃት ቀን ሆነ::

ባሕሩም ማዕበል ሞገዱን ያወጣ ጀመር፤ እርሱ እንደተራራዎች መሬትን ሁሉ ሸፈነ:: ከቃኤል ልጆች ጋር በርኩሰት /በዝሙት/ የወደቁ የሴት ልጆችን በተመለከቱ ጊዜም እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ እንደተቆጣ ኖኅ የነገራቸውም እውነት እንደሆነ ዐወቁ፤ ሁላቸውም ወደ መርከቡ ወደ ኖኅ ሮጡ፤ መግባት

[95] ዘፍ.፯÷፩-፭

ስለማይችሉ በሩን ይከፍትላቸው ዘንድ ፈልገው ለመኑት፤ እነርሱም እንደ እሳት ከሆኑ ድንጋዮች ወደ ደብር ቅዱስ ይወጡ ዘንድ ነበር::

መርከቧ ግን በእግዚአብሔር ኃይል ፈጽማ ተዘጋች:: የእግዚአብሔር መልአከም ለኖኅ፣ ለልጆቹ፣ በመርከቡ ላሉት ሁሉ እንደ አለቃ በመርከቡ ተቀምጦ ነበር:: በቃኤል ልጆች ላይ የጥፋቱ ውኃ በዛባቸው፤ በእነርሱ ላይ ሠለጠነባቸው፤ ያልቁም ጀመር፤ በእነርሱ ላይ የጥፋት ውኃ እንደሚመጣ እንደሚያሰጥማቸው ኖኅ ያስተማረው ቃልም ተፈጸመ፤ ውኃውም በመርከቡ እስኪ ወጡ ድረስ በላይም በታችም በእነርሱ ላይ ሞልቶ ተረፈ::[96]

ከውኃው ኀይል የተነሣ ሥጋዊ፣ ደማዊ ፍጥረት ሁሉ በምድር ይርመሰመስ ነበር፣ ውኃውም መሬትን ሁሉ፣ ታላላቅ ተራሮችንም ሸፈነ::

ውኃውም በእነርሱ ላይ በታላላቅ ተራሮች ራስ ላይም በመንፈስ ቅዱስ ከንድ ዐሥራ አምስት ከንድ ያህል ወጣ:: የመንፈስ ቅዱስ ከንድ ሲተረጐምም ሦስቱ ከንድ አርባ ዐምስት ከንድ ይሆናል:: ውኃውም ከፍ ከፍ አለ:: መርከቧንም ተሸከማት ወደ ገነት ታችም ወሰዳት:: ውኃዎች ዝናማት፣ አውሎ ነፋስ /ጥቅል ነፋስ/ ከመሬትም የወጣው ሁሉ ለገነት ሰገዱ:: ኖኅም፣ ልጆቹም፣ /በመርከቡ/ ውስጥ ያሉትም ልዩ ለሆነች ገነት ሰገዱ፤ውኃውም ከሰማይ በታች ከምድር በላይ ያለውን ሁሉ አጠፋ:: መርከቧ ግን በውኃው ላይ በነፋሳትም ትንሳፈፍ /ትዋኝ/ ነበር::

የእግዚአብሔር መልአከም ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ድረስ ይነዳት፣ ያስተዳድራትም ነበር:: መርከቧም በውኃው ላይ መቶ ሃምሳ ቀናት ትሔድ ነበር:: ከዚህ በኋላ መርከቧ አራራት በተባለው ተራራ ላይ በጥቅምት ፳፯ ቀን ቆመች /ዐረፈች/:: ዳግመኛም እግዚአብሔር ለኖኅ እንዲህ ሲል መልአከቱን አስተላለፈ:: ውኃዎቹ እስኪያልቁ ድረስ ታገሥ፤ ጾጥም በል፤ ውኃዎቹም እርስ በርሳቸው ተለያዩ፤ እያንዳንዳቸውም ቀድሞ ወደ ነበሩበት ተመለሱ፤ ምንጮቹም በመሬት ላይ አልመጡም፤ ቀላያትም በምድር ገጽ ላይ እንዳይወጡ ተያዙ::

---

[96] ዘፍ.፯+፲፯-፳፫

የሰማይ በሮችም ተዘጉ፤ አርባ መዓልት፤ አርባ ሌሊት ያህል በሰማይ ላይ ማዕበል ይወርድ ነበርና። በመጀመሪያው ወር በዓሥራ አንደኛው ቀን የታላላቅ ተራሮች ጫፍም ታየ። ከዚህ በኋላ ኖኅ አርባ ቀን ያህል መንፈሱን አዝናና /አረጋጋ/። የሠራትን መርከብ የምሥራቁን መስኮትም ከፈተ። ውኃውም ከምድር ገጽ መጉደሉንና ያለ መጉደሉን ያይ ዘንድ ቁራን ላከው፤ ቁራ ግን እንደወጣ ወደ ኖኅ ፈጽሞ አልተመለሰም።[97]የየዋሂቷ የርግብ ምልክት /የወይራ ቅጠልም/ የቤተ ክርስቲያን ምሥጢር ምሳሌ ነው።

ኖኅም ውኃው ከጎደለ በኋላ መንፈሱን /ሰውነቱን/ ትንሽ አዝናና። ርግብንም ውኃው መጉደሉን ወይም አለመጉደሉን ታይ ዘንድ ላካት፤ ርግብም በወጣች ጊዜ የምታርፍበትን ቦታ፤ የምታድርበትንም አላገኘችም፤ ወደ ኖኅም ተመለሰች።[98] ዳግመኛም ኖኅ ሰባት ቀን ያህል ሰውነቱን አዝናና። ኖኅም የጥፋት ውኃ መጉደሉን ወይም አለመጉደሉን ታይ ዘንድ ርግብን ዳግመኛ ላካት፤ ርግብም የወይራ ቅጠል በአፏ ይዛ በሰርክ ወደ ኖኅ ተመለሰች። የርግብ ትርጓሜዋም የብሉይን ምሳሌ የያዘች ናት። መጀመሪያ በወጣች ጊዜ እግሮቿን የምታሳርፍበት ፈለገች፤ ግን አላገኘችም፤ ይህም የዕረፍት ቦታ ነው። እነዚህም ጸጋው ያልተረፉቸው፤ ልባቸው የደነደነ አይሁድ ናቸው። በእነርሱ ላይም ምሕረት አልቀረም አልተደረገም።

የርግብ ምሳሌ የሆነ የዋህ ክርስቶስም በእነርሱ ዘንድ የእግሩ መረገጫ አላገኘም፤ ዳግመኛም ርግብ ለእርሷ ቦታ ማግኘቷ ይህም የዕረፍት ቦታ ነው። እነሆም የቅዱስ ወንጌልን የምሥራች የተቀበሉ ውስጣቸውን ለክርስቶስ ማረፊያ የሰጡ ሕዝብና አሕዛብ ናቸው።

ለኖኅ ዘመኑ ስድስት መቶ አንድ ዓመት በሆነው ጊዜ ሚያዝያ ሁለት ቀን ውኃው በምድር ላይ ደረቀ።[99] በሁለተኛው ወር ይኸውም ግንቦት ፳፯ ቀን ነው፤ ይህም ዕለት ኖኅ ወደ መርከቡ የገባበት ቀን ነው።

ዳግመኛም ኖኅ በዚህ ዕለት በዕለተ እሑድ ከመርከቡ ወጣ። ኖኅም

[97] ዘፍ.፰-፯
[98] ዘፍ. ፰-፱

[99] ዘፍ. ፰-፲፫

በወጣ ጊዜ እርሱም፣ ሚስቱም ልጆቹም፣ የልጆቹም ሚስቶችም በአንድነት ነበሩ። እርስ በርሳቸውም አልተለያዩም። መጀመሪያ ወደ መርከቡ ሲገቡ ግን ወንዶች ከሴቶች የተለዩ ነበሩ፤ ኖኅ ስለ ግንኙነታቸው ይፈራ ነበርና፤ ጥፋቱ በተፈጸመ ጊዜ ወንዶች ከሴቶች ጋር ተቀላቅለው ወጡ።

እግዚአብሔርም በአራዊቱ፣ በአናብስቱ ላይ በመርከቡ ውስጥ ታላቅ ጸጥታን አመጣ። ከአዕዋፋትም፣ ከተሐዋስያኑም እንዲሁ እርስ በርሳቸው አይጣሉም ነበር። ኖኅም ከመርከቡ ወጣ። በተራራው ላይም መሠውያን ሠራ እንዴት እንደሚሠዋ ቍርባኑንም እንዴት እንደሚያሳርግ ያሳየው ዘንድ ፈልጎ በእግዚአብሔር ፊት ቆመ። እግዚአብሔር እንዲህ ሲል ቃሉን ወደ ኖኅ ላከ። ኖኅ ሆይ! ከንጹሑ ወገን ወስደህ ከእነርሱ በእኔ ፊት ቍርባንን ዐሳርግ፤ አራዊቱንም ከመርከቡ አሰናብት።

ኖኅም ወደ መርከቡ ገባ፣ ከአዕዋፍም ንጹሐን የሆኑትን ወሰደ። እግዚአብሔር እንዳዘዘውም ያደርግ ጀመር። በመሠውያው ላይም በእግዚአብሔር ፊት መሥዋዕትን ዐሳረገ።[100] እግዚአብሔር ለኖኅ እንደገባለት ቃል ኪዳን አምሳል፣ በሰማይ ላይም ቀስተ ደመና አሳየው። እግዚአብሔርም የኖኅን ቍርባን መዓዛ አሸተተ። እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ዳግመኛ የጥፋት ውኃን እንደማያመጣም ከእርሱ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ። እግዚአብሔር ከኖኅ ጋር የገባው ቃል ኪዳንም ይህ ነው። እግዚአብሔር ኖኅን አለው፣ የቃል ኪዳኔን ቀስት በደመናው ላይ አወጣለሁ። በታየ ጊዜም ሰዎች በእውነት እንደታየ ያውቃሉ። ቁጣ በሆነ ጊዜ ቀስተ ደመና ይታያል፤ በሰው ዘንድ ላመጣ የምፈልገው መቅሰፍትም ይቀራል።

ዳግመኛም ኖኅ ሆይ! የቃል ኪዳኔን ቀስት ፍጥረታት ሁሉ ያዩት ዘንድ በሰማይ ላይ እንዳደረግሁት በመከራቸው እና በችግራቸው ወቅት የጥንቱን የሚያስቡ ይሆኑ ዘንድ ከበደላቸው ይመለሱ፣ ንስሐ ይገቡ ዘንድ።[101] እግዚአብሔርም የኖኅን ቍርባን ተቀበለ፤ እርሱንም ልጆቹንም ባረከ። ብዙ፤ ተባዙ የምድርንም ገጽ ሙሏት አላቸው። እግዚአብሔርም እንደ ጥንቱ ሣርን አራዊቱን፣ አዕዋፉቱን፣ በምድር የሚንቀሳቀሰውን ሁሉ ታወጣ ዘንድ መሬትን አዘዛት።

---

[100] ዘፍ. ፰፥፳

[101] [illegible]

ኖኅም በእግዚአብሔር ፊት ሰገደ። እርሱም ልጆቹም ሚስቶቻቸውም ስለተደረገላቸው ድኅነት አመሰገኑት፤ ኖኅም ልጆቹን ይዞ ሀገርን /መንደርን/ ሠሩ /መሠረቱ/። እነርሱ ስምንት ነፍስ ሆነው ከመርከቡ እንደወጡ በታውን ሰመናን[102] ብለው ሰየሙት፤ ኖኅና ልጆቹ ልጆችን፣ የልጅ ልጅንም እስኪያገኙ ድረስ መቶ ዘመን ያህል በዚህ በተቀደሰ ተራራ ተቀመጡ።

ኖኅም የወይን ሥርን ወስዶ ተከለ። እስኪያፈራ፣ የጣፈጠም እስኪሆን ድረስ ተንከባከበው። ዳግመኛም ኖኅ ከፍሬው ወስዶ ወይኑን ጠመቀው። አንዱን ወስዶም ከእርሱ ጠጣ፣ ሰከረም ወደ ሚስቱም ገባ፤ ልብም አያደርግም ነበር፤ ወንዶች ሴቶችን እንደሚያደርጉትም አደረገ።

ያን ጊዜም ልጁ ካም በጥዋቱ ወደ ቤት ገባ፤ የአባቱንም ዕርቃን ተመለከተ፤[103] እርሱም በወይን ሰክሮ ነበር፤ ያውቅ ዘንድም አይችልም ነበር። ልጁ ካምም ሳቀበት፤ ሰደበውም፤ አንተ ሽማግሌ ያደረግሽው ይህ ምንድን ነው? አለው። ሽማግሌውም ነገሩን ልብ አላደረገውም፤ የኖኅ ሚስት ግን ነገሩን ትረዳ ነበር፤ ካምም በአባቱ ላይ እየሳቀ ወጣ።

ወጥቶም ለወንድሞቹ ለሴምና ለያፌት የአባታቸውን ተግባር /ሁኔታ/ ነገራቸው። እርሱም በእነርሱ ላይ ነበር፤ ሽማግሌውም ሰክሮ በተመለከቱት ጊዜ ወንድሞቹ ተቆጡ፤ ካምንም ሰደቡት፤ ከሽማግሌው የተነሣ እነርሱ ስለ እርሱ ይፈሩ ነበርና። እርሱ በነገሩ /በቃሉ/ የጸና ጻድቅም እንደሆነ ያውቁ ነበርና።

ሴምና ያፌትም ፈጥነው ተነሡ፣ መጐናጸፊያም ወሰዱ። መጐናጸፊያውንም ከአግራቸው እስከሚደርስ ድረስ በጀርባቸው አደረጉት፤ ከአባታቸው እስኪደርሱ ድረስም ወደመጡበት መንገድ ፊታቸውን አዞረው ወደኋላቸው ሄዱ። መጐናጸፊያውንም ከእነርሱ ወረወሩት /አለበሱት/ ፤እንዳያያቸውም ከእርሱ ፈጥነው ወጡ። በነጋታውም ሚስቱ የካምን ተግባር፣ ያደረገውንም ለኖኅ አስረዳቻቸው። ኖኅም ይህን ነገር ባወቀ ጊዜ በልጁ በካም

102 [illegible]

103 [illegible]

ተቆጣ፣ በእርሱ ላይ ስለሳቀም የወንድሞቹ አገልጋይ ይሆን ዘንድ ረገመው።

ኖኅም መልካምን ያደረጉለት ልጆቹ ሴምና ያፌትን ባረካቸው።[104] ኖኅም የዘመኑ ፍፃሜ እስኪቃረብ ድረስ በዚህ ተራራ ይኖር ነበር። ኖኅም ከመርከብ ከወጣ በኋላ ሦስት መቶ ሃምሳ ዓመት ኖረ። ኖኅም የበኩር ልጁ ሴምን ጠራው። ከእርሱ ጋርም ተነጋገረ። ልጄ ሴም ሆይ! የማዝዝህን ስማ። እነሆ! አዝዝሃለሁ። በምሞትበት በምትቀብሩኝም ዕለት፣ ስለእኔም ማልቀሳችሁ ሲፈጸም ከጥፋት ወደዳንባት መርከብ ውጡ። የአባታችን የአዳምን ሥጋም ከእርሷ አውጣ፣ አንድም ሰው ያውቅ ዘንድ አትተው፤ ከዘርህ የሆን ነው እንጂ።

ጥሩ ማደሪያም ሥራለት፤ በዚያ ውስጥም አድርገው። ለመንገድ ስንቅ ይሆንህ ዘንድም ዳቦ ያዝ። በመንገድህ ትጠጣ ዘንድም ወይንን ያዝ፣ ምድር ፈጽማ ተቸግራለችና፤ ተርባለችምና። የልጅህ የቃይናምን ልጅ ትንሹ መልከ ጼዴቅንም ከአንተ ጋር ውሰድ። ከዚህ ሁሉ ሰው /ልጆች/ እርሱን እግዚአብሔር መርጦታልና። በእግዚአብሔር ፊት በአምልኮት ይቆም ዘንድ። ለአባታችን ለአዳም ሥጋም አገልጋይ ይሆን ዘንድ። የአዳምን ሥጋም በመሬት አስቀምጥ፣ መልከ ጼዴቅንም በእርሱ ዘንድ የጸና አድርገው። እግዚአብሔርን እንዴት እንደሚያገለግልም አስረዳው አለው።

ዳግመኛም ኖኅ ልጁ ሴምን ትእዛዜን ብትሰሙ፣ ሥራዬን ብትከተሉ የእግዚአብሔር መልአክ ከእናንተ ጋር ይኀዛል። የምትሄዱባትን መንገድም ያሳያችኋል። ሥጋውን ከምታኖሩበት ቦታ ከምድር መካከል እስክትደርሱ ድረስ፤ በዚህ ቦታም እግዚአብሔር ለዓለሙ ሁሉ መድኃኒትን ያደርጋልና። ልጄ ሆይ! መልካሙን ትእዛዝ እኔ አመለክትሃለሁ። ልጆቻችን የተከተሉትን፣ ከደብር ቅዱስም የወረዱትን፣ ከቃኤል ልጆችም የተቀላቀሉትን ተው። ልጄ ሆይ! እንደጠፉም ዕወቅ፤ ከአዳም ጀምሮ እስከዚህች ቀን ድረስ ከሥጋ በሚያርፉበት ጊዜ ከአረጋውያን አንዱ አንዱን ያዝዘዋልና፤ እያንዳንዳቸውም ያስተምራሉና።

በመጀመሪያ ያስተማረ፣ ይህን ትእዛዝም ያሳየ አባታችን አዳም ልጁ

[104] ዘፍ.፱+፳፭-፳፯

ሴትን አዘዘው፤ ትእዛዙንም ተቀበለ፡፡ ሴትም ልጁ ሄኖስን አዘዘው፤ ትእዛዙንም ተቀበለ፡፡ ሄኖስም ልጁ ቃይናንን አዘዘው፤ ትእዛዙንም ተቀበለ፡፡ ቃይናንም ልጁ መላልኤልን አዘዘው፤ ትእዛዙንም ተቀበለ፡፡ መላኤልም ልጁ ያሬድን አዘዘው፤ ትእዛዙንም ተቀበለ፡፡ ያሬድም ልጁ ሄኖክን አዘዘው፡፡ ትእዛዙንም ተቀበለ፡፡ ሄኖክም ልጁ ማቱሳላን አዘዘው፣ ትእዛዙንም ተቀበለ፡፡ ማቱሳላም ልጁ ላሜህን አዘዘው፤ ትእዛዙንም ተቀበለ፡፡ ላሜህም እኔን አዘዘኝ፤ እኔም ትእዛዙን ተቀበልሁ፡፡

ዳግመኛም አያቴ ማቱሳላ ታላቅ ትእዛዝን አዘዘኝ፤ ተቀበልሁት፡፡ እንደዚህም እኔ አዝዝሃለሁ፤ትእዛዜንም ተቀበል፤ ነገሬንም ልብ አድርግ፤ ይህን ምሥጢርም በልብህ አስቀምጠው፡፡ ከዘመዶችህ ሁሉ ለአንዱ ስንኳን እንዳትገልጸው፡፡ የአባታችን የአዳምን ሥጋ ሂድና በመሬት ውስጥ አኑረው፤ በዚህም እስከመዳን ቀን ይቀመጥ አለው፤ መርከቧም በኖኅ ዘመን ተዘግታ ነበር፤ አንዱ ስንኳ ሊነካት አይችልም ነበር፤ እየመጡ ይባረኩባት ነበር እንጂ፡፡ ከእርሷ የተነሣም ያደንቁ ነበር፡፡

ኖኅም ምሽት፣ ምሽት ወደ እርሷ ይገባ ነበር፡፡ በአባታችን በአዳም ዘንድ ያዘጋጀውንም መብራት ያበራ ነበር፤ ከአባታችን ከአዳም ሥጋም ይባረክ ነበር፤ አስቀድሞ በቤተ መዛግብት እያለ እንደነበረውም በክፍሉ ማብራትን አያስታጉልም ነበር፡፡ ኖኅም መርከቧ ከእርሱ በኋላ ተዘግታ እንደማትቀር በተረዳ ጊዜ፣ ልጆቹም እንደሚለያዩ፣ ያዩት ዘንድም ወደ አባታችን ወደ አዳም ሥጋ እንደማይመለሱ፣ በምድር ክፋት፣ በሰውም ሽንገላ እንደሚበዛ ባወቀ ጊዜ ከዕረፍት በኋላ ፈጥኖ የአባታችን የአዳምን ሥጋ ይዞ እግዚአብሔር እንዳዘዘው ወደምድር መካከል /ቀራንዮ/ ይወስደው ዘንድ ልጁ ሴምን አዘዘው፡፡ ኖኅም ለአባታችን ስለ አዳም ሥጋ ማዘዙን በፈጸመ ጊዜ ልጁ ሴምን ልጄ ሴም ሆይ! ስለአባታችን ስለ አዳም ሥጋ ማዘዙን በፈጸመ ጊዜ ልጁ ሴምን ልጄ ሴም ሆይ! ከእርሱ ወንድሞችህን ከእኔ አድርሳቸው፣ ወደ እኔም አምጣቸው፣ አለው፡፡ ከእርሱ በደረሱ ጊዜም ኖኅ አያቸው፤ እንዲህም አላቸውም፤ ልጆቼ ሆይ! ከሞትሁ በኋላ

ትለያያላችሁ፤ ከዘራችሁም ብዙ ችግር ይሆናል፤ እኔ ምድርን ከሦስት እከፍልላችኋለሁ፤ ከእናንተ እያንዳንዱ በየድርሻው ይደርስ ዘንድ።።

የበኩር ልጁ ሴም ድርሻም ከኢየሩሳሌም እስከ መቅርዶንዮን፣ እስከ እንዱኪያም ሆነ፣ ይህችም ታላቅ ሀገር ናት።። የደረሰው ተራራም የግብጽ ምድርና የፍልስጥኤም መካከል እስከ ሆኅት ግፋር ድረስ ይደርሳል።። ሁለተኛ ልጁም ካም ነው፤ ክፍሉም ከአሪስ እስከ ሰሜን፣ እስከፈርድንዮን፣ እስከ ወማዱዮን እስከ ምዕራብ ዳርቻም ነው።። የሦስተኛው ልጁ ይኸውም ያፌት ነው።። ክፍሉም /ድርሻውም/ ከሰሜን ምዕራብ ሜፍ እስከ ታላቋ ሀገር ዳማት፣ እንዲሁም ደቡብ ሁሉ እስከ አሪስ ድረስ የእርሱ ነበር።።[105]

ከእናንተም እያንዳንዱ ድርሻውን ይያዝ / ይውሰድ/፤ እያንዳንዱም በየደረሰው ይቀመጥ /ይኑር/ አላቸው።። እንዳዘዛቸውም ተቀመጡ።። እያንዳንዳቸውም በአባታቸው በኖኅ ዘመን ወንድ ልጅ፣ ሴት ልጅ ተወለደላቸው።። ኖኅም በሦስቱ ወንድሞች መካከል መጣላት እንዳይኖር በእግዚአብሔር ትእዛዝ መሬትን አከፋፈላቸው።። ኖኅም ሴምንና ወንድሞቹን አዝዞ ከፈጸመ በኋላ እጆቹ ዛሉ፤ አንደበቱም ዲዳ ሆነ፣ ዐይኖቹም ተከደኑ፤ እንደ አባቶቹም ዐረፈ።። ዕረፍቱም በዘጠኝ መቶ ሃምሳ ዓመት፡[106] ረቡዕ ዕለት፣ ግንቦት ሁለት ቀን መርከቧ በነበረችበት በተራራው ነበር።። እግዚአብሔር እስከ ገለጠው ድረስም ቆየ፤ አርባ ቀንም ያለቅሱለት ነበር።።

የጻድቃን፣ የሰማዕታት፣ የአበው፣ የሐዋርያት፣ የነቢያት ወላጆች፣የአባታችን የአዳም፣ የእናታችን የሔዋን ጸሎታቸው፣ በረከታቸው፣ አማላጅነታቸው፣ የይቅርታ ልመናቸውም ከጥምቀት ልጆቻቸው ከሁላችንም ጋር ይሁን፣ ለዘለዓለሙ አሜን።።

---

105 የኖኅ ልጆች ዓለምን ሲካፈሉ የደረሳቸው ሀገር፡-
ለሴም፡- ኤፍራጥስ፣ ከለዳ፣ ባቢሎን፣ ፋርስ፣ ፍርግያ፣ሕንደኬ፣ ቴማን ናቸው።።
ለያፌት፡- ኩራስ፣ መቄዶንያ፣ ሮም፣ አርማንያ፣ ጤግሮስ፣ እንጾኪያ፣ ኪልቅያ፣ ቲልዶቅያ፣ በራንጥያ፣ ቆጵሮስ፣ አቴንስ ናቸው።።
ለካም፡- ሶርያ፣ ከነአን፣ ግብጽ፣ ኢትዮጵያ ናቸው።። /ጊዮርጊስ ወልደ አሚድ የዓለም ታሪክ፡ ገጽ ፳፩-፳፭/
ለያፌት፡- ልጆች በአውሮፓ፣ የሴም ልጆች በእስያ፣ የካም ልጆች በአፍሪካ ይኖራሉ።። /የኢትዮጵያ ታሪክ አለቃ ተክለ ኢየሱስ፡ ገጽ ፮/

106 ዘፍ.፱-፳፰

## ምዕራፍ ዐሥር

## ገድለ አዳም ዘጥር

አንድ አምላክ በሆኑ በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም ጥር ስድስት ቀን የሚነበብ የአባታችን የአዳም፣ የእናታችን የሔዋን የገድላቸው ዜና ይህ ነው። ጸሎታቸው፣ በረከታቸው፣ አማላጅነታቸው፣ የይቅርታ ልመናቸው ከሊቃነ ጳጳሳቱ አለቃ ከባስልዮስ፣ ከንጉሣችን ከኀይለሥላሴ፣ ከንግሥታችን ከወለተ ጊዮርጊስ ነፍስ ጋር ይሁን፣ ለዘለዓለሙ አሜን።

ለቅሶውን /ኃሐዘኑን/ ከፈጸሙ በኋላም የእግዚአብሔር መልአክ ለመልከ ጼዴቅ አባት ለቃይናም እንዲህ ሲል በራእይ ተገለጠለት። ቃይናም ሆይ ታውቀኛለህን? አለው። አቤቱ ጌታዬ ሆይ! አላውቅህም አለው። እኔ የእግዚአብሔር መልአክ ነኝ። ይህንን ትእዛዝ እነግርህ ዘንድ ወደ አንተ ላከኝ፣ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ አትተላለፍ አለው። ቃይናንም ከእግዚአብሔር መልአክ ይህን በሰማ ጊዜ አደነቀ። ጌታዬ ሆይ ተናገር፤ አለው።

የእግዚአብሔር መልአክም አባትህ አዳምን ከገነት በነበረ ጊዜ ወደታች ያመጣሁት እኔ ነኝ፤ በመሠውያው ላይ ደሙን በሠዋ ጊዜ ከእርሱ ጋር እግዚአብሔርን የለመንሁት እኔ ነኝ፤ የጻድቁን የአቤልን ነፍስ የተቀበልሁ እኔ መልአኩ ሚካኤል ነኝ፤ በቤት በተወለደ ጊዜ ከሴት ጋር የነበርሁት መልአክም እኔ ነኝ። ከሄኖስ፣ ከቃይናም፣ ከመላልኤል፣ ከያሬድ፣ ከሄኖክ፣ ከማቱሳላ፣ ከላሜህ፣ ከኖኅ ጋር የነበርሁም እኔ ነኝ። ባረፈ ጊዜም ከበኩር ልጁ ከሴም ጋር ነበርሁ።

አሁንም መልከ ጼዴቅ ልጅህን አወስደው ዘንድ እግዚአብሔር ወደ አንተ ላከኝ። በእግዚአብሔር ዘንድ ታላቅ ይሆናልና። በመሄዱ ልብህ አይሰማው /አይዘን/ አለው። ቃይናም ይህን ነገር ከእግዚአብሔር መልአክ በሰማ ጊዜ በፊቱ ሰገደ። የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁንም አለው። እኔም ልጄም

እነሆ! በእጆቹ ነን፣ የወደደውን ያድርግ አለው፡፡ መልአኩ ለቃይናም መታየቱም ስለንጽሕናው፣ ስለጽድቅም አይደለም፡፡ ስለ መልከ ጼዴቅ ስለ ጽድቁም፣ ስለንጽሕናውም ነው እንጂ፡፡

መልአኩም ቃይናምን ይህን ምሥጢር ከሴም በቀር ለአንዱ ስንኳ እንዳትናገር አለው፡፡ ከእርሱም ሄደ፤ የእግዚአብሔር መልአክም በዚህች ሌሊት ወደ መልከ ጼዴቅ መጣ፡፡ /መልከ ጼዴቅም/ ተኝቶ ነበር፡፡ እንደ እርሱ በጐልማሳ አምሳል ተገለጠለት፡፡ ቀኝ ጐኑንመ መታው፤ ከእንቅልፉም አነቃው፡፡ በተነሣ ጊዜም ፊቱ በብርሃን ተመልቶ፣ በፊቱም ተቀምጦ በተመለከተ ጊዜም ከመልአኩ የተነሣ ፈራ፡፡ ያለ እርሱ ፈጽሞ መልአክ ማዬት አልለመደም ነበርና፡፡ መልአኩም ፍርሀትን ከእርሱ አስወገደለት፡፡ በራሱ፣ በጀርባው ላይ ቀባው፤ እኔ ወደ አንተ የተላከሁ የእግዚአብሔር መልአክ ነኝና አትፍራ፡፡ ይህች መልእክትም ለአምላክህ ታደርግ ዘንድ ነው አለው፡፡

መልከ ጼዴቅም ይህች መልእክት ምንድን ናት? አለው፡፡ ጐልማሳው ልቡ ፍጹም ነበርና ከአባታችን ከአዳም ሥጋ ጋር እስከምድር መካከል ድረስ ትሄድ ዘንድ፣ በፊቱ ለማገልገል ትቆም ዘንድ፣ እግዚአብሔርንም ታመልከው ዘንድ ከታናሽነትህ መርጦሃልና፣ አንተ ከተባረኩ ዘር ነህና አለው፡፡ መልከ ጼዴቅም መልአኩን የአባቴን የአዳምን ሥጋ የሚወስድ ከእርሱም ጋር የሚወስደኝ ማን ነው? አለው፡፡ መልአኩም የአባትህ አያት የኖኅ ልጅ /ሴም/ ነው፤ አለው፡፡ መልአኩም ልቡናውን አቀናለት፤ ለአንድ ሰዓትም አረጋጋው፡፡ ነገር እንዳይወጣ ይህን ምሥጢር ለአንዱ ስንኳ አትናገር አለው፡፡ በአዳም ሥጋ እንዳይጸኑ እግዚአብሔር ወደ አዘዘበት ቦታም ይሄድ ዘንድ አይተውትምና፡፡

መልአኩም ከእርሱ ሄደ፤ ወደ ኖኅ ልጅ ወደ ሴምም መጣ፡፡ አባትህ ኖኅ እንዳዘዘህ ተነሥና የአዳምን ሥጋ ውሰድ፤ አለው፡፡ መልከ ጼዴቅንም ከአንተ ጋር ውሰደው፤ እግዚአብሔር ወደ አዘዘህ ቦታም ከእርሱ ጋር ሒድ፣ አትዘግይም፤ አለው፡፡ በነጋ ጊዜም ያማረ መርከብ አዘጋጀ፤ በመርከቡም

አስገባው፤ ለስንቅ ይሆነው ዘንድም ኅብስት፣ ወይን አዘጋጀ::

የእግዚአብሔር መልአክም ወደ ቃይናም መጣ፤ ልጁ መልከ ጼዴቅንም ፈለገው:: ቃይናምም መልአኩ የነገረውን ሁሉ ይነግረው ጀመር፣ ልጁ መልከ ጼዴቅንም በአማረ ልቡና ሰጠው:: ቃይናምንም ይህን ምሥጢር ሰውር፣ ለአንዱ ስንኳ አትግለጥ፤ አለው:: ሴምም መልከ ጼዴቅን ወሰደው፤ ከእርሱ ጋርም አህያን ጫኑ፤ ወደመርከቡም ሄዱ፤ መርከቡን የሚከፍቱበት ቁልፍ ግን ከእነርሱ ጋር አልነበረም:: ኖኅ ከእርሷ ከወጣ በኋላ ከፍል አድግሎላት ነበርና፤ ከእርሷ በደረሱ ጊዜም በምን እንደሚከፍቷት አሰቡ:: ሴምም ወደበሩ ወጣ፤ መልከ ጼዴቅንም በእግዚአብሔር ዘንድ ታላቅ የሆንህ ሆይ! ና ከፈተው፥ አለው::

መልከ ጼዴቅም ሰምቶ ወደ በሩ መጣ፤ መከፈቻውንም ያዘ፤ ያንጊዜም በሩ ተከፈተ:: ከመርከቡ ውስጥም "የልዑል እግዚአብሔር ካህን ሆይ! ደስ ይበልህ" የሚል ቃል ተሰማ:: ትከፈትልህ ዘንድ አንተ የተገባህ ሆነሃልና:: በመጀመሪያ ዓለምን የፈጠረ የእግዚአብሔር ካህን ሆይ! የሚል ቃልም ነበር፤ ይህም ከመንፈስ ቅዱስ ነበር፤ መልከ ጼዴቅም በቃሉ እርሱ በፊቱ እፍ ያለበት እንደሆነ ዐወቀ:: ዳግመኛም በውስጡ ያለውን ታላቅ ጸጋ ተረዳ፤ አደነቀም::

ሴምንም ጌታዬ ሆይ! በፊቴ እፍ ያለብኝ፣ እንደሆነ ዐውቃለሁ:: ከእኔ ጋር የሚነጋገር ድምፅ እሰማለሁ፤ ፊቱን ግን አላይም:: ከአባታችን ከአዳም ሥጋ አንድ ስንኳ ይህን አላየም:: ሴምም ደነገጠ፤ የሚለውንም ዐላወቀም:: እነርሱም በመርከቡ በር ይህን እያደነቁ ሳሉ ካህን ያደረግሁህ እኔ ነኝ የሚል ቃል ከሰማይ መጣ:: ከቦታዬም በውስጥህ እፍ አልሁብህ፣ አንተም እውነተኛ ካህኔ ነህ፤ አንተም የፈጠርኩትን የአዳምን ሥጋ ትሸከም ዘንድ የተገባህ ሆንህ:: ከቦታዬም እፍ አልሁብት፤ ካህንም፣ ንጉሥም፣ የጽድቅ ነቢይም አደረግሁት:: መልከ ጼዴቅ ሆይ! ግባና ሥጋውን አውጣ፤ አለው::

ወደ መርከቡም ገባ፤ የአባታችን የአዳምን ሥጋም እጅ ነሣ፤ ተባረከም፣

አወጣውም:: መልአኩ ሚካኤልም እስከ ማሸከም ድረስ ይረዳው ነበር:: ዳግመኛም ሴም ገባ:: ወርቁን፣ ዕጣኑን፣ ከርቤውን ከአባታችን ከአዳም ሥጋ ጋር አወጣው:: ሥጋውንም ከሣጥኑ አደረጉት፤ ዘጉትም? ዳግመኛም ጥንት እንደነበረው የመርከቡን በር ዘጉ:: ሴምም መልከ ጼዴቅን የአባታችን የአዳምን ሥጋ ያዝ  አለው::

ወደ መንገድም ሄዱ:: የእግዚአብሔር መልአከም ከእነርሱ ጋር ይሔድ ነበር፤ የሚሄዱበትንም ይመራቸው ነበር፤ እስከ ምሽት ሂደውም ወደ ሚያርፉበት ቦታ ወረዱ:: መልከ ጼዴቅና ሴምም ይጸልዩ ዘንድ ቆሙ፤ ሲጸልዩም ከአዳም ሥጋ ሣጥን እንዲህ የሚል ቃል ወጣ:: ለፈጠረኝ፣ ለአዳነኝ፣ ለአሳረፈኝ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን፤ ዳግመኛ እርሱ ከእርሷ ወደ ፈጠረኝ ወደ መሬት ይመልሰኛል:: ቃሉ ግን ጐልማሳው መልከ ጼዴቅን ባረከው፤ ከዘራችን ሁሉ እንደአንተ አንዱን ስንኳ እግዚአብሔር አልመረጠውም፤ ከእርሱም ያለ እንደአንተ ካህን ይሆን ዘንድ በእጁ አልቀባም፤ በአንተ ላይ እፍ እንዳለም በአንዱ ፊት ስንኳ እፍ አላለም:: ልጄ ሆይ! እኔ ግን በእግዚአብሔር ዘንድ ለዚህ ክብር የተገባህ ሆነህ ስለተገኘህ ደስተኛ ነኝ፤ ቃሉም ከመልከ ጼዴቅ ቆመ::

መልከ ጼዴቅም ከውስጥ ከሚመጣው ቃል የተነሣ አደነቀ:: ነገር ግን ይህ በእግዚአብሔር ኀይል ሆነ:: ሴም ይህን ድንቅ ተአምር በተመለከተ ጊዜ በመልከ ጼዴቅ ተደነቀ:: ከደስታው ብዛት የተነሣም በዚህም ሌሊት ምግብ አልቀመሰም:: እግዚአብሔርን ያመሰግን ዘንድ አዳም ባለበት ሣጥን ፊት ቆሞ ቀረ እንጂ፤ እስኪነጋም ይጸልይ ነበር::

መልከ ጼዴቅ ይህን ራእይ የተመለከተውም በዐሥራ አምስት ዓመቱ ነው:: ሴምና መልከ ጼዴቅም ሣጥኑን በአህያ ላይ ጫኑ፣ የእግዚአብሔር መልአከም ከእነርሱ ጋር ይሄድ ነበር:: ከሚያስቸግሩ ቦታዎች በደረሱ ጊዜም መልአኩ በእግዚአብሔር ኀይል ይመራቸው፣ በእርሷም ያሳድራቸው ነበር::

ባሕሮችም፣ ተራሮችም ቢሆኑ በሁለተኛው ቀንም እስኪመሽ ድረስ በመንገድ ይሄዱ ነበር፤ እንደልማዳቸውም ያርፉ ዘንድ ወረዱ።

መልከ ጼዴቅም ከእርሱ ጋር የእግዚአብሔር ኀይል እንዳለ ተረዳ። እነርሱም ወደ ስርግ እንደሚሄዱ ደስተኞች ሆኑ። እንደልማዳቸውም በአባታችን በአዳም በድን ፊት ይጸልዩ ዘንድ ቆሙ። ከበድኑም ለመልከ ጼዴቅና ለሴም እንዲህ የሚል ቃል መጣ እግዚአብሔር ወደ ወሰነልን ቦታ እነሆ! ደረስን። ቃልም መልከ ጼዴቅን የምንሄድባት ምድር የእግዚአብሔር ኀይል በእርሷ ላይ ይወርዳል። ሥጋዬም በሚኖርበት በዚህ ቦታ ይሰቀላል፤ ይታመማል። በደሙም መሐል ራሴን ያጠምቀኛል። በዚህን ጊዜ መዳኛዬ ይሆናል፤ ወደ ክብሬም ይመልሰኛል። ክህነቴን፣ ትንቢቴንም ይሰጠኛል /ይመልስልኛል/። ቃሉም በእግዚአብሔር ኀይል ዝም አለ። ከእነርሱ ጋር ስለሚነጋገረው ቃልም መልከ ጼዴቅና ሴም አደነቁ። መልከ ጼዴቅም ሌሊቱን ሙሉ እስኪነጋ ድረስ ይጸልይ ዘንድ በደስታ ቆመ።

የአባታችን የአዳምን ሥጋም በአህያ ጫኑ። ወደ መንገድም ሄዱ። የእግዚአብሔር መልአክም ከቦታው እስኪደርሱ ድረስ ከእነርሱ ጋር ነበር። የእግዚአብሔር መልአክም ቀድሞ በአህያው ፊት ቆመ። በድኑ /የአዳም ሥጋም/ ለብቻው ከአህያው ወረደ። እንደ መጀመሪያው እንደ ሁለቱ ፊጽሞ መልከ ጼዴቅ ያወረደው አይደለም። በድኑ /የአዳም ሥጋ/ ከዐለቷ በደረሰ ጊዜ [ዐለቷ] ከሁለት ተከፈለች /ተሰነጠቀች/፤ የበድኑ ማስቀመጫም ሆነች።

ሴምና መልከ ጼዴቅም እግዚአብሔር የፈቀደው ቦታ እንደ ሆነ ተረዱ፤ መልአኩም ከእነርሱ ወደ ሰማይ ወጣ። ለአምላክነቱ የአዳም ሥጋ ወደ ቦታው መጣ፤ ምን ላድርግ? ይል ዘንድ የእግዚአብሔር ቃልም እንዲህ ሲል ወደመልአኩ መጣ። ወደ መልከ ጼዴቅ ውረድ፤ ልቡንም አጽናናው፤ በአዳም ሥጋ በአጠገቡ ይቀመጥ ዘንድም እዘዘው፤ ሴም ባረፈ ጊዜም ከሴም ኀብስት ከእርሱ ጋር ያለ ኀብስትንም ይወስድ ዘንድ እንዲሄድ እዘዘው፤ በእርሱ ዘንድም

ይጠብቀው አለው፡፡

የእግዚአብሔር መልአከም ከሰማይ ወረደ፤ በሰው አምሳልም ለመልከ ጼዴቅና ለሴም ታያቸው፡፡ ልቡናቸውንም አበረታታቸው፤ የአባታችን የአዳምን ሥጋም በዚህ ቦታ አስቀመጠው፡፡ መልከ ጼዴቅንም ከሴም ኅብስትንና ወይንን ውሰድ አለው፡፡ መልከ ጼዴቅም መልአኩ እንደነገረው ኅብስትንና ወይኑን ወሰደ፤ ከጥዋት እስከ ማታም በሥጋው ላይ ይጸልይ ዘንድ ቆመ፤ በሥጋው ላይም ታላቅ ብርሃን ወረደ፡፡ መላእከትም በዚህች ቦታ ወደ አባታችን ወደ አዳም ሥጋ ይወጡ፣ ይወርዱ ነበር፡፡ እርሱም ደስተኛ ነበር፣ እንዲህ ሲልም ያመሰግን ነበር፡፡ ጌታዬ ሆይ! ዓለማትን የፈጠርህ፣ መሬታውያንንም የፈጠርህ፣ ከሰማያውያን የሚሻሉም ያደረግሃቸው[107] አምላኬ ሆይ! ምስጋና ለአንተ ይገባሃል፡፡

መላእከትም በአባታችን በአዳም ሥጋ ላይ እስኪነጋ ድረስ እንዲህ ያደርጉ ነበር፤ ፀሐይ በወጣ ጊዜም የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል ወደ መልከ ጼዴቅ መጣ፡፡ ከእነዚህ ድንጋዮች ዐሥራ ሁለት ድንጋዮችን ውሰድ፤መሠውያም አድርጋቸው፡፡ በእነርሱ ላይም በሴም ዘንድ ካለው ከኅብስቱና ከወይኑ ዐሳርግ፤ እርሱም አንተም ተቀበሉት፡፡

መልከ ጼዴቅም የእግዚአብሔርን ቃል በሰማ ጊዜ በተራራው መካከል ሰገደ፤ እግዚአብሔር እንዳዘዘውም ፈጥኖ አደረገ፡፡ በመሠውያው ላይ ቊርባንን በዐሳረገ ጊዜም እግዚአብሔር ይቀድስለት፣ /ይባርከው/ ዘንድ ፈለገ፡፡ መንፈስ ቅዱስም በቊርባኑ ላይ ወረደ፤ ተራራውም ብርሃንን ተመላ፡፡ መላእከትም ምስጋና ይግባውና ይህ ቊርባን መሬታውያንን በፈጠረ፣ ታላላቅ ምሥጢራትንም በገለጠላቸው በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለው ነው አሉ፡፡ የእግዚአብሔር ቃልም ለመልከ ጼዴቅ ታየው፡፡ እነሆ! ካህንም አድርጌሃለሁ፤ አንተ ያሳረግኸውን ይህን ቊርባን በመጀመሪያ አንተና ሴም ተቀበሉት አለው፡፡



[107] ዘፍ.፩+፳፮-፳፰

አንተ እነዚህን ዐሥራ ሁለት ድንጋዮች ለጽኑዕ መሠረትነት እንዳቆምህ፣ እኔም የዓለም አዕማድ የሆኑ ዐሥራ ሁለት ሐዋርያትን አቆማለሁ /አስነሣለሁ/፡፡[108] እነርሱም ጽኑዓን ናቸው፡፡ ይህን መሥዋዕት እንዳዘጋጀህ እኔም እንዲሁ በዓለም ሁሉ መሥዋዕትን አዘጋጃለሁ፡፡ ኅብስትንና ወይንን ቁርባን አድርገህ እንዳሳረግህ እኔም እንዲሁ ሥጋዬንና ደሜን ቍርባን አድርጌ ዐሳርጋለሁ፡፡ የኃጢአት ማስተስረያም አደርገዋለሁ፡፡[109]

አንተ የቆምህባት፣ የአዳም ሥጋም ያለበት ይህን ቦታ በምድር ያሉ ፍጥረታት ሁሉ ይባረኩበት ዘንድ እኔ የተቀደሰ ቦታ አደርገዋለሁ፤ ወደዚህ ለሚመጡት ሁሉ ኀጢአትን የሚያስወግድ አደርገዋለሁ፡፡ የእግዚአብሔር ቃልም መልከ ጼዴቅን ባረከው፤ ካህንም አደረገው፤ ከመላእክት ጋርም በደስታ፣ በምስጋና ወደ ሰማይ ዐረገ፡፡

መልከ ጼዴቅም እግዚአብሔርን አመሰገነው፡፡ እርሱም ሴምም ቁረቡ /መሥዋዕቱን ተቀበሉ/፡፡ ሴምም በመንገድ ከነበረው ድካም ያርፍ ዘንድ ከእርሱ ጋር ይህችን ቀን ተቀመጠ፡፡ በነጋ ጊዜም ሴም ይሄድ ዘንድ ተዘጋጀ፤ ከመልከ ጼዴቅ ጋርም ተሰማሙ፤ ባረከውም፡፡ ከአንተ ጋር ከዚህ ቦታ እስከንደርስ መሪያችን የሆነ እግዚአብሔር አምላክም ወደ ቦታህ እስክትደርስ ይምራህ፤ አለው፡፡ ዳግመኛ መልከ ጼዴቅ ሴምን አባቴ እና እናቴ ስለእኔ በጠየቁህ ጊዜ ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ መንገድ አትምራቸው፤ ተሰወረ፤ አሰዋወሩ እንዴት እንደሆነ ግን አላውቅም በላቸው አለው፤ ይህን በምትላቸው ጊዜ ተስፋ ይቆርጣሉ፡፡ በአንተ ላይ እንዳይከብዱብህ፤ ትመጣ ዘንድም እንዳያስገድዱህ፣ ሐሳባቸው ይጠፋል /ይሟጠጣል/፡፡

ሴምም ሄደ፤ ወደ ዘመዶቹም ተመለሰ፡፡ መልከ ጼዴቅም እግዚአብሔርን ያገለግል ዘንድ፣ ሁል ጊዜም ያመልከው ዘንድ በአባታችን በአዳም ሥጋ /በድን/ ፊት ቁሞ ቀረ፤ መልአኩም ይጠብቀው ነበር፡፡ እስከ ታላቁ ሸማግሌ እስከ <u>አብርሃም ዘመንም</u> ምግቡን ያመጣለት ነበር፡፡

[108] ማቴ.፲፥፩-፬
[109] ማቴ.፳፮፥፳፯

የመልከ ጼዴቅ ልብሱም ቆዳ /ሌጦ/፣ በወገቡ ያለ መታጠቂያውም ሌጦ ነበር፡፡ በታላቅ ጾምና ጸሎትም ለእግዚአብሔር ይገዛ ነበር፡፡ ሴምና ልጆቹም በምድር ላይ በዙ፤ ተባዙም፡፡ ልጆችን፣ የልጅ ልጆችንም ወለዱ፤ ለሴም ዐምስት መቶ ሃምሳ ዓመት እስኪሆነው እንዲህ ሆኑ /ተገዙ/፡፡ ሴምም ሞተ ፤ገነዙትም፤ አርባ ቀንም ሲያለቅሱለት ቆዩ፡፡

ከዚህ በኋላ የሴም ልጅ አርፋክስድም አራት መቶ ስልሳ ዐምስት ዓመት ኖረ፤ ሞተም፤ ገነዙትም፤ አርባ ቀንም አለቀሱለት፡፡ ከዚህ በኋላም የአርፋክስድ ልጅ ቃይናም እርሱም የመልከ ጼዴቅ አባት ነው፡፡ ዐምስት መቶ ስልሳ ዘጠኝ ዓመት ኖረ፤ ሞተም፡፡ ከዚህ በኋላም የቃይናም ልጅ የመልከ ጼዴቅ ወንድም ሳላ አራት መቶ ስምንት ዓመት ኖረ፤ ከዚህ በኋላ ልጁ ኤቦር አራት መቶ ሠላሳ አራት ዓመት ኖረ፤ ሞተም፡፡

ፋሌቅም በአባቱ ዘመን በሁለት መቶ ሦስት ዓመት ተወለደ፤ በፋሌቅ ዘመንም ሦስቱ የኖኅ ልጆች ምድረ ርስትን ተካፈሉ፡፡[110] እነዚህም፥ ሴም፣ ካም፣ ያፌት ናቸው፡፡ ስለዚህም እርስ በርስ በመለያየታቸው ታላቅ ኃዘን ሆነባቸው፡፡ በአባታቸው ሕይወት በመሰብሰባቸው፣ ከመለያየት የተነሣም ታላቅ ድንጋጤ ደረሰባቸው፤ በዚህች ጊዜም ተለያዩ፡፡

ፋሌቅም ሞተ፤ በሀገሩም ቀበሩት፤ እነርሱ ሀገር መሥርተዋልና ስሟንም በእርሱ ሰይመዋታል፡፡ አሟሟቱም በአራት መቶ ሠላሳ ዓመቱ ሕንፃን በሠሩ ጊዜ እግዚአብሔር ለያይቷቸዋልና፡፡ በእነርሱ ላይም አፈረሰው ከእነርሱ የተረፉትንም ቋንቋቸውን ለያየው፡፡ እነርሱ ያለልክ ሠርተዋልና፡፡ ስለዚህም እግዚአብሔር ለያያቸው፤በታተናቸው፡፡[111]

ከዚህ በኋላም በእነርሱ ላይ መከፋፈል ሆነ፤ አንዱ የተናገረውን ሌላው እስከማያውቅ ድረስ፤ የቋንቋዎቹ ቁጥርም ሰባ ሁለት ነው፡፡ ከያፌት ዘር ሰባት ሕዝቦች ነበሩ፤ ዳግመኛ የፋሌቅ ልጅ ራግው ሁለት መቶ ሠላሳ ሁለት ዓመት ኖረ፤ ሞተም፡፡ ከዚህም በኋላ የራግው በኵሩ መቶ ሠላሳ

110 ኵፋ.፰+፴

111 ዘፍ.፲፩+፮-፱

ዓመት ኖረ፣ በመጨረሻውም በምድር ላይ ከእነርሱ አንዱ ነገሠ:: የዚህ ንጉሥ ስምም ራዓይታይ ናምሩድ ይባላል:: ይህ ናምሩድም በሰይጣን አማካኝነት ከሰማይ የምታበራ ደመናን ተመለከተ:: ልቡን አዘነበለ፣ ደምግባቷንም ወደደ::ስንጣል የተባለውን አንዱን ሠዓሊም ጠራው፤ የወርቅ አክሊልን እንደዚህች ደመና አድርገህ ሣልልኝ አለው:: እርሱም ይህን አክሊል ሠራለት፤ናምሩድም ወስዶ በራሱ ላይ አደረገው:: ስለዚህም ደመና ከሰማይ መጣች ይሉ ነበር፤ አምላክ ነኝ ብሎ እስከማሰብም ደረሰ:: የዚህ የራግው ዘመንም አጠቃላይ መቶ ሠላሳ ነበር፤ በመቶ ሃምሳ ዓመት በራግው ዘመን በግብጽ ምድር ያኑፍ ነገሠ:: ይህ ንጉሥም በመጀመሪያ ነገሠ፤ ያኑፍም የመኒኑፍ ሀገርን መሠረተ፤ በስሙም ሰየማት፣ የዚህች ምድር የስሟ ትርጉምም ምስሬን ማለት ነው፤ እርሱም ሞተ::

በቦታውም በራግው ዘመን የሳባን ሀገር የሠራ፣ ከሕንደኬም ምድር ስሙ ስቤን የሚባል ነገሠ:: በዚህች ሀገር የነገሡት ሁሉም እንደ ሀገሩ ስም ሳባውያን ይባላሉ:: እስከ ሰሎሞን ንግሥና ድረስ እንዲህ ሆኑ፣ ከዚህ በኋላ በወርቅ ድንጋዮች ሶሪር የተባለች ሀገርን የሠራ ፊርዖን በሳፊር ልጆች ላይ ነገሠ፤ ይህችም የሦርዓንያ ሀገር ናት::

ስለ ወርቅ ድንጋዮችም የዚህች ሀገር ተራሮች፤ ድንጋዮች ወርቅ ናቸው ይላሉ:: በሕንደኬ ምድር ከሚኖሩ ከስቤንሳ ልጆች ብህሉ የተባለች ሀገርን ያቀና ስሙሙ ብህሉል የተባለውን በእነርሱ ላይ አነገሠ:: ራግውም በሁለት መቶ ሠላሳ ሰባት ዓመት ዐረፈ:: ከዚህ በኋላ የነገሠው በዘመኑ በዓለም የድንጋይ ጣዖትን ማምለክ የተስፋፋበት ሴሩህ ነበር:: የሰው ልጆች የድንጋይ ጣዖታትን መሥራት ጀመሩ::

የመጀመሪያዎቹም ከሲጦን እና ሔሎዶን ነበሩ:: የሰው ልጆችም በምድር ላይ በዙ:: ከፋታቸውም በዛ፤ ሕግና ሥርዐት አልነበራቸውምና፤ የሚያስተምሯቸውም መምህራን አልነበሩም::

በእያንዳንዳቸው የሚፈርድም አንድ ስንኳ አልነበረም፡፡ ስለዚህም ከእግዚአብሔር መንገድ ጠፉ፤ ራቁም፡፡ እያንዳንዱም ሰውነቱ የወደደችውን ያደርግ ነበር፡፡

ያማልከትን ጣዖታት ይሠሩ፣ ይሰግዱላቸውም ነበር፡፡ የሙታን መካሻትንም ተስፋ አያደርጉም፤ ከእነርሱ አንዱ ሲሞት ይቀብሩታል፡፡ በመቃብሩ ላይም ጣዖታትን ያቆማሉ፤ አምላኩ ይህ ነው፤ በመቃብሩም ይማረው ይሉ ነበር፡፡ ስለሞተ ሰውም በመቃብሩ ላይ አምላኩ ባሰበ ጊዜ መታሰቢያው ከምድር ገጽ አይቋረጥም፤ ይሉ ነበር፡፡ ሰይጣን ያመጣው ይህ ምስል በጣዖትነት ምድርን ሁሉ ሞላ፡፡ ጣዖቶቻቸውም የወንዶችና የሴቶች ምሳሌዎች ነበሩ፡፡

ከዚህ በኋላ ሴሩህ በሁለት መቶ ሠላሳ ዓመት ሞተ፡፡ ገንዘውም በስሙ በተሠራች በሀገሩ በውርአንያ ቀበሩት፡፡ ከዚህ በኋላ ናኮር ሃያ ዘጠኝ ዓመት በሆነው ጊዜ ታራን ወለደው፡፡ ለናኮር ሥልሳ ሰባት ዓመት ሲሆነውም እግዚአብሔር የሰው ልጆች እንደጠፉ፣ ለጣዖትም እንደሰገዱ ተመለከተ፡፡ ጣዖታቱ እርስ በርሳቸው እስኪንቀጠቀጡ ድረስ አውሎ ነፋስን አመጣ፣ ምድርንም አነዋወጣት፡፡ የሰው ልጆችም ከኀጢአታቸው ያድናቸው ዘንድ ወደ እግዚአብሔር አልተመለሱም፤ በከፋታቸው ላይ ከፋትን ጨመሩ እንጂ፤ ታራ በነበረበት በሃያ ዘመን አምልኮ ጣዖት ከምድር ገጽ ጠፉ፡፡ የዕቤር ልጅ በርዊን ወደሠራት እህረት ወደ ተባለች ሀገር ተወገደች፡፡

በዚህ ዘመንም በዚህ የሚኖር ባለጸጋ ሰው ነበር፤ ሞተም፡፡ ልጁም በአባቱ አምሳል የወርቅ ጣዖት ሠራ፤ በመቃብሩም አስቀመጠው፡፡ ከአገልጋዮቹ አንዱንም ከጣዖቱ ጋር ይቆምና አካባቢውንም ያጸዳ ዘንድ፤ ውኃም ይደፋበት፤ ያጥነውም ዘንድ አዘዘው፡፡

ሰይጣንም ይህን በተመለከተ ጊዜ በወርቁ ጣዖት አደረ፡፡ በሞተ በጌታው አምሳልም ከአገልጋዩ ጋር ተነጋገረ፡፡ ከዚህ በኋላ የሞተው ልጅ

ጕልማሳውንም ሸነገለው /አታለለው/:: እያለቀሰም ወደ አባቱ መቃብር መጣ:: እርሱም አባቴ ሆይ! ገንዘቦቼ ሁሉ ከእኔ ራቁ አለ:: ሰይጣንም እንዲህ ሲል መለሰለት:: ዛሬ አትቁም፤ ሄደህ ልጅህን አምጣ፤ መሥዋዕት አድርገህም ለእኔ አቅርብልኝ፤ እኔም ገንዘብህን ሁሉ እመልሳለሁ አለው::

ጕልማሳውም በልጁ ላይ ሰይጣኑ እንዳዘዘው አደረገ፤ በዚህ ጊዜ ሰይጣን አደረበት፤ ሥራይን፣ ምትሐትን፣ ጥንቆልናን ማድረግን አስተማረው፤ ይህም መጀመሪያ ሰዎች ልጆቻቸውን ለጣዖት፣ ለሰይጣን ወስደው መሥዋዕት አድርገው ያቀረቡበት ምሳሌ ነው:: እግዚአብሔር በናኮር ዘመን በመቶ ዓመት ለጣዖት ልጆቻቸውን የሚሠው የሰው ልጆችን ተመለከተ:: እግዚአብሔርም የነፋሳት መዛግብት ይከፈቱ ዘንድ አዘዛቸው:: በምድር ላይ የጣዖታቱ ምስላት፣ ሁሉም እስኪሰበሰቡ ድረስ ዓውሎ ነፋስን፣ ጉሞችን አመጣ::

ተራሮችም ፈጽመው ታላላቅ ነበሩ:: እስከዚህች ዕለት ጣዖታቱ ተቀብረው ቀርተው ነበር:: ብዙ ጥበበኞች ይህ ነፋስ የጥፋት ነፋስ እንደሆነ ጻፉ:: ከእነርሱ ብዙዎችም የጥፋት ውኃ ነው አሉ:: ተራሮችንም የሰበሰበ እርሱ ነው አሉ:: እንደዚህም ሳቱ፤ በዚህም ዋሹ፤ ምድር የጥፋት ውኃ ከመምጣቱ በፊት ጣዖታቱ፣ ምስላቱ ሳይኖሩ ነበረችና:: እርስ በእርሳቸው በደልን፣ ኀጢአትን በማድረጋቸው በዚህ ዘመን በሰዎች ላይ ጥፋት መጣ እንጂ:: እነዚህም የቃኤል ልጆችን የተከተሏቸው ናቸው::

ዳግመኛም በዚህ ዘመን የሴት ልጆች ከነበሩባት ከገነት ምድር /ደብር ቅዱስ/ በስተቀር መሬት ሁሉ በሰው የተመላች አልነበረችም:: የቃኤል ልጆች የነበሩባት ቦታም ከዚህ በኋላ ራቁቷን /ባዶዋን/ ቀረች:: ጥፋት በመጣ ጊዜ መርከቧን ተሸከማት:: እስከዚህች አድካሚ ምድርም አመጣት፤ ይህች ምድርም ከሰው የተነሣ መላች:: ዳግመኛም ምድሪቱ ምድረ በዳ ሆነች:: በንጉሡ በናምሩድ ዘመንም በምሥራቅ በኩል እሳት ሲንበገበግ ተመለከተ:: ይህችም /እሳት/ ከምድር ትወጣ ነበር:: ናምሩድም ይህቺ እሳት ምንድን ናት?

አለ። ወደ እርሷም ሄደ፤ ባያት ጊዜም ሰገደላት፤ ዕጣንን ያሳርግ፤ መሥዋዕትም ያቀርብ፣ እንዲሁም ያገለግልም ዘንድ በእርሷ ዘንድ ካህን /አገልጋይ/ አዘጋጀ።

በዚህ ዘመንም የፋርስ ሰዎች እሳትን ማምለክ ጀመሩ። ጣዖታትን የሚያዘጋጅ ሰይጣንም ከእሳቱ ጉድጓድ ቅርብ የሆነ ውኃን ተመለከተ። ወደ እርሷም መጣ፤ አያትም፤ የወርቅ ፈረስም አደረገ /አዘጋጀ/፤ በውኃ ዳርም አቆመው። በዚህች ውሃ የሚታጠቡትም ለወርቁ ፈረስ ይሰግዱለት ነበር። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የፋርስ ሰዎች ለፈረስ መስገድ ጀመሩ። ናምሩድ፣ ያስቀመጠው ካህንም ለእሳቱ ይገዛ /ያገለግል/፣ ያጥንም ነበር። በአራተኛው በኖኅ ልጅ በረዊን እንደ ናምሩድ ጥበበኛ መምህር ይሆን ዘንድ ወደደ። ናምሩድ እንዳደረጋት ይህ ካህን ጣዖት ሰይጣንን ይለምን ነበር። እርሱም በእሳት ፊት ቆሞ ነበር። ሰይጣንም በረዊን ለእርሱ እንደተገዛለት ቁሞ በተመለከተው ጊዜ ከእርሱ ጋር ተነጋገረ።

በእኔ ዘንድ ሰው መምህር፣ ጥበበኛ፣ ታላቅ ሊሆን አይችልም፤ ከእኔ ቢሰማ ከእኔ ጋርም እናቱን፣ እኅቱን፣ ልጁን ያስተምር ዘንድ ይሄዳል እንጂ አለው። እርሱ እንዳዘዘውም ሰማ፤ ጥበባትን፣ ክፋትን ሁሉ አስተማረው። በዚህች ጊዜም የፋርስ ሰዎች እስከዚህች ዕለት ድረስ ኀጢአትን መሥራት ጀመሩ፤ ናምሩድም በምሥራቅ በኩል ታላላቅ ሀገሮችን ሠራ።

ለታራ ሁለት መቶ ሠላሳ ዓመት ሲሆነው ታመመ፤ ታራም ልጁ አብርሃምን ጠራው። ልጄ ሆይ! እኔ እሞት ዘንድ እወዳለሁ፥ አለው። አብርሃምም ቆሞ አጽናናው። አከበረውም፤ እርሱ ጣዖታትን ስለሚሠራም ይኸ በመሆኑ አብርሃምን አላሳዘነውም።

ልጁ አብርሃም ግን ጻድቅ ሰው ነበር። ጣዖታትን የሚወድም አልነበረም። እርሱ አባቱ ስለሆነ አከበረው እንጂ። ታራም ሞተ፤[112] አብርሃምና ናኮርም ወስደው በተራራው ላይ ቀበሩት።

ልማናቸው፣ አማላጅነታቸው ከሊቃነ ጳጳሳቱ አለቃ ከአባ

ባስልዮስ፣ ከንጉሣችን ከኀይለ ሥላሴ ጋር ይሁን፤ ለዘለዓለሙ አሜን።

## ምዕራፍ ዐሥራ አንድ

## ገድለ አዳም ዘየካቲት

አንድ አምላክ በሆኑ በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም የካቲት ስድስት ቀን የሚነበብ የአባታችን የአዳም፣ የእናታችን የሔዋን የገድላቸው ዜና ይህ ነው። ጸሎታቸው፣ በረከታቸው፣ የይቅርታ ልመናቸው ከጸጸሳቱ አለቃ ከባስልዮስ፣ ከንጉሣችን ኀይለ ሥላሴ፣ ከሰማንው፣ ከአንባቢውም ጋር ይሁን፤ ለዘለዓለሙ አሜን።

አብርሃም ባደገ ጊዜም እግዚአብሔር አብርሃም ሆይ! ከሀገርህ፣ ከወገንህ፣ ከአባትህም ቤተሰብ ተለይተህ ውጣ። እኔ ወደ ማሳይህ ሀገርም /ምድርም/ ና አለው።[113] አብርሃምም ተነሥቶ ሚስቱ ሣራን የወንድሙን ልጅ ሎጥን ያዘ፤ ወደ አሞራውያን ሀገርም መጣ። አብርሃምም ይህን ራእይ ባየ ጊዜ ሰብዐ ዓመት ሆኖት ነበር። ይህም ምንጩ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ በሆነው በኤፍራጥስ[114] መሻገሩ የመጀመሪያው ነበር፤ አብርሃምም መጥቶ በነገሥታቱ መካከል ተቀመጠ።

ነገሥታቱም በወንድሙ ልጅ ተነሡበት፤ ማረኩትም፤ አብርሃምም አገልጋዮችን፣ አሽከሮቹን ሁሉ ይዞ ወደ ወንድሙ ልጅ ደረሰ። ከእነርሱም አዳነው።[115] በዚህን ጊዜም ለአብርሃም ሰማንያ ዓመት ሆኖት ነበር። ልጅም አልወለደም ነበር። ሚስቱ ሣራ መካን ነበረችና። ከነገሥታቱ ጋር ተዋግቶ በተመለሰ ጊዜም በናቡስ ላይ እስኪያልፍ ድረስ የእግዚአብሔር ጸጋ ሳበችው። ከናቡስ በኋላም ከመሠራቷ በፊት ወደ ኢየሩሳሌም አቅራቢያ ደረሰ።

የልዑል እግዚአብሔር ካህን መልከ ጼዴቅም መጣ፤ በደስታም ተቀበለው። አብርሃምም መልከ ጼዴቅን በተመለከተ ጊዜ ፈጥኖ

---

[113] ዘፍ.፲፪+፩-፫፣ ኩፋ.፲፩+፲

[114] "ኤፍራጥስ" ከአራቱ አበይት ወንዞች አንዱ ነው። እነዚህም ጤግሮስ፣ ኤፍራጥስ፣ ኤፌሶን፣ ግዮን ናቸው። /ዘፍ.፪+፲፬/.

[115] ዘፍ.፲፬+፲፬

ሰገደለት፤ አፉንም ሳመው፡፡ መልከ ጼዴቅም አብርሃምን መልካም ቡራኬን ባረከው፡፡ አብርሃምም በእርሱ ዘንድ ካለው ሁሉ ከዐሥር አንድ ለመልከ ጼዴቅ ሰጠው፡፡[116]

ከዚህ በኋላ አብርሃምም በመልከ ጼዴቅ እጅ ከተቀደሰው /ከተባረከው/ ምስጢራተ ቅድሳት /ኅብስተ አኮቴት፣ ጽዋዐ በረከት/ ተቀበለ፡፡ ይህ ቦታ ታላቅ ነውና፡፡ መቀባቱ /መሾሙ/ በሰው እጅ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ነውና፡፡ አብርሃም ከመልከ ጼዴቅ በተቀበለ /በቁረበ/ ጊዜ እግዚአብሔር አብርሃምን በፊቴ ታላቅ ፍርሀትን አትፍራ፤ አገልጋዬ መልከ ጼዴቅ እንደባረከህ፣ በምሥጢራተ ቅድሳትም ከእርሱ ጋር አንድ እንዳደረገህ፣ እኔም ሰማያዊት በሆነች ጸጋ ከእርሱ ጋር አንድ አደርግሃለሁ፡፡

ዳግመኛም እግዚአብሔር አብርሃምን እኔ መባረክን እባርክሃለሁ፤ ዘርህንም በምድር ላይ መብዛትን አበዛሃለሁ÷[117] አለው፡፡ ከዚህ በኋላ በፍልስጥኤም ምድር ራብ ሆነ፡፡ አብርሃምም ወደ ግብጽ ምድር ወረደ[118] ሚስቱ ሣራም ከእርሱ ጋር ነበረች፡፡ ለሚያያትም መልከ መልካም ነበረች፡፡

አብርሃም ሣራን እንዳይገድሉኝ፣ አንቺንም እንዳይወስዱ እኔ እኅቱ ነኝ በይ እንጂ የአብርሃም ሚስቱ ነኝ አትበይ አላት፡፡ ግብጽ በደረሱ ጊዜም ከዚህ ሰው አለ፤ ከእርሱ ጋር ያለች እኅቱም መልከመልካም ናት ብለው ለግብጽ ንጉሥ ለፈርዖን ነገሩት፡፡ ፈርዖንም ልኮ ወደ እርሱ ወሰዳት፡፡ አብርሃምም እያለቀሰ ቀረ፡፡

ነገር ግን እግዚአብሔር ከምሕረቱ የተነሣ መልአኩን ላከ፤ ፈርዖንንም መታው፤ እግዚአብሔር እንዳይገድልህ የአብርሃምን ሚስት ወደ እርሱ መልስ አለው፡፡ በነጋ ጊዜም ፈርዖን አብርሃምን ጠራው፤ ይቅር በለኝም አለው፡፡ ሣራ ሚስቱንም ሰጠው /መለሰለት/፡፡ ግብጻዊቷ አጋርን ብዙ ሀብትንም ለእርሷ ሰጣት፡፡[119] ከዚህ በኋላ አብርሃም ሚስቱ ሣራን፣ አገልጋይዋ አጋርን ወስዶ ወደ

116 ዘፍ.፲፬+፲፰-፳.
117 ዘፍ.፲፪+፪



118 ዘፍ.፲፪+፲-፲፬
119 ዘፍ.፲፪+፲፮-፳

ፍልስጥኤም ምድርም ተመለሰ:: ከዚህ በኋላ አብርሃም አጋርን አገባት፤ እስማኤልንም ወለደችለት::

ለአብርሃምም ሰማንያ ሰባት ዓመት ሆነው:: አብርሃም ሣራ እኅቴ ናት፣ በማለቱ አልዋሸም፣ አባቱ ታራ ሁለት ሴቶችን አገባ:: የአንዲቱ ስሟ ቶና ነው፤ ይህችም የአብርናም እናት ናት:: አብርሃምን ከወለደችው ከትንሽ ጊዜ በኋላ ሞተች፤ዳግመኛም ታራ ስሟ ተሕዳፍ የሚባል ሌላ ሴት አገባ፤ ሣራንም ወለደችለት:: ይህችም /ሣራም/ አብርሃም ያገባት ናት፤ ስለዚህም በአባቴ በኩል እኅቴ ናት ፤በእናቴ ግን አይደለችም ሲል እኅቴ ናት አለ::

ከዚህ በኋላ አብርሃም በድንኳን ቤቶቹ ሆኖ በተመለከተ ጊዜ እግዚአብሔር ከመላእክቱ[120] ጋር ወደ እርሱ ደረሰ:: የልጁ የይስሐቅን ምልክትም ሰጠው:: ከዘመኖቹ በመቶኛው ዓመት መጨረሻ ላይ ከሣራ ይወለድለት ዘንድ እግዚአብሔርም ብዙ ምሥጢራትን አሳየው:: ከዚህ ጊዜ በኋላ እግዚአብሔር አብርሃምን አለው:: ይስሐቅ ዐሥራ አራት ዓመት በሆነው ጊዜ ልጅህ ይስሐቅን ቍርባን አድርገህ ዐሳርግልኝ /ሠዋልኝ/፤ አብርሃምም በረታ፤ በዚህች መከራም ጸና:: ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ይሆን ዘንድም ልጁን አመጣው:: እግዚአብሔርም በዕንጨት በታሰረ በግ ይስሐቅን አዳነው::[121] ዳግመኛም አብርሃም በጉ ታስሮ ያየባት ዕፅም በእርሷ ላይ የመስቀል ዕፅ ይተከልባታል::

ይስሐቅን ከሞት ያዳነው በግም ሁላችንንም ከሞት ያዳነ የእግዚአብሔር በግ /ክርስቶስ/ ምሳሌ ነው::[122] ይህ ተራራም[123] በውስጡ መልአኩ ቁሞ ንጉሥ ዳዊት ያየበት ነው:: በእጁም የተሳለ የእሳት ሰይፍ ነበር:: ኢየሩሳሌምንም ያጠፋት ዘንድ ወደደ፤ ይህ ቦታም አብርሃም በመንፈስ ቅዱስ ዐይን የወልደ እግዚአብሔርን ስቅለት ያየበት ነው፤ ስለዚህም እግዚአብሔር አይሁድን አባታችሁ አብርሃም ዕለቴን ያይ ዘንድ ወደደ:: አይቶም ተደሰተ አላቸው::[124] ዳግመኛም ይህ ቦታ ብፁዕ ጳውሎስ ስለ

120 ዘፍ.፲፰+፩-፩ ይህ ከዓለ ታሪክ እግዚአብሔር በሦስትነት እንደተገለጸበት ለማስጠረ ሥላሴን እንደሰጠ /ረዳው/ ያሳያል። ከመላእክቱ ጋር የሚለው ኃይለ ቃልም ለአንዳንዶቹ እንደሚመስላቸው የሥላሴን በአንድነት እና በሦስትነት የመገለጥ ምሥጢር የሚቃረን ሳይሆን ንጉሥ ባለበት ሰራዊቱም እንደሚገኙ ሁሉ ቅዱሳን መላእክትም ለተልእኮ ለምስጋና ከሥላሴ የማይለዩ መሆናቸውን ያመለክታል።

121 ዘፍ.፳፪+፩-፲፱

122 ዮሐ.፩+፳፱

123 ሞርያ ተራራ መሆኑን ልብ ይሏል

124 ዮሐ.፰+፶፮

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ ለግዝረት ተገዢ ሆነ ያለበት ነው፡፡ ይኸውም በስምንተኛው ቀን ክርስቶስ የተገረዘበት ነው፡፡

ዳግመኛም ታላቁ አባት አብርሃም ለእግዚአብሔር ቊርባንን ያሳረገበት ነው፡፡ ዳግመኛም በሙሴ ዘመን እንደነበረው ስለ ሕዝቡ ኃጢአት በግን ይሰዉ መሥዋዕቱም ከኃጢአታቸው ያነጻቸው ነበር፡፡

እንደዚህም የእግዚአብሔር በጉ ከኃጢአታችን እስኪያድነን ድረስ ራሱን ዐሳረገ /ሠዋ/፡፡ ከዚህ በኋላ መልከጼዴቅ ለሰው ተገለጠ፡፡ ዐዩት፣ በአነጋገሩም በቦታው ያሉ ሁሉ ተረጋጉ፡፡ የምድር ነገሥታት፣ አሕዛብ፣ ፍጥረታት ሁሉ ቃሉን በሰሙ ጊዜ ተሰበሰቡ፣ቁጥራቸውም ዐሥራ ሁለት ሰራዊት ነበሩ፡፡ ወደ እርሱ መጡ፣ በፊቱም ሰገዱ፣ ከእርሱም ተባረኩ፡፡ በእኛ ላይ እናንግሥህ ብለውም ለመኑት፣የልዑል እግዚአብሔር ካህን የሳሌም ንጉሥ መልከ ጼዴቅ [125] ግን አልወደደም፡፡

ነገሥታቱም ከደም ግባት የተነሣ አደነቁ፤ ልቡናቸውም ወደ አነጋገሩ ያዘነብል ነበር፡፡ ከእግሩ ጫማም ሰገዱ፤ ከእነርሱ ጋር በጠላቶቻቸው ላይ ይተባበር ዘንድ ለመኑት፤እርሱ ግን አልወደደም፡፡ ይህን ቦታ ትቼ ወደ ሌላ ቦታ ልሄድ አልችልም አላቸው፤ ነገሥታቱም እርስ በርሳቸው ተነጋገሩ፡፡ በዚህ ተራራ ለመልከጼዴቅ ሀገር እንሥራ ዘንድ ከእኛ እያንዳንዱ የሚቻለውን ሁሉ ያምጣ አሉ፤ ይህን ተግባርም በሙሉ ልባቸው ወደዱት /ተቀበሉት/፤ብዙ ገንዘብም ሰበሰቡ፡፡ ትርጓሜዋ የምድር መካከል[126] የተባለች የኢየሩሳሌም ሀገርንም ሠሩ፡፡ መልከ ጼዴቅም በዚህች ቦታ ነዋሪ ሆኖ ቀረ፤እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ፣ ከዚህ ዓለምም እስኪፈልስ /እስኪያርግ/ ድረስ ነገሥታቱም ወደ እርሱ እየመጡ ይባረካሉ፡፡

ከዚህ በኋላ አብርሃም ለልጁ ለይስሐቅ ሚስት ይወስድ ዘንድ ከአገልጋዮቹ አንዱን አዘዘው፤ ይስሐቅን ያለወገኑ እንዳያጋባውም አማለው፤[127]

125 ዕብ ፯+፩

126 የምድር መካከል /ማዕከለ ምድር/ ያላትም ክርስቶስ የተሰቀለባት ቀራንዮ ናት፡፡ መዝ. ?



127 ዘፍ.፳፬+፩-፱

አብርሃምም በመቶ ሰባ አምስት ዓመት ዐረፈ፤ ልጆቹ ይስሐቅና ይስማኤልም[128] ቀበሩት፡፡

ከዚህ በኋላ ይስሐቅ የአርባ ዓመት ጐልማሣ እያለ አገባ፤ ሥልሳ ዓመት ሲሆነውም ዔሳውንና ያዕቆብን ወለደ፤ እግዚአብሔርም ይስሐቅን መልካም ቡራኬን ባረከው፡፡ ከዚህ በኋላ ያዕቆብ ወደ እናቱ ወንድም ወደ ላባ ወደ ካራን ምድር ሄደ፡፡[129] ሁለት ልጆቹን ልያንና ራሔልንም አገባ፡፡ ከልያም ሮቤልን፣ ስምዖንን፣ ሌዊን፣ ይሁዳን፣ ይሳኮርን፣ ዛብሎንን ወለደ፤ከራሔል ዮሴፍን፣ ብንያምን ወለደ፤ ከልያ አገልጋይ ከዘለፋም ጋድን፣ አሴርን፣ ወለደ፡፡ ከራሔል አገልጋይ ከላበም ዳንን፣ ንፍታሌምን ወለደ፡፡ ከካራን ምድር ያዕቆብ ከመውጣቱ ከሃያ ዓመት በኋላ፣ አባቱ ይስሐቅም ከመሞቱ በፊት ወንድሞቹ በዮሴፍ ላይ ስለቀኑ ዮሴፍን ሸጡት፡፡[130] አባታቸው ይስሐቅ በሞተ ጊዜም ልጆቹ ያዕቆብና ኤሳው ወደ እርሱ መጡ፤ ገንዘውም በአባቱ መቃብር ቀበሩት፡፡ እርሱ ከሞተ ከሰባት ዓመት በኋላ ርብቃ ሞተች፤ በአብርሃም ሚስት በሣራ መቃብርም ቀበሯት፡፡[131]

ከእርሷ በኋላም የያዕቆብ ሚስት ልያ ሞተች፤ በእነርሱ ዘንድም ቀበሯት፡፡ ከዚህ በኋላ ይሁዳ ስሟ ደብዋዲያ የምትባል ሚስት አገባ፤ትርጓሜዋም የቤት እመቤት ማለት ነው፡፡ ሴዋም ትባላለች፤ እርሷም ከከነአናውያን ወገን ነበረች፤ ያዕቆብም ስለ እርሱ ፈጽሞ ልቡን አስጨነቀ፡፡ ይህችን ልጅ ያገባ ልጁ ይሁዳንም የአብርሃም የይስሐቅ አምላክ እግዚአብሔር ይህችን ከነናዊት ሴት ዘሯ ከወገኔ ጋር ይቀላቀል ዘንድ አይተው አለው፡፡

ከዚህ ዘመን በኋላ ሴዋ ሦስት ልጆችን ዔርን፣ አውናንን፣ ሴሎምን ከይሁዳ ወለደች፡፡ ልጁ ዔርን አባቱ ይሁዳ ሌዊ የተባለ የቃዴስ ልጅ የምትሆን ትእማር የምትባል ሴት አጋባው፡፡ ዔርም ከእርሷ ጋር ብዙ ዘመን ኖረ፡፡ እርሱም ከእርሷ ጋር እንደ ሰዶምና እንደ ገሞራ ሰዎች አደረገ፡፡

128 ይስማኤልን መጽሐፍ ቅዱስ እስማኤል ይለዋል
129 ዘፍ.፳፰+፩
130 ዘፍ.፳፯+፩-፲፬
131 ዘፍ.፳፱+፲፯-፳፩

እግዚአብሔርም ከፉ ሥራውን ተመለከተ፤ ይህን ስላደረገም ገደለው፡፡ ዳግመኛም ይሁዳ ለወንድሙ ዘርን ይተካ ዘንድ ትእማርን ለልጁ አጋባው፤ ወደ ሚስቱ ወደ ትእማርም ገባ፡፡ ከእርሷ ጋርም ብዙ ዘመን ተቀመጠ፡፡ በያዕቆብ ርግማን ምክንያት ዘሩ ከዘሯ ጋር እንዳይቀላቀል ወደ እርሷ በሚገባበት ከእርሷ ጋር በሚተኛበት ጊዜም ወደ እርሷ ከመምጣቱ በፊት በፊቲው ከመጨነቁ የተነሣ ዘሩን በምድር ያፈሰው ነበር፤ እግዚአብሔርም ከፉ ሥራውን በተመለከተ ጊዜ ገደለው፡፡[132]

የከነአናውያን ዘርም ከጻድቁ ከያዕቆብ ዘር ጋር ይቀላቀል ዘንድ አልተወውም፡፡ ስለዚህም ትእማር ወደ አማቷ ወደ ይሁዳ ወጣች፤ ተቀበለችውም፡፡ ከእርሷ ጋርም ተቀመጠ፤ እርሷ የልጁ ሚስት እንደሆነችም አላወቃትም፤ ከእርሷም ፋሬስና ዛራ /የተባሉ መንትያ የሆኑ ልጆችን/ ወለደ፡፡[133]

ከዚህ በኋላ ያዕቆብ ወደ ልጁ ዮሴፍ ሄደ፡፡ ከእርሱም ጋር በግብጽ ምድር ዐሥራ ሁለት ዓመት ተቀመጠ፤ ያዕቆብ በመቶ ሃምሳ ሰባት ዓመት መጨረሻ በግብጽ ምድር ሞተ፤ ለዮሴፍም ሃምሳ ሦስቱ ዓመት መልካም ነበር፡፡ ያዕቆብ በሞተ ጊዜም ዮሴፍ የግብጽን ጠቢባን ጠራ፤ ጥሩ አገናነዘንም ገነዙት፤ ዮሴፍም ያባቱን ሥጋ እስከ ከነአን ምድር ድረስ ተሸከመ፤ በአባቶቹ በአብርሃም፣ በይስሐቅ መቃብርም ቀበረው፡፡[134]

ከዚህ በኋላ ፋሬስ ኤስሮምን ወለደ፤ ኤስሮምም አራምን ወለደ፤ አራምም አሚናዳብን ወለደ፤ አሚናዳብም ነአሶንን ወለደ፤ ይህ ነአሶንም በይሁዳ ልጆች ዘንድ ታላቅ ሆነ፡፡

መቅሰፍቱ ጸጥ እስከሚል ድረስ ወደ እግዚአብሔር የጸለይህ አንተ ልጄ ሆይ! ከመጀመሪያ እስከዚህ ድረስ ያሉ ትድለቶችን እነሆ! ገለጥሁልህ፤ በይሁዳ ልጆች መካከል ታላቅ ከሆነው ከነአሶን በኋላ መንግሥትና ክህነት ከእርሱ ትወጣ ዘንድ ጀመረች፡፡ አይሁድም እርሱን እጅ ነሱ፡፡ ነአሶንም ሰልሞንን ወለደው፤ ሰልሞንም ቡኤዝን ከራኬብ ወለደ፡፡

132 ዘፍ.፴፰÷፯-፲
133 ዘፍ.፴፰÷፲፩-፴
134 ዘፍ.፶÷፩-፲፬

ዛሬም ከቡኤዝ፣ ከሞአባዊቷ ከሩት መንግሥት እንደጀመረች አመላከ ትሃለሁ /አሳውቅሃለሁ/:: ለሎጥ ለወንድሙ ለአብርሃምም በመንግሥት ተከፍሎ ውስጥ አንድነት ይኖራቸው ዘንድ:: እግዚአብሔር ለሎጥ ዘርን አልከለከለውምና፤ ዘርም ይቆርጥባት /ያቆምባት/ ዘንድ አልወደደም:: ይህ ሎጥም ከአብርሃም ጋር ድካምን ሁሉ የተቀበለ ጻድቅ ነበር:: በሰዶምና በገሞራም መላእክትን ተቀበለ፤[135] ስለዚህም እግዚአብሔር ለእርሱ የልጅ ዘርን፣ በመንግሥትም አንድነትን አደረገለት::

ስለዚህም አብርሃምና ሎጥ በመንግሥት ተከፍሎ የሚታሰቡ ሆኑ፤ ክርስቶስ ከዘራቸው /ከወገናቸው/ ተወልዷልና:: ዳግመኛም የሩት ልጅ ኢዮቤድም እናቱ ከሎጥ ዘር ናት፤ ኢዮቤድም እሴይን ወለደ፣ እሴይም ንጉሥ ዳዊትን ወለደ፤ ዳዊትም ከኦርዮን ሚስት ሰሎሞንን ወለደ፤[136] ዳግመኛም ከሎጥ ዘር የሆነ የአሞን ንጉሥ የዳን ልጅ እምናን ነበረች፤ ይህችን የዳን ልጅም ንጉሥ ሰሎሞን ሚስት ትሆነው ዘንድ ወሰዳት፤ ከእርሷም ሮብአምን ወለደ፤ እርሱም ከሰሎሞን በኋላ የነገሠ ነው::

ዳግመኛም ንጉሡ ሰሎሞን ብዙ ሴቶችን አገባ:: ሰባት መቶ የነገሥታት ልጆች ሦስት መቶም እቁባቶች ነበሩ፤ ሰሎሞን ያገባቸው እነህ ሴቶች ሁሉ ብዙዎች ፤ቁጥራቸው አንድ ሺኽ ነበሩ፤ በአሞን ንጉሥ ከዳን ልጅ ከእምናን ነው እንጂ ከእነርሱ ወንድ ልጅ አልወለደም፤ ይህ ዳንም ከተባረከ ዘር ነው:: ዳግመኛም እግዚአብሔር የከነአናውያንን ዘሮች እግዚአብሔር ካፈለሳቸው ከአሕዛብ ዘር ጋር ይቀላቀሉ ዘንድ አልተዋቸውም፤ ይኸውም የክርስቶስ ምሳሌ ነው:: ከተባረከ አባት ከአብርሃም ዘር ከወንድሙ ልጅ ከሎጥም ተገኘ::

ሁላቸውም በግብጽ ምድር የእስራኤል ልጆች ጉደሎዎች ነበሩ:: ሌዊ፣ አብርሃም፣ ሙሴ፣ ኢያሱ፣ የዮፎኒ ልጅ ካሌብ እነህ በሕዝቡ ላይ ታላላቅ አለቆች ነበሩ:: ሙሴን ግን ወደ ባሕር በጣሉት ጊዜ የፈርዖን ልጅ ስፋራ[137] ከውኃው

135 ዘፍ.፲፱+፩-፱፣ ዕብ.፲፫+፩

136 ፪ኛሳሙ.፲፱+፳፬

137 የብሉይ ኪዳን ትርጓሜ ሙሴን ከውሃ አውጥታ የወሰደችውን ሴት "ተርሙት ወለተ ፈርኦን" ይላታል

አወጣቻው:: የዕብራውያን ወገን የምትሆን ይህችንም የሙሴ እኅት ማርያም ይሏታል::

ሙሴም ዐርባ ዓመት በፈርዖን ቤት ተቀመጠ:: ሌላ አርባ ዓመትም በምድያም ምድር እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከመነጋገሩ አስቀድሞ በአማቱ፤ በካህኑ በዮቶር ዘንድ ነበር:: ዳግመኛም በዕፀ ጳጦስ እግዚአብሔር በተነጋገረው ጊዜ እንደበቱ ዲዳ ነበር:: እግዚአብሔር እንዳለ ከአገልጋዩ ከሙሴ ጋር በተናገረው ጊዜ አንደበቱ ልቱት /ጉልዳፋ/ ነበር::[138]

ሙሴም አርባ ዓመት በግብጽ ኖረ፤ አርባ ዓመትም በምድያም ምድር በካህኑ፣ በአማቱ በዮቶር ዘንድ ኖረ፤ ሌላ አርባ ዓመትም በበረሃ ኖረ፤ መቶ ሃያ ዓመት ሲፈጸምም ሙሴ ሞተ::[139] ከእርሱ በኋላም የነዌ ልጅ ኢያሱ ተተካ:: በእስራኤል ልጆች ላይም ሃያ ሰባት ዓመት ገዢ ሆነ፤ በፍርድም ገዛቸው:: በእነርሱ ላይም ነቢይ ነበር፤ ይጠብቃቸውም ነበር፤ በጽድቅ መንገድም መራቸው፤ ዘጠና ዓመት ሲፈጸምም ዐረፈ::[140]

ከእርሱ በኋላም ገዢ ኮሳራት ስምንት ዓመት ተሾመ፤ ሞተም:: ከእርሱ በኋላም የካባ ልጅ ፋጣምያል በእስራኤል ልጆች ላይ አርባ ዓመት ነገሠ፣ ሞተም:: ከእርሱ በኋላም የፋሩ ልጅ ናዖድ እስራኤልን ሰማንያ ዘመን ገዛ:: ለናዖድ ሃያ ዐምስት ዘመን ሲሆነው አራት መቶ ዓመት ተፈጸመ:: ከአዳም ጀምሮ ሃያ ዐምስት ዓመት /ትውልድ/ ሲፈጸም ናዖድ ሞተ::

ከእርሱ በኋላም በእስራኤል ልጆች ሲካር ነገሠ:: በንግሥናው ዘመንም ከነዓን ነገሠ:: በሲካር ላይም ተነሣ፤ ይጣላው ዘንድም ወደደ፣ እግዚአብሔርም ሲካርን በእርሱ ላይ አበረታው፤ አሸነፈውም፤ሲካርም አርባ ዓመት ተቀመጠ፤ ከእርሱ በኋላም ያሮድ እስራኤልን ሠላሳ ዓመት ገዛ:: ከእርሱ በኋላም አቤሜሌክ ዐሥር ዓመት ነገሠ፤ሞተም፤ ከእርሱ በኋላም የዮናኒ ልጅ ባኑ ሃያ ሦስት ዓመት ገዛ፤ ሞተም:: ከእርሱ በኋላም ያርእምፌላ ሃያ ሁለት ዓመት ነገሠ፣ ሞተም::

138 ዘኍ.፲፪+፰

139 ዘዳ.፴፬+፭-፰

140 ኢያ.፳፬+፳፱

ከእርሱ በኋላም የአሚናባአ ልጅ ሃምሳ ስምንት ዓመት ነገሠ፣ ሞተም። ከእርሱ በኋላም የነስያሙ ልጅ ሰባት ዓመት ገዛች፤ ሞተችም። ከእርሷ በኋላም አውስዮስ ሰባት ዓመት ገዛ። እግዚአብሔርም ለኀይለኛው ለሶምሶን እጅ አሳልፎ ሰጠው፤ ገደለውም፤ ኀይለኛው ሶምሶንም ተነሣ፤ በእስራኤል ልጆች ላይም ሃያ ዓመት ነገሠ።ከዚህ በኋላ የእስራኤል ልጆች ዐሥራ ሁለት ዓመት ያለ ገዢ ነበሩ። ካህኑ ኤሊ ለአርባ ዓመት ያህል የእስራኤል ልጆችን መግዛት ጀመረ፤[141]ሞተም፡

ከእርሱ በኋላም ሳሙኤል በእስራኤል ልጆች ለሃያ ዓመት ገዛ፤ ሞተም። ከእርሱም በኋላ ሳዖል በእስራኤል ልጆች ላይ አርባ ዓመት ነገሠ፣ ሞተም፤ ከዚህ በኋላም ዳዊት አርባ ዓመት ያህል በእስራኤል ልጆች ላይ ነገሠ፤ ሞተም።

ከእርሱ በኋላም ልጁ ሰሎመን ተነሣ፤ በእስራኤል ልጆችም አርባ ዓመት ነገሠ።[143] በምድር ላይም ብዙ ድንቅ ነገሮችን አደረገ። ከእርሱ በፊት ከነበሩ ነገሥታትም ሁሉ ጥበብን አበዛ። በዚህ ዘመን እግዚአብሔር ጥበብን የመላበት፣ ብዙ ተአምራትንም ያደረገበት ዘመን ነው፤ ታገለግለው ዘንድ መርከብን ሠርቷልና። ሰፌር እስከተባለች ሀገርም ሄደ፤ የተደረደረ ወርቅንም ያዘ፤ ወደ ኢየሩሳሌምም አመጣ። በንግሥናው ዘመንም ታላቅ ሰላም ሆነ፤ መደንገጥም አልነበረም።

በእርሱና በዱር ንጉሥ በኪራም[144] መካከልም ሰላም ነበር። ይህም ዱር በተባለች ሀገር ዐምስት መቶ ዘመን የነገሠ ነው፤ ንግሥናውም ከንጉሥ ሰሎሞን ጀምሮ እስከንጉሡ ሴዴቅያስ ነበረች። ከዘመኑ ከዓመቶቹ ብዛት፣ ከንግሥናው ታላቅነት የተነሣም ኮራ፤ እኔ አምላክ ነኝ እንጂ ሰው አይደለሁም አለ።

እግዚአብሔርም ከፉ ሥራውን ተመለከተ። በንጉሥ ናቡከደነጾር እጅም አሳልፎ ሰጠው፤ ገደለውም፤ሰራዊቱንም አጠፋ፤ ገንዘቡንም ወሰደ። እኛ ግን በምግባራት እናስረዳችኋለን። ሰሎሞን በየቀኑ ይሰጣቸው ነበር፤ ከሴቶቹ /

141 ፩ኛሳሙ.፬+፲፰
143 ፪ዜና መዋ. ፱+፴

144 ፪ዜና መዋ. ፪+፲፬

ከሚስቶቹ/ ብዛት የተነሣ በቤቱ ቅሮስ በተባለ ሠላሳ መስፈሪያ ዱቄት ይጋግሩ ዘንድ ያደርግ ነበር፤ የስንዴ ዱቄት መስፈሪያም አይበቃም ነበር፡፡

በየቀኑም ዐሥር ያማሩ የበሬ ኮርማዎችን፣ ሃያ የሰቡ ላሞችን፣ ከሚጠብሷቸው ሌላ መቶ በጐችንም ያርዱ ነበር፤ ቶራት /አጋዘኖች/፣ ሚዳቆዎች፣ ዋልያዎች ሳይቀሩ ሳያድኗቸው በየዕለቱ ይመጡ ነበር፡፡ በቤቱ በየዕለቱ የሚጠጣውም አራት መቶ የወይን ጋን ነበር፤ ብዙ ተግባራትንም ይሠራ ነበር፤ በዚህች ታላቅ መንግሥት ሁሉ በጥበብ የነገሠ እርሱ ነፍሱን አልጠበቀም፡፡ ልቡናው ሴትን ወደ መውደድ አዘነበለ እንጂ፡፡ የፈጠረውን፣ ይህችን መንግሥት የሰጠውንም ማምለክ ተወ፤ ኀጢአትንም አበዛ፤ በዚህ ከህደቱ /ጥፋቱ/ የተነሣ ሞተ፡፡[145]

ከእርሱ በኋላም ልጁ ሮብአም ዐሥራ ሰባት ዓመት ነገሠ፤ ክፋንም አደረገ፤ በዘመኑም ብዙ ዝሙትን /በደልን/ ሠራ፤ እግዚአብሔርም ፈጥኖ መንግሥቱን ከእርሱ ቆረጠ፡፡ ሮብአም በነገሠ በዐምስት ዓመት የቤተ መቅደሱን ንዋያት የወሰደ ስሙ ሱስቀም የሚባል ንጉሥ ወደ ኢየሩሳሌም መጣ፤ የንጉሥ ሮብዓምን ሀብቱን ሁሉ ማረከ፤ የዳዊትንም ቤት /ወገን/ ሁሉ ማረከ፤ ወደ ሀገሩም አፍልሶ ወሰዳቸው፡፡ እርሱ ተመካ፤ አይሁድንም አላቸው፤ ከእናንተ የማረኳቸው ሥራዎች /ንዋያት/ እስከዚህ ቦታ ድረስ በመምጣት አባቶቻችሁ የማረኳቸው የአባቶቼ ገንዘቦች ናቸው፡፡ እነሆ! እኔም ከእናንተ ወሰድሁ፤ አላቸው፡፡ ሮብዓምም በክሕደቱ ሞተ፡፡

ከእርሱ በኋላም ልጁ አብዮስ በእስራኤል ልጆች ላይ አንድ ዓመት ነገሠ፡፡ ዳግመኛም እርሱ በአቤሴሎም ልጅ በእናቱ በማልያ በአባቱም ምግባር /መንገድ/ ሄደ፤ ስለዚህም ብዙ ክፉ ተግባራትን አደረገ፤ ሞተም፡፡

ከእርሱ በኋላም ልጁ አሳፍ በእስራኤል ልጆች ላይ አርባ አንድ ዓመት ነገሠ፡፡ በእግዚአብሔር ፊት ቅን ፍርድን፣ እውነትን፣ መልካምን ሁሉ አደረገ፤ በዘመኑ የነበሩ ጣዖታትንም ሰበራቸው፤ መሠረታቸውንም ከምድር ገጽ

145 ነቢየ እግዚአብሔር ሰሎሞን በመጀመሪያ ጊዜ እግዚአብሔርን በማሳዘኑ "ሞተ" ቢባልም በኋላ ግን በንስሐ ከፈጣሪው ጋር ከመታረቁም በተጨማሪ ለምእመናን ጠቃሚ የሆኑ ዐምስት መጻሕፍትን የጻፈ ቅዱስ ነቢይ ነው፡፡

አስወገደ፡፡ የሪከሰች እናቱ ሐናንም ወሰዳት፤ ከሰገነት ወደታችም ጣላት፤ በዝሙት/በበደል/ እንዳለችም ሞተች፡፡

ከዚህ በኋላም አሳፍን ይወጋ ዘንድ ጥቁሩ የአንዴናው ንጉሥ አልዓዛር መጣ፡፡ እግዚአብሔርም ለአሳፍ እጅ አሳልፎ ሰጠው፤ አሸነፈውም፡፡ ከዚህ በኋላ አሳፍ ሞተ፤ ልጁ ኢዮሳፍጥም ነገሠ፡፡ ዳግመኛም እርሱ እውነትን፣ ቸርነትን በእግዚአብሔር ፊት አደረገ፡፡ በዘመኑም እግዚአብሔርን ደስ አሰኘው፤ ኢዮሳፍጥም ሞተ፡፡

ልጁ አራምም ነገሠ፤ የእግዚአብሔርን ትእዛዝም ተላለፈ፤ ሕጉንም ተወ፤ ለጣዖታትም ሠዋ፡፡ ዘንበሪም በእርሱ ላይ ተነሣ፣ ወጋው፣ በክሕደቱም ሞተ፤ ልጁ ዮሰያም ነገሠ፡፡ በመተላለፉም እግዚአብሔር በጠላቶቹ እጅ ሰጠው፤ ገደሉትም፤ በሞተ ጊዜም እናቱ በመንግሥት ልጆች ላይ ሁሉ ተነሣች፤ ገደለቻቸውም፡፡ እኔ ከዳዊት ቤት /ወገን/ መንግሥትን እወስዳለሁ አለች፤የአራም ንጉሥ ልጅ ዮሳቤትም ተነሣች፡፡ አግራግሪናንም ይዛ በቀሩት በነገሥታቱ ፊት ገደለችው፡፡ በገደለችው ጊዜም ፈራች፤ እርሷ፣ ከእርሷ ጋር ያሉትም በአልጋው ውስጥ ተሸሸጉ፡፡

ጐቶንያልም በእስራኤል ልጆች ላይ ነገሠ፤ ሞተም፡፡ የእስራኤል ሕዝብም ቀሩ፤ በእኛ ላይ ማንን ንጉሥ ታደርጋላችሁ? አሉ፡፡ ታላቁ ካህን ዮዳ ይህን ሲነጋገሩ በሰማ ጊዜ ሁሉንም አይሁዳውያን በእግዚአብሔር ቤት ሰበሰባቸው፤ መቶ እልፍ ሁነው አስኪገቡ ድረስም ቆየ፡፡ ካህኑ ዮዳም ከእኔ የምትፈልጉት ምንድን ነው? በዳዊትም ቤት ይነግሥ ዘንድ የምትወስዱት ማን ነው? አላቸው፤ሥልጣኑ የአንተ ነው+ አሉት፡፡

ካህኑ ዮዳም ተነሣ፤ በርስያንም ያዘው፤ ከእነርሱ ፊትም አደረሰው፤ይህ ሊነግሥላችሁ ይገባል አላቸው፤ ሕዝቡም ወደዱት፤ ወደ እግዚአብሔር ቤትም አመጡት፤ በንግሥና ወንበርም አስቀመጡት፤ ሕዝቡ ሁሉ ተደሰቱበት፤ ሀገሪቱ ሁሉም ጸጥ አለች፤ ንጉሡም ሠላሳ ዓመት ያህል በኢየሩሳሌም ተቀመጠ፡፡

ዳግመኛም ባርስያ ካህኑ ዮዳ ያደረገለትን መልካም ሥራ ሁሉ አላሰበም፤ የዮዳን ልጅ ገደለው፤ ከዚህም በኋላ ጠላቶቹ ተነሥተው ባርስያን ገደሉት፡፡ ከዚህ በኋላ ልጁ አሜስያስ ሃያ ዘጠኝ ዓመት ነገሠ፡፡ አሜስያስም አባቱን የገደሉትን ገደላቸው፤ አባቱን የገደሉትን ልጆቻቸውን ግን አልገደለም፡፡ የሙሴ ሕግ በእርሱ ይፈጸም ዘንድ ሕግ በአባታቸው ኀጢአት ልጆችን አይግደሉ ይላልና፡፡ አሜስያስም ሞተ፡፡ ከእርሱ በኋላም ዖዝያን ሃምሳ ሁለት ዓመት ነገሠ፡፡ በንግሥናውም፣ የእውነት ፍርድን፣ ቅንነትን በእግዚአብሔር ፊት አደረገ፤ አንዲት በደል ግን ሠራ፡፡ ይህችውም ያለጸታው /ወገኑ/ ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን ማሳረጉ ነው፤ የማይገባውንም አቀረበ፣ ሞተም፡፡

ከዚህ በኋላ ልጁ ዮናታን ዐሥራ ሰባት ዓመት ነገሠ፡፡ በንግሥናው ዘመንም በእግዚአብሔር ፊት ክፋትን አደረገ፤ ፈጣሪውንም አስቆጣ፤ ሕጉን፣ ትእዛዙንም ተወ /ተላለፈ/፡፡ ለጣዖታትም ዕጣንን አሳረገ /ሠዋላቸውም/፡፡ ስለዚህም እግዚአብሔር በአልምሳል እጅ አሳልፎ ለሞት ሰጠው፡፡ የአልምሳል ንጉሥ ባፈለሰው ጊዜም ከቤተ እግዚአብሔር ውስጥ ያገኘውን ሁሉ ንዋያት ወሰደ፤ እስከ ታላቁ አልምሳል ንጉሥም ላካቸው፡፡ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥም ንዋያትን አልተውም፤ በዚህ ንጉሥ ዘመንም እስራኤላውያን ፈጽመው ተሰደዱ /ተማረኩ/፡፡ ወደ ሀገሩም ወሰዳቸው፤ የእስራኤል ምድርም ራቁቷን ቀረች፡፡ በእስራኣል ፋንታም ይጠብቋት ዘንድየአልምሳል ንጉሥም በዚህች ምድር ይኖሩ ዘንድ ሰውን ላከ፤ ሰዎቹ በደረሱ ጊዜም በሀገሪቱ ተቀመጡ፤ አራዊቱም ነጥቀው ይበሏቸው ነበር፡፡ በአራዊትም እስከ ምድር ጫፍ ድረስ አስጨነቃቸው፡፡

ወደ ንጉሡም ላኩ፤ በአነጋገራቸውም አስረዱት፤ ኡርየስ የተባለውን ካህን ይልከላቸው፣ አራዊት እንዳይቀርቧቸው በእነርሱ ላይም እንዳይከፉ ሕግን ይሰጣቸው ዘንድም ለመኑት፡፡ ንጉሡ ይህን በሰማ ጊዜም ካህኑ ኡርያስን ላከላቸው፤ አራዊት እንዳይከፉባቸው ከእነርሱ ጋር የሚኖር ሕግን ይሰጣቸው

ዘንድ አዘዘው፤ አይሁድም ሕግን ሰጧቸው፤ በእጃቸውም ያነቡት ነበር፤ ይሠሩበት /ይጠቀሙበትም/ ነበር፤ እነዚህም ሳምራውያን ናቸው፡፡

ስለ እርሱ የተናገርነው ይህ ንጉሥም የእስራኤልን ምድር ይጠብቁ ዘንድ የላካቸው ነው፡፡ የናታንም ሞተ፤ ከእርሱ በኋላም ልጁ አካዝ ነገሠ፡፡ በእግዚአብሔር ዘንድም ደግነትን አደረገ፤ አካዝም ሞተ፡፡ ከእርሱ በኋላም ልጁ ሕዝቅያስ ነገሠ፤ እርሱም የሃያ አምስት ዓመት ልጅ ነበር፤ በንግሥናውም ሃያ ዘጠኝ ዓመት ተቀመጠ፤ ጥሩ ፍርድንም አደረገ፤ በእውነትም ገዛ፤እግዚአብሔርንም አስደሰተ፤ ሕጉን፣ ትእዛዙን ፈጸመ፡፡ ጣዖታትን ሰበረ፡፡ የጣዖታቱን ቤትም አፈረሰ፡፡

በነገሠ በአራት ዓመትም የአሶርዮን ንጉሥ ሰናክሬም ደረሰ፤ከእስራኤል ልጆች የተረፉትንም ማረካቸው፤ እስከባቢሎን ግን አልወሰዳቸውም ነበር፤ ሕዝቅያስም ለአምላኩ ለእግዚአብሔር ይገዛ ነበር፡፡ እስኪታመመበት፣ ፈጽሞ እስከደከመበት ጊዜ ድረስም ሕጉን እንዲህ ይፈጽም ነበር፡፡ ከደዌው ብዛት / ጽናት/ የተነሣም ብዙ ችግር ደረሰበት፣ ልቡም ታመመ፤ በሰውነቱም አለ፡፡ ወዮልኝ! እኔ ከእኔ በኋላ የሚነግሥ ልጅ ሳልወልድ ልሞት ነው፡፡ በበሽታው እያለም በእግዚአብሔር ፊት አለቀሰ፡፡ ጌታዬ ሆይ! ወዮልኝ እነሆ! ያለልጅ ልሞት ነው፤ እነሆ! ለዳዊት የገባኸው ቃል ኪዳን ከእኔ ይጠፋል /ያቆማል/፤ ከዳዊት ወገንም መንግሥት ይቋረጣል፡፡ ነገር ግን ጌታዬ ሆይ! ከእኔ በኋላ የሚነግሥ ልጅ ስጠኝ፤እግዚአብሔርም ወደ ልቡናው ኃዘን፣ ወደ ሕማሙም ተመለከተ፡፡ ደዌው የሚያስጨንቅ ነበርና፤ እግዚአብሔርም ይቅር አለው፡፡ ከሐዘኑ ብዛት የተነሣም እግዚአብሔር በዘመኑ ላይ ዐሥራ አምስት ዓመት አትርፎ ሰጠው፣ ከደዌውም ፈወሰው፤[146] ከዚህ በኋላም እግዚአብሔር ከሚያስጨንቅ ደዌ አስነሣው፤ በሦስት ዓመቱም ምናሴን ወለደ፤ ሕዝቅያስም ሞተ፤ በዙፋኑ የሚቀመጥ ልጅ ስለተወለደለትም ታላቅ ደስታ ሆነለት፡፡

ከእርሱ በኋላም ልጁ ምናሴ በኢየሩሳሌም ዐሥራ ሁለት ዓመት ነገሠ፤



146 ፪ነገ.፳+፩-፯

ታላቅ ክፋትም አደረገ፤ የኢየሩሳሌም ሕዝቦችንም ለጣዖት ይሰግዱ ዘንድ አስገደዳቸው:: የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በተላለፈ. ጊዜም ነቢዩ ኢሳይያስ ወደ እርሱ መጣ፤ ስለሠራው ክፉ ሥራም ተቆጣው፤ ምናሴም በእርሱ ላይ ተቆጣ:: ነቢዩ ኢሳይያስን ይይዙት ዘንድም ኃይለኞችና ክፉዎች የሆኑ ሰዎችን ላከ:: በዱር ዕንጨቶች መካከል በዕንጨት መጋዝ ከእግር እስከራሱ ይሰነጥቁት ዘንድ፣ ለአራዊትም ይጥሉትና ይበሉት ዘንድ አዘዘ፣ እንዲህም አደረጉበት::

ኢሳይያስም የመቶ አንድ ዓመት ሰው ነበር፤ ለሰውነቱ ያለው ልብሱም ከፍየል ጸጉር የተሠራ ሰቅ[147] /ማቅ/ ነበር፤ ዘመኑን ሁሉ ሰኞ ሰኞ ይጾም ነበር:: ምናሴም ሞተ፤ ከእርሱ በኋላም ልጁ አሞጽ ነገሠ፤ በእግዚአብሔር ፊትም ክፋትን አደረገ:: እርሱ ወንዶችን ሴቶችን ልጆች ለጣዖት ሠዋላቸው:: አሞጽም[148] ሞተ፤ ከእርሱ በኋላም ልጁ ኢዮስያስ ነገሠ:: በነገሠ ጊዜም ስምንት ዓመቱ ነበር፤ በንግሥናውም ሃያ ሁለት ዓመት ተቀመጠ::

በእግዚአብሔር ፊትም ቅንነትን፣ እውነትን አደረገ:: ሙሴ በገዳም /በምድረ በዳ/ እያለ ካደረገው በቀር እስራኤል እንደእሱ ማድረግ ያልተቻላቸውን የእግዚአብሔርን ፋሲካ አደረገ፤ ይህ ንጉሥ ኢየሩሳሌምን ከክፉ ሁሉ ያነጻት ነው::

እንካሳው የግብጽ ንጉሥ ፈርዖንም በቀርሜሎስ ኢዮስያስን ገደለው:: ከእርሱ በኋላም አካዝ ሦስት ወር ነገሠ፤ ፈርዖንም አካዝን በሰንሰለት አሰረው፤ ወደ ግብጽ ምድርም ላከው:: ከሞተ በኋላም ወንድሙ ኢዮአቄም ዐሥራ አንድ ዓመት ነገሠ፤በነገሠ በሦስት ዓመቱም ናቡከደነጾር ወደ ኢየሩሳሌም ሀገር መጣ፤ እግዚአብሔርም በኢዮአቄም እጅ አሳልፎ ሰጠው፤[149] ኢዮአቄምም በትእዛዙ ሥር ነበር፤ ይሸነግለው፤ እጅ መንሻም ይሰጠው ነበር፤ ታሞም ሞተ::

ከእርሱ በኋላም ወንድሙ ኢኮንያን ነገሠ:: ሦስት ወራት ያህልም ተቀመጠ፤ ናቡከደነጾር መጣ፤ ኢኮንያንንም ሠራዊቱንም ሁሉ ማረከው:: ወደ ባቢሎንም ላካቸው፤ በመጀመሪያው ምርኮ የማረከውም ኢዮአቄምን

147 "ሰቅ" ማለት ሻካራ፣ የሚኮሰኩስ የሐዘን ልብስ ማለት ነው::
148 ነቢዩ አሞጽ አለመሆኑን ልብ ይሏል::

149 ትን.ዳን.፩+፩

ነው፤ሚስቱም ነቢዩ ዳንኤልን ፀንሳ ነበር፤ ሌሎችን ታላላቆችንም ከኢየሩሳሌም ወደ ባቢሎን ማረከ፤ የዳንኤል እናትም በባቢሎን መንገድ ወለደችው:: ዳግመኛም የኢኮንያስ ልጆች አናንያ፣ አዛርያ፣ ሚሳኤል በኢዮአቄም የመጀመሪያው ምርኮ እንዲሁ ተወለዱ:: ኢኮንያንም ሞተ፤ ከእርሱ በኋላም ሴዴቅየስ ዐሥራ አንድ ዓመት ነገሠ፤ እርሱም በእስራኤል ልጆች በይሁዳም ሁሉ የነገሡ ነገሥታት መጨረሻ ነው::

ከእርሱ በኋላም መንግሥት አልቀረላቸውም:: ለሴዴቅያስ ዐሥራ አንድ ዓመት ሲፈጸምም ንጉሥ ናቡከደነጾር መጣ::[150] የኢየሩሳሌምን ሰዎችም እስከ ምዕራብ እስከ ኤፍራጥስ ወንዝም፤ እስከ ዓባይ ወንዝም አፈለሳቸው፤ ዑርን ምድረ በዳ አደረጋት፤ በእሳትም አቃጠላት:: አምስት መቶ ዓመት የነገሠ የዑር ንጉሥ ኪራምንም ገደለው:: ከዚህ በኋላ ናቡከደነጾር ወደ ግብጽ ወረደ፤ ፈርዖንን ገደለው፤ ሰራዊቱንም አጠፋ፤ ሀገሩ ግብጽንም ምድረ በዳ አደረጋት፤ ኢየሩሳሌምንም ያዛት /የእርሱ አደረጋት/:: እግዚአብሔርም ሴዴቅያስን በእጁ ሰጠው::

በጣዖታቱ ፊትም ይዞ አቀረበው:: በሕዝቡ ፊትም አቀረበው፤ ያለርኅራኄም ልጆቹን በፊቱ ገደለበት፤ ይዞም ዐይኑን አሳወረው፤ እግሩንም በሰንሰለት በዛንጀር የእግር ብረት አሰረው፤ ወደ ባቢሎንም ወሰደው:: ስለከንቱነቱ፣ በነቢዩ ኤርምያስም ስላደረገው ክፋት፣ እርሱ ወደ ጉድጓድ ወርውሮታልና::

ከዚህ በኋላም የንጉሡ ባለሥልጣናት፣ አለቃ ናቡዛዳን የኢየሩሳሌምን ቅጽሮች አፈረሰ፤ የእግዚአብሔርን ቤትም በእሳት አቃጠለ፤ ከፉውን ሁሉ አደረገ::[151] ስምዖን ካህንም በንጉሥ ሹማምንት አለቃ ፊት ሞገስን፣ ጸጋን አገኘ:: የመጻሕፍቱን ቤት ይሰጠው ዘንድ ፈልጐ እርሱን ለመነው:: በዚህም አዘዘለት፤ ካህኑ ስምዖንም ገባ፤ የተቃጠሉ መጻሕፍትንም ሰበሰበ፤ በእንግዳ ቤትም አስቀመጠው::

150 ትን.ኤር.፶፪+፩

151 ኤር.፶፪+፲፫

ታላቁ ካህን ስምዖንም የብረት ማዕጠንት ያዘ፤ ፍምም አደረገበት፤ በውስጡም ንጹሕ ዕጣን ጨመረበት፡፡ በውስጧ የመጻሕፍት አመድ /የተቃጠሉ መጻሕፍት/ ባሉበት ቦታ በእንግዳ ቤትም ሰቀላት፡፡ ኢየሩሳሌምንም እንደሜካ ምድረበዳ አደረጓት፤ ኤርምያስም ሃያ ዘመን ስለ ኢየሩሳሌም እያለቀሰ ኖረ፤ ከዚህ በኋላ ነቢዩ ኤርምያስም ወደ ምድረ ግብጽ ሄዶ፣ በዚያም ሞተ፡፡

ነቢያትን፣ ሐዋርያትን፣ አበውን፣ ጻድቃንን፣ ሰማዕታትን የወለዱ የአባታችን የአዳም፣ የእናታችን ሔዋን ጸሎታቸው፣ በረከታቸው፣ የይቅርታ ልመናቸው ከሊቃነ ጳጳሳቱ አለቃ ከባስልዮስ፣ ከንጉሣችን ከኀይለ ሥላሴ ጋር ይሁን፣ ለዘለዓለሙ አሜን፡፡

## ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት

## ገድለ አዳም ዘመጋቢት

አንድ አምላክ በሆኑ በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም መጋቢት ስድስት ቀን የሚነበብ የአባታችን የአዳም፣ የእናታችን የሔዋን የገድላቸው ዜና ይህ ነው፡፡ ጸሎታቸው፣ በረከታቸው አማላጅነታቸው፣ የይቅርታ ልመናቸው ከሊቃነ ጳጳሳቱ አለቃ ከባስልዮስ፣ ከንጉሣችን ከኀይለ ሥላሴ ከወገኖቻቸው ከእኛም ጋር ይሁን፤ አሜን፡፡

ጸሐፊዎችና ሙተርጉማንም መጻሕፍቱን አጠፉ፡፡ ዕብራውያንም መጻሕፍቱን ለወጡ፤ ሶርያውያንና የናናውያንም ከመጻሕፍቱ ታላቁን ከፍል ጣሉት፤ የእሕዛብን ልጆች ይገልጡ ዘንድም አልቻሉም፡፡ ከእነርሱ ጋር ከነበሩት ከትንሾቹ በቀር ከእናቶቻቸው በፊት የነበሩ ሴቶችንም ወንዶችንም መግለጥ አልቻሉም፡፡

ይህም ኢየሩሳሌም ምድረ በዳ ከሆነ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ርእሶች ብቻ እንጂ በእውነተኛ መጻሕፍት ውስጥ አይገኝም፡፡ እነዚህን መጻሕፍት

የተረጐሙትም ኢየሩሳሌም ምድረ በዳ ከመሆኗ በፊት የነበረውን ነው፤ ዳግመኛም ከመጻሕፍቱ በተለወጠ ጊዜ ያውቁ ዘንድ አልቻሉም።

እንዴት እንደ አገቡ? ስማቸው ማን እንደሆነ? ልጆች ሴቶቻቸውን እንዴት ዐወቁ የሚሉ ጉድለቶቻቸውንም ዐላወቁም። የልጆቻቸውን ቁጥር፣ ካህናቶችንም ዐላወቁም። ኢኮንያንም በባቢሎን ታሥሮ ሃያ ሰባት ዓመት በሥር ቤት ውስጥ ቆየ፤ ከዚህ በኋላ የባቢሎን ንጉሥ መርዙቅ አወጣው። የኤልያቄምን ልጅ ደሊላ የምትባል ሴትም አጋባው። በባቢሎን እያለ ከእርሷ ሰላትያልን ወለደ፤ የሰላትያል አባት ኢኮንያንም በባቢሎን ሞተ።

ሰላትያልም የሕልቃናን ልጅ ሐድስትን አገባት፤ ከእርሷም ዘሩባቤልን ወለደ።[152] ዘሩባቤልም ስሟ መልካ የምትባል የጸሐፊው የዕዝራን ልጅ አገባ፤ ከእርሷም በባቢሎን እያለ አልወለደም። በዚህ በታላቁ፣ በዘሩባቤል ዘመን በእስራኤል ልጆች ላይ ስሙ ቂሮስ የተባለ ፋርሳዊ በባቢሎን ነገሠ። ምስሐር የተባለች ሴትም አገባ። ይህችም የእስራኤል ልጆች ታላቅ የሆነ የዘሩባቤል እኅት ነበረች። እንደ ፋርስ ነገሥታት ሕግም ንግሥት አደረጋት።

ንግሥት በሆነች፣ በንጉሡ ዘንድም ባለሟልነትን ባገኘች ጊዜ ደቂቀ እስራኤልን ይቅር ይላቸው ዘንድ፣ ወደ ኢየሩሳሌምም ይመልሳቸው ዘንድ ለመነችው። ቂሮስ ንጉሥም የዘሩባቤልን እኅት ምስሐርን እንደራሱ አድርጎ ይወዳት ነበር። በሥልጣኑም በባቢሎን ቤተ መንግሥት ደቂቀ እስራኤልን ይሰበስባቸው ዘንድ የከለዳውያንን ምድር ሁሉ እንዲዞር አዘዘ፤ በንጉሥ ትእዛዝም ተሰበሰቡ።

ንጉሥ ቂሮስም የሚስቱ ወንድሟ የሆነ ዘሩባቤልን ሕዝብህን ውሰድ፤ ወደ ሀገርህ ወደ ኢየሩሳሌምም ሂድ፤ እንደነበረችውም ሥራት /ገንባት/ አለው። ይህ ንጉሥ ቂሮስ ባዘዘ ጊዜም ወደ መቅደሷ ምድር ወደ ኢየሩሳሌም መመለሳቸውን ሰማ። እግዚአብሔርም አንተ ይህን እንዳደረግህ ቂሮስ መሲሐዊ[153] ይልሃል፤ ይህ ስም ለአንተ የተሰጠህ፣ መሲሐዊ የተባልህም

152 ዕዝ.፫+፪፣ ማቴ.፩+፲፪

153 ነጋሢ ለማለት ነው።

ሰደተኞችን ወደ ሀገራቸው ስለመለስህ ነው፤ የኢየሩሳሌምን ሀገር ቤተ መቅደስ እንዲታነፅ ስላዘዝህም ነው አለው::

ከባቢሎን ፍልሰት በኋላም መጡ:: ዘሩባቤልም በእነርሱ ላይ አለቃ ሆነ፣ ከአሮን ወገን የሚሆን የሳዶቅ ልጅ ኢያሱም እግዚአብሔር እንደተናገረው ከነቢዩ ዘካርያስ ጋር በእነርሱ ላይ ታላቅ ሆነ:: በእግዚአብሔር ፊት የቆሙት ሁለት ልጆች እንደሚገባው አገዛዝ መሬትን ሁሉ ይገዛሉ አለው::

ከባቢሎን ምድር ስደት በመጡ ጊዜ ለንጉሡ ቂሮስ መንግሥትን ከያዘ ሁለት ዓመት ሆኖት ነበር:: ከዚህ ከሁለት ዓመት ፍጻሜ በኋላም ለአዳም አምስት ሺኹ ዘመን ተፈጸመለት፤ ከባቢሎን በወጣ ጊዜም በውስጧ ተቀመጠ፤ ጸሐፊው ዕዝራም የመጻሕፍት አመድ ወዳለበት፣ ካህኑ ስምዖንም ወዳለበት፣ ወደ እንግዳ ቤት ገባ::

ጸሐፊው ዕዝራም፣ እሳትን የተመላ ማዕጠንት ተሰቅሎ አገኘ፤ ከእርሱም ዕጣኑ ወደላይ ይወጣ ነበር:: ዕዝራም በብዙ ለቅሶ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፤ እጁንም በነቢያትና በሕግ መጻሕፍቱ አመድ ላይ ዘረጋ፤ ከአመዱም ሦስት ጊዜ ቃመ፤ በዚህ ጊዜም የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሱ ላይ አደረ፤ በነቢያት ይናገር የነበረ መንፈስም በእርሱ ላይ ተናገረ፤ ሕግንና ነቢያትንም ጻፈ፤ ፈጽሞ ሌላ፣ አዲስም አደረጋቸው::

በማዕጠንቱ ያገኛት እሳትም በቤተ እግዚአብሔር ሁልጊዜ ያለ ልዩ መለኮታዊ እሳት ነው:: ዘሩባቤልም በደቂቀ እስራኤል ላይ እንደንጉሥ ሆኖ ተቀመጠ:: የታላቁ ካህን የሳዶቅ ልጅ ኢያሱም፣ ነቢያትንና ሕግን የጻፈ ዕዝራም በደቂቀ እስራኤል ላይ እንዲሁ ታላቅ ነበር:: ደቂቀ እስራኤልም ከባቢሎን ምርኮ በመጡ ጊዜ ለእግዚአብሔር መልካም ፋሲካን አደረጉ::

ደቂቀ እስራኤል በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ ፈጽመው ተሰብስበው ያከበሯቸው ታላላቅ የፋሲካ በዓላት ሦስት ናቸው:: የመጀመሪያው በሙሴ ዘመን የግብጽ ፋሲካ ነው:: ሁለተኛው ፋሲካ በንጉሥ ኢያሱ ዘመን ነው::

ሦስተኛው ፋሲካ ከባቢሎን ምርኮ በመምጣታቸው /በመመለሳቸው/ ያደረጉት ነው:: የዳንኤልን እናት የማረኩትም በመጀመሪያ የባቢሎን ምርኮ ነው:: እርሷም እስከ ሁለት ዓመት ፀንሳ ነበር::

ንጹሑና ነቢዩ ኤርምያስ እንደተነበየው ደቂቀ እስራኤል በፋርሳዊው በቂሮስ የተማረኩበት ሰባ ዘመን ይሆናል::[154] ደቂቀ እስራኤልም በዘሩባቤል፣ በሳዶቅ ልጅ በኢያሱ፣ በጸሐፊው በዕዝራ ዘመን የእግዚአብሔርን ቤት ይሠሩ ዘንድ ጀመሩ:: አርባ ስድስት ዓመት እስኪፈጸም ድረስም ሲሠሩ ቆዩ፤ እነርሱ አርባ ስድስት ዘመን ሲሠሩ እንደቆዩም በቅዱስ ወንጌል እንዲሁ ተጽፏል::[155]

ዳግመኛም ጸሐፍያን የእንግዶች ጉድለቶችን /ሕጹጻንን/ ሠሩ:: የወንዶችን ስሞች ጠሩ /አሰቡ/:: የሴቶችን ስም ግን ያስቡ ዘንድ አልቻሉም፤ ከትንሾቹ በቀር እነርሱ ስሞቻቸውን አላወቁምና:: ወንድሜ ሆይ! እኔ ግን በጣም ተጋሁ፤ በዮናናውያን፣ በቀዳማውያን ዕብራውያን መጻሕፍትም ብዙ ፈለግሁ፤ በውስጣቸውም የሴቶች ስም ተጽፎ አገኘሁ:: የእስራኤል ልጆች ከባቢሎን በመጡ ጊዜ ዘሩባቤል ከጸሐፊው ከዕዝራ ልጅ ከውከብ አብድዩን እንደወለደ እኔ አግኝቻለሁና:: አብድዩም የታላቁ ካህን የሳዶቅን ልጅ ድሚታን አገባ፤ ኢዮአቄምንም ወለደችው:: ኢዮአቄምም የአራምን ልጅ ሕዝብያን አገባ፤ አልአዛርንም ወለደችው::

አልዓዛርም ከለበይዳ ሳዶቅን ወለደ:: ሳዶቅም የወይቃንን ልጅ ላካሌምን አገባ፣ ሐኪምንም ወለደችው:: ሐኪምም አስበዲን አገባ፣ ኤልዩድንም ወለደችው:: ኤልዩድም የጋስልያስን ልጅ አዋድን አገባ፤ አዋድም አዛርን ወለደች:: አዛርም የወልሑ ልጅ ሕያትን አገባ፤ ሕያትም ማታንን ወለደችው:: ማታንም የፊልዮስን ልጅ ሰበርትያልን አገባ፣ መንታም ወለደች፤ እነዚህም ያዕቆብና ኢዮአቄም ናቸው::

ያዕቆብም የአልዓዛርን ልጅ ጋዳትን አገባ፤ የድንግል ማርያምን ዕጮኛ ዮሴፍንም ወለደች::[156] የያዕቆብ ወንድም ኢዮአቄምም የታላቅ ሰው ልጅ ሐናን

154 ዕዝ.፩÷፩፤፩-፩
155 ዮሐ.፪+፲፱-፳፩

156 ማቴ.፩+፲፪

አገባ። ሐናም ክርስቶስ ከእርሷ የተወለደ ንጽሕት፣ ቅድስት፣ ድንግል ማርያምን ወለደቻት።

የመጀመሪያዎቹ ጸሐፍያን የጎደሉትን፣ ድንግልን፣ እንግዶችን፣ አባቷን ይገልጡ ዘንድ አልቻሉም። ስለዚህም አይሁድ ክርስቲያኖችን ይዘባበቱባቸው፣ ይሰድቧቸው፣ ይዋሿቸው ነበር። የድንግል ማርያም አባቶች /ወላጆቿን/፣ ሕዝቧን፣ ነገዷን አስረዱን ይሏቸው ነበር።

በእርሷ ላይም፣ በክርስቶስም ይሳደቡ ነበር፤ ዛሬ ግን የመናፍቃን / የተጠራጣሪዎች/ የአይሁድ አንደበታቸው ይዘጋል፤ ማርያም ከንጉሡ ከዳዊት ዘር፣ ከታላቁ አረጋዊ ከአብርሃም ዘር እንደሆነች ያውቃሉና። ተጠራጣሪዎች አይሁድም ትምህርታቸው ለጽድቅ ጉድለት አልነበረበትም። ከእነርሱ ሦስት ጊዜ ያቃጠሉት ስለ ነቢያት፣ ስለ ሕግ መጻሕፍት፤ መጀመሪያ እንዴት እንግዳ እንደነበሩ አላወቁም።

መጀመሪያ በአንጥያኮስ ዘመን ቤቱን ሁሉ ያቃጠሉ፣ ሁለተኛም የኢየሩሳሌም ቅጽር ፈጽሞ የፈረሰውን፣ ሦስተኛም መጻሕፍትን ያቃጠሉትን ጉድለቶችን ሁሉ እናስረዳችኋለን።

ይሁዳም ፋሬስን ወለደው። ፋሬስም የሌዊን ልጅ በይራህን አገባ፤ ኤስሮምንም ወለደ። ኤስሮምም የባቢሎንን ልጅ ቃኒታን አገባ፣ ከእርሷም አራምን ወለደ። አራምም የይሁዳን ልጅ ፎዚብን አገባ፣ ከእርሷም አሚናዳብን ወለደ። አሚናዳብም የኤስሮምን ልጅ ጥህራን አገባ፤ ነአሶንንም ወለደ። ነአሶንም የዮሐንስን ልጅ ሲማርን አገባ፤ ሰልሞንንም ወለደ። ሰልሞንም የአሚናዳብን ልጅ ሰፈላቅን አገባ፤ ቡኤዝንም ወለደ። ቡኤዝም ከሎጥ ዘር የሆነች ሞአባዊቷ ሩትን አገባ፤ ኢዮቤድንም ወለደ።

ኢዮቤድም የሶርያስን ልጅ አባሊትን አገባ፤ እሴይንም ወለደ። እሴይም የአቡርያስን ልጅ ሕብሊአርን አገባ፤ ንጉሥ ዳዊትን ወለደ። ንጉሥ ዳዊትም የኦርዮን ሚስት ቤርሳቤህን አገባት፤ ሰሎሞንንም ወለደ። ሰሎሞንም

ናንን አገባ ይህችም ከሎጥ ወገን የሆነ የአሞን ንጉሥ የዳን ልጅ ምክያ ናት፡፡ ሮብአምንም ወለደ፡፡ ሮብአምም የቢሎስን ልጅ ማኪንን አገባ፤ አብያንም ወለደ፡፡ አብያም የአቤሲሎምን ልጅ መልኪታን አገባ፤ አሳፍንም ወለደ፡፡ አሳፍም የሳላን ልጅ ኒሮናን አገባ፤ ኢዮሳፍጥንም ወለደ፡፡ ኢዮሳፍጥም የአብድዩን ልጅ መልከያን አገባ፤ ኢዮራምንም ወለደ፡፡ ኢዮራምም የገፍራንን ልጅ ፊታልያን አገባ፤ ዖዝያንንም ወለደ፡፡ ዖዝያንም የሕብናልያስን ልጅ ሶፍያን አገባ፤ ኢዮአታምንም ወለደ፡፡ ኢዮአታምም የቂራን ልጅ ባሕዱትን አገባ፤ አካዝንም ወለደ፡፡

አካዝም የዘካርያስን ልጅ ቢካዝን አገባ፡፡ ሕዝቅያስንም ወለደ፡፡ ሕዝቅያስም የብርቴናስን ልጅ በሴርን አገባ፤ ምናሴንም ወለደ፡፡ ምናሴም አሚሲላንን አገባ፤ አሞጽንም ወለደ፡፡ አሞጽም ንድያስን አገባ፤ ኢዮስያስንም ወለደ፡፡ ኢዮስያስም የኤርምያስን[157] ልጅ ደሊላን አገባ፤ ኢዮአቄምንም ወለደ፡፡ ኢዮአቄምም የፋሌቅን ልጅ ፋርድያን አገባ፤ በባቢሎን ምርኮ ጊዜም ኢኮንያንና ወንድሞቹን ወለደ፡፡

በባቢሎን የነገሠ መርዝም ኤኮንያንን ከእስር ፈታው፤ ስሟ ደሊላ የተባለች የኤልያቄምን ልጅም አጋባው፤ ከእርሱም ሰላትያልን ወለደ፡፡ ምናሴም አሚሲላንን አገባ፤ አሞጽንም ወለደ፡፡ አሞጽም ንድያስን አገባ፤ ኢዮስያስንም ወለደ፡፡ ኢዮስያስም የኤርምያስን[157] ልጅ ደሊላን አገባ፤ ኢዮአቄምንም ወለደ፡፡ ኢዮአቄምም የፋሌቅን ልጅ ፋርድያን አገባ፤ በባቢሎን ምርኮ ጊዜም ኢኮንያንና ወንድሞቹን ወለደ፡፡

በባቢሎን የነገሠ መርዝም ኢኮንያንን ከእስር ፈታው፡፡ ስሟ ደሊላ የተባለች የኤልያቄምን ልጅም አጋባው፡፡ ከእርሱም ሰላትያልን ወለደ፡፡ ኢኮንያንም በባቢሎን ሞተ፡፡ ከእርሱ በኋላም ሰላትያል አርባ ዘጠኝ ዓመት ኖረ፤ የሕልቃናን ልጅ ሐደስትንም አገባ፤ ዘሩባቤልንም ወለደ፡፡ ዘሩባቤልም የጸሐፊው የዕዝራን ልጅ መውካብን አገባ፤ አብዩድንም ወለደ፡፡ አብዩድም



157 ነቢዩ ኤርምያስን አለመሆኑን ልብ ይሏል፡፡

የታላቁን ካህን የሳዶቅን ልጅ ጸደዩትን አገባ፤ ኤልያቄምንም ወለደ፡፡

ኤልያቄምም የአራምን ልጅ ኩብይደይን አገባ፤ አዛርንም ወለደ፡፡ አዛርም ሰላምቤታን አገባ፤ ሳዶቅንም ወለደ፡፡ ሳዶቅም የወይቃንን ልጅ ከሊምን አገባ፤ አኪምንም ወለደ፡፡ አኪምም ዘበይዳን አገባ፤ ኤልዩድንም ወለደ፡፡ ኢልዩድም የጋስልያስን ልጅ አዋድን አገባ፤ አልዓዛርንም ወለደ፡፡ አልዓዛርም የወልሐን ልጅ ሐያትን አገባ፤ ማታንንም ወለደ፡፡ ማታንም የፋንዮስን ልጅ ሰርትያን አገባ፤ ከእርሷም መንታ ወለደ፡፡ እነዚህም ያዕቆብና ኢዮአቄም[158] ናቸው፡፡ ያዕቆብም የአልዓዛርን ልጅ ጋዳትን አገባ፤ የማርያምንም እጮኛ ዮሴፍንም ወለደ፡፡ ኢያቄምም የተመካሒ /የታላቅ/ ሰው ልጅ ሐናን አገባ፤ንጽሕት ማርያምንም ወለደ፡፡ ስለ ንጽሕት ድንግል ማርያም የምናነሣው ጥያቄ ጉድለትም ተፈጸመች /አበቃች/፡፡

ወንድሜ ሆይ! ከዛሬ ጀምሮ እውነትን አቆምሁልህ፤ ጉድለቶችንም ገለጥሁልህ፤ ከጸሐፍያኑ፣ ከጠቢባኑ አንድ ስንኳን ይገልጠው ዘንድ ያልቻለውን ያህን መሠረት አጸናሁልህ፡፡ ወንድሜ ሆይ! ልብህን ስጠኝ፤ የቀሩትን ምግባራት፣ የጉድለቶችንም ቁጥር እንዴት እንደሆነ እነግርህ ዘንድም ልብህን አጥራው /አንጻው/፡፡ ሁሉም ዘሩ ከክርስቶስ ልደት ደርሰው ቆሙ፤ ለአይሁድ እውነተኛ ጉድለት አልነበረም፤ ክርስቶስ የጉድለቶቹ መጨረሻ /ፍጻሜ/ ነበረ እንጂ፤ ወስዶም ለእኛ ሰጠን፡፡

ልጄ ሆይ! አምስት ሺኽ ዘመን በፋርሱ ንጉሥ በቂሮስ ዘመን እንጂ በአዳም ዘመን አልተፈጸመም፡፡ ከቂሮስ መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መከራ እስከሚቀበልም ዳንኤል እንዲህ ሲል እንደተናገረው "ከሰባት ሱባዔ በኋላ ክርስቶስ ይመጣል፤ ይገደላልም፡፡"[159] ሰባቱ ሱባዔም አራት መቶ ስልሳ ዓመት ነው፡፡ ታላቁ ሱባዔም ሰብአ አመት ነው፡፡

ነቢዩ ይህን ማለቱም ከሰባት ዓመት በኋላ ዐሥር ዓመትን ገለጠልን፤ እርሱም ሰባቱ ሱባዔ ከተፈጸመ በኋላ ክርስቶስ ይመጣል አላለም፡፡ ከሰባት

159 ዳን. ፱፥፳፭-፳፯

ሱባዔ በኋላ ይገደላል አለ እንጂ:: የዚህች የኋለኛዋ ዐሥር ዓመት ትርጓሜም ዐምስት መቶ ዓመት ተፈጸመች:: ይህችውም በመጨረሻው ያድነው ዘንድ እግዚአብሔር ለአዳም የገባለት የቃል ኪዳኑ ፍጻሜ ነው:: ዛሬ ግን የአይሁድ እንደበታቸው ይዘጋል:: ለእነርሱም እፍረት ነው:: እነርሱ ይሳደባሉ፤ እስከ ዛሬም አልመጣም ይላሉና:: ይህን ነገር ሲናገሩ ከዚህ በኋላ እውነት እንደሆነ በመጀመሪያው ቃል ያምናሉ:: ዳግመኛም በሐሰት ክርስቶስ መጣ ቢሉ የዳንኤልን ትንቢት ያምናሉ::

አሁን ግን የዳንኤል ትንቢት እንደተፈጸመ ተመለከቱ፤ ቤተ መቅደሱም ከእነርሱ ምድረ በዳ ሆነ፤ ከህነትም ተሻረች፤ ሰባት ሱባዔም ተፈጸመች፤ክርስቶስም መጣ፤ ተገለጠም፤ ከንጉሡ ከአስባስያኖስና ከልጁ ከጥጦስ የተነሣ ምድረ በዳ የሆነችው ሀገርም ተቀደሰች::

ዳግመኛም ልጄ ሆይ! አስረዳሃለሁ:: በወንጌል እንደተጻፈው አውግስጦስ ቄሣር በነገሠ በአርባ ሁለት ዓመት የይሁዳ ዕፃ በምትሆን በቤተልሔም ክርስቶስ ተወለደ:: ትንቢቱ በተፈጸመ ጊዜ ክርስቶስ እንደመጣ እነሆ ተገለጠልን:: ነቢዩ ሚክያስ "አንቺ የይሁዳ ዕፃ /ክፍል/ ቤተልሔም የይሁዳ ነገሥታት ከሚነግሡባቸው አህጉር አታንሺም፤ ሕዝቦቼ እስራኤልን የሚጠብቃቸው ንጉሥ ከአንቺ ይወጣልና"::

ዛሬስ አይሁድ ይፈሩ፤ ዳንኤልን ቢዋሹት ዳግመኛም ነቢዩ ሚክያስን ይዋሹት ዘንድ አይችሉም ነበር፤[160] የማይዋሿቸው ከሆነ የይሁዳ ክፍል በሆነች በቤተልሔም እነሆ! ክርስቶስ ተወለደ::[161] በይሁዳ ክፍል በሆነች በቤተልሔም ክርስቶስ በተወለደ ጊዜም ኮከብ በምሥራቅ ተገለጠ፤ ሰብአ ሰገልም ተመለከቱት፤ በከዋክብት ሁሉ መካከልም በሰማይ እርሱ ያበራ፣ ያብረቀርቅም ነበር፤ በከዋክብት መካከል እንደተቀመጠች ድንግል የቆነጀች ሴት ፊትም ነበር::

እርሷም ባለጥሩ መልክ ትንሽ ሕፃን ይዛም ታንቦገቡግ /ታበራ/ ነበር:: ከመልኩ ደምግባትና ከበርሃኑ የተነሣ ላዩንም፣ ታቹንም ያበራ ነበር፤ ይህ



160 ሚክ. ፭+፪

161 ማቴ. ፪+፩

ሕፃንም ከድንግል ሴት መሐል እጅ ነበር፤ የምታበራ ደመናም /ጸዳል/ እንደ አክሊል በሕፃኑ ራስ ላይ ነበረች፤ የሰማይ ከዋከብትን ሲመለከቱ የከለዳውያን ልማድ ነበር፡፡ ይፈትኗቸው ከዋከብትም በእነርሱ ይቆጠሩ ነበር፤ በዚህ አምሳል ኮከቡን በተመለከቱ ጊዜ በታላቅ ድንጋጤ ተያዙ፤ እርስ በርሳቸውም የሄሎናውያን ንጉሥ ይወጋን ዘንድ በእውነት ተዘጋጅቷል አሉ፡፡ እነርሱም ከጠንቋዮች፣ ከፈላስፎች ዘንድ መረመሩ፡፡ እነርሱም እውነትን መሠረቱ፡፡ የእስራኤል ንጉሥ እንደተወለደም ገለጡ፡፡ በዚህ በከዋከብት ተግባር /ቆጠራም/ የሚሆነውን ታላቅ ነገር ከመሆኑ በፊት ያውቁት ነበር፡፡ ዳግመኛም በታላላቅ መርከቦች ያሉ ሊቃናት በባሕር በሄዱ ጊዜ የነፋስ፣ የዓውሎ /ጥቅል ነፋስ/ የጉም፣ የጭጋግ ምልክት ይደረስባቸው ነበር፡፡

እንዲሁም ሰብአ ሰገል በመጻሕፍቶቻቸው ያለውን ባነበቡ ጊዜ በይሁዳ ምድር ክርስቶስ ከእነርሱ እንደሚወለድ ዐወቁ፤ ሰብአ ሰገልም በምዕራብ በኩል እየመጡ በምሥራቅ በኩል ወዳለው ታላቅ ተራራ ወጡ፡፡ ጉዞ ከመጀመራቸው በፊት ያዘጋጇቸውን እነዚህን እጅ መንሻዎች ወሰዱ፤ እነዚህም ወርቅ፣ ዕጣን፣ ከርቤ ናቸው፡፡ ወርቁ ስለ ግንሥናው፣ ዕጣን ስለ አምላክነቱ፣ ከርቤውም ስለሞቱ ነው፡፡ የፋርስ ንጉሥ ሖር ስለ ነገሥታቱ ንጉሥ የተባለውን በሰማ ጊዜ ሠረገላ አዘጋጀ፤ በእነርሱ ላይም ተጫነ፡፡

ዳግመኛም የሳባ ንጉሥ በስናጥር፣ ሌላው የምሥራቅ ንጉሥ ወቀርሱዳን ወጣ፡፡ ሌላም አዘጋጀ፣ ወጣም፤ በታላቅ ድንጋጤ ውስጥም ነበር፡፡ ዳግመኛም በምዕራብ ጫፍ የሚገኙ ሌሎች ነገሥታት ሁሉ ከእነርሱ ጋር ተነዋወጹ፤ በምሥራቅ በኩል የሚገኝ ሀገር ሁሉ ምስጋናውን ስለተመለከቱ በታላቅ ድንጋጤ ውስጥ ነበሩ፡፡

የሐዱት ሰብአ ሰገልም ይህ ኮከብ ያለ ተግባር /ምክንያት/ አልወጣም አሉ፤ ሰብአ ሰገልም ኢየሩሳሌም እስኪደርሱ ድረስ ይጓዙ ነበር፤ ንጉሥ ሄሮድስ በሰማ ጊዜ ደነገጠ፡፡ ወደ እርሱ ጠራቸው፤ ከእነርሱ ጋርም ተጨዋወቱ፤

ሁኔታውንም ገለጡለት:: እርሱም ሰራዊቱም ተነዋወጡ /ተረበሹ/፤ ሰብአ ሰገልንም ሄዳችሁ ሕፃኑን በኀይል ፈልጉት፤ ባገኛችሁት ጊዜም እኔም መጥቼ እሰግድለት ዘንድ መጥታችሁ ዐሳውቁኝ አላቸው::[162]

ያን ጊዜም ሰብአ ሰገል ወደ ቤተልሔም ሔዱ፤ ክርስቶስንም አገኙት:: የእጅ መንሻዎችንም አቀረቡለት፤ ወደ ሄሮድስም አልተመለሱም፤ ወደ ሀገራቸው ሄዱ እንጂ:: ከዚህ በኋላም ሄሮድስ ወደ ሀገራቸው በመሄዳቸው ተቆጣ፤ የሁለት ዓመት ከዚያም የሚያንሱ ሕፃናትን ይገድሉ ዘንድ አዘዘ::

የእግዚአብሔር መልአክም ለዮሴፍ ተገለጠለት፤ ሕፃኑንና እናቱን ይዘህ ተነሥ፣ ወደ ግብጽ ምድርም ሂድ፤ እስከምነግርህም በዚያ ኑር፤ አለው:: ዮሴፍም ወደ ግብጽ ሀገር ሄደ፤[163] ሄሮድስም ከሕፃናት አንድ ስንኳን እስከማይገኝ ድረስ ሕፃናቱን ሁሉ አስገደለ፤ ሄሮድስም ከፉ አሟሟትን ሞተ:: ከሞተ በኋላም የእግዚአብሔር መልአክ ለዮሴፍ በግብጽ ሀገር ታየው:: ከግብጽ ወጣ፤ እርሱ፣ ሕፃኑ፣ እናቱ ማርያምም ናዝሬት ገበተው አደሩ::

ለክርስቶስ ሠላሳ ዓመት እስኪሞላው ድረስ በኢየሩሳሌም ኖሩ፤በዮሐንስም ተጠመቀ::[164] ይህ ዮሐንስም መላ ዘመኑን ሁሉ በበረሃ ነበር፤ ምግቡም አንበጣ የጋጃ ማር ነበር፤ በጢባርዮስ ዘመን በዐሥራ ዘጠነኛው ዓመት ጌታችን ክርስቶስ ተሰቀለ፤ በሥጋ ሞተ ተቀበረም፤ እንደተጻፈም በሦስተኛው ቀን ከሙታን መካከል ተነሣ:: ወደ ሲኦልም ወርዶ አዳምና ሔዋንን፣ ጻድቃን ዘራቸውንም አስቀድሞ እንደገባው እውነተኛ ቃል ኪዳኑ አዳናቸው::

ነቢያት ስለ እርሱ የተናገሩትን /የተነበዩትን/ ሁሉ ፈጸመ፤ ወደ ሰማይም ዐረገ፤[165] ዳግመኛ ከቅዱሳን መላእክቶቹ ጋር በምስጋና ይመጣል::[166] በሕያዋንና በሙታን ይፈርድ ዘንድ፤ ፍጹም ምስጋና ክብር፣ ኀይል፣ ስግደት ለእርሱ ይሁን፤ ለዘለዓለሙ አሜን::

ይቅርታው፣ ቸርነቱ፣ የረዳትነቱ ሀብት ከሊቃነ ጳጳሳቱ አለቃ ከባስልዮስ፣ ከንጉሣችን ከኀይለ ሥላሴ፣ ከንግሥታችን ነፍስ ከወለተ ጊዮርጊስ፣ ከንግሥና

163 ማቴ. ፪÷፲፫-፲፭
164 ማቴ. ፫÷፲፫፣ ማር.፩÷፱፣ ሉቃ. ፫+፳፩-፳፫
165 ማር. ፲፮÷፲፱፣ ሉቃ. ፳፬+፶፩
166 ማቴ. ፳፭÷፴፩

ወራሽ ከአምኃ ሥላሴ፣ ከጌታችን ከአርአያ ዮሐንስ ነፍስ ከሁላችንም ከሰማነው፣ ከአንባቢውም ጋር ይሁን፤ ለዘለዓለሙ አሜን፡፡

የአዳም የዕድሜዎቹ ቁጥር ሴትን እስኪወልድ ሁለት መቶ ሠላሳ ዓመት ነው፡፡ ሴትም ሄኖስን እስኪወልድ ሁለት መቶ አምስት ዓመቱ ነበር፤ ሄኖስም ቃይናንም እስኪወልድ ድረስ መቶ ዘጠና ዓመቱ ነው፡፡ ቃይናንመ መላልኤልን እስኪወልድ ድረስ መቶ ሰብዐ ዓመቱ ነው፡፡ መላልኤልም ያሬድን እስከወለደበት ጊዜ ድረስ መቶ ስልሳ አምስት ዓመቱ ነው፡፡ ያሬድም ሄኖክን እስከወለደበት ጊዜ ድረስ መቶ ስልሳ ሁለት ዓመቱ ነው፡፡ ሄኖክም ማቱሳላን እስኪወልድ መቶ ስልሳ ዐምስት ዓመቱ ነበር፤ ማቱሳላም ላሜህን እስኪወልድ ድረስ መቶ ሰማንያ ስድስት ዓመቱ ነበር፤

ላሜህም ኖኅን እስኪወልድ ድረስ መቶ ሰማንያ ሁለት ዓመቱ ነበር፤ ከኖኅ ጀምሮ ጥፋቱ /የጥፋት ውኃው/ እስከወረደበት ጊዜ ድረስ ስድስት መቶ ዓመት ነው፤ ሁሉ ሲደመርም ሁለት ሺኽ ሁለት መቶ ሃምሳ ስድስት ዓመት ነው፤ ሴምም ከጥፋት በኋላ አርፋክስድን እስኪወልድ ድረስ ሁለት ዓመት ኖረ፡፡ አርፋክስድም ቃይናንን እስኪወልድ ድረስ መቶ ሠላሳ አምስት ዓመቱ ነበር፡፡

ቃይናንም ሳላን እስኪወልድ ድረስ መቶ ሠላሳ ዓመቱ ነበር፤ ሳላም ኤቦርን እስኪወልድ ድረስ መቶ ሠላሳ ዓመቱ ነበር፤ ኤቦርም ፋሌቅን እስኪወልድ ድረስ መቶ ሠላሳ አራት ዓመቱ ነበር፡፡ በኤቦር ዘመን ጥፋት ከመውረዱ በኋላ በአምስት መቶ ሠላሳ አንድ ዓመት ቤት ተሠራ፡፡ ፋሌቅም ራግውን እስኪወልደው ድረስ መቶ ሠላሳ አራት ዓመቱ ነበር፤ በፋሌቅ መወለድ ጊዜም ቋንቋዎች ተከፋፈሉ፡፡[167]

ራግውም ሴሩህን እስኪወልድ መቶ ሠላሳ ሁለት ዓመቱ ነበር፤ በራግው ዘመንም ናምሩድ ነገሠ፤ ሴሩህም ናኮርን እስኪወልድ መቶ ሠላሳ ዓመቱ ነበር፤ በዘመኑም የካም ልጅ የሆነ የምስራም ልጅ ፋሮቀስ ነገሠ፡፡ ናኮርም

167 ዘፍ. ፲፩+፻

ታራን እስኪወልድ መቶ ዓመቱ ነበር፤ ሲደመርም ሦስት ሺኽ ሰምንት መቶ ሃምሳ ዓመት ነው፤ ቤቱ ከተሠራ ጀምሮ ደግሞ ሰድስት መቶ አንድ ዓመት ነው::

አብርሃም ይስሐቅን እስኪወልድም መቶ ዓመቱ ነበር፤ ይስሐቅም ያዕቆብን እስኪወልድ ስልሳ ዓመቱ ነበር፤ ያዕቆብም ሌዊን እስኪወልድ ሰማንያ አምትስ ዓመቱ ነበር፤ ሌዊም ቀአትን እስኪወልድ አርባ ዓመት ነበር፤ ቀአትም እንበረምን እስኪወለድ ስልሳ ዓመት ነበር ፤ እንበረምም ሙሴን እስኪወልድ ሰማንያ ዓመት ነበር:: ሲደመርም ሦስት ሺኽ ሰባት መቶ ሰባ አምስት ዓመት ነው፤ከአብርሃም ጀምሮ ደግሞ አራት መቶ ሃያ ዐምስት ዓመት ነው::

ሙሴ ከፈርዖን ጋር እስከተነጋገረበት ጊዜ ድረስም ሰማንያ ዓመት ነበር፤ በግብጽ ሁለት መቶ ዐሥራ አምስት ዓመት ከአብርሃም ጀምሮ ደግሞ አምስት መቶ አምስት ዓመት ከተቀመጡ በኋላም እስራኤልን አወጣቸው፤ በገዳምም አርባ ዘመን ገዛቸው:: ከዚህ በኋላ ኢያሱ አርባ ዓመት አስተዳደራቸው፤ የሶርያ ንጉሥ ኩሣ ስምንት ዓመት ገዛቸው፤ የቄኒዝ ልጁ ጎቶንያልም አምስት ዓመት ገዛቸው::

ሞአባዊው ኢግሎምም ዐሥራ ስምንት ዓመት ገዛቸው:: የብንያም ወገን ፈያድም ሰማንያ ዓመት ገዛቸው፤ የከነአን ንጉሥ ኢያሚንም ሃያ ዓመት ገዛቸው፤ የንፍታሌም ወገን ባርቅም አርባ ዓመት ገዛቸው፤ የምድያም ነገሥታት ዛብሄልና ስልማናም ሰባት ዓመት ገዟቸው፤ የምናሴ ወገን ጌዴዎንም ዐርባ ዓመት ገዛቸው፤ ልጁ አቤሜሌክም ሦስት ዓመት ገዛቸው፤ የይሳኮር ወገን የፎሐ ልጅ ቶላም ሃያ ሦስት ዓመት ገዛቸው፤ ገለአዳዊው ኢያኤርም ሃያ ሁለት ዓመት ገዛቸው::

ኢሎፍሊና የአሞን ልጆችም ዐሥራ ስምንት ዓመት ገዟቸው:: ገለአዳዊው ዮፍታሔም ሰባት ዓመት ገዛቸው፤ የቤተልሔሙ ሄሴቦንም ሰባት ዓመት ገዛቸው፤ ዛብሎናዊው አሎምም ዐሥር ዓመት ገዛቸው፤ የኤፍራታዊው ልጅ

ሎቦንም ስምንት ዓመት ገዛቸው፤ ኢሎፍሊም ዐርባ ዓመት ገዛቸው፤ የዳን ወገን ሶምሶንም ሃያ ዓመት ገዛቸው።

ከዚህ በኋላ በሚካ ዘመን ያለ ገገር ዐሥራ ሁለት ዓመት ተቀመጡ፤ያን ጊዜ ፊንሐስ ሞተ፤ ልጁ ኤሊም አርባ ዓመት ገዛቸው። ከእርሱ በኋላም ሳሙኤል ሃያ ዓመት፣ የመሳፍንቱ ዘመንም በአምስት መቶ አርባ ስምንት ዓመት ተፈጸመ፤ በምድሩም ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ አራት ሺኽ ሦስት መቶ ሠላሳ ሰባት ዓመት ነው።

ከዚህ በኋላ የብንያም ወገን ሳኦል አርባ ዓመት ነገሠ፤ ዳዊትም አርባ ዓመት ነገሠ፤ ሰሎሞንም አርባ ዓመት ነገሠ፤[168] በሰሎሞን ልጅ በሮብዓም የመጀመሪያው የንግሥና ዓመትም ኢዮርብአም በዐሥሩ ነገድ ሃያ ሁለት ዓመት ነገሠ፤ ልጁ ናዳብም ሁለት ዓመት ነገሠ፤ ባዖስም ሃያ አራት ዓመት ነገሠ። ልጁ ኤላም ሁለት ዓመት ነገሠ፤ ዘንበሪም ሰባት ቀን ነገሠ፤ አምሪም ዐሥራ ሁለት ዓመት ነገሠ።

አከአብም ሃያ ሁለት ዓመት ነገሠ፤ ልጁ አካዝም ሁለት ዓመት ነገሠ፤ ወንድሙ ኢዮራም ዐሥራ ሁለት ዓመት ነገሠ፤ ኢዩም ገደለው። ኢዩም ሃያ ስምንት ዓመት ነገሠ፤ ልጁ ኢዮአካዝ ዐሥራ ሰባት ዓመት ነገሠ። ልጁ ኢዮርብአምም አርባ አንድ ዓመት ነገሠ፤ ከዚህ በኋላ ደቂቀ እስራኤል ዐሥራ አንድ ዓመት ያለ ንጉሥ ኖሩ።

ከዚህ በኋላ ልጁ ዘካርያስ ሰባት ወር ነገሠ፤ ሴሎምም አንድ ወር ነገሠ፤ ምናሄም ዐሥር ዓመት ነገሠ፤ ልጁ ፋቂስያስም ሁለት ዓመት ነገሠ፤ ፋቁሄም ሃያ ዓመት ነገሠ፤ ከዚህ በኋላ ዓሥር ዓመት ያለ ንጉሥ ኖሩ። የሄላ ልጅ ሆሴዕም ዘጠኝ ዓመት ነገሠ፤ሕዝቅያስ በነገሠ በስድስት ዓመቱ ያን ጊዜ ዐሥሩ ነገድ ተማረኩ። ከኢዮርብአም ጀምሮ እስከዚህ ድረስ ሁለት መቶ ስልሳ አንድ ዓመት ይሆናል። በድምሩም አራት ሺኽ ሰባት መቶ ሰማንያ አንድ ዓመት ነው። የሰሎሞን ልጅ ሮብአም በሁለቱ ነገድ ዐሥራ ሰባት ዓመት ነገሠ።

168 ፩ዜና መዋ. ፱+፲

አብያም ሃያ ዓመት ነገሠ፤ አሳፍም አርባ አንድ ዓመት ነገሠ፤ ኢዮሳፍጥም ሃያ አምስት ዓመት ነገሠ፤ ኢዮራምም ዐሥር ዓመት ነገሠ። አካዝያስ አንድ ዓመት በዙፋን ነገሠ፤ ጎቶልያ ሰባት ዓመት ነገሠ፤ ኢዮአስ አርባ ዓመት ነገሠ፤ አሜስያስም ሃያ ዘጠኝ ዓመት ነገሠ። ዖዝያን ሃምሳ ሁለት ዓመት ነገሠ፤ ኢዮኢታምም ዐሥራ ሰባት ዓመት ነገሠ፤ አካዝ ዐሥራ ሰባት ዓመት ነገሠ።

ሕዝቅያስም ሃያ ዘጠኝ ዓመት ነገሠ፤ ምናሴ ሃምሳ አምስት ዓመት ነገሠ፤ አሞጽ ሁለት ዓመት ነገሠ፤ ኢዮስያስም ሠላሳ አንድ ዓመት ነገሠ፤ኢዮአካዝ ሦስት ወር ነገሠ፤ ኤልያቄምም ዐሥራ አንድ ዓመት ነገሠ፤ ኢኮንያንም ሦስት ወር ነገሠ፤ ሴዴቅያስም የሁለታቸውን ዐሥራ አንድ ዓመት ነገሠ፤ ከሳኦል እስከ ምርኮ ድረስ አምስት መቶ ዐሥራ ዘጠኝ ዓመት ይሆናል። የዐሥሩ ነገድ ምርኮ በመቶ ሠላሳ ሦስት ዓመት ከሰባት ወር ነበር፤ ያን ጊዜ ናቡከደነጾር በነገሠ በዐሥራ ዘጠኝ ዓመተ ዓለም ፤በተፈጠረ በአራት ሺኽ ዘጠኝ መቶ ዐሥራ አምስት ዓመት ከሰባት ወር የይሁዳን ቤት ማረከ።

የፍጥረታት ሁሉ የመጀመሪያ የሆኑ የአባታችን የአዳም የእናታችን የሔዋን የገድላቸው ዜና ይህች ናት። ይህችም በዘመኑ ሁሉ ተርጓምያን፣ ጥበበኞች የሆኑ ሰባ ሁለቱ ሊቃናት ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የጻፏት ናት። እነዚህም አርባ ስድስቱን የቅዱሳን ነቢያት መጻሕፍት የተረጐሙ ናቸው። የዕብራውያን ቋንቋ ከሆነው ከዕበራይስጥ ቋንቋ፣ የጽርአውያን ቋንቋ ወደ ሆነው ወደ ጽርአ /ግሪክኛ/ ቋንቋ /ተርጒመዋል/። በዮናናውያን መጻሕፍት አስቀድሞ እንደተጻፈ በየዋህነት፣ በእውነተኛ ልቡና ሁነው የቀደሙትንና የኋለኞችን አባቶች የገድላቸውን ዜና የሚያምኑ ሰዎች የማያልቅ፣ ፍጹም ደስታ ካለባት ወደ ዘለዓለም ሕይወት ወደ መንግሥተ ሰማያት ይገባል።

ሐሰት ነው በማለት የቅዱሳንን የገድላቸውን ዜና የማያምኑ ግን ዕድላቸው ሃይማኖታቸውን ከካዱ ከአርዮስ፣ ከሰባልዮስ ጋር ይሆናል።

ማደሪያቸውም ወደ ጥልቁ ጥልቅ የወረዱ፣ ዕረፍትም ለሌላቸው፣ ሰይጣንና አጋንንት የተዘጋጀው ቅጣት ያለበት የስቃይ ጉድጓድ እሳተ ገሃነም ይሆናል:: ለዘለዓለሙ አሜን::

በመንፈስ ቅዱስ ያከበርሃቸው የአዳምና የሔዋን አምላክ ሆይ! መጀመሪያም፣ መጨረሻም፣ ራስም አንተ ነህ::[169] ለቀደሙት፣ ለኋለኞች ለታላቁ፣ ለታናሹም አስገኝ የሆኑ የአዳምና የሔዋንን የገድላቸውን ዜና የምናምን እኛን ለቅዱሳን ሞገስ በሆነች በቀናች ሃይማኖት ጠብቀን /አጽናን/:: ከመከራ ሥጋ፣ ከመከራ ነፍስም፣ አድነን:: ከዲያብሎስ ወጥመድም ጠብቀን::

በደኅናና በሰላም ላስፈጸመን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይግባው:: ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ አሜን:: የአባታችን የአዳም፣ የእናታችን የሔዋን ገድል ተፈጸመ:: ያለዛሬና ያለትላንት፣ ከዓለም በፊት በነበረ በእግዚአብሔር አብ ሰላም፣ ዛሬ ባለ ነገም በሚኖር፣ በኋለኛውም ዘመን ቅድስት፣ ድንግል ከሆነች ከማርያም በተወለደው በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ፈቃድ፣ ሳይቀድም፣ ወደ ኋላም ሳይሆን ፍጹም ከሆነ ከአብ በሠረፀ በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ፣ ቅድስት ንጽሕት በሆነች በእመቤታችን በድንግል ማርያም ጸሎት መታሰቢያቸው ከፍ ያለ በአዳምና በሔዋን ልመና፣ ሐዲስ ወንጌልን / የምሥራችን/ በጻፈ በዮሐንስ ዘመን በአንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ሰባት ዓመተ ምሕረት ነፃ የምታወጣ፣ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ በነገሡበት ዘመን፣ በኢትዮጵያዊው ፓትርያርክና በተክለሃይማኖት መንበር ዕጨጌ በሆኑ በአባታችን ባስልዮስ የርእሰ ሊቀ ጳጳሳትና ሹመት ዘመን ተፈጸመ::

ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ አሜን፤ አሜን ይሁን ይደረግ::

መንግሥተ ሰማይን ተስፋ በማድረግ ይህችን መጽሐፍ የጻፋት / የገለበጣት/ መኩብበ ሥላሴ ነው::[170] የአዳምና የሔዋን የረድኤታቸው ጥላ፣ መኪታ ይሁነው፤ በአልፋ /በክርስቶስ/ ፊት በሚቆምበት ጊዜ በኬፋ /በጴጥሮስ/

170 መኩብበ ሥላሴ ለጠቅላይ ቤተ ክህነት ቤተ መጻሕፍት ያገለግል ዘንድ በ፲፱፻፶፯ ዓ.ም. ከግዕዝ ቋንቋ ወደ ግዕዝ ቋንቋ የገለበጠ ጸሐፊ እንጂ የመጽሐፉ ደራሲ /ተርጓሚ/ አለመሆኑን ልብ ይሏል::

## ዋቢ መጻሕፍት


፩. ሃየሎም በርሄ /መሪጌታ/፣ ፲፱፻፺፭ ዓ.ም.፣ ሁለቱ ኪዳናት፣ አዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ።

፪. ሠናይ ምስክር /አባ/፣ ፲፱፻፺፱ ዓ.ም.፣ አከሲማሮስ። ባሕርዳር።

፫. ትርጓሜ አሪት፣ ፲፱፻፺፱ ዓ.ም.፣ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት።

፬. ኪዳነ ወልድ ክፍሌ /አለቃ/፣ በ፲፱፻፵፰ ዓ.ም.፣ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፣ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

፭. ቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ፣ ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት።

፮. ኤፍሬም እሸቴ /ዲ/ን/፣ ፲፱፻፺፪ ዓ.ም.፣ የገድሎች አዘማገናዊ አከፋፈልና ሥነ ጽሑፋዊ ፋይዳ፣ አዲስ አበባ፣ /ዐውደ ጥናት ላይ የቀረበ ጽሑፍ/

፯. ገብረ ዮሐንስ ገብረ ማርያም፣ ፲፱፻፺፰ ዓ.ም.፣ ጊዮርጊስ ወልደ አሚድ። /ትርጉም/ አዲስ አበባ

፰. ፳፻፩ ዓ.ም.። ዜና አይሁድ /ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን/። አዲስ አበባ።

፱. ገድለ ተክለሃይማኖት፣ ፲፱፻፹፱ ዓ.ም./አራተኛ እትም/፣ አዲስ አበባ።

፲. ገድለ አርሴማ፣ ፲፱፻፺፭ ዓ.ም.፣ አዲስ አበባ፣ ዓለም አታሚዎች።

፲፩. ገድለ ክርስቶስ ሠምራ፣ ፲፱፻፺፪ ዓ.ም.፣ አዲስ አበባ፣ ተስፋ ገብረሥላሴ ማተሚያ ቤት

፲፪. ገድለ ገብረ መንፈስ ቅዱስ፣ ፲፱፻፺፪ ዓ.ም.፣ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት


፲፫. Allen C. Myers, 1987, The Eerdmans Bible Dictionary

፲፬. Ephrem Eshete, 1999, Narrative Techniques of

Three Selected Ethiopian Hagiographies, Addis Ababa University (MA thesis)

፲፩. Kineferegb Zeleke, 1975, Bibliography of the Ethiopian Hagiographical Traditions; Journal of Ethiopian Studies.Vol.13.No 2.

፲፪. The Forgotten Books of Eden — The First and Second Book of Adam and Eve.




ኢትዮጵያውያን አበው ውለታ የማይረሱ ናቸው። ይህም የሚታወቀው ለሰው ልጆች አባት ለአዳም ገድሉን ተርጉመው በማስቀመጣቸው፤ ታቦት ቀርጸው በማክበራቸው ፤ዕለት ወስነው በመዘከራቸው ነው።

ገድለ አዳም የአዳምን ብቻ ሳይሆን የልጅ ልጆቹን ታሪክ እንደ ኦሪት ዘፍጥረት እና እንደ መጽሐፈ ኩፋሌ የሚተርክ ነው። በአብዛኛው ከዮሴፍ ወልደ ኮርዮን መጽሐፍ ጋር ይመሳሰላል። በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪካቸው በመጠኑ የተጻፈላቸው አዳም እና ሔዋንን የደስታቸውንም የመከራቸውንም ዘመን በዘመኑ አብረናቸው ያለን እስኪመስለን ድረስ ያሳየናል። ታሪካቸውን ከውጪ ብቻ ሳይሆን ልቡናቸውን ገልጦ እያየ ውሳጣዊ ስሜታቸውንም ይተርክልናል፡

ስለዚህ ምድር እንግዳ ሆነው ሲመጡ፣በመሬት የመጀመሪያውን ጎጆ ሲቀልሱ፣ የመጀመሪያውን ትዳር ሲያቆሙ፣የመጀመሪያውን እርሻ ሲያርሱ፣የመጀመሪያውን ኀዘን ሲያዝኑ፣ የመጀመሪያዎቹን ልጆች ሲወልዱ አዳምና ሔዋን ምን አሉ? ምን ሆኑ? ምን አጋጠማቸው?... እነሆ ገድለ አዳም ይተርክልናል። "የጻፈ፣የተረጎመ" ከሚለው በረከት አዘጋጆቹ፣ "ያነበበ" ከሚለው በረከት ደግሞ እኛ እናገኛለን።

ዲያቆን ዳንኤል ክብረት

የኀገረ ቤተክርስቲያን ጉዳዮች

ጸሐፊ እና ተመራማሪ

ዋጋ ብር 55.00

PRINTED BY H&F 0911 51 79 26